# ልብን
# መቀስቀስ

*2007፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

**አሳታሚ**
የኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ

የመልእክት ሳጥን ቁጥር፡ 102
ስልክ፡ 251-116627751
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የመጀመሪያው ዕትም፡ መስከረም 1996 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም፡ ግንቦት 2007 ዓ.ም

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

# <u>ከባብ ጽሑፎች</u>

## (1)

### ለመጀመሪያው የሕያዉ ፈደል የተጻፈ መልዕክት

ከእኛ ዘንድ ለሰው ዘር ሁሉ እንደ ምክር ያገለግል ዘንድ፣ ይህ በእርሱ፣ አምላክ በሚከስተው ለሚያምነው ለመጀመሪያ አማኝ የገለፅነው ነው።

በእጅግ በጣም ተወዳጁ፣ በፍፁም ኃያሉ ስም።

እርሱ የሰማይና የምድር እንዲሁም በመካከላቸው የሚገኘው የማናቸውም መንግሥታት ሉዓላዊ ጌታ የሆነው የተመሠገነና የተከበረ ነው። በል፣ በእውነቱ ሁሉም ወደ እርሱ ይመለሳሉ፤ የፈለገውንም ሰው ሁሉ በራሱ ትእዛዝ የሚመራው እርሱ ነው። በል፤ ሁሉም ሰዎች የእርሱን ቡራኬ ይማፀናሉ፤ እርሱም በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ የላቀ የበላይ ነው። እርሱ በእርግጥ ፍፁም ክብር የተመላው፣ ኃያሉ፣ በጣም ተወዳጁ ነው።

ይህ ከፊደል *'ዘ'*[1] ለእርሱ የመጀመሪያው አማኝ ለሆነው የተፃፈ መልእክት ነው። በእውነቱ እርሱ እኔ፣ ራሴ፣ ሉዓላዊው፣ ሁሉን ቻዩ መሆኑን መሥክር። እርሱ ህይወትንና ሞትን የሚያዘው ነው፣ ሁሉም ወደ እርሱ ይመለሳሉ። በእርግጥ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ሰዎችም ሁሉ በማምለክ በፊቱ ያጎነብሳሉ። በእውነት፣ ጌታህ አምላክ፣ ወዲያው እንዳዘዘ፣ እንዲያውም *'ሁን፣ ሆነም'* የሚሉትን ቃላት ከመናገር በፈጠነ ጊዜ እያንዳንዱን ሰው

---

[1] ይህ ዛማሪህ (ፍሬ) የሚለው ቃል የመጀመሪያ ፊደል ነው። ሾጊ ኤፌንዲ በጽሑፎቹ ውስጥ ባብን እንደ ዛማሪህ ማለትም የአምላክ ተከታታይ ክስተቶች ዛፍ ፍሬ አድርጎ ይጠቅሰዋል። (ሾጊ ኤፌንዲ በናውሩዝ 110 ለምስራቅ ባሃኢዎች የፃፈውን ደብዳቤ ገፅ 5 ይመልከቱ)።

ፊትህን ወደኔ መልስ፣ ስለመጪውም ሁኔታ አትሥጋ። በእውነቱ በመንግሥተ ሰማያት ሠራዊት መካከል አንተ የተከበርከው ነህ፤ ሕቡዕ መሥጢርህም፣ በእውነቱ፣ በሚነደው ቁጥቋጦ መሐል በፍጥረት ጽላት ላይ ተመዝግቧል። የእርሱ ግዛት ከመላው ፍጥረት የሰፋ ስለሆነ፣ ሳይቆይ አምላክ በሰዎች ሁሉ ላይ ገዢነትን ያጎናጽፍሃል።

(7)

የምዕራብ ሕዝቦች ሆይ፣ የምህረት ጌታ፣ መላዕክት ውዳሴውን ከፍ ከፍ እያደረጉ፣ ለእነዚያ በምልክቶቻችን በእውነት ላመኑት ይቅርታን እየለመኑ፣ ዙሪያውን እየተሽከረከሩ በደመናዎች ጥላ ከሚወርድባት ቀን በፊት ከከተሞቻችሁ ውጡና ለአምላክ እርዳታ አድርጉ። በእውነቱ የእርሱ አዋጅ ታውጇል፤ የአምላክም ትእዛዝ፣ እናት መጽሐፍ በሆነው እንደተሰጠው፣ በእርግጥ ተገልጿል…

በእውነቱ አምላክ በእምነት ወንድሞቻችሁ ለሆኑት ልቦቻችሁ መስተዋት እንዲሆኑ ስለሚፈልግ፣ እናንተ በእነርሱ ውስጥ ተንፀባርቃችሁ፣ እነርሱም በእናንተ ውስጥ ተንፀባርቀው ራሳችሁን ታገኙ ዘንድ፣ በአንድና በማይከፋፈለው የአምላክ ሃይማኖት እንደ እውነተኞች ወንድማማቾች ከመለያየት ነፃ ሁኑ። ይህ የአምላክ፣ የፍጹም ኃያሉ እውነተኛ መንገድ ነው፤ እርሱም በእርግጥ ተግባሮቻችሁን ተመልካች ነው።

(8)

ታማኞቹ የዚህ መጽሐፍ ጥቅሶች ሲደገሙ በሰሙ ቁጥር ዓይኖቻቸው በእንባዎች ይጥለቀለቃሉ፤ ለአምላክ፣ ፍጹም ለተወደሰው ባላቸውም ፍቅርምክንያት፣ በእርሱ ከሁሉ በበለጠው ትውስታ ልቦቻቸው በጥልቀት ይነካሉ። እርሱ አምላክ፣ ሁሉን

አዋቂው፣ ዘለዓለማዊው ነው። እነርሱ በእውነቱ፣ ከሁሉ በላይ የሆነችው ገነት ነዋሪዎች ናቸው። በእውነቱ እነርሱ በዚያ ውስጥ፣ ከአምላክ ከወጣው በቀር ሌላ ምንም አያዩም፤ ከመረዳት ችሎታቸው ክልል ውጪ የሚሆን ምንም ነገር አይኖርም። እዚያ 'ሰላም፣ ሰላም የሚሉት ቃላት ከከናፍሮቻቸው ላይ ሳይለዩ የሚያነጋግሯቸውን አማኞች በገነት ያገኙዋቸዋል…'

የታማኞች ሠራዊት ሆይ! በዚህ የአምላክ ትውስታ ለታወጀው፣ ለድምጼ ጆሮዎቻችሁን አቅኑ። በእውነቱ በእኔ የተዘረዘረው የትውስታው መንገድ ትክክለኛው የአምላክ መንገድ መሆኑን፣ ከዚህ ከቀጥተኛ እምነት በቀር ሌላ ሃይማኖት የሚከተል ማንም ሰው፣ በፍርድ ቀን ሲጠየቅ፣ በመጽሐፉ ውስጥ እንደተመዘገበው ከአምላክ ሃይማኖት ምንም ጥቅም እንዳልሰበሰበ ይረዳል።

የነገሥታት ሠራዊት ሆይ፣ የእርሱ ትውስታ በሆነው ድንቅ አንደበት እንደተነገረው፣ እውነቱ ከመጽሐፍና ከምልክቶች ጋር ከአምላክ ከመጣላችሁ በኋላ፣ የእርሱ ትውስታ (ባብ)ከሆነው እንደራቃችሁ እንዳትቀሩ፣ አምላክን ፍሩ። በእርሱ ከአመናችሁ በኋላ፣ አምላክ ስፋቱ እንደመላው ገነት ስፋት የሆነውን የአትክልት ሥፍራ ያዘዘላችሁ ስለሆነ፣ ከአምላክ ጸጋ ፈልጉ። በዚህ ታላቅ እምነት ምክንያት፣ በእናት መጽሐፉ እንደታዘዘው፣ ፍጹም ኃያሉ በጸጋው ከሰጣቸው ስጦታዎችና ችሮታዎች በቀር በዚያ ሌላ ምንም አታገኙም።

## (9)

ፍላጎታችን ቢሆን ኖሮ፣ በራሳችን አንዲት ፊደል መሣሪያነት ብቻ ዓለምና በውስጧ ያለው ሁሉ፣ ከአንዲት የዓይን መርገብገብ በአነሰች ጊዜ ውስጥ፣ የእምነታችንን እውነተኛነት እንዲቀበል

---

[1] ቁርአን 6፡10

[2] ቁርአን 3፡172

ይከሳል።

አንተ በአምላክና በምልክቶቹ ማመንህንና በአንተም በትክክል መመራት ምክንያት እያንዳንዱ ሰው በትክክል መመራቱን፣ በእውነቱ አምላክ በመጽሐፉ ውስጥ መሥክሯል፤ እንዲሁም የእርሱ መላእክት ሠራዊት፣ መልእክተኞቹና እነዚያም መለኮታዊ ዕውቀት የተሰጣቸው መሥክረዋል። ይህ በእውነቱ ምን ጊዜም ሕያው የሆነው አምላክ፣ በገዛ ራሱ የሚኖረው፣ በጸጋው ቀድሞ ያጎናፀፈህ፣ ወደፊትም የሚያጎናፅፍህ ወሰን የሌለው ፀጋ ነው። ከፍጥረት በፊት በአምላክ፣ በማመንህም፣ እርሱ በእውነቱ፣ በራሱ ትእዛዝ፣ በእያንዳንዱ ግልጸት ጊዜ አስነሥቶሃል። ከእርሱ ከሉዓላዊው ጠባቂ፣ ፍጹም ክብር ከተመላው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

የአምላክን እምነት ከእርሱ ዘንድ እንደ ፀጋ ምልክት ለተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ማወጅ አለብህ፣ ከእርሱ ከእጅግ በጣም ለጋሡ፣ ከሁሉን አስገዳጁ በቀር ሌላ አምላክ የለም።

እንዲህ በል፡- ሁሉም ነገሮች ከአምላክ መፅሐፍ ውስጥ መታየት አለባቸው፤ እኔ በእርግጥ በአምላክና በምልክቶቹ ለማመን የመጀመሪያው ነኝ፤ እውነቱን ይፋ የማወጣውና የማውጀው እኔ ነኝ፤ እያንዳንዱን የኃያሉ፣ ወደር የሌለው አምላክ የላቀ ስያሜ ተሰጥቻለሁ። በእውነቱ የመጀመሪያውን ክስተት ቀን ተቀዳጅቻለሁ። በጌታ ትእዛዝና እንደ ጸጋው ምልክት፣ የኋለኛውንም ክስተት ቀን እቀዳጃለሁ። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ በተወሰነውም ሰዓት እያንዳንዱ ሰው በማምለክ በፊቱ ያጎነብሳል።

ባለፉትም ዘመናት በመጪዎቹም ዘመናት የእርሱን እምነት የሚያብራራ በመደረግ በእርሱ በመመረጤ አምላክን አመሠግናለሁ፤ ደግሞም አወድሠዋለሁ፤ ከእርሱ ከተከበረው፤ ከፍፁም ተወዳሹ፣ ከዘላለም ነዋሪው በቀር ሌላ አምላክ የለም። በሰማያት ውስጥና በምድር ላይ የሚገኙ ማናቸውም ነገሮች የእርሱ ናቸው፣ በእርሱም በትክክል እንመራለን።

የባያን ሕዝብ ሆይ! በመጽሐፉ ውስጥ እንደታዘዘው፣ እነዚያ እውነትን የሚቀበሉ ወደ እኔ መዞር አለባቸው፤ እኔ ዘንድ መቅረብን ለሚቀዳጀውም ለማንኛውም ሰው መለኮታዊ መርሖ ይሠጠዋል።

(2)

**ለሙሐመድ ሻህ ከተላከው መልዕክት።**

አምላክ እኔን የፈጠረበት ነገር ሌሎቹ የተቀረጹበት የሸክላ አፈር አይደለም። እርሱ፣ ዓለማዊ ጠቢባን ሊገነዘቡት፣ ታማኞቹም ሊደርሱበት ከቶ የማይችሉትን አጎናጽፎኛል ... እኔ የአምላክ የመጀመሪያ ቃል ደጋፊ ምሰሶዎች ከሆኑት አንዱ ነኝ። እኔን ያወቀ ማንም ሰው፣እውነትና ትክክል ከሆነውን ሁሉ አውቋል፤ መልካምና ተገቢ የሆነውንም ሁሉ ተቀዳጅቷል፤ እኔን ሳይቀበል የቀረውም ማንም ሰው፣ እውነትና ትክክል ከሆነው ሁሉ ፊቱን አዙሯል፤ ለእያንዳንዱ ክፉና ተገቢ ያልሆነ ነገርም ተሸንፏል።

በጌታህ፣በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ጌታ፣ በዓለማት ሁሉ ጌታ ትክክለኝነት! አንድ ሰው በዚህ ዓለም የሚቻለውን ብዛት ሕንጻዎች ቢያቆምና የአምላክ ዕውቀት በሚያቅፈው መልካም ተግባር ሁሉ አምላክን ቢያመልክ፣ ጌታ ዘንድ መቅረብንም ቢቀዳጅ፣ ግን በአምላክ ፊት ሊቆጠር ከሚችል ያነሰ መጠን እንኳ ቢሆን፣ ለእኔ የክፋት ምልክት በልቡ ቢኖረው፣ ተግባሮቹ ሁሉ ወደ ባዶነት ይለወጣሉ፤የአምላክንም የፍቅር እይታዎች ይነፈጋል፤የቁጣም ማረፊያ ይሆናል፤ በእርግጥም ይጠፋል። በእውቀቱ ግምጃ ቤት የሚገኘው መልካም ነገር ሁሉ የሚደረስበት ለእኔ በመታዘዝ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የተመዘገበውም እያንዳንዱ እሳት ለእኔ ባለመታዘዝ እንደሚደርስ አምላክ ወስኗልና። በዚህ ቀንና ከዚህም ደረጃ፣ እነዚያን፣ ፍቅሬን የሚናፍቁትንና ትእዛዜን የሚከተሉትን፣ በገነት ውስጥ በሚገኙ ቤተ-

መንግሥቶች ሲኖሩ፣ መላውን የጠላቶቼን አጀብ ደግሞ ወደ ገሀነመ እሳት የመጨረሻ አዘቅት ተላልፈው የምመለከታቸው ይመስለኛል።

በሕይወቴ! የእርሱን አምላክ ምሥክር የሆነውን እምነቱን መቀበል ግዴታ ባይሆን ኖሮ … ይህን ባላወጅኩልህ ነበር....አምላክ የመንግሥተ-ሰማያትን ቁልፎች በሙሉበቀኝ እጄ፣ የገሀነምንም ቁልፎች በግራ እጄ ለማድረግ መርጧል …

እኔ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ የፈለቁበት ቀዳማዊ ነጥብ ነኝ። እኔ ድምቀቱ ሊጋረድ ከቶ የማይችል የአምላክ ገጽታ፣ ጮራው ሊደበዝዝ ከቶ የማይችል የአምላክ ብርሃን ነኝ። እኔን ለሚቀበለኝ ሰው፣ መጽናናትና መልካም ነገር ሁሉ ተዘጋጅቶለታል፣ እኔን ሳይቀበል የሚቀረውንም ሰው፣ ገሀነማዊ እሳትና ክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቀዋል …

ወደር በሌለው፣ ተመዛዛኝ በሌለው፣ በእውነተኛው አምላክ እምላለሁ፡- እርሱ ፍጹም ከፍተኛው የአምላክ ምሥክር፣ ግልጽ ምልክቶችና መታወቂዎች ያጎናጸፈኝ፣ ሁሉንም ሰዎች ለእርሱ እምነት መገዛትን ለማስቻል ዓላማ እንጂ ለሌላ ለምንም ምክንያት አይደለም።

በእርሱ፣ ፍጹሙ እውነት በሆነው ትክክለኝነት፣ ግርዶሹ ቢነሣ ኖሮ፣ በዚህ በምድራዊ ዓለም ደረጃ፣ ሰዎች ሁሉ በአምላክ ቁጣእሳት፣ በኃይለኛውና ከገሃነም እሳት በበለጠው እሳትክፉኛ ሲሰቃዩ ባየህ ነበር፣ ከእነዚያ በፍቅሬ ዛፍ ጥላ ሥር መጠለያ ከፈለጉት በቀር። እነርሱ በእርግጥ፣ ከእነዚያ በሐሴት ከተመሉት ናቸውና . . .

(3)

<u>ለመካ ሹም (ሸሪፍ) የተፃፉ ቃላት ካሉበት መልእክት።</u>

ሸሪፍ ሆይ! … ሕይወትህን በሙሉ ለእኛ ስግደት

አቅርበሃል፤ ራሳችንን በከሰትንልህ ጊዜ ግን፣ ለማስታወሻችን ከመመሥከር፣ እርሱ በእርግጥ ከሁሉም በላይ የተከበረ፣ ሉዓላዊው እውነት፣ ፍጹም ክብር የተመላው መሆኑን ከማረጋገጥ ወደኋላ ቀርተሃል። ስለዚህ ጌታህ በትንሣኤ ቀን ፈትኖሃል። በእውነቱ እርሱ ሁሉን አዋቂው፣ ፍጹም ጠቢቡ ነው።

መጽሐፉን በላክንልህ ጊዜ *'እዚህ ነኝ'* ብለህ በተናገርከ ኖሮ፣ ወደ እነዚያ በእውነት ወደሚያምኑት አገልጋዮቻችን ማኅበር እንድትገባ በፈቀድንልህ፣ ሁሉም ሰዎች ለፍርድ እፊታችን እስከሚቀርቡባትም ቀን ድረስ በመጽሐፋችን በጸጋ በአመሰገንህ ነበር። ይህ በእውነት ሕይወትህን በሙሉ፣ እንዲሁም መጀመሪያ ከሌለው መጀመሪያጀምሮ ለጌታህ አምልኮት ከአከናወንክባቸው ተግባራት በሙሉ የበለጠ በጠቀመህ ነበር። ያለምንም ጥርጥር ይህ ከሁሉ በላይ የሆኑትን ጥቅሞችህን አሁንም፣ ለዘለዓለምም በጠበቀ ነበር። በእውነቱ እኛ ሁሉን ነገሮች እናውቃለን። ሆኖም ምንም እንኳ በትንሣኤ ቀን እኛ ዘንድ መቅረብን ለመቀዳጀት ዓላማ ወደ መኖር የጠራንህ ቢሆንም፣ አንተ ያለ ምንም ምክንያት ወይም ያለግልጽ ጽሑፍ ራስህን ከእኛ ጋርደሃል፤ ከእነዚያ የባያን ዕውቀት ከተለገሡት መካከል ብትሆን ኖሮ፣ ገና መጽሐፉን ስታይ፣ ወዲያውኑ ከእርሱ፣ በአደጋ ጊዜ ረዳት፣ በገዛ ራሱም ከሚኖረው በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ በመሠከርክ ነበር፤ እርሱ ቁርአንን የገለጸው፣ ይህንንም መጽሐፍ የገለጸ መሆኑን፣ እያንዳንዱም የዚያ ቃል ከአምላክ መሆኑን፣ ለዚያም እኛ ሁላችን እንደምንገዛ በአረጋገጥክ ነበር።

ሆኖም፣ ያ አስቀድሞ ታዞ የነበረው ተፈጸመ። ገናግልጸት በእኛ በኩል መገለጹን እየቀጠለ እያለ ወደ እኛ ብትመለስ፣ እሳትህን ወደ ብርሃን እንለውጣለን። በእውነቱ በነገሮች ሁሉ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን ነን። ግን ይህን ተግባር ሳትፈጽም ብትቀር፣ የአምላክን እምነት ከማቀፍና፣ እርሱ በጸጋው ለመበልፀግእንዲያስችልህና እሳትህ ወደ ብርሃን እንዲለውጥልህ ያደርግ ዘንድ፣ በማን የማመንህ ጉዳይ

ወደ እርሱ፣ አምላክ ወደሚከስተው ፊት እንዲቀርብ ከመማፀን በቀር ሌላ ክፍት የሚሆንልህን መንገድ አታገኝም። ይህ ያ ከላይ ወደ እኛ የተላከው ነው። ይህ ሳይፈጸም ቢቀር፣ እኛ ያሠፈርነው ማንኛውም የጸና ይሆናል። በአምላክ፣ በአደጋጊዜ ረዳቱ፣ በገዛ ራሱ ነዋሪውም በማይለወጥ ሁኔታ ይታዘዛል (ይፈረዳል)፤ ስለዚህም ከእኛ በኩል የፍትሕ ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ከእኛ ዘንድ እንድትባረር እናደርጋለን። በእውነቱ በፍርዳችን ትክክል ነን።

## ከቃይሙል - አስማ የተወሰዱ።

(4)

'በእውነቱ ዕድሜው ከሃያ አምስት ዓመት ያልበለጠ ሆኖ እያለ ስለአምላክ እንዴት ሊናገር ይችላል?' አትበሉ። አዳምጡኝ። በሰማያቱና በምድሩ ጌታ እምላለሁ፦ እኔ በእውነቱ የአምላክ አገልጋይ ነኝ። ከእርሱ ለረዥም ጊዜ ከተጠበቀው የአምላክ ምልክት ዘንድ የማይረቱ ማስረጃዎች ተሸካሚ ተደርጌአለሁ። በእውነቱ በአምላክ ዘንድ በእናት መጽሐፍ እንደተፃፈው፣ መጽሐፌ ይኸው በዓይኖቻችሁ ፊት ነው። በእውነቱ በምገኝበት በማንኛውም ሥፍራ አምላክ ብሩክ አድርጎኛል፤ በምድር ላይ በመካከላችሁ እስከኖርኩበትም ጊዜ ድረስ ጸሎትንና ጥንካሬን እንዳሳይ አዞኛል።

(5)

የምድር ሕዝብ ሆይ! በአንዱ እውነተኛ አምላክ ትክክለኝነት፤ እኔ፣ ለጋና ተርገብጋቢ የሆንኩ፣ ከድፍን ሩቢ በተቀረጸ ቤተ መንግሥት ውስጥ በመኖር ላይ የምገኝ፣ በባሃ መንፈስ የተወለድኩ የመንግሥተ ሰማያት ድንግል ነኝ፣ በዚህ ኃያል ገነት ውስጥ የዚህን አረባዊ ወጣት መልካም ምግባሮች ከፍ ከፍ በማድረግ፣

ያንን የአምላክን ትውስታ ከሚያውጀው በቀር ሌላ ምንም ነገር አይቼ አላውቅም። በእውነቱ ከጌታችሁ፣ ከፍጹም መሐሪው በቀር ሌላ አምላክ የለም። እነሆ በፍጹም ከፍተኛው ገነት እጅግ በጣም ማዕከላዊ እምብርት ውስጥ፣ የእርሱ ውዳሴ በሚነገርበት አዳራሽ፣ እንደ አምላክ ምስጋና ራሱን ያቀረበ ስለሆነ ደረጃውን ከፍ ከፍ አድርጉ።

አንድ ጊዜ ራሱን፣ ዘለዓለም ነዋሪውን፣ የቀናትቀደምቱን ሲያሞግሥ፣ በሌላም ጊዜ ስለእጅግ በጣም ክቡር ስሙ ምሥጢር ሲናገር ድምጹን እሰማለሁ። ስለአምላክ ታላቅነት መዝሙር በሚዘምርበት ጊዜ፣ ውብቱን አትኩሮ ለመመልከት በሚሰማው ናፍቆት፣ መላው ገነት ዋይታ ያሰማል፤ የአምላክን ውዳሴና ሙገሣ ከፍ ከፍ የማድረግ ቃላትንም በሚደግምበት ጊዜ፣ መላው ገነት ልክ በውርጭ በተዘጋ ተራራ ልብ ውስጥ እንደተዘጋ በረዶ እንቅስቃሴ አልባ ይሆናል። እያንዳንዱ ገነት የእርሱ የራሱ ገነት፣ እያንዳንዱ መንግሥተ-ሰማይ የእርሱ የራሱ መንግሥተ-ሰማይ፣ መላው ምድርና በውስጧ ያሉት ሁሉ ደግሞ በአገልጋዮቹ ጣት ላይ እንዳለች ቀለበት በሚታይበት፣ በቀጥተኛውና በመካከለኛው መንገድ እየተጓዘ እንዳለ ዓይነት በራዕይ የማየው ይመስለኛል። የእርሱ ፈጣሪ፣ የዘለዓለም ገዢነት ጌታ፣ የአምላክ ክብር ይስፋ። በእውነቱ እርሱ የአምላክ አገልጋይ፣ የጌታህ፣ የአምላክ ቀሪ ምልክት በር፣ ሉዓላዊው እውነት እንጂ ሌላ አይደለም።

## (6)

አንተ ከሁሉ በላይ የላቅህ የአምላክ ቃል ሆይ! ለእነዚያ ለጥሪህ ምላሽ ለሰጡት፣ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች በፍጹም ተወዳጁ ዘንድ እንደታወቀውና የአንተን ፍላጎት በመከተል፣ የኃጢአትን ይቅር ባይነት ስለአረጋገጥንላቸው፣ አታስብ፣ ወይም አትዘን። በእውነቱ የእርሱ ዕውቀት ሁሉን ነገሮች ያቅፋል። በሕይወቴ እማለድሃለሁ፤

ለማሥገደድ ችሎታ አለን …

በእርግጥ ከአንተ በፊት ሌሎች መልእክተኞች በፌዝ ተሰቀባቸዋል፣[1] አንተ በእውነት ኃይል ተደግፈህ የኖርክ የአምላክ አገልጋይ እንጂ ሌላ አይደለህም። በቅርቡ በእዚያ እጆቻቸው በሠሩዋቸው ሥራዎች ምክንያት የእነዚያን እውነቱን አንቀበልም ያሉትን ሰዎች ጊዜ እናራዝማለን፤[2] አምላክ ደግሞ በእውነቱ በማንም ላይ፣ በቴምር ፍሬ ላይ ያለች ነጥብ የምታክል ያህልም እንኳ ፍትሕ አያጓድልም።

(10)

እናንት የምድር ሕዝቦች ሆይ! በአምላክ በእውነተኛው ትክክለኝነት፣ የእርሱ በሆነው ትውስታ የተገለጸው ምሥክርነት፣ የመሐሪው ጌታ እጅ በእጅግ በጣም ማዕከላዊ የሰማይ እምብርት፣ በቀትር ሙሉ ድምቀቷ ወደምታበራበት ከፍታ ከፍ እንዳደረጋት ፀሐይ ነው…

ስለአምላክ ትውስታና ስለእርሱ ቀን፣ ቀድሞ ከላክናቸው ነቢያት ከእያንዳንዱ ነቢይ ጋር የተለየ ቃል ኪዳን መሥርተን ነበር። በክብር ዓለምና በእውነት ኃይል አማካይነት፣ በእርሱ የምሕረት ዙፋን ዙሪያ በሚሽከረከሩ መላእክት ዓይኖች ፊት፣ የአምላክ ትውስታና የእርሱ ቀን ግልጽ ናቸው።

(11)

ይህ ሃይማኖት በእውነቱ፣ በአምላክ ፊት፣ የሙሐመድ እምነት ፍሬ ነገር ነው፣ እንግዲህ በአምላክ ምልክቶች ማስረጃዎች ፊት ታጋሾችና አመሥጋኞች ለመሆን ብትችሉ፣ በአንዱና እውነተኛ አምላክ ዘንድ ወደምትገኘው ወደ መለኮታዊ ገነትና የመልካም ደስታው እጅግ በጣም ከፍተኛዋ የአትክልት ሥፍራ ለመድረስ ፈጠን በሉ።

(12)

የንጹህ ፍትሕ ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ስለትውስታችን እምነት ወደ እያንዳንዱ ነቢይ በእርግጥ የምሥራች ልከን ነበር፣ አምላክ በእውነቱ በዓለም ሕዝቦች ሁሉ ላይ የላቀ የበላይ ነው።

<u>ከፋርስኛው ባያን</u>

(13)

በምድር ላይ የሚገኘው ሃብት ሁሉ ባለቤት ከመሆን፣ አንድን ነፍስ መምራትይሻላል፤ ምክንያቱም የምድራዊ ሀብት ባለቤትነት በሞት ጊዜ የሚቆም ሲሆን፣ ያ የተመራው ነፍስ በመለኮታዊ አንድነት ዛፍ ጥላ ሥር እስከሆነ ድረስ ግን፣ እርሱም የመራውም ሰው የአምላክ የራኅራኄ ምሕረት ተቀባዮች ይሆናሉ። የመርሖመንገድ የፍቅርና የርኅራኄ እንጂ፣ የኃይልና የማስገደድ አይደለም። የአምላክ መንገድ ቀድሞም ይህ ነበር፣ ለወደፊቱም እንዲሁ መሆኑን ይቀጥላል! እርሱ የፈለገውን ወደ ምህረቱ ጥላ ሥር እንዲገባ ያደርገዋል። በእውነቱ፣ እርሱ የላቀው ጠባቂ፣ ፍጹም ቸሩ ነውና።

ለማንኛውም ነፍስ ለቀኑ የአምላክ ክስተት ከመገለጥ፣ ጥቅሶቹን ከመስማትና በእነሱ ከማመን፣ ሌላ ዘንድ ሳይሆን ወደ አምላክ ዘንድ መቅረብ ወደሆነው፣ ወደ እርሱ ዘንድ መቅረብን ከመቀዳጀት፣ በመልካም ደስታው መለኮታዊ መንግሥት ባሕር ላይ ከመጓዝ፣ ከእርሱም መለኮታዊ አንድነት ገነት ምርጥ ፍሬዎች ከመሳተፍ የሚበልጥ ድንቅ ገነት የለም።

(14)

አምላክን፣ ስግደትህ ወደ እሳት ቢመራህም፣ በአምላለክህ ምንም ለውጥ በማይፈጥር ሁኔታ አምልክ፣ ካሣህ ገነት ቢሆንም

እንዲሁ። ለአንዱና እውነተኛው አምላክ የሚገባው ስግደት እንዲህ ያለና እንዲህ ያለ ብቻ ነውና። በፍርሐት ምክንያት ብታመልከው፣ ይህ እርሱ ለሚገኝበት የተቀደሰ መንበር ተገቢ አይደለም፣ ለሕያውነቱ አንድነት በአንተ እንደቀረበ ተግባርም ሊቆጠር አይችልም። ወይም ትኩረትህ በገነት ላይ ቢሆን፣ እንዲህ ያለውንም ተስፋ በማደረግ ብታመልከው፣ ምንም እንኳ ገነት በሰዎች የምትፈለግ ብትሆንም፣ የአምላክን ፍጡር ከእርሱ ጋር ተጋሪ ታደርጋለህ።

ገሃነምም ገነትም በአምላክ ፊት አጎንብሰውና ተዘርረው ይሠግዳሉ። ለእርሱ ሕልውና ብቁ የሚሆነው፣ ያለ እሳት ፍራቻ፣ ወይም ያለ ገነት ተስፋ፣ ለራሱ ተብሎ እርሱን ማምለኩ ነው።

ምንም እንኳ እውነተኛ ሥግደት ሲቀርብ፣ ሥግደት አቅራቢው ከእሳት የሚድን፣ ወደ አምላክ መልካም ደስታ ገነትም የሚገባ ቢሆንም፣ የተግባሩ አነሳሽ እንዲህያለ ነገር መሆን የለበትም። ነገር ግን የአምላክ ችሮታና ፀጋ፣ የእርሱ በምርምር ሊታወቅ የማይቻል ጥበብ በሚጠይቀው ሁኔታ ምን ጊዜም ይጎርፋሉ።

ከሁሉ የበለጠ ተቀባይነት ያለው ጸሎት በከፍተኛ መንፈሳዊነትና ደስተኝነት የተደረገው ነው፤ እርዝማኔው በአምላክ ተወዶም አያውቅም አይወደድምም። ጸሎቱ ይበልጥ የተላቀቀና ይበልጥ ንጹህ በሆነ ቁጥር በአምላክ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ ይሄዳል።

(15)

በመለኮታዊ አንድነት አማኞች አስተሳሰብ፣ የአምላክን ትዕዛዛት ከመታዘዝ ይበልጥ ከፍ ያለ ገነት የለም። በእነዚያ አምላክንና ምልክቶቹን በአወቁት ሰዎች ዓይኖች፣ ሕግጋቱን ከመተላለፍና የሰናፍጭ ፍሬን ያህልም እንኳ ቢሆን፣ ሌላውን ነፍስ ከመጨቆን የሚብስ ገሀነመ እሳት የለም። በትንሣኤ ቀን አምላክ፣ በእውነት፣በሰዎች ሁሉ ላይ ፍርድ ይሰጣል። በእውነቱ እኛ ሁላችንም ለጸጋው እንማጸናለን።

(16)

አምላክ እነዚያን ንጹሃን የሆኑትን ይወዳል። በባያን ውስጥና በአምላክ ፊት ከንጹህነትና ጉድፍ ከማይገኝበት ንጽህና ይበልጥ የተወደደ ምንም ነገር የለም …

በባያን ክፍለ ዘመን፣ አምላክ ማንኛውንም ነፍስ ከሐሴትና ከደስታ ተነፍጎ ለማየት አይሻም። እርሱ በእውነቱ ለሌሎች ቀርቶ፣ ለራሳቸውም እንኳ የማስጠላት ስሜት እንዳይሰማ፣ በሁሉም ሁኔታ ሥር ሆነው በውሳጣዊውም ረገድ፣በከፍተኛ ንጽህና እንዲያጌጡ ይሻል።

(17)

ከህይወታችሁ መጀመሪያ ጀምራችሁ እስከ መጨረሻ ሥራዎቻችሁን ለአምላክ ብላችሁ ታከናውናላችሁ፤ነገር ግን አንድም ተግባር ለእርሱ፣እያንዳንዱ መልካም ተግባር ወደ እርሱ ለሚመለሰው ለአምላክ ክስተቱ ተብሎ አይደለም።በዚህ አኳኋን ሠርታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ በትንሳኤ ቀን በከባድ ሁኔታ ባልተሰቃያችሁ ነበር።

እምነቱ እንዴት ታላቅ እንደሆነ፣ ሆኖም ሕዝቡ እንዴት በመሸፈኛ እንደተጠቀለለ ተመልከቱ። ለአምላክ የቀረበ እያንዳንዱ እውነተኛ ውዳሴና ተግባር ለእርሱ፣አምላክለሚከስተው የተደረገ ውዳሴና ተግባር እንጂ ሌላ እንዳልሆነ በተቀደሰው የአምላክ ሕልውና እምላለሁ።

ባለ መልካም ምግባር ሳትሆኑ ባለ መልካም ምግባር የሆንነው ለአምላክ ብለን ነው ብላችሁ እራሳችሁን አታታልሉ። በእውነት ሥራችሁን ለአምላክ ብላችሁ የምትሠሩ ብትሆኑ ኖሮ፣ ለእርሱ፣ አምላክ ለሚከስተው በመሥራት፣ ስሙንም ከፍ ከፍ በማድረግ ላይ በሆናችሁ ነበር። ከእውነት የመረዳት ችሎታ የተራቁቱ የዚህ ተራራ ነዋሪዎች፣ 'ከአምላክ በቀር ሌላ አምላክ የለም' የሚሉት ቃላት ያለማቋረጥ ይናገራሉ፤ ግን ምን ጥቅም ይሠጣቸዋል? ልክ

በመጋረጃ እንደተዘጋ ሰው፣ ከእርሱ፣ የግልጸት የቀን ምንጭ ከሆነው እንዳትዘጉ፣ ለጥቂት ጊዜ አሰላስሉ።

## (18)

አምላክ በሁሉ ጊዜና በሁሉም ሁኔታ፣ ከፍጡሮቹ ሙሉ በሙሉ ነፃ ነበር። እርሱ ሰዎች ሁሉ በከፍተኛ ፍቅር የገነቱ አትክልት ሥፍራዎች እንዲቀዳጁ፣ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ፣ ማንም ሌላውን እንዳያሳዝን፣ የእርሱ አምላክ የሚከሰተው ግልጸት የቀን ምንጭ መጀመርን እስከሚያመለክተው እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ፣ ሁሉም በእርሱ ጥበቃና ደህንነት አንቀልባ ውስጥ እንዲኖሩ የጠበቀ ፍላጎት ነበረው፣ ለዘላለምም ይኖረዋል።

የበረከቱ መውረድ የማያቋርጥና ወሰን የሌለው ስለሆነ፣ የሁለንተን ዓለም ጌታ ነቢይ አስነስቶ፣ መጽሐፍም ልኮ ከሁሉም ሰዎች ጋር ቃል ኪዳኑን ሳይመሠርት፣የሚቀጥለውን ግልጸትና የሚቀጥለውን መጽሐፍ እንዲቀበሉ ሳይጠራቸው ቀርቶ ከቶ አያውቅም።

## (19)

በእያንዳንዱ የሥነ-ፍጥረት ዕውቀት የተካነ ሕዝብ ቁጥር እንዴት ሰፊ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ የእያንዳንዱ ሥነፍጥረት ዕውቀት ፍሬ፣ መለኮታዊ ሕግጋትንማወቅና ለእርሱም መልካም ደስታ መገዛት ስለሆነ፣ እምታቸውን የሚወስነው የአምላክን ቅዱስ ቃል የመከተላቸው መጠን ነው።

## (20)

የባያን ሕዝብ ሆይ! በትንሣዔ ቀን ማንም የሚሸሽበት ሥፍራ አያገኝምና ተጠንቀቁ። እርሱ በድንገት ያበራል፤ፍርድንም እንደፈለገ

ይፈርዳል። ፍላጎቱ ከሆነ ልክ በባያን እንዳደረገው የተዋረዱትን እንዲከበሩ፣ የተከበሩትንም እንዲዋረዱ ያደርጋል፤ ለመረዳት ብትችሉ ኖሮ። ከእርሱ በቀር ማንም ከዚህ ጋር አይስተካከልም። እርሱ ያዘዘው ማንኛውም ነገር ይፈጸማል፤ ምንም ነገር ሳይፈጸም አይቀርም።

(21)

ሰዎች ሁሉ ከአምላካዊነቱና ከገዥነቱ ምልክቶች ጥላ ስለመነጩ፣ ሁል ጊዜ በክቡርና ከፍ ባለ መንገድ ለመጓዝ ወደ መምረጥ ያዘነብላሉ። ተወዳጃቸውን ለማወቅ የሚያይ ዓይን የሌላቸው በመሆናቸውም፣ ለእርሱ ቅንነትንና ትህትናን የማሳየት ተግባራቸውን ለመፈጸም ሳይበቁ ይቀራሉ። ሆኖም፣ ከሕይወታቸው መጀመሪያ እስከ መጨረሻው፣ በፊተኛው ሃይማኖት የተመሠረቱትን ሕግጋት በመከተል፣ አምላክን ያመልካሉ፤ በመንፈሳዊነት ያወድሱታል፤ በመለኮታዊ እውነታው ፊት ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ፣ ለተከበረው ህልውናውም ታዛዥነትን ያሳያሉ። በእርሱ መከሰቻ ጊዜ ግን ከእውነት በራቀ እምነት፣ እርሱን ከራሳቸው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ አድርገው ስለሚቆጥሩት፣ እነርሱ ሁላቸውም ትኩረታቸውን ወደ ራሳቸው ያዞራሉ፣ በዚህም ከእርሱ ራሳቸውን ይጋርዳሉ። እንዲህ ያለው ማነጻጸር ከአምላክ ክብር የራቀ ነው። በእውነቱ፣ ያ የተከበረው ሕያው፣ ግዙፉን ፀሐይ ይመስላል፤ የእርሱ ጥቅሶች እንደጨረሮችዋ ናቸው፤ አማኞችም ሁሉ፣በእውነት የሚያምኑበት ከሆኑ፣ ፀሐይዋ በውስጣቸው እንደምታንፀባርቅባቸው መስተዋቶች ናቸው። ስለዚህ ብርሃናቸው ነፀብራቅ ብቻ ነው።

(22)

በጸሎት ጊዜያት ለብቻ መሆን የታዘዘበት ምክንያት ይህ ነው፤አምላክን ለማስታወሻ ፍፁም ትኩረትህን ለመስጠት ትችል

ዘንድ፣ በሁሉም ጊዜያት ልብህ በእርሱ መንፈስ ትነቃቃና ከእጅግ በጣም ተወዳጅህም በግርዶሽ እንደተጋረደ እንዳትጋረድ ነው። ልብህ ወደ ተከበረው የክብር ቁንጮ፣ ወደ ቁርባንም የትኩረት ነጥብ ሳይስተካከል አንደበትህ ለአምላክ አፍአዊ ውዳሴ አያቅርብ። ስለዚህ ምናልባት በትንሣኤ ቀን ብትኖር፣ የልብህ መስተዋት ወደ እርሱ ወደእውነት የቀን ኮከብ ይዞራል፤ ወዲያው ብርሃኑ ሲያበራም የዚያ ደማቅ ብርሃን በቀጥታ በልብህ ውስጥ ይንጸባረቃል። እርሱ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነውና፤ ሁሉ ነገሮችም ወደ እርሱ ይመለሳሉ። ነገር ግን አንተ በጥልቀት በማሰላሰል ወደ ራስህ ዞረህ ሳለህ እርሱ ቢገለጽ፣ እርሱ በገለጻቸው ቃላት ስሙን ካልጠራህ፣ ይህ አይጠቅምህም። ምክንያቱም በሚመጣው ግልጸት የአምላክ ትውስታ እርሱ ነውና፤ በአሁኑ ጊዜ የምታቀርባቸው ፀሎቶች በባያን ነጥብ የታዘዙትን ሲሆን፣ እርሱ በትንሣኤ ቀን በድምቀት የሚያበራው ደግሞ ከዚያ እርሱን ከቀደመው ይበልጥ ታላቅ፣ መለካት ከሚቻል በላይ ይበልጥ ታላቅ የሆነ ግልጸት -በባያን ነጥብ ውስጥ ተደብቆ የነበረው የውሳጣዊ እውንነት መገለጽ ነው።

(23)

አገልጋዬ፣ ከእያንዳንዱ ጸሎት በኋላ፣ በወላጆቹ ላይ ምህረትንና ይቅር ባይነትን ያጎናጽፍ ዘንድ፣ አምላክን መማጸን ተገቢ ነው። በዚያን ጊዜም *'ለወላጆችህ የጠየቅኸው ሺህ በሺህ እጥፍ የአንተ ካሳ ይሆናል!'*የሚል የአምላክ ጥሪ ይሰማል።ከአምላክ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ወላጆቹን የሚያስታውስ የተባረከ ነው። በእውነቱ፣ ከእርሱ፣ ከኃያሉ፣ ከእጅግ በጣም ተወዳጁ በቀርሌላ አምላክ የለም።

(24)

ይህ ሥጋዊ አቋም የውሳጣዊው መቅደስ ዙፋን እንደመሆኑ መጠን፣ በፊተኛው ላይ የሚደርስ ማንኛውም ነገር ለኋለኛው ይሰማዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ በሀሴት የሚደሰተው ወይም በሕመም የሚሰቃየው አካሉ ራሱ ሳይሆን፣ የአካሉ ውሳጣዊ መቅደስ ነው። ይህ ሥጋዊ አካል ውሳጣዊ መቅደስ የሚያርፍበት ዙፋን ስለሆነ፣ መከፋትን የሚያስከትል ምንም ሁኔታ እንዳይደርስበት፣ አካሉ በተቻለ መጠን በደህንነት ተጠብቆ እንዲቆይ አምላክ አዟል። ውሳጣዊው መቅደስ የራሱ ዙፋን የሆነውን የራሱን ሥጋዊ አካል ይመለከታል። ስለዚህ የኋለኛው ክብር ከተሰጠው፣ ልክ የፊተኛው ተቀባይ እንደሆነ ያህል ነው። ተቃራኒውም እውነት ነው።

ስለዚህ፣ አስከሬኑ በከፍተኛ ክብርና አክብሮት መያዝ እንዳለበት ተደንግጓል።

(25)

አንዱና እውነተኛው አምላክ ከፀሐይዋ ጋር፣ አማኙ ደግሞ ከፊት መመልከቻ መስተዋት ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ። መስተዋቱ ከፀሐይዋ ፊት እንደተደረገ ወዲያው ብርሃንዋን ያንፀባርቃል። የማያምነው በድንጋይ ሊመሰል ይችላል። ለፈለገው ያህል ጊዜ ለፀሐይዋ ብርሃን ቢገለጥ፣ ፀሐይዋን ሊያንፀባርቅ አይችልም። ስለዚህ ፊተኛው ሕይወቱን እንደመስዋዕት ይሰጣል፣ ኋለኛው ደግሞ በአምላክ ላይ የሚፈጽመውን ይፈጽማል። በእውነቱ አምላክ ቢፈልግ፣ ድንጋዩን ወደ መስተዋት ለመለወጥ ኃይል አለው፣ ነገር ግን ግለሰቡ ራሱ በራሱ ሁኔታ እንደተስማማ ይቀጥላል። እርሱ መስተዋት ለመሆን ፈልጎ ቢሆን ኖሮ፣ አምላክመስተዋትቅርጽ እንዲይዝ ባደረገው ነበር። በዚያ ቀን አማኙን በእርሱ እንዲያምን

የሚያነሳሳው ማንኛውም ምክንያት፣ ይኸው ደግሞ ለማያምነውም ክፍት ነው። ነገር ግን የኋለኛው ራሱን በመሸፈኛ እንዲጠቀለል ሲያደርግ፣ ያው ምክንያት በግርዶሽ እንደተጋረደ ሰው ይጋርደዋል። ስለዚህ ዛሬ በግልጽ እንደሚታወቀው፣ እነዚያ ወደ አምላክ ወደ እውነተኛው ፊታቸውን የመለሱት፣ በባያን ምክንያት ሲያምኑት፣እነዚያ የተጋረዱት ደግሞ በዚያው ምክንያት ተነፈጉ።

(26)

ከህልውናችን ፍሬ ጥቅም እንድናገኝ፣አምላክ ዘንድ ለመቅረብም ከሙብቃት እንዳንነፈግ፣ስለእርሱ፣በትንሣኤ ቀን አምላክ ስለሚከስተው ያወቅን ለመሆን ለአስቻለን አምላክ ምስጋና ይሁን። በእውነቱ የመፈጠራችን ዓላማና ልናከናውነው የምንችለው የእያንዳንዱ መልካም ተግባር ብቸኛ ምክንያት ይህ ነውና። አምላክ ያጎናፀፈን በረከት እንዲህ ያለ ነው፤ በእውነቱ እርሱ ፍጹም ለጋሥ፣ ፀጋ የተመላው ነው። መጠራጠር በሌለበት እምነት ብታምን፣ ይህን ዓላማ ከግቡ እንደምታደርስ እወቅ። ነገር ግን መሰናከል በሚሆነው የራስ ወዳድነት ፍላጎት ግርዶሽ ምክንያት መጠራጠር የሌለበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ ስለማትችል፣ ምንም ባይታወቅህም እንኳ፣ በገሀነም እሳት ውስጥ ትቆያለህ። በእርሱ መከሰት ቀን፣ እያንዳንዱን መልካም ተግባር ብታከናውንም እንኳ፣ በእርሱ በእውነት ከማመኑ በቀር፣ ሌላ ምንም ነገር ከገሀነም እሳት ሊያድንህ አይችልም። እውነቱን ብታቅፍ፣ እያንዳንዱ መልካምና ተገቢ ነገር በአምላክ መዝገብ ውስጥ ይሠፍርልሃል፤ በዚህ መልካም ምግባር ምክንያት እስከሚቀጥለው ትንሣኤ ድረስ በእጅግ በጣም ከፍተኛው ገነት ውስጥ ሐሴት ታደርጋለህ።

መንገዱ ከሰማያትና ከምድር በመካከላቸውም ከሚገኘው የሰፋ ሆኖ እያለ፣ በጣም ጠባብ ስለሆነ፣ በተገቢ ጥንቃቄ መርምረው። ለምሳሌ ለእነዚያ ኢየሱስ የሰጠውን የትንቢት ቃል

ፍፃሜ ይጠባበቁ ለነበሩት ሁሉ፣ የአምላክ መልዕክተኛው፣ የሙሐመድ ክስተት ፍፃሜው መሆኑ ቢረጋገጥላቸው ኖሮ፣ አንዳቸውም ከኢየሱስ ቃላት ባልተገለሉ ነበር። እንዲሁም በባያን ነጥብ ግልጸት፣ ይህ በአምላክ መልዕክተኛው በቅድሚያ የተነገረለት ያ ቃል የተገባለት ምሕዲ (ያ መርሖን የተመራው) መሆኑ ለሁሉ ቢረጋገጥላቸው ኖሮ፣ ከቁርአን አማኞች ውስጥ አንዱም ከአምላክ መልዕክተኛው ቃላት ባልተገለለ ነበር። እንዲሁም ደግሞ በእርሱ አምላክ በሚከስተውም ግልጸት፣ ተመሳሳይ ነገር ሊደርስ እንደሚችል አስተውል፤ እርሱ ያው የባያን ነጥብ አስቀድሞ የተነበየለት *'ያ አምላክ የሚከስተው'* መሆኑ ለሁሉ ከተረጋገጠለት፣አንዱም አይገለልም።

<u>**ከዳላኢል-ኢ-ሰብዒ**</u>

(27)

ስለ ሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርቶችና ስለትዕዛዞቹ ጠይቀሃል፡- በሃይማኖት የመጀመሪያውና ቀዳሚው አምላክን ማወቅ መሆኑን ዕወቅ። ይህ፣ በተራው የእርሱ የተቀደሠና የተከበረ መቅደስ፣ የእርሱ የላቀ ግርማ መቀመጫ፣ ከሁሉ ባህርያት የነፃ መሆኑን በመግለፅ ከፍፃሜ በሚደርሰው መለኮታዊ አንድነቱን በማወቅ ይደመደማል። በዚህ በህያው ዓለም ደግሞ አምላክን ማወቅ እርሱን የመለኮታዊ እውንነት የቀን ምንጭ የሆነውን በማወቅ በቀር ሊደረስበት ከቶ እንደማይቻል ዕወቅ።

(28)

ጻጋ በተሞላው አምላክ! በአሁኑ ጊዜ በእስላም ክፍለ ዓለም ዓለምን በመግዛት ላይ የሚገኙ ሰባት ኃያላን ንጉሦች አሉ። አንዳቸውም ስለእርሱ (ስለባብ) ክስተት አላወቁም፣ ከአወቁም፣

አንዳቸውም በእርሱ አላመኑም። ማን ያውቃል፣ ይጠብቁት የነበረው ነገር መፈጸሙን ሳይገነዘቡ፣ በምኞት እንደተሞሉ ይህን ዝቅተኛውን ዓለም ትተውያልፉ ይሆናል። ወንጌልን አጥብቀው ይዘው በነበሩት ንጉሦች ላይ የደረሰው ይህ ነው። የአምላክን ነቢይ (የሙሐመድን) መምጣት ተጠባበቁ፤ እርሱ በመጣም ጊዜ፣ ሊያውቁት ሳይችሉ ቀሩ። በግዛቶቻቸው ስለ አምላክ ክስተቱ እነርሱን የማሳወቅ ሃላፊነት የተሰጠው ባለሥልጣን ለመመደብ ትንሽ ሃሳብ እንኳ ሳይኖራቸው፣እነዚህ ንጉሦች ወጪ የሚያደርጉት ገንዘብ ብዛት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አስተውል! በዚህ መንገድ የተፈጠሩበትን ዓላማ ከፍፃሜ ባደረሱ ነበር። ምኞታቸው ሁሉ የስሞቻቸውን ምልክቶች ከኋላቸው ከመተው ጋር ተጣብቆ ነበር፣ አሁንም እንደተጣበቀ ነው።

(29)

እስኪ አንዳንድ ምክንያትን የተከተሉ ማስረጃዎች ላቅርብልህ። አንድ ሰው ዛሬ የእስላምን እምነት ለመቀበል ቢፈልግ፣ የአምላክ ማስረጃዎች አሳማኝ ይሆኑለታልን? አይሆኑም ብለህ የምትከራከር ከሆነ፣ ከሞት በኋላ አምላክ የሚቀጣው፣ በሕይወትም ሳለ፣ ከሐዲ የሚለው ፍርድ የሚፈረድበት እንዴት ነው? ማስረጃው በቂ ነው የምትል ከሆነ፣ ይህን በማስረጃ እንዴት ታረጋግጣለህ? ማስረጃህ ሲነገር በሚሰማው ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ እንግዲህ ቃላት ብቻ እንደ በቂ ማስረጃ ተቀባይነት የላቸውም፣ ግን ቁርአንን እንደ ማስረጃ ከወሰድክ ይህ ከባድና ግልፅ ማስረጃ ይሆናል።

አሁን የባያንን ግልጸት አስተውል። የቁርአን ተከታዮች፣ በእነዚያ በእስላም በማያምኑት ላይ ከሚጠቀሙበት ማስረጃ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ማስረጃ በራሳቸው ላይ ቢጠቀሙ ኖሮ፣ አንድም ነፍስ ከእውነትባልተነፈገ ነበር፤ በትንሣኤም ቀን እያንዳንዱ መዳንን በተቀዳጀ ነበር።

አንድ ክርስቲያን *“ልረዳው የማልችል ሆኜ እያለሁ ቆርአንን እንደማስረጃ እንዴት አድርጌ ልውሰደው?”* ብሎ ቢከራከር፣ እንዲህ ያለው ክርክር ተቀባይነት የለውም። እንዲሁም የቆርአን ሕዝብ *“በባያን የሚገኙት ጥቅሶች የሚናገሩትን ልንገነዘብ አንችልም፣ እንዴት እንደማስረጃ ልንወስደው እንችላለን?”* በማለት በንቀት ይናገራሉ። እንዲህ ያሉትን ቃላት ለሚናገረው፣ እንዲህ በለው፡- “አንተ ያልተማርክ ሆይ! የእስላምን ሃይማኖት የተቀበልከው በምን ማስረጃ ነው? አይተሃቸው በማታውቃቸው ተአምሮች ነውን? እስላምን ሳታውቀው ተቀብለህ እንደሆነ፣ ስለምን እንዲህ አደረግህ? ግን እምነቱን የተቀበልከው ቆርአንን እንደማስረጃ ወስደህ፣ የተማሩትና ታማኞቹ በእርሱ ፊት ኃይል አልባነታቸውን ስለገለጹ፣ ወይም መለኮታዊ ጥቅሶችን በሰማህበት ጊዜ ለእውነተኛ የአምላክ ቃል ወዲያው በተሰማህ ፍቅር ምክንያት፣ ከዕውነተኛ ፍቅርና ግንዛቤ እጅግ በጣም ኃያል ምልክቶች መካከል አንዱ በሆነው መንፈስ ምክንያት፣ በፍጹም ትሕትናና ዝቅተኛነት መንፈስ ከተቀበልክ፣ እንዲህ ከሆነ፣ እንዲህ ያሉት ማስረጃዎች እንደትክክል ተቆጥረዋል፤ ለዘለዓለምም እንዲሁ እንደትክክል መቆጠራቸውን ይቀጥላሉ።

## (30)

ከአምላክ በቀር ከሁሉም ነገሮች ቁራኝነት ራስህን አላቅቅ። ከእርሱም በቀር ሌላው ነገር ሁሉ እንዲቀርብህ በማድረግ (ለመተው) ራስህን በአምላክ አበልጽግና ይህን ጸሎት ድገም፡-

> በል፡- አምላክ ሁሉን ነገሮች ከሁሉም ነገሮች በላይ ያረካል፤ በሰማይ ወይም በምድር ወይም በመካከላቸው በሚገኘው በማንኛውም ከጌታህ፣ ከአምላክ በቀር የሚያረካ የለም። በእውነቱ፣ እርሱ በራሱ፣ አዋቂው፣ ሕይወት ሰጪው፣ ምንም

የማይሳነው ነው።

የአምላክን ሁሉን አርኪነት ኃይል ከእውነት እንደራቀ ከንቱ እምነት አትቁጠር። ይህም በእያንዳንዱ ዘመን ለአምላክ ክስተት የሚኖርህ እውነተኛ እምነት ነው። በምድር ላይ ከሚገኙት ነገሮች በላይ እንደሚያረካው ያለው ጽኑ እምነት ነው። አማኝ ካልሆንክ፣ የመለኮታዊ እውነት ዛፍ የሕልውናህን መቋረጥ ፍርድ ይፈርድብሃል። አማኝ ከሆንክ ግን፣ ምንም ነገር ባይኖርህም እንኳ፣ እምነትህ በምድር ላይ ከሚገኙት ነገሮች ሁሉ በላይ በቂ ይሆንሃል።

(31)

ከመላው ሕዝበ ክርስቲያን ውስጥ የአምላክ መልእክተኛውን እምነት የተቀበሉት ከሰባ ሰዎች እንደማይበልጡ በመንፈሳዊ ታሪክ ውስጥ ተመዝግቧል። ወቀሳው በሊቃውንቶቻቸው ላይ ይወድቃል፣ ምክንያቱም እነዚህ ቢያምኑ ኖሮ፣ ብዙሃኑ የአገራቸው ሰዎች በተከተሉአቸው ነበርና። እንግዲህ የተፈጸመውን አስተውል! የክርስቲያን ምሁራን እንደ ምሁራን የሚቆጠሩት የክርስቶስን ትምህርት ደህንነት ለመጠበቃቸው ምክንያት ነው፤ ዳሩ ግን እነርሱ ራሳቸው እንዴት ሰዎች እምነቱን እንዳይቀበሉና መዳንን እንዳይቀዳጁ ምክንያት እንደሆኑ አስተውል!አሁንም በእነርሱ ፈለግ ለመከተል ፍላጎትህ ነውን? የኢሱስ ተከታዮች በትንሣኤ ቀን ለመዳን ብለው ቀሳውስቶቻቸውን ታዘዙ፣ በዚህ መታዘዝ ሳቢያም በመጨረሻው ወደ ገሃነመ እሳት ገቡ፣ የአምላክ መልዕክተኛውም በመጣበት ቀን የተከበረውን ማንነቱን ከማወቅ ራሳቸውን ዘጉ። እንዲህ ያሉትን ካህናት ለመከተል ትፈልጋለህን?

የለም፣ በአምላክ፣ እነዚህ ሁለቱም በትንሣኤ ቀን ሰለሚጠፉ፣ የማስተዋል ኃይል የሌለው ካህንም የማስተዋል ኃይል የሌለው ተከታይም አትሁን። ይልቁንም የሚያስተውል ካህን፣ ወይም ከማስተዋል ጋር እውነተኛውን የሃይማኖት መሪ በመታዘዝ በአምላክ

መንገድ መጓዝ ይገባሃል።

በእያንዳንዱ አገር እውነተኛ የማስተዋል ችሎታ የሌላቸው በብዛታቸው ከቁጥር በላይ የሆኑ የሃይማኖት ጉዳይ መሪዎች ታያለህ፣ በእያንዳንዱም ሕዝብ መካከል ይኸው ባሕርይ የሌላቸው እልፍ አእላፍ ተከታዮች ያጋጥሙሃል። ለትንሽ ጊዜ በልብህ አሰላስል፤ በራስህ ላይ ኃዘኔታ ይኑርህ፣ ትኩረትህንም ከማረጋገጫዎችና ከማስረጃዎች አታዙር። ሆኖም ማረጋገጫዎችንና ማስረጃዎችን ከእውነት በራቀ ከንቱ እምነት ላይ አትመሥርት፤ ይልቁንም፣ማስረጃዎችህን በዚያ አምላክ በመደበው ላይ መሥርት። ከዚህም በላይ፣ የዕውቀት ሰው መሆንም ሆነ ተከታይ መሆን፣ በራሱ የክብር ምንጭ እንዳልሆነ እወቅ። የእውቀት ሰው ብትሆን ዕውቀትህ ክብር የሚሆነው፣ ተከታይም ብትሆን፣ አመራር መከተልህ ክብር የሚሆነው፣ እነዚህ የአምላክን መልካም ደስታ የተከተሉ ከሆኑ ብቻ ነው። የአምላከንም መልካም ደስታ ከእውነት እንደ ራቀ እምነት እንዳትቆጥር ተጠንቀቅ። ይህም ከእርሱ መልእክተኛ መልካም ደስታ ጋር አንድ ነው። ስለኢየሱስ ተከታዮች አስብ። የአምላክን መልካም ደስታ በጉጉት ይፈልጉ ነበር፤ ዳሩ ግን ከእነዚያ የእርሱን እምነት ከአቀፉት በስተቀር፣ አንዳቸውም ከአምላክ መልካም ደስታ ጋር አንድየሆነውን፣ የእርሱን መልእክተኛ (የሙሐመድን) መልካም ደስታ አልተቀዳጁም።

## ከስሞች መጽሐፍ (ከኪታቢ አስማ)

(32)

አንድ ሰው አንድ እምነት አለኝ ብሎ ማስረጃዎቹን ቢያቀርብ፣ እነዚያ የእርሱን እውነተኛነት አንቀበልም ለማለት የሚፈልጉትም የእርሱን የመሳሰሉ ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ለማድረግ ከቻሉ፣ የእርሱ ቃላት ከንቱ መሆናቸው ይረጋገጥና እነርሱ ያሸንፋሉ፤ ያለበለዚያ የእርሱ ቃላት

(እውነተኛነት) አያቋርጥም፤ ማስረጃዎቹም የጸኑ ይሆናሉ። እናንተ በባያን የተጎናፀፋችሁ ሆይ፣ እውነት በጥብቅ ተደላድሎ የሚቆም ሲሆን ከዚያ በስተቀር ሌላው ማንኛውም ነገር የሚጠፋ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ እውነተኝነታችሁን ለማረጋገጥ ከፈለጋችሁ፣ እርሱ ከአቀረባቸው ማስረጃዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ማስረጃዎች ሳታቀርቡ ማንንም ሰው እንዳትከራከሩ አስጠነቅቃችኋለሁ።

አምላክ ወደ እርሱ ከላካቸው ማስረጃዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ማስረጃዎች ለማምጣት ኃይል ስላልነበራቸው ከአምላክ መልእከተኛው፣ ከሙሐመድ ጋር ክርክሮች ገጥመው የነበሩና በመጨረሻም የተደመሰሱ ሕዝቦች ቁጥር እንዴት የበዛ ነው።ቢያፍሩና ትሁታን ቢሆኑ ኖሮ፣ እርሱ የተጎናጸፋቸውም ማስረጃዎች ባህርይ እንዴት የተከበሩ እንደሆኑ ቢያውቁ ኖሮ፣ እርሱን ከቶ ባልተፈታተኑት ነበር። እነርሱ ግን ራሳቸውን እንደ ሃይማኖታቸው ጀግኖች ቆጠሩ። ስለዚህም አምላክ እንደየሥራቸው እጁን ጫነባቸው። ለእውነትም በእውነትኃይል አማካኝነት ተበቀለለት። ዛሬም እናንተ በመሐመዳዊው ግልጸት፣ በግልጽ የምታዩትን ይህንኑ ነው።

የፍጥረት ሁሉ ዕድል በእነርሱ የሚወሰን ሆኖ ሳለ፣ በእያንዳንዱ ዘመን የተከበሩትን የእውንነት ዙፋኖች ለመፈታተን የሚችል ሰው ከመካከላቸው ማነው? መጀመሪያ ከሌለው መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አምላክ እነዚያን እነርሱን የተቃወሙትን ሁሉ ጠራርጎ በማጥፋት በማያዳግም ሁኔታ በእውነት ኃይል አማካኝነት እውነትን አሳይቷል። በእውነቱ፣ እርሱ ኃያሉ፣ ምንም የማይሳነው፣ ፍጹም ኃይል የተመላው ነው።

(33)

በእያንዳንዱ ግልጸት መምጫ ወቅት፣ እነዚያ ለዚያ ግልጸት

ባለቤት ልቦቻቸውን የሚከፍቱት እንዴት እውነቱን እንደሚቀበሉ፣ የእነዚያ እውነቱንሳይቀበሉ የሚቀሩት ሰዎች ልቦች ደግሞ ራሳቸውን ከእርሱ በመጋረዳቸው ምክንያት እንዴት እንደሚዘጉ አስተውል። የልብ ክፍትነት ግን ለሁለቱም ወገኖች በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠ ነው። እርሱ (ሰውየው) ራሱን በመሸፋፈኛዎች እንዲጠቀለል በሚያደርግበት ጊዜ በስተቀር አምላክ ከሌሎች የበላይ የሆነውን ፍጡር ልብ ይቅርና፣ የማንንም ልብ፣ የጉንዳንን እንኳ ለመዝጋት አይፈልግም፣ አምላክ የሁሉ ነገሮች ፈጣሪ ነውና።

የእርሱን፣ አምላክ የሚከስተውን እምነት እንዲያቅፍ በመርዳት የአንድ ነፍስ ልብ እንኳ ብትከፍት፣ በጣም ውሳጣዊው ተፈጥሮህ በዚያ በተከበረው ስም አነቃቂ መንፈስ ይሞላል። ስለዚህ አብዛኞቹ ሰዎች ምስኪን በመሆናቸው፣ ልቦቻቸውን ብትከፍትና ጥርጣሬያቸውን ብታስወግድ፣ ወደ አምላክ እምነት መግባትን ይቀዳጃሉ። በትንሣኤ ቀናት ይህን ተግባር ማከናወን ይጠበቅብሃል። ስለዚህ በእርሱ አምላክ በሚከስተው ቀናት ችሎታህ እስከፈቀደ ድረስ ይህን ባህርይ አንፀባርቅ። በእውነቱ ለእርሱ ብለህ የአንድ ሰው ልብ ብትከፍት፣ ይህ ከእያንዳንዱ መልካም ተግባር ይሻልሃል፣ ተግባራት በእርሱ ከማመን፣ በእውነቱም እርግጠኛ ከመሆን ጋር ሲነፃፀሩ በሁለተኛ ደረጃ ናቸውና።

## (34)

ወንጌል ስለተሰጣቸው ሕዝብ አሰላስል። የሃይማኖት መሪዎቻቸው እንደ እውነተኞች የወንጌል መንገድ መሪዎች ይቆጠሩ ነበር፤ ሆኖም፣ ምንም እንኳ ገነትን ለመቀዳጀት ሲሉ የሕይወታቸውን ጊዜ ሁሉ የሃይማኖታቸውን ሕግጋት በታማኝነት ያከብሩ የነበረ ቢሆንም፣ከአምላክ መልእክተኛው ከሙሐመድ ራሳቸውን በዘጉ ጊዜ፣ ወደ ሥሕተት መንገድ መሪዎች ተለወጡ፤ ከዚያም አምላክ ገነት ለእነርሱ እንድትታወቅ በአደረገ ጊዜ፣ እነርሱ ወደዚያ ሊገቡ

አልፈለጉም። እነዚያ ቁርአን የተሰጣቸውም እንደዚያው አደረጉ። እርሱ እነርሱን በገነት ከፃድቃን ጋር ለመቀላቀል እንደሚያስችላቸው ተስፋ በማድረግ፣ ለአምላክ ሲሉ የስግደት ተግባራቸውን አከናወኑ። ነገር ግን፣ የገነት በሮች በፊቶቻቸው ወለል ተደርገው ሲከፈቱላቸው፣ እነርሱ አንገባም አሉ። ምንም እንኳ፣ ከገሃነም እሳት ወደ አምላክ መሸሺያ ሲፈልጉ የነበሩ ቢሆኑም፣ ራሳቸውን ወደዚያው (ወደ ገሃነም) እንዲገቡ አደረጉ።

በል፡- በእውነቱ፣ እውነቱ ከስሕተት የሚለይበት መመዘኛ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ አይገለጽም። ከእነዚያ እውነትን ከሚያፈቅሩት ብትሆኑ፣ ይህን ታውቃላችሁ። እስከ ትንሣኤ ቀን ምፅዓት ድረስ፣ በዚያ በባያን ውስጥ በተገለጸው መሠረት እውነትን ከሌላ ከማንኛውም ትለያላችሁ።

በመለኮታዊ ጥበብ በመጽሐፉ ውስጥ እንደታዘዘው፣ የመፈጠራቸው ዓላማ ከሆነው፣ ከእርሱ አምላክ ከሚከሰተው ልክ በግርዶሽ እንደተጋረዱ ራሳቸውን ስለሚዘጉና በማምለክ በፊቱ ስለማያጎነብሱ፣ በትንሣኤ ቀን ራሳቸውን እንደትክክለኞች የሚቆጥሩ፣ ግን በአምላክ ዘመን ወቅት ሐሰተኞች ሆነው የሚገኙ ሰዎች ቁጥር እንዴት ብዙ ነው።

## (35)

የመለኮታዊ መርሐንና የጽድቅን አልባስ ከራሳቸው በመግፈፋቸው ምክንያት ሕይወታቸውን ሙሉ የእሳት ልብስ ለብሰው እያሉ፣ በሐር መጎናጸፊያ ራሳቸውን የሚያስጌጡ ሰዎች ቁጥር እንዴት ብዙ ነው፣ እነዚያ ዕድሜያቸውን ሙሉ ከጥጥ ወይም ከሻካራ ሱፍ የተሠራ ልብስ የሚለብሱ፣ ሆኖም የመለኮታዊ መርሐና የጽድቅ ልብስ የተለገሡ በመሆናቸው በእውነቱ በገነት ልብስ ያጌጡና በአምላክ መልካም ደስታ የሚደሰቱትም ሰዎች እንዴት ብዙ ናቸው። ብትችሉ፣ በእውነቱ፣ ራሳችሁን በመለኮታዊ መርሐና በጽድቅ

በማስጌጥና ምርጥ ሐር በመልበስ ሁለቱን ብታጣምሩ በአምላክ ፊት የተሻለ ነው። ካልሆነ ግን ቢያንስ ቢያንስ ከጽድቅ ሥራ በራቀ ሁኔታ አትሥሩ፤ ይልቁንም የሃይማኖተኛነትንና የመልካም ምግባርን ሥራ ሥሩ።

ለእርሱ በዚህ ሕዝብ መካከል መገኘት ብቸኛ ምክንያት ባይሆን ኖሮ፣ ምንም ሕግ ባልደነገግን፣ ምንም ክልከላም ባላሠፈርን ነበር። በእርሱ መከሰት ሰዓት፣ በእርሱ አማካይነት የአምላክን መልካም ደስታ ትቀዳጁ ዘንድ፤ ለእርሱ ከሚያስጠሉትም ነገሮች ትርቁ ዘንድ፣ በፍላጎታችን አንዳንድ ሕግጋት የገለጽነው፣ ወይም የምንጠላቸውን ተግባራት የከለከልነው፣ ለስሙ መወደሻና ለእምነቱ መከበሪያ ብቻ ነው።

በል፡- የእርሱ፣ አምላክ የሚከስተው መደሰት የአምላክ መደሰት ሲሆን፣ የእርሱ፣ አምላክ የሚከስተው መከፋት ደግሞ የአምላክ መከፋት እንጂ ሌላ አይደለም። ከእርሱ መከፋት ራቁ፣ ለመሸሺያም ወደ መልካም ደስታው ሽሹ። በል፡- ወደ እርሱ መልካም ደስታ መንገድ መሪዎች የሆኑት፣ እነዚያ በእርሱ በእውነት የሚያምኑትና በእምነታቸው በጣም የጠለቁት ሲሆኑ፣ የእርሱ መከፋት ሕያው ማስረጃዎች ደግሞ እነዚያ ከእርሱ ዘንድ የተላኩትን የአምላክ ጥቅሶች በሚሰሙበት ወይም በእርሱ የተገለጹትን መለኮታዊ ቃላት በሚያነቡበት ጊዜ እምነቱን ወዲያው የማይቀበሉት፣ እርግጠኝነትም የማይቀዳጁት ናቸው።

## <u>ከተለያዩ ጽሑፎች</u>

## (36)

በል፡- አምላክ ጌታ ነው፤ ሁሉም ለእርሱ ሠጋጆች ናቸው።

በል፡- አምላክ እውነተኛው ነው፤ ሁሉም ለእርሱ ታዛዥነትን ይገልፃሉ።

ይህ እግዚአብሔር ጌታችሁ ነው፤ ወደ እርሱም

ትመለሳላችሁ።

ስለአምላክ አንዳች ጥርጣሬ አለን? እርሱ እናንተንና ሁሉን ነገሮች ፈጠረ። እርሱ የሁሉ ዓለማት ጌታ ነው።

(37)

የእርሱ፣ አምላክ የሚከሰተው ክብሩ ለመለካት በማይቻል ሁኔታ ከእያንዳንዱ ሌላ ክብር በላይ ነው፤ ግርማውም ከእያንዳንዱ ሌላ ግርማ በጣም ከፍ ያለ ነው። የእርሱ ውበት ከሌላ ከእያንዳንዱ የውበት ማኅደር ይልቃል፣ የእርሱ ታላቅነትም ከሌላ ከእያንዳንዱ የታላቅነት ክስተት በእጅጉ ይበልጣል። በእርሱ ብርሃን እንፀባራቂነት ፊት፣ እያንዳንዱ ብርሃን ይደበዝዛል፣ በእርሱ የምሕረት ምልክት ፊት፣ ሌላ እያንዳንዱ የምሕረት ምልክት ያንሣል። በእርሱ የተሟላ ፍጹምነት ፊት፣ እያንዳንዱ ሌላ ፍጹምነት እንደ ኢምንት ነው፣ በፍጹም ኃያልነቱም ፊት ሌላው እያንዳንዱ የኃያልነት ትዕይንት ምንም ኃይል እንዳልሆነ ነው። የእርሱ ስሞች ከሁሉም ሌሎች ስሞች የበላይ ናቸው። የእርሱ መልካም ደስታ ከማናቸውም ሌላ የመልካም ደስታ ገለጻ ቅድሚያን ይይዛል። የእርሱ የላቀ ባለክብር ልዕልና፣ ሌላው እያንዳንዱ የልዕልና ምልክት ሊደረስበት ከሚችለው በላይ በጣም ከፍ ያለ ነው። የእርሱ መልክ ውበት ከሌላ ከማንኛውም መልክ ውበት በጣም ይልቃል። የእርሱ መለኮታዊ ሥውርነት ከማንኛውም ሌላ ሥውርነት በጣም የበለጠ ጥልቅ ነው።የእርሱ ምጥቅት ከእያንዳንዱ ሌላ ምጥቀት ሊለካ ከሚቻል በላይከፍ ያለ ነው። የእርሱ ጸጋ የተመላው ችሮታ በምንም የችሮታ ማስረጃ አይደረስበትም። የእርሱ ኃይል እያንዳንዱን ኃይል ይበልጣል። የእርሱ ሉዓላዊነት በእያንዳንዱ ሌላ ሉዓላዊነት ፊት ሊሸነፍ አይችልም። የእርሱ መለኮታዊ ገዥነት፣ ከእያንዳንዱ ሌላ ገዥነት በላይ በጣም የተከበረ ነው። የእርሱ እውቀት የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ይናኛል፣ ፍፁም ሥልጣኑም ሕያዋንን ሁሉ የሚሸፍን ነው።

(38)

ሁሉም ሰዎች ከአምላክ መጡ፣ ወደ እርሱም ይመለሳሉ። ሁላቸውም ለፍርድ እርሱ ፊት ይቀርባሉ። እርሱ የትንሣኤ፣ የእንደገና መወለድና የመጠየቂያ ቀን ጌታ ነው፤ የተገለፀው ቃሉም ሚዛኑ ነው።

እውነተኛ ሞት የሚገኘው አንድ ሰው በእርሱ መከሰቻ ጊዜ እርሱን በቀር ሌላ ምንም እስከማይፈልግ ድረስ ለራሱ ሲሞት ነው።

እውነተኛ ከመቃብር ትንሣዔ ማለት፣ በፈቃዱ በመገዛት በእርሱ ቃላት ኃይል ሕያው መሆን ነው።

ገነት የእርሱን መልካም ደስታ መቀዳጀት ነው። ዘለዓለማዊ የገሀነም እሳትም በፍትህ የሚፈርድ የእርሱ ፍርድ ነው።

እርሱ ራሱን የሚገልጽበት ቀን እርሱ ለሚወስነው ጊዜ የሚቆይ የትንሳኤ ቀን ነው። ሁሉ ነገር የእርሱ ነው፣ የተፈጠረውም በእርሱ ነው። ከእርሱ በቀር ሁሉም ፍጡሮች ናቸው።

(39)

በስመ እግዚአብሔር፣እጅግ በጣም በተከበረው፣ በእጅግ በጣም ከፍተኛው።

በእውነቱ እኔ አምላክ ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ በል፡- ከእኔ በቀር ሌላው የእኔ ፍጥረት ብቻ ነው።እንግዲህ እናንተ ፍጡሮቼ ሆይ፣ አምልኩኝ።

እኔ ወደ መኖር ጠራሁህ፣ መገብኩህ፣ ጠበቅሁህ፣ አፈቀርኩህ፣ አስነሣሁህና በእኔ እንደታዘዘው፣ ጥቅሶቼን ትደግም ዘንድ፣ የፈጠርኩትንም ሰው ሁሉ፣ ክብር የተመላውና የተከበረ መንገድ እንጂ ሌላ ምንም ወዳልሆነው ሃይማኖቴትጠራ ዘንድ፣ የገዛ ራሴ ክስተት እንድትሆን በፀጋ መረጥኩህ።

የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ለአንተ ብዬ ፈጠርኩ፣ በፈቃዴ

ኃይል በሁሉም የሰው ዘር ላይ ሉዓላዊ ገዥ አድርጌ ሠየምኩህ። ከዚህ በላይ፣ ማንም ኃይማኖቴን የሚያቅፍ ሁሉ፣ በአንድነቴ እንዲያምንደነገግሁ፣ ይህንንም እምነት አንተን ከመዘከር ጋር፣ ከአንተም በኋላ አንተ በፍቃዴ፣“ሕያዋን ፊደላት”እንዲሆኑ የአደረግሃቸውን፣ ከሃይማኖቴም በባያን የተገለጸውን ማንኛውንም ነገር ከመዘከር ጋር አንድ አደረግሁ። ይህ በእውነቱ፣ ከአገልጋዮቼ መካከል እውነተኞቹን ወደ መንግሥተ-ሰማያዊ ገነት መግባትን ለማግኘት የሚያስችላቸው ነው።

በእውነቱ፣ ከአገልጋዮቼ መካከል እውነተኛ አማኞች በእርሷ መውጣት የእያንዳንዱን ዘመን ንጋት እንዲገነዘቡ፣ ፀሐይ ከእኔ ዘንድ ማወቂያ ምልክት ናት።

በእውነቱ፣ እኔ በአንተ አማካኝነት ፈጠርኩህ፤ ከዚያም በራሴ ትዕዛዝ በቃልህ የፈጠራ ኃይል አማካኝነት ሁሉን ነገሮች ፈጠርኩ። እኛ ፍጹም ኃይል የተመላን ነን። የመጀመሪያና የመጨረሻ፣ የሚታየውና ድብቁ እንድትሆን ሰይመንሃል። በእውነቱ፣ እኛ ሁሉን አዋቂ ነን።

ከአንተ በቀር ሌላ ማንም የነቢይነት ማዕረግ የተጎናጸፈ ወይም እስከ መቼውም የሚጎናፀፍ የለም፤ ለአንተም በቀር ለሌላ ለማንም ምንም ቅዱስ መጽሐፍ አልተገለጸም ለወደፊቱም አይገለጽም። በእርሱ ሁሉን በሚከበው፣ በእጅግ በጣም ተወዳጁ የተወሰነው ትእዛዝ እንዲህ ያለ ነው።

ባያኑ በእውነቱ ለተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ አሳማኝ ማስረጃችን ነው፤ የዓለም ሕዝቦችም ሁሉ በጥቅሶቹ መገለጽ ፊት ኃይል አልባ ናቸው። በዚህ ቀን አንተ የማስረጃዎቻችን ሁሉ ማጎደር እንደሆንክ ሁሉ፣ እሱ (ባያን) የሁሉን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የአለፉትንም ዘመናት፣ የወደፊቱንም ጠቅላላ ድምር ያጠቃልላል። እኛ የፈለግነውን ማንኛውንም ሰው ወደ እጅግ በጣም ቅዱሱ፣ ወደ እጅግ በጣም ከፍተኛው ገነታችን የአትክልት ሥፍራዎች እንዲገባ

እናደርገዋለን። መለኮታዊ ግልጸት በእያንዳንዱ ዘመን በዚህ ዓይነት በትእዛዛችን ተመርቆ ይከፈታል። እኛ በእውነቱ፣ የላቀው ገዢ ነን። በእውነቱ፣ በመጪዎቹ ቀናት የማይታደስ ምንም ሃይማኖት አንመሠርትም። ይህ በክብር ያደረግነው ቃል ኪዳን ነው። በእውነቱ እኛ በሁሉም ነገሮች ላይ የላቅን ነን....

(40)

እርሱ አምላክ፣ ሉዓላዊው ጌታ፣ ፍጹም ክብር የተመላው ነው።

በል፦ የፈለገውን ማንኛውንም ሰው እርሱን ለማምለክ በጸጋው ለሚያስችለው ለአምላክ ምስጋና ይሁን። በእውነቱ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። እጅግ በጣም የላቁት ስያሜዎች የእርሱ ናቸው፤ እንደፈለገ ቃሉ እንዲሟላ የሚያደርግ እርሱ ነው፤ እነዚያንም የተቀበሉትንና የጽድቅ መንገድ የሚሹትን የሚመራው እርሱ ነው።

ጌታህን አምላክን ፍራ፣ ሌት ተቀን ስሙን አንሣ። ከእውነት ከራቁ የከንቱ እምነቶች አራማጆች ጋር እንዳትቆጠር፣ የእምነተ-ቢሶችን ግፊቶች አትከተል። ጌታ ራሱ የሆነውን ቀዳማዊውን ነጥብ በታማኝነት ታዘዝ፣ ከጻድቃንም አንዱ ሁን። ምንም ነገር አያናውጥህ፣ በዚህ እምነት ሊፈጸሙ የታቀዱትም ነገሮች አይረብሹህ። ለአምላክ ብለህ በቁርጠኝነት ትልቅ ጥረት አድርግ፣ በጽድቅ መንገድም ተራመድ። የማያምኑት ቢያጋጥሙህ፣ በዚህም በሚቀጥለውም መንግሥታት አምላክ አርኪዬ ነው እያልክ፣ ሙሉ እምነትህን በጌታህ በአምላክ ላይ አድርግ።

አምላክ ታማኞችን አንድ ላይ የሚሰበስብበት ቀን እየተቃረበ ነው። በእውነቱ፣ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም።

የአምላክ ሰላም ከእነዚያ በመለኮታዊ መርሖ ኃይል ወደ ትክክለኛው መንገድ ከተመሩት ጋር ይሁን።

(41)

እርሱ ሉዓላዊው ገዢ፣ የላቀው እውነት፣ የእርሱ እርዳታ በሁሉም የሚለመነው አምላክ ነው።

የሰማያትና የምድር ገዢነት የእርሱ የሆነው፣ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ መንግሥት በእጁ የሚገኘውና ሁሉም ወደ እርሱ የሚመለሱት የተከበረ ነው። ለእያንዳንዱና ለሁሉ ነገር የተመደበውን መጠን የሚሰጥ፣ በተቀደሰው መጽሐፉም፣ ለእነዚያ ስለእምነቱ ምሥጋና ለሚያቀርቡት ጥቅም፣ መልካም ስጦታዎቹንና ቡራኬዎቹን የሚገልጽ እርሱ ነው።

በል፦ ይህ ምድራዊ ሕይወት ያልፋል፤ እያንዳንዱም ይሞታል፤ የእነዚያን በትዕግስት የሚችሉትን ሰዎች ተግባራት በእጅግ በጣም ምርጥ ሥጦታዎች ወደሚከሰው ወደ ጌታዬ ወደ አምላክ ይመለሳል። በእውነቱ አምላክህ የሁሉንም የተፈጠሩ ነገሮች መጠን በትእዛዙ እንደፈቀደ ይመድባል፤ እነዚያ የጌታህን መልካም ደስታ የሚከተሉት ደግሞ፣ እነርሱ በእርግጥ ከእነዚያ ሐሴት ከሚያደርጉት ናቸው።

በአምላክ የተገለጹትን ጥቅሶች ብታሰላስሉ፣ ጌታችሁ በቀድሞ ጊዜ ሕዝቡን ወደ ጌታው ለመጥራት ሳይችል የቀረ ነቢይ አስነሥቶ ከቶ አያወቅም፣ ዛሬም በእርግጥ እንዳለፉት ዘመናት ነው።

አምላክ ነቢዩን ሙሐመድን በላከ ጊዜ፣ በዚያን ቀን የትንቢታዊ ዑደት መደምደም በአምላክ ዕውቀት አስቀድሞ ተወስኖ ነበር። አዎን፣ ያ የተስፋ ቃል በእርግጥ እውን ሆኗል፤ የአምላክ ትእዛዝም እርሱ ወስኖት እንደነበረው ተፈጽሟል። እኛ ዛሬ በእርግጥ በአምላክ ቀናት ጊዜ እየኖርን ነን። እነዚህ ከዚህ በፊት በተመሳሳያቸው ላይ ፀሐይ ወጥታ የማታውቅ ስመ ጥር ቀናት ናቸው። እነዚህ፣ በአለፉት ዘመናት ሕዝቡ በጉጉት ሲጠባበቃቸው የነበሩት ቀናት ናቸው። ታዲያ በጥልቅ ያንቀላፋችሁት ምን ወርዶባችሁ ነው? እነዚህ አምላክ፣ የእውነት የቀን ኮኮብ

በአንፀባራቂነት እንዲያበራ ያደረገባቸው ቀናት ናቸው። ታዲያ ዝም እንድትሉ ያደረጋችሁ ምንድነው? እነዚህ እናንተ በቀድሞ ጊዜ በናፍቆት ስትጠባበቁዋቸው የነበራችኋቸው ቀነ ቀጠሮዎች - የመለኮታዊ ምፅዓት ቀናት ቀነ ቀጠሮዎች ናቸው። ስለዚህ እናንተ የአማኞች ሕዝበ ሠራዊት ሆይ፣ ለአምላክ ምስጋና አቅርቡ።

የእነዚያ እውነትን የሚክዱት ሰዎች አድራጎቶች እንደ ግርዶሽ እንዲጋርዷችሁ አታድርጉ። እንዲህ ያሉት ሰዎች ሥልጣን ያላቸው በአካላችሁ ላይ ብቻ ነው፤ አምላክም በመንፈሶቻችሁ፣ በነፍሶቻችሁና በልቦቻችሁ ላይ ሥልጣን አልሠጣቸውም። ምናልባት መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ፣ አምላክን ፍሩ። ሁሉም ነገሮች ለእናንተ ሲባል ተፈጠሩ፤ ፍጥረታችሁ ለሌላ ለማንም ተብሎ አልታዘዘም። አምላክን ፍሩ፤ ቅርጾችና ሽፋኖችም እርሱን ከማወቅ እንዳይከለክሏችሁ ተጠንቀቁ። ምናልባት በምህረት ይይዛችሁ ዘንድ ለአምላክ ምስጋና አቅርቡ።

ይህ አላፊ ሕይወት እንደሚጠፋ የታወቀ ነው፤ ደስታዎቹም ከመጥፋት የማይድኑ ናቸውና፤ ሳይዘገይ በፀፀት ሥቃይ ተጨንቃችሁ ወደ አምላክ ትመለሳላችሁ፤ ምክንያቱም ድንገት ከእንቅልፋችሁ ትቀሰቀሳላችሁ፤ ወዲያውኑም ራሳችሁን በአምላክ ዘንድ ታገኙታላችሁ፤ ስለሥራዎቻችሁም ትጠየቃላችሁ።

በል፦ በቀድሞ ዘመን የተገለጹትን የአምላክ መጻህፍት ታነባላችሁ፣ በአንፃሩ ግን ከፍትህ ሰማይ የተላኩትን የአምላክ ጥቅሶች እንዴት ያለ እፍረት ለመካድ ትደፍራላችሁ? አስቀድሞ የተሠየመላችሁን፣ ከጌታችሁ ጋር መገናኘትን አንቀበልም ብላችሁ፣ በዚህ ቀን እንዴት ማስጠንቀቂያውን መቀበል ይሳናችኋል?ከእነዚያ ጌታቸው ዕውቀት ከሰጣቸውና በዚህ ቀን ተለይተው ከእውነተኛው የአምላክ እምነት ጋር የታወቁ ለመሆናቸው በረከት፣ ለእርሱ ምስጋና ከሚያቀርቡት በቀር፣ ሌሎቻችሁ፣ በእውነቱ ቅርጾችን በመያዝና የራስ ወዳድነት ፍላጎታችሁን ግፊቶች በመከተል፣ ከጌታችሁ መልካም ደስታ

ራሳችሁን ነፍጋችኋል። ስለዚህ ምናልባት ይገነዘቡ እንደሆን፣ መልዕክቱን ለእነዚያ መልካም ተግባር ለሚያንጸባርቁት አውጁላቸው፤ የአንዱን እውነተኛ አምላክ መንገዶች አስተምሩአቸው።

አንደበትህን ሊያሳዝንህ የሚችለውን ነገር ከመናገር ግታው፤ ለምህረትም አምላክን ተማጸን። ምንም ነገር ማንኛውም ቢሆን በሰማያት ወይም በምድር ላይ ከእርሱ ዕውቀት ለማምለጥ የሚችል ስለሌለ፣ በእውነቱ እርሱ ስለጻድቃን ሙሉ በሙሉ ያውቃል፤ እርሱ ከእነዚያ በእውነት ከሚያምኑበት አገልጋዮቹ ጋር ነውና፣ የችግር ፈጣሪዎችንም ተግባራት የማያውቅ አይደልምና።

ግልፅና አሳማኝ የሆኑት እነዚህ ጥቅሶች፣ የጌታህ ምሕረት ምልክትና ለሁሉም የሰው ዘር የመርሆ ምንጭ ናቸው። ለእነዚያ ለሚያምኑባቸው ብርሃን፣ ለእነዚያ ፊታቸውን ለሚያዞሩና ለሚከዱአቸው ደግሞ የአስጨናቂ ሥቃይ እሳት ናቸው።

(42)

ከእርሱ ከኃያሉ፣ከእጅግ በጣም ተወዳጁ በቀር ሌላ ምንም አምላክ ከቶ እንደሌለ አምላክ ይመሠክራል።

በትንሣኤ ቀን ትኩረትህን በእርሱ፣ አምላክ በሚከስተው ላይ አድርግ፣ ከዚያም በዚያ በእርሱ በተላከው በጥብቅ እመን።

በል፡- አምላክ በእያንዳንዱ ድል አድራጊ ላይ የማያከራክር አሸናፊነት አለው። በሰማይ ወይም በምድር ወይም በመካከላቸው በሚገኘው በማንኛውም፣ የእርሱን አሸናፊነት የላቀ የበላይነት ለማጨናገፍ የሚችል ማንም የለም። እርሱ በትእዛዙ ኃይል የፈለገውን ማንኛውንም ነገር ወደ መኖር ይጠራል። በእውነቱ፣ አምላክ ኃያልነቱየላቀው፣ ሕይወት ሰጪ፣ ረዳቱና ተከላካዩ ነው።

ጸሎቶችና ሱባኤዎች

(43)

አምላኬ ሆይ፣ በእውነቱ እኔ አገልጋይህ፣ ምስኪንህና ተማፃኝህ፣ ችግረኛ ፍጡርህም ነኝ። መጠለያህን በመሻት በበራፍህ ደርሻለሁ። የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ከከፍተኛ ህላዌህ የተዘጉ መሆናቸውንና መላ ፍጥረት ወደእጅግ በጣም ውስጣዊው ሕያውነትህ ከመድረስ የታገደ መሆኑን የማውቀው ብሆንም፣ በፍቅርህ በቀር ምንም እርካታ፣ በትዝታህበቀር ምንም ደስታ፣ ላንተ በመታዘዝ በቀር ምንም የመንፈስ ንቃት፣ በቅርበትህ በቀር ምንም ሐሴት፣ ከአንተ ጋር እንደገና በመገናኘትም በቀር ምንም ሰላም አላገኘውም። ወደ አንተ ለመቅረብ በሞከርኩ ቁጥር፣ በውስጤ ከጸጋህ መታወቂያ ምልክቶች በቀር ምንም ነገር አላስተውልም። በሕያውነቴም ፍቅራዊ ደግነትህን ከሚገልጹ ነገሮች በቀር ምንም አላይም። ምንም የተፈጠረ ነገር ምን ጊዜም ከአንተ ጋር ለመነዳኘት፣ ወይም አንዳች ነገር ሊገነዘብህ ከቶ የማይችል ሆኖ እያለ፣ አንድ የአንተ ፍጡር የሆነ ሰው፣ ከአንተ ጋር እንደገና ለመገናኘት ሊፈልግና አንተ ዘንድ ሊደርስ እንዴት ይችላል? የግዛትህን ክስተቶች የሚገልጹ ነገሮችና የሉዓላዊነትህን ድንቅ ማስረጃዎች ብታዘጋጅለትም እንኳ፣ አንድ ዝቅተኛ አገልጋይህ አንተን ሊያውቅህና ውዳሴህን ከፍ ከፍ ሊያደርግ እንዴት ይችላል? ስለዚህ እያንዳንዱ የተፈጠረ ነገር በውሳጣዊ እውንነቱ ላይ በተደረገበት ውስንነት ምክንያት፣ ከቅርበትህ መቅደስ የተዘጋ መሆኑን ይመሠክራል። ለአምላካዊነትህ የተቀደሰ መንበር የሚገባው መላው ፍጥረት ከሚደርስበት በላይ የላቀ ቢሆንም፣ የስህበትህ ኃይል ግን ለዘላለም፣ የእጅህ ሥራ እውንነቶች ውሳጣዊ ባሕርይ ሆኖ የሚኖር መሆኑ አያከራክርም። አምላኬ ሆይ፣ ይህ እንኳንስ የመለኮታዊ አንድነትህን ለማወቅ ሙብቃት ወይም ወደ ምሥጋናህ፣ ወደ ቅድስናህና ወደ ክብርህ ግልጽ ምልክቶች ለመድረስ መቻል ቀርቶ፣ አንተን ለማሞገሥ እንኳ ኃይል አልባነቴን ያመለክታል

እንዲሁም ለአንተ ምስጋና ለማቅረብ ችሎታ እንደሌለኝ ይገልጻል። የለም፣ በኃያልነትህ፣ ከአንተ ከራስህ በቀር ሌላ ምንም አልናፍቅም። ከአንተም በቀር ሌላ ማንንም አልሻም።

## (44)

አምላክ ሆይ፣ ስምህ የተመሠገነ ይሁን። አንተ በእውነቱ ጌታችን ነህ፣ አንተ በሰማያትና በምድር ላይ ስለሚገኘው ስለማንኛውም ነገር ታውቃለህ። እንግዲህ የምህረትህን ምልክት ላክልን። በእውነቱ፣ አንተ ምህረትን ከሚያሳዩት መካከል የማይደረስብህ ነህ። ጌታ ሆይ! ምሥጋና ሁሉ ላንተ ይሁን። ከአንተ ዘንድ ያንን ከአገልጋዮችህ መካከል የቅኖችን ልቦች የሚያጽናናውን እዘዝልን። አምላክ ሆይ፣ የተከበርክ ነህ፤ አንተ የሰማያትና የምድር የዚያም በመካከላቸው የሚገኘው ፈጣሪ ነህ። አንተ ሉዓላዊ ጌታ፣ እጅግ በጣም ቅዱሱ ፍፁም ኃያሉ፣ ፍፁም ጠቢቡ ነህ። አምላክ ሆይ፣ ስምህ የተከበረ ይሁን፤ ለእነዚያ በአምላክና በምልክቶቹ ለአመኑት መላውን የሰው ዘር ድል ለመንሳት የሚያስችላቸውን ኃይል እርዳታ ላክላቸው።

## (45)

ጌታ ሆይ፣ ምሥጋና ለአንተ ይሁን። ኃጢያታችንን ይቅር በለን፣ በእኛ ላይ ምህረት ይኑርህ፤ ወደ አንተም ለመመለስ አስችለን። በአንተ ላይ በቀር በሌላ በምንም ላይ እንዳንተማመን አድርገን፤ በጸጋህ አማካኝነት፣ያንን አንተ የምትወደውንና የምትሻውን፣ ለአንተም ፍጹም የሚገባውን ስጠን። የእነዚያን፣ በእውነት ያመኑትን ደረጃ ከፍ አድርግ፤ ጸጋ በተመላበት ይቅር ባይነትም ይቅር በላቸው። በእውነቱ፣ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህና።

(46)

አምላክ ጌታችን ሆይ! ለአንተ ከሚያጸይፈው ከማንኛውም ነገር በጸጋህ ጠብቀን፤ ለአንተ ተገቢ የሆነውንም ስጠን። ከሰፊ በረከትህ ጨምርልን፤ እንዲሁም ባርከን። ለአደረግናቸው ነገሮች ይቅርታ አድርግልን፤ ኃጢያታችንንም ከላያችን አጠብልን፤ ጸጋ በተመላበት ይቅር ባይነትም ይቅር በለን። በእውነቱ አንተ እጅግ በጣም የተከበረው፣ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህና።

ፍቅር የተመላበት አምላካዊ ጠባቂነትህ፣ በሰማያትና በምድር የሚገኙትን የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ ከቧል፤ ይቅር ባይነትህም ከመላው ዓለም አልፏል። ሉዓላዊነት ያንተ ነው፤ የፍጥረትና የግልጸት ዓለማት በእጅህ ናቸው፤በቅኝ እጅህ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ይዘሃል፤ የይቅርባይነትህም የተመደቡ መጠኖች በመዳፍህ ውስጥ ናቸው።ከአገልጋዮችህመካከል ለፈልግከው ለማንኛውም ይቅር ትለዋለህ። በእውነቱ አንተ ዘለዓለም ይቅር ባይ፣ ሁሉን አፍቃሪ ነህ። ምንም ነገር ማንኛውም ቢሆን፣ ከዕውቀትህ አያመልጥም፤ ከአንተ የተሠወረ ምንም ነገር የለም።

አምላክ ጌታችን ሆይ! በኃያልነትህ ኃይል ጠብቀን፣ በመትመም ላይ ወደአለው ድንቅ ውቅያኖስህ ለመግባት አስችለን፣ ለአንተ በጣም ተስማሚ የሆነውንም ፍቀድልን።

አንተ ሉዓላዊው ገዢ፣ ኃያሉ አድራጊ፣ የተከበረው፣ ሁሉን አፍቃሪው ነህና።

(47)

ክብር ለአንተ ይሁን፣ ጌታ አምላኬ ሆይ! ምንም ነገር ማንኛውም ነገር ቢሆን፣ ከዕውቀትህ አያመልጥም፣ እንዲሁም በሰማይም ሆነ በምድር፣ የቀድሞ ወይም የወደፊት፣ ከመዳፍህ ለመውጣት ወይም፣ ዓላማህን ለማደናቀፍ የሚችል ምንም ነገር

የለም።

ገነትንና በዚያ ነዋሪዎችን ታያለህ፤ ታችኛውን ዓለምና በዚያ ነዋሪዎችን ትመለከታለህ። ሁሉ አገልጋዮችህ ናቸው፤ በመዳፍህም ውስጥ ተይዘዋል።

ጌታ ሆይ! በመንገድህ ሰማዕትነትን ስለፈለጉ፣ ለታጋሽ አገልጋዮችህ ተገቢ ድል በመፍቀድ ድል አድራጊዎች አድርጋቸው። ያንን ለአእምሮዎቻቸው መጽናናትን፣ የሚያመጣውን፣ ውሳጣዊ፣ ሕያውነቶቻቸው ሐሴት እንዲያደርጉ የሚያደርገውን፣ ለልቦቻቸው እርግጠኝነት፣ ለአካሎቻቸውም መረጋጋትን የሚሰጠውንና ነፍሶቻቸውን ወደ አምላክ፣ እጅግ በጣም ወደተከበረው ዘንድ ለመውጣት፣ ወደ ላቀው ገነትና አንተ ለእውነተኛ የዕውቀትና ለእውነተኛ የመልካም ተግባር ሰዎች ወደ አዘጋጀሃቸው የክብር አካባቢዎች ለመድረስ የሚያስችላቸውን ላክለቸው። በእውነቱ አንተ ሁሉን ነገሮች ታውቃለህ፤ እኛ ግን አገልጋዮችህ፣ ምርኮኞችህ፣ ባሮችህና ምሥኪኖችህ ነን። አምላክ ጌታችን ሆይ፣ ከአንተ በቀር ሌላ ጌታ አንጠራም፤ አቤቱ አንተ ለዚህ ዓለምና ለሚቀጥለው የምሕረት አምላክ የሆንክ ሆይ፤ ከአንተም በቀር ከሌላ ከማንም ቡራኬዎችን ወይም ጸጋን አንማፀንም። የአንተ መላው ሕያውነት የሀብት፣ የነፃነት፣ የክብር፣ የግርማና የወሰን አልባ ጸጋ ምሳሌ ሲሆን፣ እኛ ግን የድህነት፣ የኢምንትነት፣ የረዳተ- ቢስነትና የጥፋት ማኅደሮች ብቻ ነን።

ጌታ ሆይ፣ ካሣችንን፣ ከዚህ ዓለምና ከሚቀጥለው ዓለም መልካም ነገሮች፣ በሰማይ ጫፍ ጀምሮ ከዚያ በታች እስከአለችው ምድር ከተዘረጉትም ብዙና ልዩ ልዩ ጸጋዎች፣ ለአንተ በጣም ወደተስማማህ ለውጠው።

በእውነቱ አንተ ጌታችንና የሁሉ ነገሮች ጌታ ነህ። ከአንተ ለሆኑት ነገሮች በመጓጓት ሁኔታ፣ ራሳችንን አሳልፈን ለአንተ ሰጥተናል።

(48)

ጌታ ሆይ፣ ስምህ የተከበረ ይሁን! በእውነቱ አንተ አምላኬና ተወዳጄ የሆንክ እያለህ ለተገን ወደ ማን ልሸሽ? አንተ ጌታዬና እኔ የእርሱ የሆንኩ እያለህ ለመጠጊያ ወደ ማን ልዞር፤ በእውነቱ አንተ የእኔ ጌታና ማምለጫ ቦታዬ እያለህ ወደ ማን ልሸሽ፤ በእውነቱ አንተ የሀብት ግምጃ ቤቴና የምኞቴ ዓላማ እያለህ ማንን ልማፀን፣ በእውነቱ አንተ የላቀ ተስፋዬና የላቀ ምኞቴ እያለህ በማን በኩል አስተዛዝኜ በፊትህ ልለምን? ለመንግሥተ-ሰማያዊ ጸጋህ ካለው ናፍቆት በቀር እያንዳንዱ ተስፋ ተቀጭቷል፤ ወደ ቡራኬዎችህም መነሻ ምንጭ ከሚመራው በር በቀር እያንዳንዱ በር ተዘግቷል።

ጌታዬ ሆይ፣ በጮራው ፊት እሳት ወደ ብርሃን በተቀየረበት፣ ሙታን ወደ ሕይወት በተመለሱበትና እያንዳንዱ ችግር ወደ ምቾት በተለወጠበት፡- በብሩክነቱ ፊት እያንዳንዱ ነፍስ ለአንተ በመሥገድ በትሕትና በሚያጎነብስበትና በሚዘረርበት፣ በእጅግ በጣም አንፀባራቂው ታላቅነትህ እማፀንሃለሁ። በዚህ ታላቅ፣ በዚህ አስደናቂታላቅነትና በተከበረው ሉዓላዊነትህ ክብር፣ አቤቱ አንተ የማይበገረው ኃይል ጌታ የሆንከው ሆይ፣ በጸጋህ አማካይነት አንተ ራስህ ወዳለህ ነገር እንድትለውጠንና የብርሃንህ መፍለቂያዎች ለመሆን እንድታስችለን፣ ለላቀው ግዛትህ ግርማ ተገቢ የሆነውንም በምሕረትህ እንድትሰጠን እማፀንሃለሁ። ጌታ ሆይ፣ እጆቼን የዘረጋሁት ለአንተ ነውና፤ ጌታ ሆይ፣ ጥላ የሚሰጥ ድጋፍ ያገኘሁት በአንተ ነውና፤ ጌታ ሆይ፣ ራሴንም የተውኩት በአንተ ነውና፤ ጌታ ሆይ ሙሉ እምነቴንም ያኖርኩት በአንተ ላይ ነውና፤ ጌታ ሆይ፣ የተጠናከርኩትም በአንተ ነውና።

በእውነቱ ኃይልም ሆነ ብርታት በአንተ በቀር በሌላ የለም።

(49)

ጌታ ሆይ፣ በደሎቼ በአንተ ዘንድ ፊቴን በእፍረት እንደሸፈኑት፣ በፊትህም ጀርባዬን እንደከበዱት፣ በእኔና በውብ ገጽታህ መካከል ግርዶሽ እንደሆኑ፣ ወደ መለኮታዊ ኃይልህ ግልጸቶች እንዳልገባ ከሁሉ አቅጣጫ እንደከበቡኝና ከሁሉም በኩል እንደ አገዱኝ አውቃለሁ።

ጌታ ሆይ! አንተ ይቅር ካላልከኝ፣ ታዲያ ይቅርታ የሚያደርግልኝ ማን አለ፤ አንተ በእኔ ላይ ምሕረት ካልኖረህ ርኅራኄ ሊያሳየኝ ችሎታ ያለው ማነው? ክብር ለአንተ ይሁን፤ አንተ ያልነበርኩ በነበርኩበት ጊዜ ፈጠርከኝ፤ ከምንም የመረዳት ችሎታ ባዶ በነበርኩበትም ጊዜ መገብከኝ። ምሥጋና ለአንተ ይሁን፤ የበረከት ማስረጃ ሁሉ ከአንተ ይፈልቃል፣ የጸጋ መታወቂያ ምልክት ሁሉ ከአንተ ይመነጫል።

(50)

ጌታዬ ሆይ፣ አቤቱ አንተ የጌቶች ጌታ፣ እርሱ ተፈላጊውን የሚሰጠውና በሮቹን የሚከፍተው የሆንክ ሆይ፣ የአንተን ስም ለማንሣት በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ስም ማንሣት፣ ለአንተ ውዳሴም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ውዳሴ፣ በቅርበትህ ምክንያት ከተደሰትኩት ደስታም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ደስታ፣ ከአንተ ጋር በመቃረብ ምክንያት ለአገኘሁት እርካታም በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ እርካታ፣ ለፍቅርህና ለመልካም ደስታህም ሐሴት በቀር ለእያንዳንዱ ሌላ ሐሴት፣ ከአንተ ጋር ምንም ግንኙነት ለሌላቸው ከእኔ ጋር ግንኙነት ለነበራቸው ነገሮች ሁሉ ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ።

(51)

አምላክ ሆይ፣ ክብር ለአንተ ይሁን! አንተ ከሁሉ ነገሮች

በፊት የነበርክ፣ ከሁሉ ነገሮችም በኋላ የምትኖርና ከሁሉ ነገሮችም በኋላ አልፈህ የምትቆይ አምላክ ነህ። አንተ ሁሉን ነገሮች የሚያውቀው፣ በሁሉ ነገሮችም ላይ የላቀ የበላይ የሆነው አምላክ ነህ። አንተ በሁሉ ነገሮች ላይ በምሕረት የሚሠራው፣ በሁሉ ነገሮችም መካከል የሚፈርደው፣ የማየት ኃይሉም ሁሉን ነገሮች የሚያቅፈው አምላክ ነህ። አንተ አምላክ ጌታዬ ነህ፤ አንተ ስለሁኔታዬ ታውቃለህ፤ አንተ ውስጣዊውንና ውጪአዊውን ሕያውነቴን ታያለህ።

ለእኔና ለጥሪህ መልስ ለሰጡት አማኞች ይቅርባይነትህን ስጠን፣ ኃዘን ሊያደርስብኝ ሊፈልግ ከሚችለው ወይም ክፉ ከሚመኝብኝ ከማንኛውም ሰው ክፋት የሚከላከልልኝ አርኪ ረዳቴ ሁነኝ። በእውነቱ አንተ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ጌታ ነህ። አንተ እያንዳንዱን ሰው ታረካለህ፤ ነገር ግን ማንም ያለ አንተ እርዳታ ራሱን የቻለ ለመሆን አይችልም።

(52)

በዚህች ጊዜ ከዚያ መልካምና ተገቢ ከሆነው ነገር ሁሉን መጠን እንድታዝልን፣ ከጸጋህ ጎርፎችም እያንዳንዱን ድርሻ እንድትወሰንልን በክቡር ፊትህ ብርሃን ድምቀት፣ በጥንታዊው ታላቅነትህ ግርማና በላቀው ሉዓላዊነትህ ኃይል እማፀንሃለሁ። ሥጦታዎችን መስጠቱ አያጎድልብህም፣ ችሮታዎችን መለገሡም ሃብትህን አይቀንሰውምና።

ጌታ ሆይ አንተ የተከበርክ ነህ! በእውነቱ እኔ ድሀ ነኝ፣ አንተ ግን በእውነቱ ሀብታም ነህ፣ በእውነቱ እኔ ዝቅተኛ ነኝ አንተ ግን ኃያል ነህ፣ በእውነቱ እኔ ኃይል አልባ ነኝ፣ አንተ ግን በእውነቱ ኃይል የተመላህ ነህ፣ በእውነቱ እኔ የተዋረደኩ ነኝ፣አንተ ግን እጅግ በጣም የተከበርክ ነህ፣ በእውነቱ እኔ የተጨነቅሁ ነኝ፣ አንተ ግን በእውነቱ የኃያልነት ጌታ ነህ።

ጌታ ሆይ፣ አንተ የፈጠርከውን ለወደፊትም የምትፈጥረውን

እያንዳንዱን መልካም ነገር እዘዝልኝ፣ እንዲኖሩ ከአደረግካቸው ወይም ከምታደርጋቸው ነገሮች መካከል አንተ ከምትጠላቸው ከማናቸውም ከልለኝ። በእውነቱ ዕውቀትህ ሁሉን ነገሮች ያቅፋል።የተቀደስክ ሁን፣ በእውነቱ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ምንም ነገር በሰማያት ውስጥ ወይም በምድር ላይ በመካከላቸውም የሚገኝ ማናቸውም ነገር መቼውንም ዓላማህን ለማሰናከል ከቶ አይችልም። በእውነቱ አንተ በሁሉ ነገሮች ላይ ሥልጣን ያለህ ነህ።

አምላኬ ሆይ፣ ማንም የአንተን ፍቅራዊ ደግነት ወይም ችሮታ መሻቱ፣ ከአንተ ሕያውነት ቅድስና የራቀ ይሁን። ለልግሥናዎችህና ርኅራኄ ለተሞላበት ምሕረትህ ማስረጃዎች ማንም አንተን መማጸኑ ከላቀው ክብርህ የራቀ ይሁን። ማንኛውም ነፍስ ጸጋ የተሞላበትን የስጦታህንና ፍቅራዊ እንክብካቤህን ትዕይንት ለመማጸን በጣም ከፍ ያልክ፣ ማንም ሰው የቡራኬዎችህን እንዲሁም የመንግሥተ-ሰማያዊ በረከቶችህንና የጸጋህን ኀርፎች ከአንተ ከመለመን፣ ክብርህ እጅግ በጣም የተቀደሰ ነው። ብዙ ልዩ ልዩ በረከቶች በተሰጠው በሰማይና በምድር መንግሥትህ ሁሉ፣ ምንም ተነፃፃሪነት ሊደረግበት ከሚቻል ከማንኛውም ነገር በላይ፣ ሊለካ ከሚቻል በላይ የተከበርህ ነህ።

አምላኬ ሆይ የምለምንህ፣ ነፍሴ ከአካሌ ከመለየቷ በፊት፣ እጥረቱ ከአንድ የሰናፍጭ ፍሬ እጅግ በጣም ትንሽ ከፍልፋይ ለአነሰች ጊዜ የሚፈቀድልኝ ቢሆንም እንኳ፣ ለአንተ መልካም ደስታ ለመብቃት እንድታስችለኝ ብቻ ነው። ምክንያቱም አንተ ተደስተህብኝ እያለህ ብትለይ፣ ከዚያ በኋላ፣ ከሁሉ ሃሳብና ጭንቀት ነፃ እሆናለሁ፤ ነገር ግን አንተ አዝነህብኝ እያለህ ጥላኝ ብትሄድ፣ ከዚያ በኋላ፣ ምንም እንኳ እያንዳንዱን መልካም ተግባር ፈጽሜ የነበርኩ ብሆንም እንኳ፣ ማንኛቸውም አንዳች ጥቅም አይሰጡኝም፤ እንዲሁም እያንዳንዱን ክብርና ስመ - ጥርነት አግኝቼ የነበርኩ ብሆንም እንኳ፣ አንዳቸውም ሊያስከብሩኝ አይችሉምና።

አምላኬ ሆይ፣ እንግዲህ፣ አንተ ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ በግዛትህ ለሚኖረው ሕዝብ የእጅግ ሰፊ በረከት አምላክ፣በሁሉን ቻይነትህ የተከበረ ሰማይ ለሚኖሩትም ሁሉ የእጅግ በጣም የላቁ ስጦታዎች ጌታ ስለሆንክ፣ ወደ አንተ እንዳርግና በቅዱስነትህ ዘንድ እንድቀርብ በምታደርገኝ ጊዜ፣ በጸጋህ አማካኝነት መልካም ደስታህን እንድታጎናጽፈኝ አጥብቄ እማፀናለሁ።

(54)

ቃልህን ከፍ ለማድረጋቸው፣ የመለኮታዊ አንድነትህም ክብር እንዲታወቅ ባለማድረጋቸው፣ በመንገድህ ለከባድ ውርደት የተጋለጡ ወደ ሕይወት እንዲነሡ የተደረጉ ነፍሶች፣ እንዴት ብዙ ናቸው! የመለኮታዊ ተልዕኮህን እውነተኝነት ለመግለፅ፣ ምሥጋናህንም ለመግለጽ ምሥጋናህንም ለማሰማት ለእምነትህ የፈሰሰው ደም እንዴት ብዙ ነው! የቅድስናህን ታላቅነት ለማረጋገጥና ክብር የተመላውን ስምህንም ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ በፍቅርህ መንገድ በግፍ የተወሰደው ንብረት እንዴት ብዙ ነው! ቅዱስ ቃልህን ለማጉላት፣ ክብርህንም ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ በአቧራ ላይ የተጓዙ እግሮች እንዴት ብዙ ናቸው! በሰቆቃ የጮሁ ድምጾች፣ በፍርሃት የተዋጡ ልቦች፣ ከአንተ በቀር ለሌላ ማንም ሊያሰላቸው የማይችላቸው ከባድ ዋይታዎች፣ ለራስህ በቀር ለሌላ ለማንም በምርምር ሊታወቁ የማይችሉ ሆነው የሚቆዩ ችግሮችና መከራዎች፣ እንዴት ከቁጥር በላይ ናቸው፤ ይህ ሁሉ የሆነው፣ አምላኬ ሆይ፣ የቅድስናህን ምጥቀት ለማረጋገጥና የክብርህን ልቀት ሁኔታ ለመግለጽነው።

እነዚህ ትእዛዞች በአንተ የታዘዙት፣ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ፣ እነርሱ ወደ መኖር የተጠሩት ለአንተ ሲባል በቀር፣ ለሌላ ለማንም እንዳይደለ ይመሰክሩ ዘንድ ነበር። ሊሸነፍ የማይችለው ኃይልህ ሁሉን ነገሮች ስለሚናኝ፣ እስከ መጨረሻም ምንም ነገር

ሊገታው ስለማይችል፣ ከአንተ ቅዱስ ሕያው ጋር የተዛመደ ማንኛውም ነገር፣ እነርሱን ሊያረካቸው ከሚችል ከምንም ሌላ ነገር በላይ ብልጫ ያለውና የተከበረ መሆኑን በእርግጠኝነት ያውቁ ዘንድ፣ አንተ ለልቦቻቸው እርጋታን የሚያመጡትን ነገሮች ወደኋላ አስቀረህባቸው።

እነዚያ በመገንዘብ ችሎታ የታደሉት፣ እነዚህ የአንተን መለኮታዊ ምጥቀት ለማሳየትና የቅድስናህን ክቡርነት ለማረጋገጥ ሲባል በአንተ የታዘዙ መሆናቸውን ወዲያው ያውቁ ዘንድ፣ በእርግጥ አንተ እነዚህን ታላላቅ ሁኔታዎች እንዲፈጸሙ አድርገሀል።

## (55)

ጌታ ሆይ፣ ክብር ለአንተ ይሁን! አንድን ሰው ከምድራዊ ሃብት ሁሉ የተራቆተ ብታደርገውና ከሕይወቱ መጀመሪያ ጀምሮ ወደ አንተ እስከ ሚያርግበት ጊዜ ድረስ፣ በትዕዛዝህ ሥራ ወደ ድህነት እዲቀየር ብታደርገው እንኳ፣ ከፍቅርህ ዛፍ እንዲገኝ ካደረግኸው፣ በችሮታዎችህ መገለጽ አማካይነት፣ መንግሥተ-ሰማያዊውን ቤት ስለሚወርስ፣ በዚያ ከአዘጋጀሃቸውም መልካም ሥጦታዎች ስለሚካፈል፣ በእውነቱ እንዲህ ያለው በረከት በሰማይና በምድር በመካከላቸውም በሚገኘው ውስጥ ከፈጠርካቸው ነገሮች ሁሉ በጣም ይሻለዋል፤ አንተ ጋ የሚገኙ ነገሮች የማያልቁ ናቸውና። ይህ በእውነቱ አንተ በፈቃድህ መልካም ደስታ መሠረት እነዚያን በፍቅርህ መንገድ የሚራመዱትን የምታጎናጽፋቸው በረከት ነው።

በቀድሞ ጊዜያት ለአንተ ብለው የተገደሉት፣ በስሞቻቸውም አሁን ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን የሚያኩራሩ ነፍሶች እንዴት ብዙ ናቸው፤ የእነዚያም ምድራዊ ሀብቶችን ለማካበት ያስቻልካቸው፣ ከእውነትህ ተነፍገው እያሉም ያካበቷቸውና በዚህ ቀን ወደ መረሳት ያለፉት ቁጥራቸው እንዴት ብዙ ነው። አሳዛኝ ቅስፈትና ከባድ ቅጣት የእነርሱ ነው።

ጌታ ሆይ! ለመለኮታዊ አንድነትህ ዛፍ የተፋጠነ ዕድገት አስፈላጊውን ነገር አመቻች። እንግዲህ፣ ጌታ ሆይ፣ በመልካም ደስታህ ወራጅ ውሀዎች አጠጣው፤ በመለኮታዊ ዋስትናህም መገለጽ ፊት፣ ለመወደሻህና ለመከበሪያህ፣ ለሞገሥህና ለምሥጋናህ፣ ለስምህም ከፍ ከፍ መደረግ፣ ለሕላዌህም አንድነት መጉላትና ለአንተም ሥግደት ማቅረቢያ የምትሻቸውን ፍሬዎች እንዲያፈራ አድርገው። ይህ ሁሉ በመዳፍህ ውስጥ እንጂ በሌላ በማንም መዳፍ ውስጥ አይደለምና።

የእነዚያ አንተ የማረጋገጫህን ዛፍ በደማቸው እንዲያጠጡ፣ በዚህም መንገድ የቅዱሱንና የማይለወጠውን ቃልህን ክብር ከፍ ከፍ እንዲያደርጉ የመረጥካቸው ሰዎች ቡራኬአቸው ታላቅ ነው።

ጌታዬ ሆይ፣ የሁሉን ነገሮች አስቀድሞ የታዘዘ መጠን በእጅህ መዳፍ ውስጥ ይዘሃልና፣ ለእኔና ለእነዚያ ለሚያምኑብህ ያንን በእናት መጽሐፍ እንደሠፈረው፣ በአንተ አስተሳሰብ ይበልጥ የሚጠቅመንን እዘዝልን።

መልካም ሥጦታዎችህ፣ በእነዚያ ፍቅርህን በሚወዱት ላይ ያለማቋረጥ ይዘንባሉ፣ የመንግሥተ-ሰማያዊ በረከቶችህም ድንቅ ምልክቶች፣ ለእነዚያ መለኮታዊ አንድነትህን አውቀው ለሚቀበሉት በበቂ መጠን ይሰጣሉ። ለእኛ ያዘጋጀህልንን ማንኛውንም ነገር ለጥበቃ ለአንተ እንሰጣለን፤ ዕውቀትህ የሚያቅፈውንም መልካም ነገር ሁሉ እንድትሰጠን እንማጸንሃለን።

ጌታዬ ሆይ፣ ሁሉን አዋቂነትህ ከሚያየው ክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀኝ፤ ኃይልና ብርታት በአንተ እንጂ በሌላ የለምና፤ ድል አድራጊነትም ካንተ ዘንድ በቀር ከሌላ አይመጣምና፤ ማዘዙም የአንተ ብቻ ነው። አምላክ የፈቀደው ማንኛውም ነገር ሆኗል፤ እርሱ ያልፈቀደውም አይሆንም።

እጅግ በጣም በተከበረው፣ በእጅግ በጣም ኃያሉ አምላክ በቀር ኃይልም ብርታትም የለም።

(56)

ጌታ ሆይ! ማንም የተፈጠረ ሕያው ከመልካም ደስታህ ከልሎች ውጪ እንዳይቀር፣ ሁሉንም የምድር ሕዝቦች ወደ እምነትህ ገነት የመግባትን ፀጋ ለማግኘት አስችላቸው።

አንተ ሊታወስ ከማይቻል ጊዜ ጀምሮ የሚያስደስትህን ለማድረግ ችሎታ ያለህ፣ ከምትሻውም ከማንኛውም ነገር በላይ ሆነህ ኖረሃልና።

(57)

አምላኬ ሆይ፣ የፍቅርህንና የመልካም ደስታህን ሙሉ መጠን ስጠኝ፤ አቤቱ አንተ የላቀው ማስረጃና የተከበረው የሆንክ ሆይ፣ በአንፀባራቂ ብርሃንህም ስበቶች ልቦቻችንን አስደስት። የበረከት ጌታ ሆይ፣ ለጸጋህ ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ቀኑንም ሙሉ በሌሊትም ጊዜያት ሕይወት ሰጭ እስትንፋስህን በላዬ ላይ ተንፍስልኝ።

አምላኬ ሆይ፣ ፊትህን ለማየት ለመብቃት፣ ምንም ተግባር አልፈጸምኩም፤ የአገልጋይ ደረጃ ወደ ቅዱስ ክልሎችህ መግቢያ መንገድ ለማግኘት ምን ጊዜም እንከን ስለማያጣው፣ በረከትህ ካልደረሰኝ፣ ፍቅራዊ ምሕረትህም ካልኖኘኝ፣ ፍቅራዊ ደግነትህም ካልከበበኝ፣ ዓለም እስካለ ብኖርም እንኳ ለዚህ ችሮታ ብቁ ለመሆን የሚያስችለኝን ተግባር ለመፈጸም እንደሚሳነኝ ያለጥርጥር አውቃለሁ።

አቤቱ አንተ ከእርሱ በቀር ምንም ሌላ አምላክ የሌለው ሆይ፣ ምሥጋና ሁሉ ለአንተ ይሁን። ወደ አንተ ለማረግ፣ በቅርበትህም የመኖር ክብር ለማግኘትና ከአንተ ጋር ብቻ ለመቋረብ በጸጋህ አስችለኝ። ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለምና።

በእውነት አንዱን አገልጋይ ቡራኬ ለማጎናጸፍ ብትሻ የአንተን የራስህን ስም ማንሳት በቀር፣ እያንዳንዱን ሌላ ስም ማንሳት

ወይም ዝንባሌ ከልቡ ዓለም ታጠፋለህ፤ ሌላውን አገልጋይ ደግሞ እጆቹ በፊትህ በግፍ በሠሩት ሥራ ምክንያት ከፉ ብታዝበት፣ በዚያ በመጠመድ አንተን ማስተወስ ይረሳ ዘንድ በዚህና በሚቀጥለው ዓለም ጥቅሞች ትፈትነዋለህ።

(58)

አቤቱ አንተ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ በትእዛዝህ ኃይል ወደ መኖር ያመጣህ ጌታ ሆይ፣ ክብር ለአንተ ይሁን።

ጌታ ሆይ! እነዚያን ከአንተ በስተቀር ሌላውን የተውትን እርዳቸው፤ ታላቅ ድልም አቀዳጃቸው። ጌታ ሆይ፣ አገልጋዮችህን ለመርዳት፣ ለማጽናናትና ለማጠናከር፣ የሥራ መቃናትም ለመቀዳጀት ለማስቻል፣ ለመደገፍ፣ ገናናነትን፣ ክብርንና ከፍተኛነትን ለማጎናጸፍ፣ ለማበልጸግና በድንቅ ድልም ድል አድራጊዎች ለማድረግ፣ በሰማይና በምድር በመካከላቸውም ሁሉ የሚገኙትን የመላዕክት ሠራዊት ላክላቸው።

አንተ የእነርሱ ጌታ፣ የሰማያትና የምድር ጌታ፣ የሁሉ ዓለማት ጌታ ነህ። ጌታዬ ሆይ፣ በእነዚህ አገልጋዮችህ ኃይል፣ ይህን እምነት አጠናክረው፤ የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ ድል እንዲነሱ አድርጋቸው፤ እነርሱ በእውነቱ ከአንተ በስተቀር ከማንኛውም ነገር ራሳቸውን ያላቀቁ አገልጋዮችህ ናቸውና፤ አንተ ደግሞ በእውነቱ የእውነተኞች አማኞች መከታ ነህና።

ጌታ ሆይ፣ በእነርሱ ለዚህ ለማይደፈረው እምነት ማደር አማካይነት፣ ልቦቻቸው በሰማያትና በምድር በመካከላቸውም ከሚገኘው ከማንኛውም ነገር የበለጠ እየጠነከሩ ይሄዱ ዘንድ፣ ፈቃድህ ይሁን፤ ጌታ ሆይ፣ በሁሉም የሰው ዘር ያተኮረ ዕይታ ፊት ኃይልህን ያሳዩ ዘንድ፣ እጆቻቸውንም በድንቅ ኃይልህ ምልክቶች አበርታ።

## (59)

ጌታ ሆይ! ለተገን ወደ አንተ ሸሽቻለሁ ወደ ምልክቶችህም ሁሉ ልቤን አቅንቻለሁ።

ጌታ ሆይ! በጉዞ ላይ ሆኜ ወይም በቤት፣ በሙያዬ ወይም በሥራዬ ላይ ሆኜ፣ መላ እምነቴን በአንተ ላይ አድረጌአለሁ።

እንግዲህ ከሁሉም ነገሮች ነፃ ታደርገኝ ዘንድ፣ አቤቱ አንተ በምሕረትህ ተወዳዳሪ የሌለህ ሆይ፣ በቂ እርዳታህን ስጠኝ!

ጌታ ሆይ እንደፈለግህ ድርሻዬን አጎናጽፈኝ፣ አንተ በአዘዝህልኝ ነገር እንድረካ አድርገኝ።

ለማዘዝ ፍፁም የሆነ ሥልጣን ያንተ ነው።

## (60)

ጌታ ሆይ! አንተ ጥልቅ ኃዘንን ሁሉ አስወጋጅ፣ መከራንም ሁሉ አጥፊ ነህ። አንተ እርሱ ሀዘንን ሁሉ የሚያጠፋው፣ ባሪያውን ሁሉ ነፃ የሚያወጣው፣ ነፍስንም ሁሉ የሚዋጀው ነህ። ጌታ ሆይ በምሕረትህ መዳንን ስጠኝ፤ ከእነዚያም መዳንን ከአገኙት አገልጋዮች ጋራ ቁጠረኝ።

## (61)

ጌታ ሆይ፣ ከአንተ በቀር ሌላው ሁሉ ችግረኛና ምስኪን ሲሆን፣ አንተ ግን ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ ነበርክ፤ ለዘለዓለምም አንዱና እውነተኛ አምላክ ሆነህ ትቀጥላለህ። አምላኬ ሆይ በገመድህ ላይ አጥብቄ በመንጠላጠል፣ ከሰው ሁሉ ራሴን አላቅቄአለሁ፤ ፊቴንም ወደ ፍቅራዊ ምሕረትህ መኖሪያ በማዞር፣ ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ አዙሬአለሁ። አምላኬ ሆይ ከአንተ በቀር ሌላ ኃያልና ሁሉን አዋቂ ለማግኘት ስለማይቻል፣ በጸጋህና በቸርነትህ፣ በክብርህና በግርማህ፣ በገዢነትህና በታላቅነትህ በጸጋህ አነቃቃኝ። አምላኬ

ሆይ፣ በአንተ ላይ በቀር በሌላ በማንም ላይ ሙሉ እምነቴን ለማድረግ ስለማልችልና ከአንተም በቀር ሌላ ተገን ስለሌለ፣ በመጠቀው፣ በሁሉን አርኪ ክብርህ ኃይል እንዲሁም በሰማያትና በምድር ሠራዊቶች አማካኝነት ጠብቀኝ።

ጌታዬ አንተ አምላክ ነህ፤ ችግሮቼን ታውቃለህ፤ ሁኔታዬንም ታያለህ፤ በትዕዛዝህ ምክንያት ምን እንደደረሰብኝ፣ የበረከትህና የችሮታህ ምልክት ይሆን ዘንድ፣ በፈቃድህ ችዬ ያሳለፍኳቸውን ምድራዊ ሥቃዮች ደህና አድርገህ ታውቃለህ።

(62)

አምላኬ ሆይ የክብሮች ክብርና እጅግ በጣም አንጸባራቂ ብርሃን በአንተ ላይ ይረፍ። ግርማህ በጣም የመጠቀ በመሆኑ ምንም የሰው ሃሳብ ሊደርስበት አይችልም፤ ፍጹም ኃይልህም በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፣ የሰዎች ልቦችና አእምሮዎች አእዋፋት ከፍታዎቹ ላይ ለመድረስ ከቶ አይችሉም። ህያዋን ሁሉ ለደረጃህ እንደሚገባ ሊያወድሱህ ኃያል አልበነታቸውን ይገልጻሉ። ለመለካት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ። አንተ በራስህ እንዳለህ የምታውቀው ራስህ ብቻ ስለሆንክ ሕያውነትህን ሊያሞግሥ፣ ወይም በእጅግ በጣም ውሳጣዊ ሕልውናህ በሚገኘው ሁኔታ የበረከትህን ማስረጃዎች ጠልቆለመረዳት የሚችል ማንም የለም።

ጌታ አምላካችን ሆይ! የፍጥረትንና የፈጠራን ዓለም ወደ መኖር ለጠራህበት በረከት፡- ከአንተ በቀር ሌላ ማንም በሚገባ ሊገምተው በማይችለው፣ በማነቃቂያህ ኃይል በድምቀት በሚያበራው ምሥጋና፣ ለአንተ ምሥጋና አቀርባለሁ። ከዚህም በላይ፣ ለዚህ ቅዱስ ቡራኬ፣ ለዚህ በግልጸትና በፍጥረት መንግሥቶችህ ለተገለጸው ድንቅ ምልክት፣ ለአስፈሪ ቅርበትህና ለአሸናፊው ግርማህ ክብር እንደሚገባው አወድሥሃለሁ፤ ምሥጋናም አቀርብልሃለሁ።

ክብር ሁሉ ለአንተ ይሁን። ያ ለአንተ የሚገባው ለመለካት

ከሚቻል በላይ የተከበረ ነው። በእውነቱ የደረጃህን ምጥቀት ማንም በቂ በሆነ ሁኔታ ተረድቶት፣ ወይም ከአንተ በቀር ሌላ ማንም ለአንተ እንደሚገባ አውቆህ አያውቅም። ከአንተ በቀር ሌላው የግልጸትህን ከፍተኝነት ለመለካት የሚችል የሌለ ሲሆን፣ አንተ በሰፊ በረከትህ ኀርፎች አማካይነት ትገለጻለህ።

ስምህ የጎላ ይሁን። ከአንተ በቀር ሌላ ማንም የባሕርይህን ፍንጭ እንኳ ለመናገር ይችል ዘንድ ነፃ ሕልውና አለውን? ከአንተም በቀር ሌላው አንተን ላውቅበት የምችልበት የአምሳል ምልክት አለውን? የታወቀ ሁሉ መታወቁን የሚያገኘው፣ እጅግ በጣም ግልጽ ከሚለው ስምህ ውበት ነው፤ እያንዳንዱ ነገር ከማይሸነፈው ፈቃድህ በሚፈልቀው እርገብጋቢ ኃይል ከሥረ- መሠረቱ ተንቀሳቅሷል። አንተ ከሁሉም ነገሮች ይበለጥ ለሁሉ ነገሮች ቅርብ ነህ።

የተመሠገንከና የተከበርክ ነህ። ምጥቀትህ ከነዚያ የመረዳት ኃይል የተለገሠት ሰዎች እጆች ወደ አንተ ለመዘርጋት ከሚችሉበት ከፍታ የላቀ ነው፤ መጨረሻ የሌለውም ጥልቀትህ የሰዎች አእምሮዎችና የመገንዘብ ችሎታዎች ወንዞች ከዚያ ለመጉረፍ ከሚችሉበት ይበልጥ ጥልቅ ነው።

## (63)

አምላኬ ሆይ! ከአንተ በቀር ሌላ ማንም የነፍሴን ጥልቅ ኃዘን የሚያስወግድ የለም። አምላኬ ሆይ፤ አንተ እጅግ በጣም ከፍተኛ ምኞቴ ነህ። ልቤ ከአንተ ጋርና ከእነዚያ አንተ ከምትወዳቸው ጋር በቀር ከሌላ ከማንም ጋር አልተቆራኘችም። ሕይወቴም ሞቴም ለአንተ እንደሆነ በአክብሮት እገልጻለሁ። በእውነቱ አንተ ወደርም አቻም የለህም።

ጌታዬ ሆይ! ራሴን ከአንተ ለመጋረዴ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ። በክብርህና በግርማህ፣ አንተ ራስህን ስታስታውቀኝና ለደረጃህ በሚገባ ሁኔታ ስታስታውሰኝ፣ እኔ ግን አንተን በሚገባ

ሳላውቅህና ሳልሠግድልህ ቀርቻለሁ። ጌታዬ ሆይ፣ በሥሕተቶቼና በበደሎቼ ምክንያት ብትይዘኝ፣ ከባድ ችግር በወረደብኝ ነበር። ከአንተ በቀር ሌላ አጋዥ አላውቅም። ከአንተ በቀር የምሸሸበት ተገን የለኝም። ያለ ፈቃድህ ከፍጡሮች መካከል አንተን ለማማለድ ለመድፈር የሚችል የለም። በመንበርህ ፊት ፍቅርህን አጥበቄ ይዣለሁ፤ በትእዛዝህ መሠረት፣ ለክብርህ እንደሚገባው አጥብቄ ወደ አንተ እጸልያለሁ። ቃል እንደገባህልኝ ጥሪዬን እንድትሰማኝ እለምንሃለሁ። በእውነቱ አንተ አምላክ ነህ፤ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ለብቻና ያለእርዳታ፣ አንተ ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ነፃ ነህ። የአፍቃሪዎችህም ሥግደቶች ሊጠቅሙህ፣ የእምነተ-ቢሶቹም ክፉ አድራጎቶች ሊጎዱህ አይችሉም። በእውነቱ አንተ ቃል ኪዳኑን ከቶ የማያጓድል አምላክ ነህ።

አምላክ ሆይ! ወደ ቅዱስ ቅርበትህ የተቀደሱ ከፍታዎች እንድታቀርበኝ፣ ወደ አንተም ንግግር በቀር ወደሌላ ወደ ማንም አሳሳች ንግግሮች ራሴን ከማዘንበል እንድትጠብቀኝ፣ በችሮታህ ማስረጃዎች እማፀንሃለሁ። አምላኬ ሆይ፣ እርምጃዎቼን ለአንተ ተቀባይነት ወዳለውና ወደሚያስደስትህ ምራቸው። ከመዓትህና ከቅጣትህ ቁጣ በኃያልነትህ መከተኝ፤ በአንተ ወደማይፈለጉ መኖሪያዎችም ከመገባት አግደኝ።

(64)

አምላኬ ሆይ! ለክብርህ እንደሚገባ ሳላውቅህ ቀርቻለሁ፤ ከደረጃዬም እንደሚጠበቀው ሳልፈራህ ቀርቻለሁ። በዚህ ሁኔታ ሆኜ ስምህን ልጠራ እንዴት እችላለሁ፤ አንተን በማምለክ ተግባሬም ወደ ኋላ ቀርቼ እያለሁ ፊቴን ወደ አንተ ለማዞር እንዴት እችላለሁ?

አንተ ምንም ካልነበረበት ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ የኖርክ አምላክ ስለሆንክ፣ ወደ መኖር የጠራኸኝ በማያሳስት ሁኔታ የሚታየውንና ግልጽ የሆነውን የኃያልነትህን ኃይል ለማሳየት

አይደለም። ይልቁንም በጸጋህ አማካይነት በማስታወሻህ አንፀባራቂ ክስተት ፊት ለስማችን መነሣት ብቻ በላቀው ኃይልህ ፈጠርከን እንጂ።

አምላኬ ሆይ፤ ጉድለቴንና ኃጢአተኛነቴን ብቻ ከሚያንፀባርቀው፣ ራስህን እንዳውቅበት ከአስተማርከኝ ዕውቀት በቀር፣ ስለአንተ ምንም ዕውቀት የለኝም። አምላኬ ሆይ፤ እንግዲህ ለአንተ አድሬ፣ አንተ የምትሻውን ለማድረግ ፈቃደኛ ሆኜ፣ እዚህ ነኝ። አንተ አምላክ በመሆንህንም፣ ተጋሪ እንደሌለህና ከአንተ ጋር የሚመሳሰል ምንም እንደሌለ እየተናዘዝኩ፣ በምሕረትህ ግልጸቶች ፊት በትሕትና ራሴን እዘርራለሁ። ለዚህም አንተ ራስህ ለክብርህ በደንብ በሚገባው ሁኔታ ትመሠክራለህ።

## (65)

አምላኬ ጌታዬና መሪዬ ሆይ! እኔ ራሴን ከዘሮቼ አላቅቄአለሁ፤ በአንተም አማካይነት በምድር ላይ ከሚኖሩት ሁሉ ነፃ ለመውጣትና በፊትህ ተመሥጋኝ የሆነውን ለመቀበል ምን ጊዜም ዝግጁ ለመሆን ተማጽኜሃለሁ። ከአንተ በቀር ከማንኛውም ነገር ነፃ የሚያደርገኝን መልካም ነገር አጎናጽፈኝ፤ ወሰን ከሌላቸው ችሮታዎችህም ይበልጥ የተሟላውን ድርሻ ስጠኝ። በእውነቱ አንተ የተትረፈረፈ ጸጋ ጌታ ነህና።

## (66)

አምላኬ ሆይ፤ በኃያልነትህ በጥብቅ እማፀንሃለሁ! በፈተናዎች ጊዜያት ምንም ጉዳት እንዳይደርስብኝ፣ አድርግ፤ በግዴለሽነት ጊዜያትም በማነቃቃትህ እርምጃዎቼን በትክክል ምራቸው። አንተ አምላክ ነህ፤ የፈለግኸውን ለማድረግ ኃይል አለህ፣ ፈቃደህን ለመቋቋም ወይም ዓላማህን ለማሰናከል የሚችል ማንም የለም።

(67)

አምላኬ ሆይ፤ ይቅር ባይነትህን እለምናለሁ፤ አገልጋዮችህ ራሳቸውን ወደ አንተ እንዲያመሩ በምትፈልግበት ሁኔታም ይቅርታህን እማፀናለሁ። ለጌታነትህ በሚገባው ሁኔታ ኃጢአቶቻችንን ከእኛ ላይ እንድታነፃ፤ እኔን፣ ወላጆቼን፣ እነዚያንም በአንተ አስተሳሰብ ከሁሉ በላይ ለሆነው ሉዓላዊነትህና የሰማይ ለሆነው ኃይልህ ክብር በሚገባ ሁኔታ፣ ወደፍቅርህ መኖሪያ የገቡትን ይቅር እንድትለን እለምንሃለሁ።

አምላኬ ሆይ! አንተ ነፍሴ ልመናዋን ለአንተ እንድታቀርብ አነቃቅተሃታል፤ አንተ ባታነቃቃኝ ኖሮ፣ ባለመንኩህ ነበር። የተመሠገንህና የተከበርክ ነህ፤ ራስህን ስለገለጽክልኝ ምሥጋና አቀርብልሃለሁ፤ አንተን የማወቅ ተግባሬን ስለአጓደልኩና በፍቅርህም መንገድ ሳልራመድ ስለቀረሁ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ።

(68)

ጌታ አምላካችን ሆይ፣ ስምህ የተመሠገነ ይሁን! በእውነቱ አንተ የማይታዩትን ነገሮች ሁሉ አዋቂው ነህ። ሁሉን የማያቅፍ ዕውቀትህ ሊለካው የሚችለውን ዓይነት መልካም ነገር እዘዝልን። አንተ ሉዓላዊው ጌታ፣ ፍጹም ኃያሉ፣ ፍጹም ተወዳጁ ነህና።

ጌታ ሆይ፣ ምሥጋና ሁሉ ለአንተ ይሁን! ተስፋ በተሰጠለት ቀን ጸጋህን እንሻለን፣ እምነታችንንም ጌታችን በሆንከው በአንተ ላይ እናደርጋለን። አምላክ ሆይ፣ ከአንተ በስተቀር ሌላውን ነገር ሁሉ ለመተው እንድንችል መልካሙንና ተገቢ የሆነውን ስጠን። በእውነቱ አንተ የዓለማት ሁሉ ጌታ ነህና።

አምላክ ሆይ! እነዚያን በቀናትህ በትዕግሥት ችለው የሚኖሩትን ካሣቸው፤ ከመንገድህም ሳይወጡ በእውነት መንገድ እንዲራመዱ ልቦቻቸውን አበርታ። እንግዲህ፣ ጌታ ሆይ! ሐሴት

ወደተመላበት ገነትህ መግባትን ለማግኘት የሚያስችሏቸውን አስደሳች ሥጦታዎች አድላቸው። የተከበርክ ነህ ጌታ አምላካችን ሆይ። የመንግሥተ-ሰማይ የሆኑት ቡራኬዎችህ ነዋሪዎቻቸው በአንተ በአመኑብህ ቤቶች ላይ እንዲወርዱ አድርግ። በእውነቱ መለኮታዊ ቡራኬዎችን በማውረድ የሚወዳደርህ የለም። አምላክ ሆይ፣ ታማኝ አገልጋዮችህን ድል አድራጊዎች የሚያደርጓአቸውን ሠራዊቶች ስደድላቸው። አንተ በትእዛዝህ የተፈጠሩትን ነገሮች እንደፈለግኸው ታደርጋቸዋለህ። በእውነቱ አንተ ሉዓላዊው፣ ፈጣሪው፣ ፍጹም ጠቢቡ ነህና።

በል፡- በእውነቱ አምላክ ሁሉን ነገሮች ሠሪው ነው። እርሱ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለፈቀደው ለማንኛውም ሰው በገፍ ይሰጣል። እርሱ ፈጣሪው፣ የሕያዋን ሁሉ ምንጭ፣ የሚያበጀው፣ ፍጹም ኃያሉ፣ ሠሪው፣ ፈጹም ጠቢቡ ነው። እርሱ በሰማያትና በምድር በመካከላቸውም በሚገኘው ሁሉ እጅግ በጣም የላቁ ስያሜዎችን የተጎናጸፈ ነው። ሁሉ ትእዛዙን ይፈጽማሉ፤ የምድርና የሰማይ ነዋሪዎችም ለእርሱ ምሥጋና ያቀርባሉ፤ እንዲሁም ሁሉም ወደ እርሱ ይመለሳሉ።

## (69)

በፈጣሪው፣ በሉዓላዊው፣ በፍጹም አርኪው፣ ፍጹም በተከበረው፣ በእርሱ፣ እርዳታውን ሁሉ ሰዎች በሚማፀኑት በጌታህ ስም፣

በል፡- አምላኬ ሆይ! አንተ የሰማናያትና የምድር ሠሪ የሆንከው ሆይ፣ የመንግሥተ- ሰማዩ ጌታ ሆይ! አንተ የልቤን ምሥጢራት ደህና አድርገህ ታውቃለህ፤ የአንተ ሕላዌ ግን ለራስህ በቀር ለሌላ ለሁሉም በምርምር ሊታወቅ አይቻልም። አንተ ከእኔ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ታያለህ፤ነገር ግን ከአንተ በቀር ማንም ይህን ለማድረግ አይችልም። ከአንተ በቀር ሁሉን ለሙተው

የሚያስችለኝን በጸጋህ ስጠኝ፤ ከአንተም በቀር ከእያንዳንዱ ሰው ነፃ የሚያደርገኝን እዘዝልኝ። በዚህ ዓለምና በሚቀጥለው፣ የሕይወቴን ፍሬ ለመሰብሰብ እንድችል ፈቃድህ ይሁን። የጸጋህን በሮች በፊቴ ከፈትልኝ፤ በጸጋህም ፍቅራዊ ምሕረትህንና ሥጦታዎችህን አጎናጸፈኝ።

አቤቱ አንተ የተትረፈረፈ ጸጋ ጌታ የሆንከው ሆይ! መለኮታዊ እርዳታህ እነዚያን የሚወዱህን እንዲከብ አድርግ፤ አንተ ያለህን ሥጦታዎችና በረከቶች በላያችን አውርድልን። አንተ ጌታችንና የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ጌታ ነህ። የአንተን በስተቀር የሌላ የማንንም ስም አንጠራም፤ ከችሮታዎችህም በቀር ሌላ ምንም አንማፀንም። አንተ የበረከትና የጸጋ ጌታ፣ በኃይልህ የማትሸነፍ፣ በሥራህም ፍጹም ጠቢብ ባለሙያ ነህ። ከአንተ የሁሉ ባለቤት ከሆንከው፣ እጅግ በጣም ከተከበርከው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

ጌታዬ ሆይ፤ በመልእክተኞች፣ በቅዱሳንና በጻድቃን ላይ ቡራኬዎችን አውርድ። በእውነቱ አንተ ወደር የሌለው፣ ሁሉን አስገዳጁ አምላክ ነህና።

## (70)

ጌታ አምላኬ ሆይ፤ የተከበርክ ነህ! በእውነቱ አንተ የነገሥታት ንጉሥ ነህ። ሉዓላዊነትን በፈለግኸው በማንኛውም ሰው ላይ ታጎናጽፋለህ፤ ከፈለግኸውም ከማንኛውም ሰው ላይ ደግሞ ትገፋለህ። የፈለግኸውን ማንኛውንም ሰው ከፍ ከፍ ታደርገዋለህ፤ የፈለግኸውንም ማንኛውንም ሰው ታዋርደዋለህ። የፈለግኸውን ማንኛውንም ሰው የፈለከውን ድል እንዲያድርግ ታደርገዋለህ፤ በፈለግኸው በማንኛውም ሰው ላይ ውርደት ታደርስበታለህ። በፈለግኸው በማንኛውም ሰው ላይ ሀብት ታወርዳለህ፤ የፈለግኸውንም ማንኛውንም ሰው ወደ ድህነት ታወርደዋለህ። የፈለግኸውን ማንኛውንም ሰው ድል እንዲያደርግ ታደርገዋለህ።

የተፈጠሩትን ነገሮች ግዛት በመዳፍህ ውስጥ ይዘሃል። በሉዓላዊ ትእዛዝህም ኃይል የፈለግኸውን ማንኛውንም ሰው ወደ መኖር ትጠራለህ። በእውነቱ አንተ ሁሉን አዋቂው፣ ሁሉን ቻዩ፣ የኃይል ጌታ ነህ።

(71)

አምላክ ሆይ፣ የተመሠገንህና የተወደሥክ ነህ! ቅዱስ ምዕዓትህ ዘንድ የመቅረብ መቀዳጃው ቀን በፍጥነት እንዲቃረብ ፈቃድህ ይሁን። በፍቅርህና በመልካም ደስታህ ኃይል ልቦቻችንን አስደስትልን፤ ለፍላጎትህና ለትእዛዝህም በፈቃደኛነት እንድንገዛ ጽኑነትን አጎናጽፈን። በእውነቱ ዕውቀትህ የፈጠርካቸውን ወይም ወደፊት የምትፈጥራቸውን ነገሮች ሁሉ ያቅፋል፤ የመንግሥተ-ሰማይ የሆነው ኃያልነትህም ወደ መኖር ከጠራኸው ወይም ወደፊት ከምትጠራው ከማንኛውም ነገር ይልቃል። ከአንተ በስተቀር የሚሠገድለት ማንም የለም፤ ከአንተ በቀር ማንም ስሜት ማራኪ የለም፤ ከአንተ በስተቀር የሚመለክ ማንም የለም፤ ከመልካም ደስታህም በቀር ምንም የሚወደድ ነገር የለም።

በእውነቱ አንተ የላቀው ገዢ፣ ሉዓላዊው እውነት፣ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፣ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህ።

(72)

አምላኬ ሆይ፣ መከራዎች ከሁሉ አቅጣጫ እንደወረዱብኝና ከአንተ በቀር ሊያስወግዳቸው ወይም ሊለውጣቸው የሚችል ማንም እንደሌለ አንተ ሙሉ በሙሉ ታውቃለህ። የመንግሥተ- ሰማይ በሆነው ገነትህ ደረጃውን ከፍ ለማድረግና ልቡ ወደዚህ ዓለም ከንቱ ነገሮች እንዳታዘነብል፣ በዚህ ምድራዊ ሕይወት በሁሉን አስገዳጅ ኃይልህ ምሽግ ለመደገፍ ካልፈለግህ ማንንም ነፍስ መከራዎች እንዲወርዱበት ከቶ እንደማታደርግ፣ ለአንተ ባለኝ ፍቅር ምክንያት

በእርግጠኝነት አውቃለሁ። በእውነቱ፣ በሁሉም ሁኔታ በሰማያትና በምድር ካሉት ነገሮች ሁሉ ባለቤትነት በጣም የበለጠ አንተን ማስታወስ እንደምመርጥ አንተ ደህና አድርገህ ታውቃለህ።

አምላኬ ሆይ፤ ልቤን ለአንተ ለመታዘዝና ለአንተ ፍቅር አጠናክራት፤ ከመላው የጠላቶችህ አጀብም የተገለልኩ እንድሆን ፈቃድህ ይሁን። በእውነቱ አንተን በቀር ምንም እንደማልናፍቅ፣ ከምሕረትህም በቀር ምንም ነገር እንደማልመኝ፣ ከፍርድህም በቀር ምንም እንደማልፈራ በክብርህ እምላለሁ። እኔንና እነዚያን የምትወዳቸውን፣ አንተ በምትፈልገው በማንኛውም መንገድ ይቅር እንድትለን እለምንሃለሁ። በእውነቱ አንተ ኃያሉና ለጋሡ ነህና።

የሰማያትና የምድር ጌታ ሆይ፤ አንተ ከሁሉ ሰዎች ውዳሤ በላይ እጅግ በጣም የተከበርክ ነህ፤ በታማኝ አገልጋዮችህ ላይ ሰላም ይረፍ፤ ለዓለማት ሁሉ ጌታ፣ ለአምላክ ደግሞ ክብር ይሁን።

## (73)

እጅግ በጣም ተወዳጁ የሆንክ ጌታ ሆይ፣ ምሥጋና ለአንተ ይሁን! በእምነትህ ጽኑ አድርገኝ፤ ከእነዚያ ቃል ኪዳንህን ካልጣሱት፣ የገዛ ራሳቸውን ከእውነት የራቁ ከንቱ እምነቶችና ጣዖቶችን ካልተከተሉትም ጋር እንድቆጠር ፈቃድህ ይሁን። እንግዲህ በአንተ ዘንድ የእውነት መቀመጫ ለማግኘት አስችለኝ፤ የምሕረትህን ምልክት አጎናጽፈኝ፤ እንዲሁም ከእነዚያ ምንም ፍርሐት ከማይኖርባቸው፣ በኃዘንም ላይ ከማይጣሉ አገልጋዮችህ ጋር እንድቀላቀል አድርገኝ። ጌታዬ ሆይ፣ ለራሴ አትጣለኝ፣ እርሱን የአንተ የራስህ ክስተት የሆነውን ከማወቅ አትንፈገኝ፤ ከእነዚያ ከአንተ ቅዱስ ዘንድ ፊታቸውን ከአዞሩትም ጋር አትቁጠረኝ። አምላኬ ሆይ፤ ከእነዚያ ውበትህን አትኩሮ በማየት ከታደሉት፣ በዚያም ትልቅ ደስታን የሚደሰቱ በመሆናቸው፣ የዚያን ትንሿን ጊዜ እንኳ፣ በሰማያትና በምድር መንግሥታት ግዛት ወይም በመላው ፍጥረተ-ዓለም

ከማይለወጡት ጋር ቁጠረኝ። ጌታ ሆይ፤ የምድርህ ሕዝቦች በአሳዛኝ ሁኔታ በተሳሳቱባቸው በእነዚህ ቀናት፣ በእኔ ላይ ምሕረት ይኑርህ፤ አምላኬ ሆይ፤ እንግዲህ ያንን በአንተ አስተሳሰብ ተገቢ የሆነውን ነገር ለግሰኝ። በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃይል የተመላው፣ ጸጋ የተመላው፣ በረከት የተመላው፣ ዘለዓለም ይቅር ባዩ ነህና።

አምላኬ ሆይ፤ ከእነዚያ ጆሮዎቻቸው ከደነቆሩት፣ ዓይኖቻቸው ከታወሩት፣ አንደበቶቻቸው ንግግር አልባ ከሆኑት፣ ልቦቻቸውም መገንዘብ ከተሳናቸው ጋር እንዳልቆጠር ፈቃድህ ይሁን። ጌታ ሆይ፤ ከድንቁርናና ከራስ ወዳድነት ፍላጎት እሳት አድነኝ፤ ወደ ላቀው ምሕረትህም ክልል ለመግባት እንዲፈቀድልኝ አድርግልኝ፤ ያንን ለሕሩያንህ ያዘዝከውንም በላዬ አውርድልኝ። የፈለግኸውን ለማድረግ ችሎታ ያለህ ነህና። በእውነቱ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፣ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህ።

## (74)

አምላኬ ሆይ፣ ጌታዬ ሆይ፣ መሪዬ ሆይ!

ከፍቅርህ በቀር ማንኛውንም ሌላ ደስታ፣ ከቅርበትህም በቀር ማንኛውንም ምቾት፣ ከመልካም ደስታህም በቀር ማንኛውንም ደስታ፣ ከአንተ ጋር መቋረብንም በቀር ሌላ ማንኛውንም ኑሮ ለመፈለጌ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ።

## (75)

ከእግዚአብሔር በስቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ?

በል፡- ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይድረሰው! እርሱ አምላክ ነው! ሁሉም አገልጋዮቹ ናቸው፣ ሁሉም በትእዛዙ ይኖራሉ።

## ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት

(76)

የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ የእግዚአብሔር ዕውቀት ነው። የነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ዓላማ በሰማያት የሚገኙትን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚገኙትንም ሁሉ ከሚናኘው ከመለኮታዊ ፈቃድ መንግሥት የተላከውን ማንኛውንም ነገር በጥብቅ ማከበር ነው።

(77)

ሊታወስ ከማይቻል ጊዜ ጀምሮ፣ እንደ እግዚአብሔር ነቢያት ሁሉ ዓላማና የተስፋ ቃል፣ እንደ መልእክተኞቹም እጅግ በጣም የተወደደ ምኞት ሲታወጅና ሲወደስ የነበረው ግልጸት፣ አሁን በፍጹም ኃያሉ ሁሉን የሚናኝ ፈቃድና ማንም ሊቋቋመው በማይችለው ትእዛዙ ኃይል ለሰዎች ተገልጿል። የዚህም ግልጸት መጽዓት በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ታውጆ ነበር። ይህም አዋጅ እያለ የሰው ዘር ከመንገዱ እንዴት እንደራቀና ከክብሩም ራሱን እንዴት እንደዘጋ አስተውሉ።

በል፡- እናንተ የአንዱ እውነተኛ አምላክ አፍቃሪዎች ሆይ! እርሱን ለይቶ ለማወቅ፣ ሕግጋቱንም በሚገባ ለማክበር ተጣጣሩ። ይህ ግልጸት፣ አንድ ሰው አንዲት ጠብታ ደም ቢያፈስለት፣ እልፍ አእላፍ ውቅያኖሶች ወሮታ የሚያገኝበት ግልጸት ነው። ወዳጆች ሆይ፣ እንዲህ ያለውን ሊገመት የማይቻል ጥቅም እንዳታጡ ወይም የላቀ ደረጃውን ችል እንዳትሉ ተጠንቀቁ። በሕዝቦቿ ከንቱ አስተሳሰቦች በተታለለች ዓለም ውስጥ የተሰውትንና አሁንም በመሰዋት ላይ የሚገኙትን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ነፍሶች አስተውሉ። የልባችሁ ፍላጎት ስለተፈጸመላችሁና ከእርሱ፣ የሕዝቦች ሁሉ ተስፋ ከሆነው ጋር አንድ ለመሆን ስለቻላችሁ ለእግዚአብሔር ምሥጋና አድርሱ። የተቀዳጃችሁትን ደረጃ ክብር፣ ክብሩ ይስፋና፣ ከአንዱና እውነተኛው

አምላክ እርዳታ ጋር ጠብቁ፤ የእርሱም እምነት የሚስፋፋበትን መንገድ አጥብቃችሁ ያዙ። እርሱ በእውነቱ፣ ትክክለኛውንናየሰውን ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚጠቅመውን ያዛችኋል። የዚህ ድንቅ መልዕክት ገላጭ የሆነው ፍጹም ምሕረተኛው የተመሠገነ ይሁን።

## (78)

ይህ ቀን፣ የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት፣ የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ጸጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የናኘበት ቀን ነው። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በማስወገድ በእርሱ እንክብካቤና ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር፣ በፍጹም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው። በዚህ ቀን፣ ደረጃዎቻቸውን ከፍ ለማድረግና ከሁሉም የበለጡ ጥቅሞቻቸውን ለማዳበር የሚጠቅመውን ማንኛውም ነገር አጥብቀው መያዝ ይገባቸዋል። እነዚያ፣ የእርሱ፣ ፍጹም ክብር የተመላው ብዕር እንዲያስታውሳቸው እንዲንቀሳቀስ የተደረገው ደስተኞች ናቸው፤ እነዚያም፣ በማይመረመረው ውሳኔአችን፣ ስሞቻቸውን ለመደበቅ የመረጥናቸውም ሰዎች የተባረኩ ናቸው።

ሰዎች ሁሉ በእኛ ፊት ተቀባይነት ያለውን ነገር ለመፈጸም በጸጋው እንዲታገዙ እንዲፈቅድ፣ አንዱን እውነተኛ አምላክ ተማጸኑ። በቅርቡ የዛሬው ጊዜ ሥርዓት ይጠቀለላል፤ በምትኩም አዲሱ ይዘረጋል። በእውነቱ፣ ጌታችሁ እውነት ይናገራል፤የማይታዩትንም ነገሮች አዋቂ ነው።

## (79)

ይህ ቀን፣ የእግዚአብሔር ምሕረት ውቅያኖስ ለሰዎች የተገለጸበት፣ የፍቅራዊ ደግነቱ የቀን ኮከብ ጮራውን በእነርሱ ላይ የፈነጠቀበት፣ የእርሱ በረከት የተመላበት ችሮታ ደመናዎች በመላው የሰው ዘር ላይ ጥላቻውን ያጠሉበት ቀን ነው። በሚያነቃቁ የፍቅርና

የወንድማማችነት፣ የወዳጅነትና የበጎ አድራጎት የሕይወት ውሃዎች አማካይነት ያዘኑትን ለማስደሰትና ለማጽናናት ጊዜው አሁን ነው።

እነዚያ የእግዚአብሔር ተወዳጆች የሆኑት፣ በማንኛውም ቦታ ሲሰበሰቡና ከማንኛውም ሰው ጋር ሲገናኙ፣ ለእግዚብሔር ባላቸው ስሜት ፣ የእርሱን ምሥጋናና ውዳሴ በሚያቀርቡበትም ሁኔታ ምክንያት፣ ከእግሮቻቸው በታች የሚገኘው አቧራ እያንዳንዱ አቶም፣ ስለፍቅራቸው ጥልቀት ይመሠክር ዘንድ፣ በጣም ከፍተኛ ትሕትናና ታዛዥነት ማሳየት አለባቸው። እነዚህ ቅዱሳን ነፍሶች ከሰዎች ጋር የሚያደርጉት ንግግር በሚያስተላልፈው ስሜት ምክንያት፣ እነዚህ የአቧራ አቶሞች በጥልቅ ስሜት እንዲነኩ እንዲያደርግ በከፍተኛ ኃይል የተሞላ መሆን አለት። በላይዋ የሚራመዱባት ምድር፡- *"እኔ ከእናንተ የተሻልኩ ነኝ፣ ምክንያቱም፣ ገበሬው የሚጭንብኝን ሸክም ለመሸከም እንዴት ትዕግሥተኛ እንደሆንኩ ተመልከቱ። እርሱ የጸጋ ሁሉ ምንጭ የሆነው አደራ የጣለብኝን ቡራኬዎች፣ ለሕያዋን ሁሉ ያለማቋረጥ የማካፍለው መሣሪያ እኔ ነኝ። የተሰጠኝ ክብርና የማይቆጠር ሀብት እያለኝ፣ የፍጥረትን ሁሉ ፍላጎት የሚያረካ ሀብት ሁሉ እያለኝ የትሕትናዬን ጥልቀት አስተውሉ፤ በምን ዓይነት ፍጹም የሆነ ተገዢነት ራሴን በሰዎች እግሮች ሥር ለመረገጥ እንደፈቀድኩ ተመልከቱ፣…"* የሚሉትን ቃላት እንድትናገራቸው እንዳይፈቀድላት፣ ራሳቸውን በጣም ከፍተኛ በሆነ ሥነ-ምግባር መምራት አለባቸው።

ለእርስ በርሳችሁ መቻቻልን፣ ደግነትንና መፈቃቀርን አሳዩ። ከመካከላችሁ አንዱ አንድን እውነት ለመገንዘብ ቢያቅተው፣ ወይም ለመረዳት በመጣጣር ላይ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር በምትነጋገሩበት ጊዜ፣ የመጨረሻ ከፍተኛ ደግነትና የበጎ ፈቃድ መንፈስ አሳዩ። ራሳችሁን ትንሽ እንኳ ከእርሱ እንደምትሻሉ፣ ወይም የበለጠ ተሰጥኦ እንዳላችሁ ሳትገምቱ እውነቱን እንዲያይና እንዲያውቅ እርዱት።

በዚህ ቀን የሰው ሙሉ ተግባር፣ ያንን እግዚአብሔር

የሚያፈስለትን የጸጋ ጎርፍ ድርሻ ለማግኘት መብቃት ነው። ስለዚህ ማንም ስለመቀበያው ትልቅነት ወይም ትንሽነት አያስብ። የእያንዳንዱ ድርሻ አንድ እፍኝ ያህል ይሆናል። የሌሎች ድርሻ አንድ ፍንጃል፣ የሌሎቹ ደግሞ አንድ ጋሎንም ይሞላ ይሆናል።

በዚህ ቀን፣ እያንዳንዱ ዓይን፣ የእግዚአብሔርን እምነት ከሁሉ ይበልጥ የሚያራምደውን መፈለግ አለበት። እርሱ ዘለአለማዊ እውነት የሆነው ይመሠክርልኛል! በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና ግጭት፣ እንደ ውዝግብ እንደ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም። በአምላክ ኃይልና በእርሱ ሉዓላዊ እርዳታ፣ ሽሿቸው፣ በእርሱም፣ በአዋሐጁ በሁሉን አዋቂው፣ በፍፁም ጠቢቡ ስም የሰዎችን ልቦች ለማስተሣሠር ተጣጣሩ።

በእርሱ መንገድ የሚከናወኑትን ዓይነት ተግባሮች ጣዕም እንድትቀምሱ፣ ለእርሱ ሲሉ ሰዎች ከሚያሳዩአቸው የትሕትናና የተኻርነት ጣፋጭነት እንድትሳተፉ እንዲፈቅድላችሁ፣ አንዱን እውነተኛ አምላክ ተማፀኑ። የገዛ ራሳችሁን ረስታችሁ ዓይኖቻችሁን ወደ ጎረቤታችሁ መልሱ። ጉልበታችሁን የሰዎችን ዕውቀት ለሚያዳብር ለማንኛውም ነገር አውሉ። ከእግዚአብሔር የተደበቀ ወይም ምንጊዜም ሊደበቅ የሚችል ምንም ነገር የለም። የእርሱን መንገድ ብትከተሉ የእርሱ ሊገመቱ የማይችሉና የማይጠፉ ቡራኬዎች ይዘንቡላችኋል። ይህ፣ ጥቅሶቹ ከእርሱ የዓለማት ሁሉ ጌታ ከሆነው የሚንቀሳስ ብዕር የጎረፉት አንጸባራቂው ጽላትነው።በልቦቻችሁ አሰላስሉት እነዚያ የእርሱን ሕግጋት ከሚያከብሩትም ሁኑ።

## (80)

ለምድር ሕዝቦችና ዘሮች አስቀድሞ የተወሰነላቸው ጊዜ አሁን ደርሷል። በእግዚአብሔር የተሰጡት ተስፋዎች በቅዱሳን

መጻሕፍት ውስጥ እንደተመዘገቡት ሁሉም ተፈጽመዋል። የእግዚአብሔር ሕግ ከጽዮን ወጥቷል፤ እየሩሳሌምም፣ ኮረብታዎችዋና ሜዳዎቿ በእርሱ ግልጸት ክብር ተሞልተዋል። በአደጋ ጊዜ ረዳት፣ በገዛ ራሱም በሚኖረው አምላክ መጻፍት ውስጥ የተገለጹትን በልቡ የሚያሰላስል ሰው ደስተኛ ነው። እናንተ የአምላክ ተወዳጆች ሆይ፣ የጽናቱን የጠሩ ውሃዎችበእርሱ ጸጋና በምሕረቱ እስከትረኩ ትጠጡ ዘንድ፣ በእርሱም እምነት ጽኑዎችና እንደተራራ የማትገፉ ትሆኑ ዘንድ፣ ይህን አሰላስሉ፣ ጆሮዎቻችሁም የእርሱን ቃል እንዲያዳምጡ አድርጉ።

በኢሳይያስ መጽሐፍ፡- *"ጌታን በመፍራትና ስለእርሱ ግርማ ክብር ቋጥኝ ውስጥ ግባ፣ በአቧራም ውስጥ ተደበቅ"* ተብሎ ተጽፏል። ይህን ጥቅስ ሚያሰላስል ማንኛውም ሰው የዚህን የእምነት ታላቅነት ለመገንዘብ አይሳነውም፤ የዚህንም ቀን፤ የአምላክን የራሱን ቀን የተከበረ ባሕርይ ሊጠራጠር አይችልም። ከዚህም ጥቅስ ቀጥለው እነዚህ፡- *"በዚያን ቀን ጌታ ብቻ የተከበረ ይሆናል፤"* የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። ይህ እጅግ በጣም ከፍተኛው ብዕር በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ያሞገሠው ቀን ነው። ከጥቅሶቻቸው ውስጥ የእርሱን ቅዱስ ስም ክብር የማይገልፅ አንድም ጥቅስ የለም፣ ከመጽሐፎቻቸውም ውስጥ ስለዚህ እጅግ በጣም ስለተከበረው አርዕስት ታላቅነት የማይመሠክር አንድም መጽሐፍ የለም። ስለዚህ ግልጸት በነዚህ መንግሥተ-ሰማያዊ መጻሕፍትና ቅዱሳት ጽሑፎች የተጠቀሱትን ሁሉ ብንጠቅስ ይህ መልእክት የማይቻል ስፋት ይኖረዋል። በዚህ ቀን፣ እያንዳንዱ ሰው በብዛትና በዓይነት ብዙ በሆኑ የአምላክ ጸጋዎች ላይ ሙሉ እምነቱን በማድረግ፣ የእርሱን እምነት እውነቶች በከፍተኛ ጥበብ ለማሰራጨት መነሣት አለበት። በዚያን ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ ብቻ መላው ምድር በእርሱ ግልጸት የንጋት ብርሃን ይሸፈናል።

(81)

ያለፈውን ጊዜ አስታውስ። በሁሉ ጊዜያት የእግዚአብሔርን ከስተቶች፣ በእርሱ ምርጦች የተቀደሱ ሰብአዊ አካላት መምጣት፣ ስንቱ ትልቁም ትንሹም፣ በናፍቆት ተጠባበቁ። መምጣቱን የተጠባበቁት እንዴት ብዙ ጊዜ ነበር፣ የመለኮታዊ ምሕረት ነፋስ እንዲነፍስና በተስፋ የሚጠበቀው ውበት ከድብቅነት መጋረጃ ወጥቶ ለዓለም ሁሉ እንዲገለጽ የጸለዩት እንዴት ብዙ ጊዜ ነበር። የጸጋ በሮች በተከፈቱ፣ የመለኮታዊ ልግሥና ደመና በሰው ዘር ላይ በዘነበና የሥውሩ ብርሃን ከመንግሥተ-ሰማያዊው ኃይል አድማስ በላይ በአበራ ቁጥር ግን፣ ሁሉም ካዱት፣ ከእርሱም ፊት፣ ከእግዚአብሔር ከራሱ ፣ ፊታቸውን አዞሩ...

(82)

የቀድሞን ትውልዶች አስብ። የመለኮታዊ ቸርነት የቀን ኮከብ የግልጸቱን ብርሃን በዓለም ላይ በተፈነጠቀ ቁጥር የዘመኑ ሰዎች እንዴት እንደተነሡበትና እውነቱን እንደተቃዎሙ ተመልከት። እነዚያ እንደ ሕዝቡ መሪዎች የተቆጠሩት፣ ሁሉም በአንድ ዓይነት ተከታዮቻቸው ወደ እርሱ፣ የአምላክ ወሰን የሌለው ቸርነት ውቅያኖስ ወደ ሆነው እንዳይመለሱ ለመከልከል ጥረት አድርገዋል።

በዘመኑ የነበሩት ካህናት ከሰጡት ፍርድ የተነሣሕዝቡ የእግዚአብሔርን ወዳጅ አብርሃምን እንዴት እሳት ውስጥ እንደጣለ፣ ከፍጹም ኃያሉ ጋር የተነጋገረውም ሙሴ እንዴት እንደ ሐሰተኛና እንደ ስም አጥፊ እንደተወገዘ ተመልከት። የእግዚአብሔር መንፈስ የሆነው የሱስ፣ ምንም እንኳ የላቀ ከፍተኛ ትሕትናውና ፍጹም ሩኅሩኅነቱ የታወቁ የነበሩ ቢሆንም ምን እንደደረሰበት አስብ። እርሱ የሕያው ሕልውና፣ የሚታዩና የማይታዩ ነገሮች ሁሉ ጌታ የሆነው

መጋፈጥ የነበረበት ተቃውሞ በጣም የከፋ ስለነበር እራሱን የሚያሳርፍበት ቦታ እንኳ አልነበረውም። ቋሚ መኖሪያም ስለተነፈገ ያለማቋረጥ ከቦታ ወደ ቦታ ተንከራተተ። የሁሉም ሕይወት ለእርሱ መስዋዕት ይሁንለትና የነቢያት መደምደሚያ በሆነው በመሐመድ ላይ የደረሰውንም አሰላስል። የአምላክን አንድነትና የመልዕክቱን እውነትነት በማወጁ፣ የሁሉም ሉዓላዊ ጌታ በሆነው ላይ በአይሁድ ሕዝብ መሪዎችና በጣዖት አምላኪዎች እጅ የደረሰበት ሥቃይ ምንኛ የከፋ ነበር! በእምነቴ ትክክለኛነት! በእነዚያ የአምላክን ቃል ኪዳን በተላለፉት፣ ማረጋገጫውን በሻሩት ማስረጃዎቹን ባልተቀበሉትና ምክንያቱንም ባስተባበሉት እጅ በደረሰበት ኃዘን ምክንያት ብዕሬ ያቃስታል፤ የተፈጠሩትም ነገሮች ሁሉ ታላቅ ልቅሶ ያለቅሳሉ። እነሆ ትገነዘብ ይሆናል በማለት በቀደምት ቀናት የሆነውን ታሪክ በዚህ ሁኔታ እንተርክልሃለን።

የእግዚአብሔር ነቢያት መልዕክተኞቹና ምርጦቹ እንዴት በሚያሳዝን ሁኔታ እንደተሰቃዩ አውቀሃል። ይህን ዓይነት ማሰቃየት ያስከተለው መነሾና ምክንያት ምን እንደሆነ አንድ ጊዜ አሰላስል። የእግዚአብሔር ነቢያት በምንም ጊዜና በማንኛውም ግልጸት ዘመን፣ ትክክለኞችና ጻድቃን መስለው ከሚታዩት ጠላቶቻቸው ስድብ፣ ከጨቋኞቻቸው ጭካኔና ከዘመናቸው ምሑራን ውግዘት አምልጠው አያውቁም። ሌት ተቀን፣ ክብሩ ይስፋና ከአንዱ እውነተኛ አምላክ ዕውቀት በቀር ሌላ ማንም ሊገምተው በማይችል ስቃይ ውስጥ አልፈዋል።

ይህን ግፍ የተዋለበትን አስብ። እምነቱን እጅግ በጣም ግልጽ ማስረጃዎች ቢያረጋግጡም፣ እርሱ በሚያሳስት ቋንቋ የተናገራቸው ትንቢቶች የተፈጸሙ ቢሆንም፣ ምንም እንኳን ከሊቃውንት እንደ አንዱ የማይቆጠር፣ ትምህርት ቤት ገብቶ ያልተማረና በወቅቱ በካሕናት መካከል በነበረው ክርክርም ልምድ ያልነበረው መሆኑ የታወቀ ሆኖ ሳለ፣ እርሱ በመለኮታዊ ኃይል

ቀስቃሽነት የተገለጹትን ብዙና ልዩ ልዩ የእውቀቱን ዝናቦች በሰዎች ላይ ያዘነበ ቢሆንም፣ ይህ ትውልድ ግን እንዴት ሥልጣኑን አልቀበልም እንዳለና በእርሱም ላይ እንዳመጸ ተመልከት! እርሱ በአብዛኛው የሕይዎቱ ዘመን በጠላቶቹ መዳፍ ውስጥ ከፉኛ ተሰቃይቷል። በዚህ የእርሱ፣ ጨቋኞች በግፍ በወረወሩበት አሰቃቂ ወህኒ ቤት አሁን ስቃዩ የባሰ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። የተፈጸሙትንና አሁንም በመፈጸም ላይ ያትን ነገሮች በአስተዋይ ዓይንና በብሩህ ልቦና እንድታስተውል፣ እነዚህን በልብህ በማሰላሰል፣ በዚህ ቀን፣ የሚበዙት ሰዎች ሊረዱት ያልቻሉትን ለመገንዘብ እንድትችል እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን። የእርሱን ቀን ጣፋጭ ሽታ ለማሽተት፣ ወሰን ከሌላቸው የጸጋው ጎርፎች ለመካፈል፣ በእርሱ ጸጋ የተሞላበት ችሮታ፣ በዚህ ቀን በጥንቱ ንጉሥ ስም ከሚሞግደው እጅግ በጣም ታላቅ ውቅያኖስ ድርሻህን ለመጠጣት፣ በእርሱም እምነት ጠንካራ ሆነህ ለመጽናትና እንደ ተራራ የማትነቃነቅ ጽኑ ሆነህ ለመዝለቅ ያስችልህ ዘንድ፣ የአምላክ ፈቃዱ ይሁን።

እንዲህ በል፡- ቅዱሳን ሁሉ በብዙና የተለያዩ የኃያልነትህ መገለጾች ፊት ምንም አቅም እንደሌላቸው እንዲያምኑ፣ እያንዳንዱም ነቢይ የነዋሪ ክብርህ ብርሃን በሚያንጸባርቅበት ጊዜ የራሱን ከምንም አለመቆጠር እንዲገልጽ ላደረግኸው ለአንተ ክብር ይሁን።በዚህ ቀን እንዳገለግልህ እንድታስችለኝና በመጽሐፍህ ውስጥ የታዘዙትን እንዳከብር እንድታጠናክረኝ፣የመንግሥተ-ሰማያት በሮች እንዲከፈቱና የሰማይ ሠራዊት በሐሴት እንዲሞሉ ባደረገው ስምህ እማጸንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፣ በአንተ ውስጥ ያለውን ታውቃለህ፣ ነገር ግን እኔ ባንተ ውስጥ ያለውን አላውቅም። አንተ ሁሉን አዋቂው ሁሉን የተረዳህ ነህና።

(83)

በእግዚአብሔር አንድነት አማኞች ሆይ፤ በአሳሳች ስሜታችሁ በመሸነፍ በእርሱ እምነት ክስተቶች በማንኛውም መካከል ልዩነት

እንዳታደርጉ፣ እንዲሁም ግልጸቶቻቸውን የአጀቡትንና የአወጁትን ምልክቶች እንዳታበላልጡ ተጠንቀቁ። ይህን እውነት ከሚረዱትና ከሚያምኑት ብትሆኑ የመለኮታዊ አንድነት እውነተኛና ምሥጢር ይህ ነው። ከዚህም በላይ የእነዚህ የአምላክ ክስተቶች የእያንዳንዳቸውና የሁሉም ሥራዎች ተግባራቸው፣ እንዲያውም ማንኛውም ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያለውና ማንኛውም እነርሱ ወደፊት የሚገልጹት ሁሉ በአምላክ የታዘዙ፣ የፍቃዱና የዓላማውም ነጸብራቅ ለመሆናቸው እርግጠኛች ሁኑ። በስብዕናቸው፣ በቃሎቻቸው፣ በመልዕክቶቻቸው፣ በተግባራቸውና በጠባያቸው መካከል የሚቻለውን የመጨረሻውን ትንሽ ልዩነት እንኳ ያደረገ ማንም ሰው፣ በአምላክ የማመን ቃሉን አጥፏል፤ ምልክቶቹን አስተባብሏል፤ የመልዕክተኞቹንም ዓላማ ክዷል።

(84)

ለእግዚአብሔር አንድነት ምሥጋና ሁሉ ይሁን፤ እንዲሁም ለእርሱ፣ ወደር ለሌለውና ፍጹም ክብር ለተሞላው የፍጥረተ-ዓለማት ገዥ፣ የሁሉን ነገሮች እውነታ ፍጹም ከሌለ ነገር ለፈጠረው፣ ከሌለው ነገር የፍጥረቱን እጅግ በጣም የተጣሩና የረቀቁ ንጥረ ነገሮች ወደ መኖር ለጠራው፣ ፍጡሮቹን ከመራቅ ውርደትና በመጨረሻም ከመጥፋት አደጋ በማዳን በእርሱ የማይበላሽ የክብር መንግሥት ውስጥ ለተቀበላቸው፣ ለሉዓላዊው ክብር ሁሉ ይሁን። ሁሉን ከሚያጥለቀልቀው ምሕረቱ በቀር ሌላ ምንም ነገር ይህን ከፍጻሜ ለማድረስ ባልቻለ ነበር። እንዲህ ባይሆን ኖሮ የሌለ ነገር ከፍጹም አለመኖር ሁኔታ በራሱ ወደ ሕያው ዓለም መሸጋገር ብቃትና ችሎታ ለማግኘት እንዴት ይቻለው ነበር?

ዓለምን፣ በውስጧም የሚኖሩትንና የሚንቀሳቀሱትን ከፈጠረ በኋላ በማይገታውና በሉዓላዊ ፈቃዱ ቀጥታ ክንዋኔ፣ እንደመላው ፍጥረት ማመንጫ አንቀሳቃሽ ኃይልና እንደቀዳሚ ዓላማ መቆጠር ያለበትን ችሎታ፣ እርሱን የማወቅና የማፍቀር ልዩ ክብርና ችሎታ

በሰው ላይ ለማጐናጸፍ መረጠ ... እርሱ በእያንዳንዱና በሁሉም የተፈጠረ ነገር ውስጣዊ እውነታ ላይ ከስሞቹ የአንዱን ብርሃን ፈነጠቀበት፤ ከባሕርይዎቹም የአንዱን ከብር ተቀባይ እንዲሆን አደረገው። በሰው እውነታ ላይ ግን የስሞቹንና የባሕርያቱን ብርሃን ሁሉ አበራበት፤ የገዛ ራሱም መንጸባረቂያ መስተዋት አደረገው። ሰው፣ ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ እርሱ ብቻ ለእንደዚህ ዓይነቱ ችሮታ፣ እንዲህ ላለው ዘላቂ በረከት ተመረጠ. . .

(85)

የአዳምን ክስተት ከዚያ ከባብ ጋር ያስተሣሡሩትን የተከታታይ ግልጸቶችን ሰንሰለት በውስጣዊ ዓይንህ ልብ ብለህ አሰላስል። እነዚህ ክስተቶች እያንዳንዳቸው፣ በመለኰታዊ ፈቃድና ዓላማ ከንዋኔ አማካይነት ወደ ምድር ተልከው የነበሩ መሆናቸውን፣ እያንዳንዳቸው የተለየ መልእክት አምጪዎች እንደነበሩ፣ እያንዳንዳቸው በመለኮታዊ ኃይል የተገለጸ መጽሐፍ ተሰጥቶአቸው እንደነበረና፣ የታላቅ መልዕክት ምሥጢር እንዲገልጹ ሥልጣን ተሰጥቶአቸው እንደነበረ በአምላክ ፊት እመሠክራለሁ። እያንዳንዳቸው የታወቁበት ግልጸት መጠኑ አስቀድሞ የተወሰነ ነበር። ከእነዚያ ይህን እውነት ከሚገነዘቡት ብትሆኑ ኖሮ፣ ይህ በእውነቱ ለእነርሱ የችሮታችን ምልክት ነው።

(86)

ስለፍጹም መሐሪው ወዳጅ ስለአብርሃም የሰማኸው እውነት ነው፤ ለዚህም ምንም ጥርጥር የለውም። የእርሱ በአምላክ እምነት የመጽናትና ከአምላክ በቀር ከዓለማዊ ነገር ሁሉ የመላቀቅ ሁኔታ ለሰዎች ይገለጽ ዘንድ፣ እስማኤልን መስዋዕት እንዲያቀርብ የአምላክ ድምጽ አዞት ነበር። ከዚህም በላይ፣ የአምላክ ዓላማ፣ እርሱን ለዓለም

ሕዝቦች ሁሉ ኃጢአትና በደል እንደቤዛ መስዋዕት ለማቅረብ ነበር። የሱስ የማርያም ልጅም ይህንኑ ክብር ያጐናጽፈው ዘንድ፣ ክብሩ ይሰፋና፣ አንድን እውነተኛ አምላክ ተማጸነ። ለዚሁ ለራሱ ምክንያት የአምላክ መልእክተኛ የሆነው መሐመድ ሁሴይንን ለመስዋዕትነት አቀረበው።

ድብቅና ወሰን የሌለውን፣ የአምላክን ጸጋ ሁኔታ ማንም ሰው እስከምን ጊዜም ተረድቻለሁ ብሎ ለመናገር አይችልም፤ የሁሉን አቀፍ ምሕረቱንም ጥልቀት ለመረዳት የሚችል ማንም አይገኝም። የሰዎች ጠማማነትና በደል ከባድ ስለሆነ፣ በእግዚአብሔር ለቢያትና በምርጦቹ ላይ ያደረሱትም ስቃይ በጣም አሳዛኝ ስለሆነ፣ የሰው ዘር በሙሉ መሠቃየትና መጥፋት በተገባው ነበር። ነገር ግን፣ የአምላክ ሥውርና እጅግ በጣም ፍቅራዊ የሆነ አምላካዊ ጥበቃ፣ በሚታዩትም ሆነ በማይታዩት ኃይሎች አማካኝነት ከከፋቱ ቅጣት ተከላከለውታል፤ ለወደፊቱም ይከላከሉለታል። እውነቱ ይገለጽልህ ዘንድ ይህን በልብህ አሰላስል፤ በእርሱም መንገድ ጽኑ ሁን።

## (87)

የአምላክ ነቢያት የተከፋፈለውን የሰው ዘር በአንድነት መንፈስ አማካኝነት ከበሽታው ይፈውሱ ዘንድ፣ ዓላማቸው ዓለምንና የሕዝቦቿን ደህንነት መጠበቅ እንደሆነ እንደሐኪሞች መቆጠር ይገባቸዋል። በሽተኛውን ተረድተናል፣ በሽታዎቹንም በትክክል ለይተናል ብለው ለመናገር የሚችሉት እነርሱ ብቻ ስለሆኑ፣ ቃላቸውን የመጠራጠርም ሆነ ተግባራቸውን የማቃለል መብት ለማንም አልተሰጠም። የመገንዘብ ችሎታው ምንም ያህል ጥልቅ ቢሆን፣ መለኮታዊው ሐኪም ከደበረሰበት ጥበበኝነትና የመገንዘብ ኃይል ከፍታ ለመድረስ ተስፋ የሚያደርግ ሰው እስከመቼም ሊገኝ ከቶ አይችልም። ስለዚህ በአሁኑ ዘመን በሐኪሙ የታዘዘው መድኃኒት ባለፈው ዘመን ከታዘዘው ጋር አንድ ዓይነት ሆኖ ሳይገኝ ቢቀር

የሚያስደንቅ አይደለም። ሕመምተኛውን የሚያሠቃዩት በሽታዎች በእያንዳንዱ የሕመሙ ደረጃ የተለየ መፈወሻ የሚያስፈልጉ ከሆኑ፣ እንዴት ከዚህ የተለየ ሊሆን ይችላል? በዚህ ዓይነት የአምላክ ነቢያት በመለኮታዊ ዕውቀት የቀን ኮከብ አንፀባራቂ ብርሃን ዓለምን ባበሩዋት ቁጥር ሁሉም በአንድ ዓይነት እነርሱ በተነሡበት ዘመን ከነበሩት ሁኔታዎች አንፃር የበለጠ ተስማሚ በሆነ መንገድ ሕዝቦቿ የአምላክን ብርሃን እንዲያቅፉ ጠርተዋል። እነርሱ በዚህ ዓይነት የድንቁርናን ጨለማ ለመበተንና የራሳቸውን ዕውቀት ክብር በዓለም ላይ ለማብራት ችለዋል። ስለዚህ የእነርሱ አንዱና ብቸኛ ዓላማ ሁል ጊዜ የተሳሳቱትን ለመምራት፣ ለተሠቃዩትም ሰላም ለመስጠት ስለሆነ የማስተዋል ኃይል ያለው የእያንዳንዱ ሰው ዓይን አቅጣጫውን ማተኮር ያለበት፣ ወደ እነዚህ ነቢያት ውስጣዊ ሕልውና ነው። እነዚህ የብልጽግናና የድል ቀናት አይደሉም። መላው የሰው ልጅ ቁጥርስፍር በሌላቸው ችግሮች መዳፍ ውስጥ ተጨብጦ ይገኛል። ስለዚህ፣ በማይሳሳተውና በፍጹም ኃያሉ ሐኪም እጅ በተዘጋጀው ፍቱን መድኃኒት አማካይነት፣ ሕይወቱን ለማዳን ጥረት አድርጉ።

## (88)

የሰው ልጅ ትንፋሹን ለአምላክ በሰጠበት ጊዜ መላው ፍጥረት በትልቅ ኃዘን እንዳለቀሰ እወቅ። ይሁን እንጂ ራሱን በመሰዋቱ፣ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ አዲስ ችሎታ ተናኘ። የዚህም ማስረጃ በምድር ሕዝቦች ሁሉ ውስጥ እንደታየው አሁን በፊትህ ተገልጿል። ሊቃውንት የተናገሩት እጅግ በጣም ጥልቅ ጥበብ፣ ማንኛውም አዕምሮ የገለጸው እጅግ በጣም ታላቅ ዕውቀት፣ እጅግ በጣም የሰለጠኑ እጆች የሠሯቸው የኪነ-ጥበብ ሥራዎች፣ እጅግ በጣም ታላቅ ኃይል ባላቸው መሪዎች የተገኙ የመለወጥ ተጽዕኖዎች ሁሉ የእርሱ የላቀ፣ በሁሉም የሚሠርጽ መንፈስ-ሕይወት ሰጭነት ኃይል ያመነጫቸው ውጤቶች ናቸው።

ወደ ዓለም በመጣበት ጊዜ የክብሩን ብርሃን በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ እንዳበራ እንመሠክራለን። በእርሱ፣ ለምፃሙ ከጠማማነትና ከድንቁርና ለምጽ ነፃ። በእርሱ፣ ንጽሕና የጐደላቸውና አመጸኞች ተፈወሱ። በእርሱ ከፍጹም ኃያሉ አምላክ የተገኘ ኃይል የዕውራን ዓይነቶች በሩ፤ የኃጢአተኛውም ነፍስ ተቀደሰች።

ለምጽ በሰውና በጌታው፣ በአምላኩ መካከል ተጋርዶ እንዳያውቀው እንደሚያደርገው እንደማንኛውም ግርዶሽ ሊተረጐም ይችላል። ራሱን ከእርሱ ለሚሠውር ለማንኛውም ነገር መንገድ የሰጠ ሁሉ፣ በእርግጥ በታላቁ፣ በፍጹም ተመሥጋኙ አምላክ መንግሥት የማይታወስ ለምፃም ነው። በአምላክ ቃል ኃይል አማካይነት እያንዳንዱ ለምፃም ከለምፃምነቱ እንደነፃ፣ እያንዳንዱ በሽተኛ እንደዳነ፣ እያንዳንዱ የሰው ዘር ድክመት እንደተወገደ እኛ እንመሠክራለን። ዓለምን ያነፃው እርሱ ነው። በብርሃንም በሚያንጸባርቅ ፊት ወደ እርሱ የዞረ፣ የተባረከ ነው።

## (89)

በእያንዳንዱ የግልጸት ዘመን የመለኮታዊው ግልጸት ብርሃን ለሰዎች የተሰጠው ከመንፈሳዊ ችሎታዎች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ እንደነበር በእርግጥ ዕወቅ። ፀሐይ ገና ከአድማስ በላይ ስትታይ ጨረርዋ እንዴት ደካማ እንደሆነ፣ ከዚያም፣ በዚያ ጊዜ ውስጥ፣ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ እየጨመረ ከሚሄደው የብርሃኗ ኃይል ጋር እየተለማመዱ ለመሄድ እንዲችሉ ለማስቻል፣ እንዴት ቀስ በቀስ እንደምትጨምር፣ ቀጥላም መጥለቂያዋ ነጥብ ላይ እስክትደርስ ድረስ ያለማቋረጠ እየቀነሰች እንዴት እንደምትሄድ አስተውል። ድንገት በአንድ ጊዜ በውስጧየተደበቀውን ኃይል በሙሉ ብትሰጥ ኖሮ፣ ያለምንም ጥርጥር በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ ጉዳት ባስከተለች ነበር . . . ። በተመሳሳይ ሁኔታ የእውነቱ ፀሐይ ወዲያው ሲከሰት፣

በአንድ ጊዜ የፍጹም ኃያሉ አምላክ ፈቃድ በአጐናጸፈው ሙሉ ኃይል ቢገለጽ ኖሮ፣ የሰው ዘር የመረዳት ኃይል ምድር ባክኖ በጠፋ ነበር፣ ምክንያቱም የሰዎች ልቦች የግልጸቱን ኃይል ለመሸከምም ሆነ የብርሃኑን ጨረር መልሰው ለማንጸባረቅ ባልቻሉም ነበርና። በኃይሉ ተሸንፈውና ተስፋ ቆርጠው መኖራቸውን በአቆሙ ነበር።

(90)

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ፣ ልባችሁን ወደ እውነተኛውና ተወዳዳሪ ወደሌለው ወዳጃችሁ ምክሮች መልሱ። የአምላክ ቃል ሥሮቹ በሰዎች ልቦች ውስጥ በተተከለ ችግኝ ሊመሰል ይችላል። ሥሮቹ ጠንክረው ይይዙ፣ ቅርንጫፎቹም እስከሰማይና ከዚያም አልፈው ይዘረጉ ዘንድ፣ በጥበብ ሕያው ውሃ፣ በተባረኩና በተቀደሱ ቃላት አማካይነት ዕድገቱን መንከባከብ አለባችሁ።

እናንት በምድር የምትኖሩ ሆይ! የዚህን ልዕልናው የላቀውን ግልጸት ከሁሉ በላይ የሆነውን ባሕርይ ከሌሎች ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያደርገው ገጽታ፣ በአንድ በኩል በሰዎች መካከል የሁከት፣ የተንኮልና የብጥብጥ ምክንያት የነበረውን ማንኛውንም ነገር ከአምላክ ቅዱስ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ ማስወገዳችን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለስምምነት፣ ለመግባባት፣ ለተሟላና ለዘላቂ አንድነት በቅድሚያ የሚያስፈልጉትን መደንገጋችን ነው። ትእዛዛቴን የሚያከብሩት የበጃቸው ናቸው።

ተወዳጆቻችንን የከፋት ሽታ ሊገኝባቸው ከሚችለው ከማናቸውም ነገሮች እንዲርቁ፣ እንዲያውም እንዲሸሹ መልሰን መላልሰን መከረናቸዋል። ዓለም በትልቅ ብጥብጥ ውስጥ ናት፣ የሕዝቦቿም አዕምሮዎች ፍጹም ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ ናቸው። በጸጋው በእርሱ ፍትሕ ክብር እንዲያንጸባርቁ እንዲያደርጋቸው፣ በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ የሚጠቅማቸውን ለማወቅ እንዲያስችላቸው፣ ፈጹም ኃያሉን እንማጸናለን። እርሱ በእውነቱ፣

ሁሉ ነገር ያለው፣ እጅግ በጣም ከፍተኛው ነውና።

## (91)

የማዝነው በመታሠሬ ስለደረሰብኝ ችግር አይደለም። በመዋረዴ ወይንም በጠላቶቼ እጅ ከምሠቃይባቸው መከራዎች የተነሣ የኃዘን ስሜት አልተሰማኝም። በሕይወቴ! ብታውቁት ኖሮ፣ እነዚህ ክብሬ፣ አምላክ ራሱን ያስገጤባቸው ክብር ናቸው።

እንድሸከመው ተደርጌ የነበረው ሐፍረት መላው ፍጥረት እንዲጐናጸፍ ተደርጎ የነበረውን ክብር አሳየ፤ ችየ በአሳለፍኳቸው ጭካኔዎች አማካይነት የፍትሕ የቀን ኮከብ ራሱን ገለጸ፤ የእርሱም ደማቅ ብርሃን በሰዎች ላይ አንጸባረቀ።

ኃዘኔ ለእነዚያ ራሳቸውን በእርኩስ ፍላጎታቸው ውስጥ ለጨመሩትና፣ ጸጋ ከተመላው፣ ከፍጹም ተወዳጁ አምላክ እምነት ወገን ነን ለሚሉት ነው።

ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ በጣም የተላቀቁ ከመሆናቸው የተነሣ፣ የገነት ነዋሪዎች ከልብሳቸው ጣፋጭ ጣዕም ያለውን የቅድስና ሽታ ያሸቱ ዘንድ፣ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ከፊቶቻቸው የፍጹም ምሕረተኛውን አንጸባራቂነት ያውቁ ዘንድ በእነርሱም አማካይነት የፍጹም ኃያሉ፣ የፍጹም ጠቢቡ አምላክ ምልክቶችና መታወቂያዎች ይሠራጩ ዘንድ፣ የባሃ ሕዝብ ለዓለምና በውስጧ ለሚገኙት ነገሮች ሁሉ መሞት ይገባቸዋል። እነዚያ የሥጋዊ ነገሮችን በመከተላቸው ምክንያት የእግዚአብሔርን እምነት መልካም ስም ያጐደፉት እነዚህ ጉልህ በሆነ ሥሕተት ውስጥ ናቸው።

## (92)

አይሁዳውያን ሆይ! የእግዚአብሔርን መንፈስ፣ የሱስን እንደገና ለመስቀል ቁርጥ ሃሣብ ካላችሁ፣ እርሱ በእኔ ስብዕና እንደገና

ተገልጿልና ግደሉኝ። በእግዚአብሔር መንገድ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠት ስለማልኩ እንዳሻችሁ አድርጉኝ። የምድርና የሰማይ ኃይላት ሁሉ ተባብረው ቢነሡብኝም እንኳማንንም አልፈራም። የወንጌል ተከታዮች ሆይ! የእግዚአብሔርን መልእክተኛ፣ መሐመድን ለመሰዋት ፍላጐት ካላችሁ፣ ያዙኝና ሕይወቴን አሳልፉ፤ እኔ እርሱ፣ ራሴም እርሱ ራሱ ነውና። ጥልቅ የልቤ ናፍቆት በእርሱ የክብር መግሥት በእጅግ በጣም ተወዳጁ ፊት መቅረብን ለመቀዳጀት ስለሆነ፣ እንደፈቀዳችሁ አድርጉኝ። ብታውቁት ኖሮ፣ የመለኮታዊው ውሳኔ እንዲህ ያለ ነው። የመሐመድ ተከታዮች ሆይ! መጽሐፉን ባያንን ወደ እናንተ እንዲላክ ያደረገውን በጥይቶቻችሁ ለመበሳሳት ፍላጐታችሁ ከሆነ፣ እጆቻችሁን ጫኑብኝና አሠቃዩኝ፣ ምክንያቱም ምንም እንኳ ስሜ ስሙ ባይሆንም እኔ የእርሱ እጅግ በጣም ተወዳጅ፣ የእርሱም የራሱ መገለጽ ነኝና። እኔ በክብር ደመናዎች ጥላ ሥር ሆኜ መጥቻለሁ፤ አምላክ የማይሸነፍ ሉዓላዊነት እንድጐናጸፍ አድርጎኛል። እርሱ፣ በእውነቱ፣ እውነት የሆነው የማይታዩትን ነገሮች አዋቂው ነው። እኔ፣ በእርግጥ፣ በእርሱ ከእኔ በፊት በመጣው ላይ ያደረሳችሁትን በእኔም ላይ እንደምትደግሙት እጠባበቃለሁ። ከእነዚያ ከሚሰሙት ብትሆኑ ኖሮ ስለዚሁ ሁሉም ነገሮች ይመሠክራሉ።

እናንተ የባያን ሰዎች ሆይ! የእርሱን ስለመምጣቱ ባብ ያወጀውን፣ እርሱ እንደሚመጣ መሐመድ የተነበየውን፣ እርሱ እንደሚገለጽ የሱስ ክርስቶስ ራሱ የአስታወቀውን ደሙን ለማፍሰስ ከወሰናችሁ፣ ዝግጁና ያለምንም መከላከያ ከፊታችሁ ቆሜአለሁ፤ እንደፍላጎታችሁ አድርጉኝ።

## (93)

ሕዝብ ሆይ! በአንዱ እውነተኛ አምላክ እምላለሁ! ይህ ባሕሮች ሁሉ ከውስጡ የወጡት፣ በመጨረሻም እያንዳንዳቸው

ውስጡ የሚቀላቀሉት ውቅያኖስ ነው። ሁሉም ፀሐዮች ከእርሱ መነጩ፤ ወደ እርሱ ሁላቸውም ይመለሳሉ። በእርሱ ኃይል አማካይነት እግዚአብሔር ብቻ ሁሉን በሚሸፍነው ዕውቀቱ ሊቆጠራቸው በሚችላቸው በሁሉም ዓለማት፣ ለእግዚአብሔር ፍጡራን መልዕክት ይዘው፣ እያንዳንዳቸው በነቢይ መልክ የተላኩ፣ የመለኮታዊ ግልጸት ዛፎች ፍሬዎቻቸውን አፈሩ። ይህንን የፈጸመው በአምላክ እውነት ኃይል ሕይወቱ በሚጠበቀው ጣቱ ተመርቶ በሚንቀሳቀሰው ብዕሩ በተገለጸው በአንዱ ብቸኛ ፊደል መሣሪያት ነው።

(94)

ፍጹም ተወዳጄ በሆነው አምላክ ትክክለኝነት! ምድራዊ መሪነትን ተመኝቼ ከቶ አላውቅም። ከዚህ ዓለም ከሆነው ነገር ሁሉ እንዲላቀቁ ያደርጋቸው ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ያልሆኑት ሊገነዘቡት፣ ሕጉን የማይከተሉትም ሊያስቡት ወደማይችሉት ከፍታዎችም እንዲደርሱ ያደርጋቸው ዘንድ፣ ብቸኛ ዓላማዬ፣ ጸጋ በተመላው፣ ወደር በሌለው አምላክ እንዳስተላልፍ የታዘዝኩትን ለሰዎች ለማስተላለፍ ነበር።

(95)

ከግልጸቱ ንጋት ጊዜ ጀምሮ፣ ይህ የተገፋው የሰውን ዘር ሁሉ ፊታቸውን የክብር የቀን ምንጭ ወደ ሆነው አቅጣጫ እንዲመልሱ እንደጠራ፣ ብልሹነትን፣ ግፈኝነትንና ጭካኔን እንደከለከለ የማያዳላ አዕምሮ ያለው ተመልካች ሁሉ በቀላሉ ይቀበላል። ሆኖም፣ የጨቋኙ እጅ የፈጸመውን ተመልከት! የግፍ ሥራውን ደፍሮ የሚዘረዝር ምንም ብዕር አይገኝም። የእርሱ የዘለዓለማዊው እውነት ዓላማ ለሰዎች ሁሉ ዘለዓለማዊ ሕይወት ለመስጠት፣ ደህንነታቸውንና ሰላማቸውን ለማረጋገጥ ቢሆንም፣ የተወዳጆቹን ደም ለማፍሰስ እንዴት እንደተነሡ፣ በእርሱም ላይ እንዴት የሞት ፍርድ እንደፈረዱ ተመልከቱ።

የዚህ ጭቆና አነሣሾች እነዚያ በጣም አላዋቂ የሆኑ ቢሆኑም፣ ከጥበበኛ እጅግ በጣም ጥበበኞች የመባልን ዝና ያገኙ ሰዎች ናቸው። ዕውርነታቸው በጣም የባሰባቸው ከመሆኑ የተነሣ፣ በግልጽ ጭካኔ፣ እርሱን፣ ለእርሱ መድረክ አገልጋዮች ተብላ ዓለም የተፈጠረችውን፣ በዚህ በተመሸገውና በአስጨናቂው እሥር ቤት ወረወሩት። የእነርሱና የእነዚያ የዚህን *"የታላቅ ለዋጅ"* እውነተኛነት የካዱት ሰዎች ሥራ እንዲህ ቢሆንም ፍጹም ኃያሉ ግን ይህንን እሥር ቤት ወደ እጅግ በጣም ከፍተኛ ገነት፣ ወደ ሰማየ-ሰማያት ቀይሮታል።

(96)

ዓለም ሥቃይ ውስጥ ናት፣ ብጥብጧም ከዕለት ወደ ዕለት ይባባሳል። ፊቷ ወደ አመጸኝነትና ወደ ክሕደት ዞሯልና። ችግሯ በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ፣ አሁን መግለጹ ጊዜውም ተገቢም አይደለም። ክፋቷ ለረዥም ጊዜ ይቀጥላል። የተወሰነው ሰዓት ሲደርስ፣ የሰውን ዘር አካላት እንዲንዘፈዘፉ የሚያደርገው በድንገት ይመጣል። ከዚያን በኋላ፣ ከዚያ በኋላም ብቻ መለኮታዊው ሰንደቅ ዓላማ ይዘረጋል፤ የገነትም ወፍ ዜማውን ያሰማል።

(97)

እንዲህ በል፡- ልትገነዘቡት ብትችሉ ኖሮ፣ የምትፈልጉት የዚህን ዓለም ሕይወትና በውስጧም ያሉትን ከንቱ ነገሮች ከሆነ፣ ገና በእናቶቻችሁ ማሕፀን ተሸፍናችሁ በነበራችሁበት ጊዜ በፈለጋችኋቸው ነበር፣ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ያለማቋረጥ ወደ እነዚህ እየቀረባችሁ ነበርና። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከተወለዳችሁና ወደ ብስለት ከደረሳችሁ ጊዜጀምሮ፣ በየጊዜው ከዚህ ዓለም እየራቃችሁ ወደ አፈርም እየቀረባችሁ ናችሁ። ቀኖቻችሁ የተቆጠሩ፣ ዕድሎቻችሁም ሊያመልጧችሁ የቀረቡ ሆኖ ሳለ፣ ታዲያ፣ የምድርን ሃብት

ለማከማቸት እንዲህ ያለ ስግብግብነት የምታሳዩት ለምንድነው? እንግዲህ፣ እናንተ ግዴለሾች ሆይ፣ እንቅልፋችሁን አታራግፉምን?

ይህ አገልጋይ ለእግዚአብሔር ብሎ ወደሚሰጣችሁ ምክሮች ጆሮዎቻችሁን አቅኑ። እርሱ፣ በእውነቱ፣ ከእናንተ ወሮታ ለመጠየቅ አይፈልግም፤ እግዚአብሔር ያዘዘለትን በትዕግሥት ተቀብሏል፣ ለእግዚአብሔርም ፈቃድ ፍጹም ተገዢ ነው።

ሕዝብ ሆይ፣ የሕይወታችሁ ቀናት አብዛኞቹ አልፈዋል፤ መጨረሻችሁም በፍጥነት እየተቃረበ ነው። ስለዚህ የፈጠራችኋቸውንና የተጣበቃችሁባቸውን ነገሮች ወዲያ ተውአቸው። እርሱ ያዘጋጀላችሁን ትቀዳጁ፣ ከእነዚያ ትክክለኛውን መንገድ ከሚከተሉትም ትሆኑ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ሕግጋት አጥብቃችሁ ያዙ። ራሳችሁን በዓለም ነገሮችና በከንቱ ጌጦቿ አታስደስቱ፤ ተስፋዎቻችሁንም በእነሱ ላይ አታድርጉ። መተማመኛችሁ እጅግ ከፍ ያለውን፣ ፍጹም ታላቁን አምላክ በማስታወስ ላይ እንዲሆን አድርጉ። እርሱ፣ ብዙ ሳይዘገይ፣ የያዛችኋቸውን ነገሮች ሁሉ እንዳልነበሩ ያደርጋቸዋል። የምትፈሩት እርሱን ይሁን፤ ከእርሱ ከእናንተ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን አትርሱ፤ ከእነዚያም ልክ በግርዶሽ ከእርሱ እንደተጋረዱት አትሁኑ።

በእግዚአብሔር ፊት በኩራት እንዳትጀነኑ፣ ተወዳጆቹንም ንቀት በተመላበት ሁኔታ እንዳትከዱ ተጠንቀቁ። ለታማኞቹ፣ ለእነዚያ በእግዚአብሔርና በመልዕክተኞቹ ለዓመኑት፣ ልቦቻቸው ስለአንድነቱ ለሚመሠክሩት፣ አንደበቶቻቸው ስለአንድነቱ ለሚያውጁት፣ በእርሱ ፈቃድ በስተቀር ለማይናገሩት ትሕትናን አሳዩ። ምናልባት ትነቁ ይሆናል በማለት በፍትሕ እንመክራችኋለን፤ በእውነትም እናስጠነቅቃችኋለን።

በራሳችሁ ላይ እንዲጫንባችሁ የማትመኙትን ሸክም በማንም ነፍስ ላይ አትጫኑ። ለራሳችሁም የማትመኙትን ነገሮች ለማንም አትመኙ። ብትከተሉት ኖሮ፣ ይህ ለእናንተ ከሁሉም የበለጠ

ምክሬ ነው።

እነዚያን በመካከላችሁ ከሚገኙት ካህናትና ጠቢባን ውስጥ ጠባዮቻቸው ከሚያስተምሩት ጋር የሚስማሙትን፣ እግዚአብሔር የወሰነላቸውን ወሰን የማይተላለፉትን፣ ፍርዶቻቸው እርሱ በመጽሐፉ ውስጥ ከገለፃቸው ትእዛዛት ጋር የሚስማሙትን አክብሩ። እነርሱ ለእነዚያ በሰማይና በምድር ለሚገኙት የመመሪያ መብራቶች እንደሆኑ ዕወቁ። እነዚያ በመካከላቸው የሚገኙትን መንፈሳዊ መሪዎችና ጠቢባን ወደ ጐን የሚተውት፣ ቸልም የሚሏቸው፣ እነዚህ በእውነቱ እግዚአብሔር የዋለላቸውን ውለታ በሌላ ለውጠዋል።

በል፦ እግዚአብሔር የዋለላችሁን ውለታ እስኪለውጥ ጠብቁ። ምንም ነገር፣ ማንኛውም ቢሆን ከእርሱ አያመልጥም። እርሱ የሰማያትንና የምድርን ምሥጢሮች ያውቃል። ዕውቀቱ ሁሉን ነገር ያቅፋል። በአደረጋችሁት፣ ወይም ወደፊት በምታደርጉት አትደሰቱ፣ ወይም ባደረሳችሁበት መከራዎች ደስ አይበላችሁ፤ ምክንያቱም ሥራችሁን በጥልቀት የመረዳት ችሎታ ብትመራመሩት ኖሮ፣ ይህን በመሰለ ሥራ አማካይነት ደረጃዎቻችሁን ከፍ ልታደርጓቸው አትችሉምና። እንዲሁም ከከፍተኝነት ደረጃችን ዝቅ ልታደርጉት ችሎታ የላችሁም። ይልቁንም የደረሰብንን መከራ በማያቋርጥ ትዕግሥት በማሳለፋችን እግዚአብሔር እኛን በሚከስበት ዋጋ ላይ ይጨምርበታል። እርሱ፣ በእውነቱ፣ የእነዚያን በትዕግሥት የሚዘለቁትን ዋጋቸውን ያበዛል። ፈተናና መከራ፣ ለማስታወስ ከማይቻልበት ጊዜ በፊት ጀምሮ፣ የእግዚአብሔር ምርጦችና የእርሱ ተወዳጆች፣ የእነዚያ ከእርሱ በስተቀር ከሌላው ነገር ሁሉ የተገለሉት፣ የእነዚያ ፍጹም ኃያሉን ከማስታወስ ሸቀጥም ሆነ ልውውጥ የማያታልላቸው፣ የእነዚያ እርሱ፣ እስኪናገር ድረስ የማይናገሩት፣ በትእዛዛቱም መሠረት የሚሠሩት ዓይነት አገልጋዮቹ ዕጣ ፋንታ እንደበረ ዕወቁ። ቀድሞ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የአምላክ ዘዴ እንዲህ ነበር፤ ለወደፊቱም በዚሁ ዓይነት ይቀጥላል። ለረዥም ጊዜ

በጽኑነት የሚችሉ፣ እነዚያ በችግርና በመከራ ጊዜ የሚታገሡ፣ በሚደርስባቸው በማንኛውም ነገር ምክንያት ሰቆቃ የማያሰሙ፣ ራስን በማስገዛት (በአምላክ ቃል) መንገድ የሚራመዱ የተባረኩ ናቸው ...

ቀኖቻችንን የሚያስታውስ፣ የፈተናችንን ታሪክ የሚተርክ፣ ከእነዚያ ያለምንም ማስረጃ ግልጽ ግፍ ከአደረሱብን ሰዎች መብታችን እንዲመለስ የሚጠይቀውን ሕዝብ እግዚአብሔር የሚያስነሣበት ቀን እየተቃረበ ነው። እግዚአብሔር፣ በእውነቱ፣ የእነዚያን ፍትሕ ያጓደሉብንን ሰዎች ሕይወት ይቆጣጠራል፤ አድራጎቶቻቸውንም በትክክል ያውቃልና። እርሱ፣ በፍጹም እርግጠኝነት ስለኃጢአቶቻቸው እጁን ያሳርፍባቸዋል። እርሱ በእርግጥ ከብድር መላሾቹ ሁሉ ይበልጥ ኃይል የመላው ነው።

ምናልባት ከእርሱ ይቅርታን ትጠይቁ፣ ወደ እርሱም ትመለሱ፣ በእውነትም ትፀፀቱ፣ ሥሕተቶቻችሁን ትገነዘቡ፣ እንቅልፎቻችሁን ተራግፉ፣ ከግዴለሽነት ትቀሰቀሱ፣ ስለአመለጧችሁ ነገሮች ንስሐ ትገቡ፣ መልካም ነገር ከሚያደርጉትም ትሆኑ ዘንድ፣ የአንዱን እውነተኛ አምላክ ታሪክ የዘረዘርንላችሁና እርሱ አስቀድሞ የወሰናቸውን ነገሮች ለእናንተ የላክንላችሁ በዚህ ዓይነት ነው። የፈለገ የቃላቴን እውነተኝነት ይቀበል፤ የማይፈልግ ደግሞ ገለል ይበል። ምናልባት ከእነዚያ ማስጠንቀቂያዬን ከሚሰሙት ብትሆኑ በማለት፣ የእኔ ብቸኛ ተግባር ለእግዚአብሔር እምነት ተግባራችሁን ሳትፈጽሙ መቅረታችሁን ማሳሰብ ነው። ስለዚህ፡- እርሱ በጸጋው ምሕረት ያደርግላችሁ ዘንድ፣ ኃጢአቶቻችሁን ከእናንተ ያጥብ ዘንድ፣ ሕግ መተላለፋችሁንም ይቅር ይላችሁ ዘንድ፣ ንግግሬን አድምጡ፤ ወደ እግዚአብሔርም ተመለሱና ንስሐ ግቡ። የምሕረቱ ታላቅነት ከንዴት ቁጣው ይልቃል፣ ጸጋውም ወደ መኖር የተጠሩትንና በሕይወት ልብስ የተሸፈኑትን ሁሉ፣ ያለፉትንም ጊዜያት ሆነ የወደፊቶቹን ያቅፋል።

(98)

የዓለም ሚዛን በዚህ ከሁሉም ይበልጥ ታላቅ፣ በዚህ አዲስ የዓለም ሥርዓት ንዝረት ኃይል ተናግቷል። በሥርዓት የነበረው የሰው ዘር አኗኗር፣ መሰሉን ሚች ዓይኖች ዓይተውት ከቶ በማያውቁት በዚህ ልዩ፣ በዚህ ድንቅ ሥርዓት ኃይል አማካይነት ተለውጧል።

ምሥጢራቱን ትገልጹና በጥልቀቱ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን የጥበብ ዕንቁዎች ሁሉ ታገኙ ዘንድ ራሳችሁን በቃላቱ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥሙ። የአምላክ ኃያልነት እምቅ ኃይሎችየተገለጹበትንና ሉዓላዊነቱም የተረጋገጠበትን እምነት የዚህን እምነት እውነነት ለመቀበል በቁርጥ ሃሣባችሁ እንዳታመነቱ ተጠንቀቁ። ፊቶቻችሁ በሐሴት እያንጸባረቁ ወደ እርሱ ገሥግሡ። ይህ ጥንትም ዘለዓለማዊ ወደፊትም ዘለዓለማዊ የሆነው የማይለወጥ የአምላክ እምነት ነው። የሚሻው ያግኘው፤ መፈለጉን እምቢ ላለው ደግሞ፣ በእውነቱ፣ አምላክ ራሱን የቻለ፣ ከማንኛውም የፍጡሮች ለእርሱ ማስፈለግ በላይ ነው።

በል፡- ከእነዚያ ይህንን እውነት ከሚያምኑትና ከአወቁት ብትሆኑ ኖሮ፣ ይህ የእግዚአብሔር እጅ ይዞት ያለው በሰማያትና በምድር ያሉት ሁሉ የሚመዘኑበት፣ ዕድላቸውም የሚወሰንበት የማይሳሳት ሚዛን ነው። በል፡- በዚህ አማካይነት ድሆች በለጸጉ፣ ምሑራንም ተገለጸላቸው፤ ተመራማሪዎችም ወደ አምላክ ቅርበት ከፍታ ለመውጣት እንዲችሉ ተደረጉ። በመካከላችሁ የመለያየት ምክንያት እንዳታደርጉት ተጠንቀቁ። በኃያሉ፣ በአፍቃሪው ጌታችሁ እምነት እንደማይነቃነቅ ተራራ የጸናችሁ ሁኑ።

(99)

የዓለም ሕዝቦች ሆይ፣ የውበቱ የቀን ኮከብ በጠለቀ ጊዜ፣ የመቅደሴ ሰማይ ከዓይኖቻችሁ በተደበቀ ጊዜ አይከፋችሁ። እምነቴን

ለማስፋፋትና፣ ቃሌን በሰዎች መካከል ከፍ ከፍ ለማድረግ ተነሡ። በሁሉም ጊዜያት ከእናንተ ጋር ነን፤ በእውነትም ኃይል አማካይነት እናጠናክራችኋለን። እኛ በእውነቱ ፍጹም ኃያልነን። እኔን ያወቀኝ ማንኛውም ሰው፣ ዓላማውን የሰማይና የምድር ኃይላት ሊያሸንፉት በማይችሉት ቁርጠኝነት ተነሥቶ ያገለግለኛል።

የዓለም ሕዝቦች በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ናቸው። ከእንቅልፋቸው ቢነቁ ኖሮ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ፍጹም ጠቢብ ወደ ሆነው አምላክ በጉጉት በገሠገሡ ነበር። ጌታቸው፣ በአንድ ቃል ብቻም ቢሆን በማነጋገር እንዲያስታውሳቸው፣ ያላቸውን ነገር ሁሉ፣ የመላው ምድርም ሀብት እንኳ ቢሆን ይተዋሉ። የሁሉም ዓለማት ምንም የማይሳነው ጠባቂ ለሆነው ለእርሱ ለራሱ በቀር ለማንም ባልተገለጸውና የፍጥረት ዓይን አይቶት በማያውቀው መልእክት፣ በእርሱ የተደበቁትን ነገሮች ዕውቀት በያዘው የተሰጣችሁ መመሪያ እንዲህ ያለ ነው። በክፉ ፍላጐቶቻቸው ስካር በጣም ከመደናገራቸው የተነሣ፣ ድምጹ ከፍ ብሎ ከሁሉም አቅጣጫ "ከእኔ ከኃያሉ፣ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም" በማለት የሚጣራውን የሁሉን ፍጥረት ጌታ ለማወቅ ኃይል አጥተዋል።

በል፦ የእናንተ በሆኑት ነገሮች አትደሰቱ፣ ዛሬ ማታ የእናንተ ናቸው፣ ነገ ሌሎች ይወስዷቸዋል። እርሱ ሁሉን ዐዋቂው ሁሉን የተገነዘበው እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃችኋል። በል፦ ያላችሁ ነገር ዘላቂ ወይም ቋሚ ነው ብላችሁ ለመናገር ትችላላችሁን? በራሴ በፍጹም ምሕረተኛው! ዓይደሉም! የሕይወታችሁ ቀናት እንደ ነፋስ ሽውታ ያልፋሉ፤ ኩራታችሁና ክብራችሁም ሁሉ እንደ እነዚያ ከእናንተ በፊት እንዳለፉት ሰዎች ኩራትና ክብር ያልፋሉ። ሕዝቦች ሆይ፣ አሰላስሉ! ያለፉት ቀኖቻችሁ፣ የጠፉት ምዕተ-ዓመቶቻችሁ እምን ደረሱ? አምላክን ለማስታወሻ የተሰጡ ቀናት የደስታ፣ ለእርሱም ለጠቢቡ ምሥጋና የዋሉ ሰዓታት የተባረኩ ናቸው። በሕይወቴ! የኃያሉም ኩራት፣ የባለጸጐችም ሃብት፣ ከእግዚአብሔር

ያልሆኑት ሰዎች የበላይነትም እንኳ ከቶ አይቀይም። ከእርሱ በሚሰጥ አንድ ቃል ሁሉም ይጠፋሉ። እርሱ፣ በእርግጥ፣ ፍጹም ኃይል የተመላው፣ ሁሉን አስገዳጅና ፍጹም ኃያሉ ነው። ሰዎች ያሏቸው ምድራዊ ነገሮች ጥቅማቸው ምንድን ነው? ያንን የሚጠቅማቸውን ፍጹም ችል ብለውታል። ሳይቀይ ከእንቅልፋቸው ይነቃሉ፣ በፍጹም ኃያሉ፣ በፍጹም ተመሥጋኙ ጌታቸው ቀን ያመለጣቸውን ለማግኘት በማይችሉበት ሁኔታ ራሳቸውን ያገኛሉ። ቢያውቁት ኖሮ ስሞቻቸው በእርሱ ዙፋን ፊት ይጠቀሱ ዘንድ ያላቸውን ሁሉ በተው ነበር። እነርሱ፣ በእውነቱ፣ በሙታን መካከል እንደሆኑ ይቆጠራሉ።

## (100)

ሕዝብ ሆይ፣ በመካከላችሁ የመገኘቴ ክብር በተገለለና የንግግሬም ውቅያኖስ ጸጥ ባለ ጊዜ ልቦቻችሁ አይሸበሩ። የእኔ በመካከላችሁ መገኘት ጥበብ አለው፣ በመካከላችሁ አለመገኘቴም ተመዛዥ ለሌለው፣ ለፍጹም አዋቂው አምላክ በስተቀር ለሌላ ለማንም የማይታወቅ ሌላ ጥበብ አለው። በእውነቱ ከክብር ግዛታችን እንመለከታችኋለን፤ ለመልዕክታችን ድል መንሣት የሚነሣውን ማንኛውንም ሰው በሰማይ ሠራዊትና በተወደዱ የእኛ መላዕክት አማካይነት እንረዳዋለን።

የምድር ሕዝቦች ሆይ! ጨቋኝ የሌለበት ጌታችሁ በተናገራቸው ቃላት ጣፋጭነት አማካይነት፣ በለዘብታ የሚፈሱ ንጹሕ ወራጅ የምንጭ ውሀዎች ከቋጥኞች የፈለቁ ለመሆናቸው ዘለዓለማዊ እውነት የሆነው አምላክ መሥክሬ ነው፤ ሆኖም እናንተ ገና በማንቀላፋት ላይ ናችሁ። ያላችሁን በመተው፣ በመላቀቅ ክንፎች ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ባሻገር ብረሩ። የብዕሩ እንቅስቃሴ የሰውን ዘር ነፍስ የለወጠው የፍጥረታት ጌታ እንዲህ ያዛችኋል።

ፍጹም ክብር የተመላው ጌታችሁ ከምን ከፍታዎች እንደሚጠራችሁ ታውቀላችሁን? የስሞች ሁሉ ጌታ የሆነው ጌታችሁ

በምን ብዕር እንደሚያዛችሁ ያወቃችሁ ይመስላችኋልን? በሕይወቴ! አላወቃችሁም። ብታውቁት ኖሮ ዓለምን በተዋችሁና በሙሉ ልባችሁ ወደ ፍጹም ተወዳጁ ቅርበት በገሠገሣችሁ ነበር። መንፈሶቻችሁ በቃሉ አማካይነት ከመመሰጣቸው የተነሣ ይበልጥ ታላቁን ዓለም በብጥብጥ ውስጥ በጣሉ ነበር፤ ይህን ትንሹን ዝቅተኛውንማ ምን ያህል የበለጠ! ከአመሥጋኞች ትሆኑ ዘንድ፣ ከጸጋዬ ምልክት፣ የቸርነቴ ዝናቦች ከፍቅራዊ ደግነቴ ሰማይ የወረዱት በዚህ ሁኔታ ነው...።

የሥጋዊና የእርኩስ ዝንባሌ ፍላጐቶች በመካከላችሁ መከፋፈልን እንዳይቀሰቅሱ ተጠንቀቁ። እንደ አንድ እጅ ጣቶች፣ እንደ አንድ አካልም ብልቶች ሁኑ። ከሚያምኑት ከሆናችሁ የግልጸቱ ብዕር እንዲህ ይመክራችኋል።

የእግዚአብሔርን ምሕረትና ስጦታዎችን አስተውሉ፤ ምንም እንኳ እርሱ ራሱ ያለፍጡራን ለመኖር የሚችል ቢሆንም፣ የሚጠቅማችሁን ያዛችኋል። ክፉ ሥራዎቻችሁ ሊጎዱን ከቶ አይችሉም፤ መልካም ሥራዎቻችሁም አይጠቅሙንም። የምንጠራችሁ ሙሉ በሙሉ ለአምላክ ብለን ነው። ለዚህም የመረዳት ችሎታና ጥልቅ ግንዛቤ ያለው እያንዳንዱ ሰው ይመሠክራል።

## (101)

የማየት ኃይላችሁን በአሳዛኝ ሁኔታ የጋረደውን ግርዶሽ በስሜ ቅደዱ፤ እንዲሁም፣ ከእግዚአብሔር አንድነት እምነታችሁ በተገኘ ኃይል አማካይነት፣ የከንቱ ማስመሰል ጣዖቶችን በታትኑ። ከዚያም ወደ ፍጹም ምሕረተኛው መልካም ደስታ ቅዱስ ገነት ግቡ። ነፍሶቻችሁን የእግዚአብሔር ካልሆኑ ከማናቸውም ነገሮች አንጹ፤ በእርሱ ሰፊና ታላቅ ግልጸት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሁሉ በላይ በሆነውና ሥሕተት በሌለበት ሥልጣኑ ጥላ ሥር የእረፍትን ጣፋጭነት ቅመሱ። የእጄ ሥራ ፍጹምነት ለሰው ሙሉ በሙሉ ይገለጽ ዘንድ፣

በእያንዳንዳችሁ ውስጥ ፍጥረቴን ፍጹም ስለአደረግሁ፣ ራሳችሁን በራስ ወዳድነት ፍላጐት ጥቅጥቅ ያሉ ግርዶሾች ጠቅልላችሁ አታሠቃዩት። ስለዚህ፣ የተከበረውን፣ የእግዚአብሔርን ውበት እያንዳንዱ ሰው በራሱ ለማወቅ ይችል እንደነበረ፣ ለወደፊቱም መቻሉን እንደሚቀጥል ከዚህ ለመረዳት ይቻላል። እንዲህ ያለ ችሮታ ባይሠጠው ኖሮ፣ ለጥፋቱ እንዴት ሊጠየቅበት ይችል ነበር። የምድር ሕዝቦች ሁሉ በአንድ ላይ በሚሰበሰቡበት ቀን፣ ማንም ሰውበእግዚአብሔር ዘንድ እንደቆመ፣ "ስለምን በውበቴ ባለማመን ከእኔ ራቅህ?" ተብሎ ቢጠየቅና ይህም ሰው መልሶ፣ "ሰዎች ሁሉ ስለሳሳቱና፣ ፊቱን ወደ እውነት ለመመለስ የፈለገ አንድም ሰው ባለመገኘቱ፣ እኔም እንዱሁ፣ የእነርሱን ምሳሌ በመከተል ዘለዓለማዊውን ውበት ለማወቅ ተሳነኝ" ቢል፣ እንዲህ ያለው ምክንያት፣ በእውነቱ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም የማንም ሰው እምነት፣ በራሱ በስተቀር በማንም ሰው እምነት ሊወሰን አይችልምና።

## (102)

የፍጥረትን አመጣጥ ስለሚመለከተው ጥያቄህ ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ፍጥረት ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ እንደበረ፣ ለዘለዓለምም መኖሩን እንደሚቀጥል በእርግጥ ዕወቅ። መጀመሪያው መጀመሪያ አልነበረውም፤ መጨረሻውም መጨረሻ አያውቅም። ፈጣሪ የሚለው ስሙ አስቀድሞ ፍጥረት እንደበረ እንደሚያስረዳ ሁሉ፣ የሰዎች ጌታ የሚለው ስያሜውም አገልጋይ እንደነበረ ያመለክታል።

እንደ እነዚያ በቀድሞ ነቢያት የተነገሩ ናቸው እንደሚባሉት፣ "መጀመሪያ እግዚአብሔር ነበረ፣ የሚያውቀው ፍጡር አልነበረም፣" እና "ጌታ ብቻውን ነበረ፣ የሚያወድሠው ማንም አልነበረም፣" እንደሚሉት ያሉትና እነዚህን የመሳሰሉት አባባሎች ትርጉም ግልጽና

የተረጋገጠ ነው፤ በምንም ጊዜም መዛባት የለበትም። እነዚህ (የሚከተሉት) እርሱ የገለፃቸው ቃላት ለዚሁ እውነትነት ይመሠክራሉ፦ “እግዚአብሔር ብቻውን ነበረ፤ ከእርሱም በቀር ማንም አልነበረም። እርሱ ከእምቅድመ ዓለም እንደነበረ ሆኖ ለሁልጊዜም ይኖራል። ”እያንዳንዱ ለማየት የሚችል ዓይን፣ ጌታ አሁን መከሰቱን ያስተውላል፤ ሆኖም የእርሱን ክብር የተገነዘበ የለም። ይህም ማለት መለኮታዊው ሕያው የሚኖርበት መኖሪያ ከእርሱ ከእራሱ በስተቀር ማንም ሊደርስበት ከሚችለው በላይ ከፍ ያለ ነው ማለት ነው። በዚህ በምድራዊ ዓለም ልንገልፀው ወይንም ልንገነዘበው የምንችለው ማንኛውም ነገር በተፈጥሮው ከተወሰኑበት ገደቦች ሊያልፍ ከቶ አይችልም። እግዚአብሔር ብቻ እንደዚህ ያሉትን ገደቦች ያልፋል። እርሱ፣ በእውነቱ፣ ከእምቅድመ ዓለም የነበረ ነው። ተወዳዳሪ ወይም የሚጋራው ተደርጐለት አያውቅም፤ ለወደፊቱም ለማጐዳኘት ከቶ አይቻልም። ማንም ሰው ከእርሱ ስም ጋር ሊጻጸር አይችልም፤ ተፈጥሮውን ምንም ብዕር ሊገልጽ አይችልም፤ ክብሩንም ምንም አንደበት ሊያብራራ አይችልም። እርሱ፣ ከራሱ በስተቀር ከሌላ ከማንም፣ ሊለካ ከሚቻል በላይ የላቀ ሆኖ ይኖራል።

ከሁሉም በላይ ከፍተኛው የእግዚአብሔር ክስተት እራሱን ለሰዎች የሚገልጽበትን ሰዓት አስቡ። ያ ሰዓት ከመምጣቱ በፊት፣ በሰዎች ያልታወቀውንና ገና የእግዚአብሔር ቃል ያልተናገረው ጥንታዊው ሕላዌ፣ እርሱን ያወቀው ማንም ሰው በሌለበት ዓለም እርሱ ራሱ ግን ሁሉን አዋቂው ነው። እርሱ በእርግጥ ያለፍጥረት ፈጣሪ ነው። ምክንያቱም ከእርሱ ግልጸት በፊት በነበረችው የመጨረሻዋ ቅጽበት፣ ሁሉና እያንዳንዱ የተፈጠረ ነገር ነፍሱን ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ ይዳርጋልና። ይህ በእውነቱ “በዚህ ቀን መንግሥት የማን ይሆናል?” ተብሎ የተፃፈለት ቀን ነው። መልስ ለመስጠት የተዘጋጀም ማንም አይገኝም!

(103)

የእግዚአብሔርን ዓለማት ስለሚመለከተው ጥያቄህ ደግሞ። የእግዚአብሔር ዓለማት በቁጥራቸው ስፍር ቁጥር እንደሌላቸውና ለስፋታቸውም ወሰን እንደሌለው በእርግጥ ዕወቅ። ከሁሉን ዐዋቂው፣ ከፍጹም ጠቢቡ አምላክ በስተቀር ሊቆጥራቸው ወይንም ሊገነዘባቸው የሚችል ማንም የለም። በአንቀላፋህበት ጊዜ የምትገኝበትን ሁኔታ አስብ። በእውነት እልሃለሁ፣ በልቦቻቸው ቢያሰላስሉት፣ ይህ ሁኔታ በሰዎች መካከል ከእግዚአብሔር መልክቶች እጅግ በጣም ምሥጢራዊው ነው። በሕልምህ ያየኸው ነገር፣ ከብዙ ጊዜ በኋላ እንዴት ሙሉ በሙሉ እውን እንደሚሆን ተመልከት። በሕልምህ የነበርክበት ዓለም፣ ከዚህ ከምትኖርበት ዓለም ጋር ልክ አንድ ዓይነት ቢሆን ኖሮ፣ በዚያ ሕልም የተፈጸመው ድርጊት፣ በዚህ ዓለምም የግድ በዚያው ሕልም በታየበት ጊዜ በተፈጸመ ነበር። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ አንተ ራስህ ባየኸው ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን ይህ የምትኖርበት ዓለም በሕልም ካወቅኸው ዓለም የግድ የተለየና ለብቻው መሆን እንዳለበት የተረጋገጠ ነው። ይህ ሕልም ያየህበት ዓለም መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የለውም። ይህ ዓለም ፍጹም ክብር በተመላው፣ በፍጹም ኃያሉ አምላክ እንደታዘዘው ከአንተው ውስጥ ያለ፣ በውስጥህም የተጠቀለለ ነው በማለት ብትከራከር እውነት ነው። መንፈስህ የእንቅልፍን ወሰን በማለፍና ከዓለማዊ ቁራኛነት ሁሉ ራሷን አላቅቃ፣ በእግዚአብሔር ክንውን፣ በዚህ ዓለም ውስጣዊ መንግሥት ተደብቆ ያለውን እውነታ እንድታቋርጥ ተደርጋ ነው ቢባልም፣ እንዲሁ ልክ ነው። በእውነት እላለሁ፣ የእግዚብሔር ፍጥረት ከዚህ ዓለም ሌሎች ዓለማትን፣ ከእነዚህ ፍጠራን በተጨማሪ ሌሎች ፍጡራንን ያቅፋል። በእነዚህ ዓለማት በእያንዳንዳቸው ከራሱ፣ ከፍጹም መርማሪው፣ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ማንም ሊመረመራቸው የማይችላቸውን ነገሮች ደንግጓል። የጌታህን፣ የዓለማት ሁሉ ጌታ የሆነውን፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማወቅ ትችል

ዘንድ በገለጽንልህ ላይ አጥብቀህ አሰላስል። በእነዚህ ድምፃችንን ከሚሰሙት ብትሆኑ፣ በእነዚያ በቃላችን አማካይነት በተፈጠሩት ሰዎች አድራጐት ሳቢያ በከበበን ኃዘን ምክንያት በዚህ ዋና ቁም ነገር ላይ ይበልጥ ከማተኮር ተቆጥበናል።

(104)

ከእግዚአብሔር ነቢያትና ከምርጦቹ በስተቀር ሌላው ሰው ከሥጋዊ ሞት በኋላ ያው የራሱ ግላዊነት፣ ስብዕና፣ ንቃተ-ሕሊናና በዚህ ዓለም ሕይወቱ የነበረውን ግንዛቤ ይዞ ይኖር እንደሆነ በማለት ጠይቀኸኛል። እንዲህ ከሆነ የምናየው እንደራስን መርሳትና እንደ ከባድ ሕመም ያለ ቀላል የአዕምሮ ጉዳት ግንዛቤውንና ንቃተ-ሕሊናውን ሲነፍጉት፣ የአካሉን መፈራረስና የንጥረ ነገሮችንመበታተን የሚያስከትለውን ሞት፣ ያንን የመረዳት ኃይል ለማጥፋትና ንቃተ-ሕሊናውን ለማጨለምእንዴት ኃይል አይኖረውም? ለኅሊናቸውና ለጠቅላላ እንቅስቃሴያቸው አስፈላጊ የሆኑት መሣሪያች ራሳቸው ፍጹም ከተበታተኑ በኋላ፣ የሰው ንቃተ-ሕሊናና ስብዕና ይኖራሉ ብሎ ማንኛውም ሰው እንዴት ሊያስብ ይችላል? በማለት ጠይቀኸኛል።

የሰው ነፍስ ከአካል ወይም ከአዕመሮ ድክመት የላቀች፣ ነፃም የሆነች መሆንዋን ዕወቅ። የታመመ ሰው የድክመት ምልክቶች የሚያሳየው በነፍሱና በአካሉ መካከል ጣልቃ በሚገቡ መሰናክሎች ምክንያት ነው፤ የነፍስ የራሷ ሁኔታ ግን በማንኛውም የአካል ሕመም ወይም በሽታ ሳይለወጥ ይኖራል። የፋኖሱን ብርሃን አስብ። ምንም እንኳ ባዕድ አካል ብርሃኑን ቢጋርድ፣ ብርሃኑ ራሱ ግን ባልተቀነሰ ኃይል ብርሃን መስጠቱን ይቀጥላል። በተመሳሳይ ሁኔታ እያንዳንዱ የሰውን አካል የሚያሠቃየው ሕመም ነፍስን የውስጥ ተፈጥሮአዊ ኃያልነቷንና ኃይሏን እንዳትገልጽ የሚከለክል መሰናክል ነው። ከአካል በምትለይበት ጊዜ ግን ምንም በምድር የሚገኝ ኃይል

በማይስተካከለው ዓይነት ከፍተኛ የበላይነት ታሳያለች፤ ታላቅ የመለወጥ ኃይልም ትገልጻለች። እያንዳንዷ የጠራችና የተቀደሰች ነፍስ ታላቅ ኃይልን ትታደላለች፤ ከመጠን በላይ በሆነ ደስታም ትፈነድቃለች።

በጋን ውስጥ የተደበቀ ፋኖስን አስብ። ምንም እንኳ ፋኖሱ እያበራ ቢሆንም፣ በርሃኑ ግን ከሰዎች ተሠውሯል። እንዲሁም፣ ብርሃኗ በደመና የደበዘዘውን ፀሐይ አጢን፣ በእውነቱ የዚያ ብርሃን ምንጭ ያልተለወጠ ሆኖ ሳለ የብርሃኗ ድምቀት የተቀነሰ እንደሚመስል አስተውል። የሰው ነፍስ በዚህ ፀሐይ፣ አካሉም በምድር ላይ በሚገኙ ነገሮች ሁሉ መመሰል አለባቸው። ምንም የውጭ ግርዶሽ በመካከላቸው ጣልቃ እስካልገባ ድረስ፣ አካል፣ በመላው፣ የነፍስን ብርሃን ማንጸባረቁን ይቀጥላል፤ በኃይሏ አማካይነትም ሕይወት ያገኛል። ወዲያው ግርዶሽ በመካከላቸው እንደገባ ግን፣ የዚያ ብርሃን ድምቀት የተቀነሰ ይመስላል።

እንደገና ፀሐይዋ ሙሉ በሙሉ ከደመናዎች በስተኋላ የተደበቀችበትን ጊዜ አጢን። ምንም እንኳ ምድር አሁንም በፀሐይዋ ብርሃን የበራች ብትሆንም፣ የምትቀበለው ብርሃን መጠን እጅግ ተቀንሷል። ደመናዎች እስካልተበታተኑ ድረስ ፀሐይዋ እንደገና በድምቀቷ ሙሉ ኃይል ልታበራ አትችልም። ነገር ግን የደመናው መኖርም ሆነ አለመኖር የፀሐይዋን ተፈጥሮአዊ ድምቀት በምንም መንገድ ሊቀይር አይችልም። የሰው ነፍስ አካሉ እንዲበራ የሚደረግበት፣ እንዲሁም በሕይወቱ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች የሚያገኝበት ፀሐይ ነው፤ በዚህም መልክ መወሰድ አለበት።

ከዚህም በላይ፣ ፍሬ ከመገኘቱ በፊት በሥውር በዛፍ ውስጥ መኖሩን አስብ። ዛፉ ቢቆራረጥም እንኳ ምንም ያህል አነስተኛ የሆነ የፍሬው ቁራጭ ወይም ምልክቱ ሊገኝ አይችልም። በሚያፈራበት ጊዜ ግን፣ ፍሬው እንዳየኸው በአስደናቂ ውበትና በተከበረ ፍጹምነቱ ራሱን ይገልፃል። በእውነቱ፣ አንዳንድ ፍሬዎች የተሟላ ዕድገታቸውን

የሚቀዳጁት ከዛፎቹ ከተቆረጡ በኋላ ብቻ ነው።

(105)

አሁን ደግሞ ስለሰው ነፍስና ከሞት በኋላ መኖር መቀጠሏን ስለሚመለከተው ጥያቄህ፣ ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ፣ ፈጣሪዋ ዘንድ እስክትደርስ ድረስ፣ የዘመናትና የመዕተ ዓመታት መለዋወጥ፣ እንዲሁም የዚህ ዓለም ለውጥና አጋጣሚ ሁሉ በማይለውጠው አኳኋን ዕድገቷን የምትቀጥል መሆኗን በእውነቱ ዕወቅ። የእግዚአበሔር መንግሥት፣ ሉዓላዊነቱ፣ ገዢነቱና ሥልጣኑ እስካለ ድረስ ትኖራለች። የአምላክን ምልክቶችና ባሕርያቱን ትገልፃለች። ፍቅር የተመላበት ደግነቱንና ቸርነቱንም ታሳያለች፤ የዚህን የተከበረ ደረጃ ከፍተኛነትና ጸጋውን በሚገባ ለመግለጽ በሚሞክርበት ጊዜ የብዕሬ እንቅስቃሴ ይቆማል። የምሕረተኛው እጅ ለነፍስ የሚያጎናጽፋትን ክብር ምንም አንደበት በሚገባ ለመግለጽ እንዲሁም ምንም ምድራዊ ወኪል ሊተነትነው አይችልም። ከሥጋ በምትለይበት ሰዓት ከዓለም ሕዝቦች ከንቱ አስተሳሰብ ነፃ የሆነች ነፍስ የተባረከች ናት። እንዲህ ያለች ነፍስ የምትኖረውና የምትንቀሳቀሰው በፈጣሪዋ ፈቃድ ስለሆነ፣ ወደ ፍጹም ከፍተኛ ገነት ትገባለች። የእጅግ በጣም ታላቁ ቤት ነዋሪዎች የሆኑት የመንግሥተ-ሰማይድንግሎች ያጅቧታል፤ የእግዚአብሔር ነቢያትና የእርሱ ምርጦች ጓደኝነቷን ይሻሉ። ያች ነፍስ ከእነርሱ ጋር በሙሉ ነጻነት ታወጋለች፤ የዓለማት ሁሉ ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር መንገድ እንድትችለው የተደረገችውን ሁሉ ታጫውታቸዋለች። በምድርና በሰማይ ዙፋን ንጉሥ በአምላክ ዓለማት፣ ይህችን ለመሰለች ነፍስ የተዘጋጀላት ነገር ለማንም ሰው ቢነገረው፣ ይህን እጅግ የተከበረ፣ ይህን የተቀደሰና የተዋበ ደረጃ ለማግኘት በጣም ከመመኘቱ የተነሣ መላ ሰውነቱ ከመቅጽበት በተቀጣጠለ ነበር. . . ከሞት በኋላ የነፍስ ሁኔታ ምን እንደሆነ ሊገለጽ ፍጹም አይቻልም፣ ሁኔታዋን በሙሉ ለሰዎች ዓይኖች መግለጹ

ተገቢም የሚፈቀድም አይደለም። ነቢያትና የእግዚአብሔር መልእክተኞች ወደዚህ ዓለም የተላኩት፣ የሰውን ዘር ወደ ቀጥተኛው የእውነት ጐዳና ለመምራት ዓላማ ብቻ ነው። የግልጸቶቻቸውም ዋና ዓላማ የሰው ልጆች በንጽሕናና በቅድስና፣ ከከንቱ ፍላጐትም በመገለል ኖረው፣ በሞት በሚለዩበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ከፍተኛ ዙፋን ለመቅረብ እንዲችሉ ለማስተማር ነው። ዓለም እንድታድግናሕዝቦችዋም እንዲበለጽጉ የሚያደርገው፣ እነዚህ ነፍሶች የሚያፈልቁት ብርሃን ነው። እነርሱ ለፍጥረተ-ዓለም ሕይወትን እንደሚሰጡ እርሾዎች፣ እንዲሁም የዓለም ኪነ ጥበብና ድንቅ ነገሮች የሚገለጹባቸው ሕይወት ሰጪ ኃይሎች ናቸው። በእነርሱ አማካይነት ደመናዎች በረከታቸውን ያዘንባሉ፤ ምድርም ፍሬዋን ትሰጣለች። ሁሉም ነገር ምክንያት፣ አንቀሳቃሽ ኃይልና ሕይወት የሚሰጥ መሠረታዊ ሕግ እንዲኖረው ያስፈልጋል። እነዚህ የመላቀቅ ምልክቶች የሆኑት ነፍሶች በፍጥረት ዓለም ውስጥ የመጨረሻ ከፍተኛ አንቀሳቃሽ ኃይል የሰጡና መስጠታቸውንም የሚቀጥሉ ናቸው። ይህ ዓለም ገና በእናቱ ማሕፀን ካለው የሕፃን ዓለም እንደሚለየው ሁሉ፣ የወዲያኛው ዓለም ከዚህኛው ዓለም የተለየ ነው። ነፍስ እግዚአበሔር ዘንድ ስትቀርብ ለዘለዓለም ሕይወቷ ይበልጥ የሚስማማና የመንግሥተ ሰማያዊው ዓለም ነዋሪነቷ ተገቢ የሆነ ሁኔታ ትይዛለች። እንዲህ ያለው አኗኗር ተለዋዋጭ እንጂ ቋሚ አይደለም፤ ምክንያቱም የመጀመሪያው መነሻ ያለው ሲሆን፣ የኋለኛው ግን ከዚህ የነፃ ነውና። ፍጹም ቋሚ ሕልውና፣ ክብሩ ይስፋና፣ ለእግዚአብሔር ብቻ የተወሰነ ነው። ይህን እውነት የተረዱ የታደሉ ናቸው። የእግዚአብሔር መልዕክተኞችን ተግባር በልብህ ብታሰላስል፣ ከዚህ ዓለም ሌላ ሌሎች ዓለማት መኖር እንዳለባቸው በእርግጥና ወዲያው ታያለህ። የክብር ብዕር በጥበብ መልእክት እንደመዘገበው፣ በሁሉም ዘመናት በእውነት ጠቢባንና ምሑራን ከሆኑት መካከል አብዛኞቹ ለዚያ የአምላክ ቅዱስ ጽሑፍ ለገለጸው

እውነተኛነት መሥከረዋል፤ ቁስ አካላውያን እንኳ ሳይቀሩ ስለ እነዚህ በመለኮት ስለተሰየሙት መልዕክተኞች ጥበብ በየጽሑፎቻቸው መሥከረዋል፤ መልዕክተኞቹ የጠቀሷቸውንም እንደ ገነት፣ የገሃነም እሳት፣ የወደፊት ዋጋና (ሽልማትና) ቅጣት የመሳሰሉት፣ የሰውን ነፍሶች ለማሠልጠንና ለማሳደግ ከነበራቸው ፍላጎት የተነሣ የሰጡት ትምህርት እንደሆነ ቆጥረዋቸዋል። ስለዚህ በጠቅላላው የሰው ዘር፣ ንድፈ ሃሣባቸውና እምነታቸው ምንም ይሁን፣ የእነዚህን የእግዚአብሔር ነቢያት ልቀት እንዴት እንዳወቁ፣ የበላይነታቸውንም እንዴት እንደተቀበሉ አስተውል። እነዚህን ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ የመወሰን ዕንቁዎች አንዳንዶቹ እንደ ጥበብ ማኅደሮች ሲገልጿቸው፣ ሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔር የራሱ እንደራሴዎች ናቸው በማለት ያምኑባቸዋል። እንዲህ ያሉት ነፍሶች፣ የእግዚአብሐር ዓለማት ሁሉ በዚህ በምድራዊ ሕይወት ብቻ የተወሰኑ መሆናቸውን ቢያምኑ ኖሮ፣ ራሳቸውን አሳልፈው ለጠላቶቻቸው ለመስጠት እንዴት ይችሉ ነበር? እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ማንም ሰው ደርሶበት ወይንም ዓይቶት የማያውቃቸውን፣ እንዲህ ያሉትን መከራዎችና ሥቃዮች በፈቃደኝነት ይቀበሏቸው ነበርን?

## (106)

የነፍስን ተፈጥሮ በሚመለከት ጠይቀኸኛል፤ በእውነቱ ነፍስ እውነታዋን በትምህርት እጅግ በጣም የላቁ ሰዎች ለመገንዘብ የተሳናቸው፣ ምሥጢሯንም፣ ምንም ያህል አስተዋይ የሆነ፣ ምንም አዕምሮ ሊፈታው ተስፋ ለማድረግ ከቶ የማይችል፣ የመንግሥተ-ሰማያዊው ዓለም ዕንቁና የአምላክ ምልክት መሆኗን ዕወቁ። ከተፈጠሩትም ነገሮች መካከል የፈጣሪዋን ፍጹምነት ለማወጅ፣ ክብሩን አውቃ ለመቀበል፣ በእውነቱም ላይ ለመጣበቅ፣ በማምለክም በፊቱ ለማጐንበስ የመጀመሪያ ናት። ለአምላክ ታማኝ ከሆነች የእርሱን ብርሃን ታንጸባርቃለች፤ በመጨረሻም ወደ እርሱ

ትመለሳለች። ለፈጣሪዋ ማደር ከተሳናት ግን ለራስ ወዳድነትና ለስሜት ተገዢ በመሆን በመጨረሻም በጥልቀታቸው ትሰጥማለች።

በዚህ ቀን፣ የሰዎች ጥርጣሬዎችና ከንቱ አስተሳሰቦች ከእርሱ ዘለዓለማዊው እውነት ፊቱን እንዲያዞሩት ያልፈቀደ፣ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ባለሥልጣኖች የቀሰቀሱት ዋካታ የእርሱን መልዕክት ከማወቅ እንዲገታው ያላደረገ፣ እንዲህ ያለው ሰው፣ በሰዎች ሁሉ ጌታ፣ በእግዚብሔር ዘንድ ከታላቅ ምልክቶቹ እንደ አንዱ፣ ከእነዚያም ስሞቻቸው ከሁሉ በላይ ከፍተኛ በሆነው ብዕር፣ በእርሱ መዝገብ ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ይቆጠራል። እንዲህ ስለአለው ነፍስ እውነተኛ ሁኔታ ያወቀ፣ ደረጃውንም አምኖ የመሠከረ፣ የእርሱን መልካምምግባራት የተገነዘበ የተባረከ ነው።

የነፍስን ዕድገት ልዩልዩደረጃዎች በተመለከተ፣ በቀድሞ መጻሕፍት ውስጥ እንደ ፍትወተ-ሥጋ፣ ቁጡነት፣ የዕውቀት ስለመሳሰሉት ብዙ ተጽፏል፤ የሆነ ሆኖ፣ ከሁሉም ይበልጥ ግልጸት፣ በጎ አድራጎት፣ እርካታ፣ መለኮታዊ መልካም ደስታና ስለመሳሰሉት ብዙ ተጽፏል፤ የሆነ ሆኖ፣ ከሁሉም ይበልጥ ከፍተኛው ብዕር፣ ስለዚህ ከመተንተን ተቆጥቧል። በዚህ ቀን በአምላክ መንገድ በትሕትና የምትጓዝና እርሱን የሙጥኝ ያለች እያንዳንዷ ነፍስ፣ በሁሉም መልካም ስሞች፣ ክብርና ማዕረግ እንዲሁም ደረጃዎች ተሸልማ ራሷን ታገኛለች።

ሰው በሚያንቀላፋበት ወቅት በነፍሱ ተፈጥሮ ላይ ምንም ውጫዊ ነገር፣ በምንም መንገድ ተጽዕኖ ያደርስበታል ለማለት አይቻልም። ከመጀመሪያ ሁኔታዋና ጠባይዋ ምንም ለውጥ ሊደርስባት የሚችል አይደለችም። ማናቸውም የአድራጎቶቿ መለዋወጥ ከውጫዊ ምክንያቶች የተነሣ እንደሆነ ተደርጎ መቆጠር አለበት። ማንኛውም አካባቢዋን የመረዳትና የግንዛቤዋ መቀያየር፣ በእነዚህ ውጫዊ ተጽዕኖዎች ምክንያት እንደሆነ ተደርጎ መወሰድ ይገባዋል።

የሰውን ዓይን አስብ። ምንም እንኳ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ለማየት ኃይል ቢኖራትም፣ ትንሽ ግርዶሽ ማንኛውንም ነገር ለማየት እስኪሳናት ድረስ የማየት ኃይሏን ሊነፍጋት ይችላል። እርሱ እነርሱን የፈጠራቸውና፣ የእነዚህ ምክንያቶች መንሥኤ የሆነው፣ በፍጥረት ዓለምም የእያንዳንዱ ለውጥና መለያየት በእነርሱ አማካይነት እንዲሆን የወሰነው (አምላክ) የተወደሰ ይሁን። በመላው ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ የተፈጠረ ነገር፣ ወደ ዕወቀቱ የሚመራ በር፣ የሉዓላዊነቱ ምልክት፣ የስሞቹ ግልጸት፣ የግርማው መለያ፣ የሥልጣኑ ምልክትና ወደ ቀጥተኛ መንገዱ ለመግባት የሚያገለግል መሣሪያ ነው …።

በእውነት እላለሁ፤ የሰው ነፍስ፣ በተፈጥሮዋ ከእግዚአብሔር ምልክቶች አንዷ፣ ከምሥጢራቱም መካከል አንዷ ምሥጢር ናት። ከፍጹም ኃያሉ ታላላቅ ምልክቶች አንዷ፣ የአምላክን ዓለማት ሁሉ እውነታ የምታውጅ የምሥራች ነጋሪ ናት። በውስጧ ያ፣ ዓለም አሁን ሊገነዘበው ከቶ የማይችለው ሁሉ ተደብቆ ይገኛል። ሕግጋቱን ሁሉ የሚናኘውን የእግዚአብሔርን ነፍስ ግልጸት በልብህ አሰላስል፤ ከዚያ ከወራዳውና ካልጠግብ ባይ ተፈጥሮ፣ ከዚያ በእርሱ ላይ ካመጸው፣ ከዚያ ሰዎችን፣ ወደ ስሞች ጌታ እንዳይዞሩ ከሚከለክላቸው፣ በፍትወተ-ሥጋቸውና በክፋታቸው መንገድ እንዲራመዱ ከሚገፋፉቸው ተፈጥሮ ጋር አነፃጽር። እንዲህ ያለው ነፍስ በእውነቱ በሥሕተት መንገድ ርቆ ተንከራቷል …።

ከዚህም በላይ፣ ነፍስ ከአካል ከተለየች በኋላ ስለሚኖራት ሁኔታ ጠይቀኸኛል፤ የሰው ነፍስ በእግዚብሔር መንገዶች ከተጓዘች፣ እርሷ ወደ ተወዳጁ ክብር በእርግጥ የምትመለስና የምትሰበሰብ መሆኗን በእውነት እወቅ። በእግዚአብሔር ትክክለኝነት! ብዕር ሊጽፈው፣ እንዲሁም አንደበት ሊገልጸው የማይችለውን ደረጃ ትቀዳጃለች። ለእግዚበሔር እምነት ታማኝ ሆና የቆየች፣ በመንገዱም ሳታወላውልጸንታ የቆየች ነፍስ፣ ከእርገቷ በኋላ፣ የሚኖራት ኃይል

ከፍ ያለ በመሆኑ የተነሣ፣ ፍጹም ኃያሉ አምላክ የፈጠራቸው ዓለማት ሁሉ በእርሷ አማካይነት ይጠቀማሉ። እንዲህ ያለች ነፍስ በፍጹም ንጉሥና በመለኮታዊው መምህር ትእዛዝ፣ ፍጥረተ- ዓለምን የሚያዳብረውን ንጹህ ቅመም ትሰጣለች፤ የዓለም ጥበብና ድንቅ ነገሮች የሚገለጹበትን ኃይል ታስገኛለች። ምግብ ለመጣፈጥ ቅመም እንደሚያስፈልገው አስተውል። እነዚያ ከዓለማዊ ነገሮች የመላቀቅ ምልክቶች የሆኑት ነፍሶች የዓለም ቅመሞች ናቸው። በዚህ ላይ አሰላስል፤ ከሚያመሠግኑትም ሁን።

ይህን አርዕስተ-ነገር በአያሌ መልዕክቶቻችን ጠቅሰናል፤ ስለነፍስም ዕድገት የተለየዩ ደረጃዎች ገለጸናል። በእውነቱ እላለሁ፤ የሰው ነፍስ ከመውጣትና ከመግባት የመጠቀች ናት። የረጋች ነች፣ ቢሆንም ትንሳፈፋለች፤ ትንቀሳቀሳለች ሆኖም የረጋች ነች። እርሷ በራሷ ለዚህ ለተለዋዋጭ ዓለም መኖር፣ እንዲሁም መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ ለሌላው ዓለም እውነት የምትመሠክር ማስረጃ ናት። ያለምከው ሕልም ከብዙ ዓመታት በኋላ እንደገና በፊትህ እንደሚፈጸም፤ በህልምህ የሚታይህ ዓለም ምሥጢር እንዴት የሚያስገርም ነገር አንደሆነ አስተውል። የማይመረመረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በልብህ አትኩረህ አሰላስል፤ በእጅግ በጣም ሰፊ ግልፀቶቹም ላይ ተመራመር . . . ።

የእግዚብሔርን የእጅ ሥራ ድንቅ ማስረጃዎች ተመልከት፤ ስፋቱንና ጠባዩንም አሰላስል። እርሱ የነቢያት መደምደሚያ የሆነው እንዲህ አለ፦ "አምላክ ሆይ፣ በአንተ መደነቄንና መገረሜን አብዛ"

ይህ ግዙፍ ዓለም ውሱንነት እንዳለው ወይም እንደሌለው ስለአቀረብከው ጥያቄህ ደግሞ፣ ይህንን ነገር ለመገንዘብ የሚቻለው እንደየተመልካቹ እንደሆነ እወቅ። በአንድ በኩል፣ የተወሰነ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከምንም ውሱንነት የላቀ ነው። አንድ እውነተኛ አምላክ ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ ኖሯል፤ ለዘለዓለምም ይኖራል። ፍጥረቱም እንዲሁ፣ መጀመሪያ አልነበረውም፣ መጨረሻም

አይኖረውም። ሆኖም፣ የተፈጠረ ነገር ሁሉ፣ በመንሥኤ የተቀደመ ነው። ይህ ሐቅ፣ ራሱ፣ የፈጣሪን አንድነት ያለ ምንም ጥርጥር ያረጋግጣል።

ከዚህም በላይ፣ ስለጠፈር ክብ አካላት ተፈጥሮ ጠይቀኸኛል፤ ተፈጥሮአቸውን ለመረዳት፣ በቀደሞዎቹ መጻሕፍት ውስጥ ስለጠፈር ክብ አካላትና ስለጠፈር የተሰጡትን ገለጻዎች ትርጉም መመርመርና ከዚህ ምድራዊ ዓለም ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጠባይ፣ እንዲሁም የሚያደርጉባትን ተጽኖ ማወቅ ያስፈልጋል። በዚህ አስደናቂ አርዕስት እያንዳንዱ ልብ በአድናቆት፣ እያንዳንዱም አዕምሮ በምሥጢሩ ግራ ተጋብቷል። መሥጢሩን ለመረዳት የሚችለው አምላክ ብቻ ነው። የዚህችን ምድር ሕይወት በአያሌ ሺህ ዓመታት የወሰኑት ምሁራን፣ በረዥም የምርምር ጊዜያቸው፣ የሌሎችን የጠፈር አካላት (ፕላኔቶች) ብዛትም ሆነ ዕድሜ ለመገመት አልቻሉም። ከዚህም በላይ በእነዚህ ሰዎችከተገለጹት ጽንሰ-ሃሣቦች የተነሣ የተፈጠሩትን ብዙ የሃሣብ ልዩነቶች አስተውል። እያንዳንዱ ቋሚ ኮከብ የራሷ ፕላኔቶች፣ እያንዳንዷም ፕላኔት ቁጥራቸውን ማንም ሰው ሊያስብ የማይችላቸው የራሷ ፍጡራን እንዳሏት እወቅ።

አንተ ዓይኖችህን በገጽታዬ ላይ ያተኮርክ ሆይ! የክብር የቀን ምንጭ፣ በዚህ ቀን፣ ብርሃኑን ገልጿል፤ ከሁሉ ይበልጥ ከፍተኛውም ድምጽ እየተጣራ ነው። ቀድሞ እነዚህን ቃላት ተናግረን ነበር፡- “ይህ ቀን ማንም ሰው ጌታውን የሚጠራጠርበት ቀን አይደለም። በእርሱ፣ የክብር የቀን ምንጭ በሆነው እንደተነገረው፣ የእግዚአብሔርን ጥሪ ያዳመጠ ማንኛውም ሰው ተነሥቶ፣ *‘እዚህ ነኝ፣ የስሞች ሁሉ ጌታ ሆይ፣ እዚህ ነኝ፣ እዚህ ነኝ፣ የሰማያት ፈጣሪ ሆይ! በግልጸትህ አማካይነት በእግዚአብሔር መጻሕፍት ውስጥ የተደበቁት ነገሮች መገለጻቸውን፣ በመልዕክተኞችህ አማካይነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተመዘገቡትም ሁሉ መፈጸማቸውን እመሠክራለሁ፤’* በማለት መጮህ ይገባዋል።”

(107)

አሁን ደግሞ የሰዎችን ነፍሶች ከአካል ከተለዩ በኋላ እርስ በርሳቸው መተዋወቃቸውን መቀጠል አለመቀጠላቸውን ስለሚመለከተው ጥያቄህ፤ ወደ ቀይዋ መርከበ ውስጥ የገቡና በዚያ የሚኖሩ የባሃ ሕዝብ ነፍሶች እርስ በርሳቸው ይወዳጃሉ፣ የጠበቀ ግንኙነትም ያደርጋሉ፣ በአኗኗራቸው፣ በፍላጐቶቻቸው፣ በዓላማዎቻቸውና በፍጥረታቸው በጣም ተቀራርበው ከመኖራቸው የተነሣ ልክ እንደ አንድ ነፍስ ይሆናሉ። እነርሱ በእርግጥ እነዚያ ስለማናቸውም ነገር ያወቁ፣ አስተዋይ አመለካከት ያላቸው፣ መገንዘብንም የተለገሡ ናቸው። በእርሱ፣ በሁሉን አዋቂው፡ በፍጹም ጠቢቡ እንዲህ ተደንግጓል።

በእግዚአብሔር መርከብ ውስጥ የሚኖሩ የባሃ ሕዝቦች እያንዳንዳቸውና ሁላቸውም እርስ በርሳቸው ስላላቸው ደረጃና ሁኔታ ደህና አድርገው ይተዋወቃሉ፤ በመቀራረብና በወዳጅነት ሰንሰለትም ይተሣሠራሉ። ሆኖም፣ እንዲህ ያለው ደረጃ በእምነታቸውና በተግባራቸው ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚያ በአንድ ክፍልና ደረጃ የሚገኙት ስለእርስ በርሳቸው ችሎታ፣ ጠባይ፣ ስለአከናወኑት ሥራና ስለተቀዳጁት ክብር ሙሉ በሙሉ ይተዋወቃሉ። እነዚያ ከዝቅተኛ ክፍል የሆኑት ግን በደረጃ ከእነርሱ በላይ የሆኑትን ክብር ሙሉ በሙሉ ሊረዱ ወይንም ተግባራቸውን ሊመዝኑ አይችሉም። እያንዳንዱ ከጌታህ ድርሻውን ይቀበላል። ወደ ሰው ሁሉ ሉዓላዊ ጌታ፣ ከሁሉ ይበልጥ ኃይል ወደተመላው፣ ወደ ዘለዓለም የቅር ባዩ፣ ወደ ፍጹም ምሕረተኛው አምላክ እስኪበር ድረስ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር አቅጣጫ ያዞረ፣ በጽናትም በፍቅሩ መንገድ የተራመደ ሰው የተባረከ ነው።

ነገር ግን የእነዚያ ያላመኑት ሰዎች የመጨረሻ ትንፋሻቸው ስትወጣ ስለአመለጧቸው መልካም ነገሮች ያውቃሉ፤ ስለምግባራቸው ይጸጸታሉ፤ በአምላክም ፊት ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ፤ ለዚህም እኔ

እመሠክራለሁ። ነፍሶቻቸው ከአካሎቻቸው ከተለዩም በኋላ በዚሁ ሁኔታ ይቀጥላሉ።

ሰዎች ሁሉ ከሥጋዊ ሞታቸው በኋላ የሥራቸውን ዋጋ እንደሚመዝኑ፣ እጆቻቸውም የፈጸሟቸውን ሁሉ እንደሚገነዘቡ ግልጽና የተረጋገጠ ነው። ከመለኮታዊ ኃይል አድማስ በላይ በሚያበራው የቀን ኮከብ እምላለሁ! እነዚያ የአንዱ እውነተኛ አምላክ ተከታዮች፣ ከዚህ ሕይወት በሚለዩበት ጊዜ፣ ለመግለጽ የማይቻል ዓይነት በጣም ከፍ ያለ ሐሴትና ደስታ የሚሰማቸው ሲሆን፣ እነዚያ በሥሕተት ውስጥ የሚኖሩት ደግሞ በጣም ከፍ ባለ ፍርሐትና መንቀጥቀጥ ይዋጣሉ፤ ተወዳዳሪ በሌለው አስፈሪ ሽብርም ይሞላሉ። ያ በእርሱ፣ የእምነቶች ሁሉ ጌታ በሆነው ጸጋ የተመላው ደግነትና ቁጥራቸው የበዛ ልዩ ልዩ በረከቶች አማካይነት ምርጡንና የማይበላሸውን የእምነት ወይን የጠጣ የታደለ ነው።

ይህ ቀን የአምላክ ተወዳጆች ዓይኖቻቸውን ወደ እርሱ ከስተት አቅጣጫ መመለስናያ ክስተት ሊገልፃቸው በፈለጋቸውም በማናቸውም ነገሮች ላይ ማተኮር የሚገባቸው ቀን ነው። አንዳንድ ያለፉት ዘመናት ልማዶች ምንም መሠረት የሌላቸው ሲሆኑ፣ በአለፉት ትውልዶች የታመኑባቸውንና በመጽሐፎቻቸው ውስጥ የሠፈሩት ሃሣቦችም አብዛኞቹ፣ በረከሱ ዝንባሌዎችና ፍላጐቶች ተጽዕኖ የደረሰባቸው ናቸው። አሁን በሰዎች ዘንድ የሚገኙት አብዛኞቹ የእግዚአብሔር ቃላት ሐተታዎችና ፍችዎች እንዴት ምንም እውነት የሌለባቸው እንደሆኑ አንተው ራስህ ትመሠክራለህ። በመካከላቸው የተጋረደው መጋረጃ ሲገፈፍ በአንዳንድ ኢጋጣሚዎች ሐሰትነታቸው ተጋልጧል። እነርሱ ራሳቸው ከእግዚአብሔር ቃላት የአንዳቸውንም ትርጉም ለመገንዘብ እንደተሳናቸው ገልጸዋል።

ዓላማችን የእግዚአብሔር ተወዳጆች በቀድሞ ዘመን ከተነገሩት ከንቱ አባባሎች ጆሮዎቻቸውንና ዓይኖቻቸውን ቢያነጹ፣ በጥልቅ ነፍሶቻቸውም የእርሱ ግልጸት የቀን ምንጭ ወደሆነውና እርሱ

ወደገለፃቸው ነገሮች ሁሉ ቢመለሱ፣ እንዲህ ያለው አድራጎት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ በጣም እንደሚያስመሠግን ሥራ እንደሚቆጠር ለማሳየት ነው።

ስሙን አወድሡ፤ ከእነዚያ ከአመሥጋኞችም ሁኑ። አምላክ ለፍቅሩ ለመረጣቸው፣ ዓላማቸውንም ከግብ ለማድረስ ለአበቃቸው፣ ለተወዳጆቹ ሰላምታዬን አቅርብልኝ። ክብር ሁሉ፣ ለዓለማት ሁሉ ጌታ፣ ለአምላክ ይሁን።

## (108)

የእግዚአብሔር መጽሐፍ በሰፊው ተገልጧል፤ ቃሉም የሰውን ዘር ወደ እርሱ እየጠራ ነው። ሆኖም፣ እምነቱን አጥብቆ ለመያዝ፣ ወይም ለማስፋፋት መሣሪያዎች ለመሆን ፈቃደኞች የሆኑ እፍኝ አይሞሉም። እነዚህ ጥቂቶች የዓለምን ቆሻሻ ወደ ንጹሕ ወርቅ ለመለወጥ በሚችል፣ አማራጭ በማይገኝለት የመለካታዊ ኀይል ቅመም ተመልተዋል፤ የሰውን ልጆች ለሚያሠቃዩትም በሽታዎች ሁሉ የማይረክስ መድኃኒት ለመስጠት ኃይል ተሰጥቷቸዋል። ማንም ሰው ከግምት በላይ የሆነውን፤ የዚህን አስደናቂና የላቀ ግልጸት እውነተኛነት ካልተቀበለ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት አይችልም።

የእግዚአብሔር ወዳጆች ሆይ፣ ጆሮዎቻችሁን ለእርሱ፣ ዓለም በደል ላደረሰበት ጌታ ድምፅ አቅኑ፣ እምነቱንም የሚያስከብረውን ማንኛውንም ነገር አጥብቃችሁ ያዙ። እርሱ፣ በእውነቱ፣ የፈቀደውን ማንንም ሰው ወደ አርሱ ቀጥተኛ መንገድ ይመራል። ይህ ለደካማው ብርታትን የሚሰጥ፣ ለምስኪኑም የሃብት ዘውድ የሚጭን ግልጸት ነው።

በከፍተኛ ወዳጅነትና በፍጹም ወንድማማችነት መንፈስ ተመካከሩ፤ የሕይወታችሁንም ውድ ቀናት ዓለምን ለማሻሻልና የእርሱን፣ የሁሉ ጥንታዊና ሉዓላዊ ጌታን እምነት ለማስፋፊያ አውሉ።

እርሱ፣ በእውነቱ፣ ሰዎች ሁሉ ትክክል የሆነውን እንዲያደርጉ ያዛቸዋል፤ ደረጃቸውን ዝቅ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ይከለክላቸዋል።

(109)

በዚያ፣ ጌታህ፣ የሰዎች ሁሉ ጌታ፣ በመጽሐፉ ውስጥ በደነገገው መሠረት፣ በእርሱ ለሰው ዘር የተለገሱት ስጦታዎች በብዛታቸው ወሰን እንደሌላቸው፣ ለወደፊቱም ለዘለዓለም እንዲሁ ወሰን አልባ ሆነው እንደሚቀጥሉ ዕወቅ። ፍጹም ኃያሉ ለሰው ካጐናጸፋቸው ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል የመጀመሪያውና ቀዳሚው፣ የመገንዘብ ችሎታ ስጦታ ነው። እንዲህ ያለውን ስጦታ ሲለግሥ ዓላማው ፍጡሩን፣ ክብሩ ይስፋና፣ አንዱን እውነተኛ አምላክ አውቆ ለመቀበል ለማስቻል በስተቀር በሌላ አይደለም። ይህ ስጦታ ሰው በሁሉ ነገሮች እውነትን እንዲያይ ኃይልን ይሰጠዋል፤ ትክክለኛ ወደ ሆነው ነገር ይመራዋል፤ የፍጥረትንም ምሥጢር እንዲፈታ ይረዳዋል። በደረጃ የሚቀጥለው ስጦታ፣ የሰው የመገንዘብ ኃይል ሊበራበት የሚችልበት ዋነኛ መሣሪያ የሆነው፣ የማየት ችሎታ ነው። የመስማት፣ የልቦናና የመሳሰሉት ችሎታዎችም እንደዚሁ ለሰው ልጅ አካል ከተለገሡት ስጦታዎች መካከል እንደሆኑ መቆጠር አለባቸው። እነዚህን ችሎታዎች የፈጠረውና በሰው አካል ውስጥ የገለፃቸው ፍጹም ኃያሉ ፈጣሪ ለመለካት ከሚቻል በላይ ከፍ ያለ ነው።

እነዚህ ስጦታዎች እያንዳንዳቸው፣ ክብሩ ይስፋና፣ የአንዱ እውነተኛ አምላክ ግርማ፣ ሥልጣን፣ የበላይነትና ሁሉን አቀፍ ዕውቀት የማያጠራጥሩ ማስረጃዎች ናቸው። የመዳበስ ችሎታን አስብ። ኃይሉ በመላው የሰው አካል ላይ እንዴት እንደተሰራጨ አስተውል። የማየትና የመስማት ሕዋሳት እያንዳንዳቸው በተለየ ማዕከል የተወሰኑ ሲሆኑ፣ የመዳበስ ሕዋስ ግን የሰውን አካል በሙሉ

ያደርሳል። ሥልጣኑ ይከበር ሉዓላዊነቱም ከፍ ይበል!

እነዚህ ስጦታዎች በሰው በራሱ ተፈጥሯዊ ናቸው። ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ የላቀው፣ በተፈጥሮው የማይበላሸውና የእግዚአብሔር የራሱ የሆነው፣ የመለካታዊ ግልጸት ስጦታ ነው። በፈጣሪ ለሰው የተሰጠው እያንዳንዱ ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ጸጋ፣ ለዚህ ግልጸት ተገዢ ነው። ይህም፣ በሕላዌው ከሰማይ የሚመጣ እንጀራ ነው፤ ለዘለዓለምም እንዲህ መሆኑን ይቀጥላል። ይህ የአምላክ እጅግ በጣም ከፍተኛ ምሥክር፣ የእውነቱ እጅግ በጣም ግልጽ ማስረጃ፣ የፍጹም ቸርነቱ ምልክት፣ ሁሉን የሚከበው መሕረቱ መታወቂያ፣ የእጅግ በጣም ፍጹም አምላካዊ ጥበቃው ማረጋገጫ፣ የእጅግ በጣም ፍጹም ጸጋው አርማ ነው። በዚህ ቀን፣ የእርሱን ከስተት የተቀበለ፣ እርሱ በእርግጥ፣ ከዚህ ከእጅግ በጣም ከፍተኛው የእግዚአብሔር ስጦታ ተካፍሏል።

እንዲህ ያለውን ታላቅ ቸርነት ለለገሥህ ጌታህ ምሥጋና አቅርብ። ድምፅህንም ከፍ በማድረግ እንዲህ በል፡- አንተ የእያንዳንዱ የሚገነዘብ ልብ ፍላጎት ሆይ፣ ምሥጋና ሁሉ ለአንተ ይሁን!

## (110)

የሃይማኖት መሪዎች ሆይ! በል፡- የአምላክን መጽሐፍ አሁን በመካከላችሁ በሚገኙት መመዘኛዎችና ሳይንሶች አትመዝኑት፤ ይህ መጽሐፍ ራሱ በሰዎች መካከል የተቋቋመ የማይሳሳት ሚዛን ነውና። የምትረዱስ ከሆነ፣ በዚህ አጅግ ፍጹም በሆነው ሚዛን፣ የምድር ሕዝቦችና ዘሮች ያላቸው ማንኛውም ነገር መመዘን አለበት። የራሱ መጠን ግን በራሱ ደረጃ መፈተን ይገባዋል።

እርሱን፣ ጧትና ማታ ቀንና ሌሊት የምትጠሩትን ማወቅ ባለመቻላችሁ፣ የፍቅራዊ ደግነቴ ዓይን አምርሮ በእናንተ ላይ አያለቀሰ ነው። ሕዝብ ሆይ፣ እንደ በረዶ በነጹ ፊቶችና በሚያንጸባርቁ

ልቦች፣ ሳድራቱል ሙንተሃ፡- "በእውነት ምንም ከማይሳነው ጠባቂ፣ ራሱን ችሎ ከሚኖረው፣ ከእኔ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤" በማለት ወደሚጣራበት ወደተባረከውና ወደ ቀዩ ቦታ ገሥግሡ።

እናንት የሃይማኖት መሪዎች ሆይ! ከእናንተ መካከል አርቆ በማየትና በማስተዋል ረገድ ሊወዳደረኝ የሚችል ማን ነው? እርሱ በንግግርም ሆነ በጥበብ እኩያህ ነኝ ለማለት የሚደፍር የት ነው የሚገኘው? በጌታዬ በፍጹም መሐሪው፣ አንድም የለም፤ በምድር ላይ ያለው ሁሉ ያልፋል፤ ይህ የጌታችሁ፣ የፍጹም ኃያሉ፣ የፍጹም ተወዳጁ ፊት ነው።

ሕዝብ ሆይ፣ የትምህርት ሁሉ ከፍተኛውና የመጨረሻ መደምደሚያ እርሱን የዕውቀት ሁሉ ዓላማ የሆነውን ማወቅ እንዲሆን ደንግገናል፤ ሆኖም ዕውቀታችሁ እንደግርዶሽ ሆኖ ከእርሱ፣ የዚህ ብርሃን የቀን ምንጭ ከሆነው፣ በእርሱም አማካይነት እያንዳንዱ ኅቡዕ ነገር ከተገለጸው እንዲዘጋችሁ እንዴት እንደፈቀዳችሁ ተመልከቱ። የዚህ የንግግር ድምቀት የሚፈልቅበትን ምንጭ ብታገኙ ኖሮ፣ የዓለምን ሕዝቦችና ሃብታቸሁን በመላ ትታችሁ፣ ወደዚህ እጅግ በጣም ወደተባረከው የክብር ዙፋን በቀረባችሁ ነበር።

በል፡- መገንዘብ የምትችሉስ ከሆነ፣ ይህ በእውነት፣ እናት መጽሐፍ የሚገኝበት መንግሥተ- ሰማይ ነው። አለቱ እንዲጮህ፣ የሚነደውም ቁጥቋጦ ከቅድስት አገር ከፍ ካለው ተራራ ላይ ድምፁን ከፍ አድርጎ፡- *"መንግሥት የሁሉ ሉዓላዊ ጌታ፣ ፍጹም ኃይል የተመላው፣ የአፍቃሪው ነው!"* ብሎ እንዲያውጅ ያደረገው እርሱ ነው።

በማንኛውም ትምህርት ቤት አልተማርንም፣ ጽሑፎቻችሁንም አላነበብንም። ዘለዓለም ነዋሪ ወደሆነው አምላክ ወደሚጠራችሁ ወደዚህ ወደአልተማረው ቃላት ጆሮዎቻችሁን መልሱ። ልትገነዘቡት ብትችሉ ኖሮ፣ ይህ በምድር ላይ ከሚገኘው

ሃብት ሁሉ ይበልጥባችኋል።

## (111)

እርሱን ከሚያፈቅሩት ሁሉ፣ የእርሱ፣ ፍጹም የተከበረው ካባ ጥዑም ሽታ ይሸተት ዘንድ፣ ሰዎችን ሁሉ፣ ከምድራዊ ነገሮች ቁራኛነት ሁሉ ወደሚቀድሷቸውና ከርኩሰቷም ወደሚያነጿቸው ነገሮች ሁሉ መጥራት የአንተና፣ የእርሱ፣ የዘለዓለማዊው እውነት ተከታዮች የሆኑት ግዴታ ነው።

በትእግሥት ለሚጸኑት ድሆች በእግዚአብሐር የተወሰነላቸው ክብር ታላቅ ስለሆነ፣ ሀብት ያላቸው ሁሉ ለድሆች ከፍተኛ እንክብካቤ ማድረግ ይገባቸዋል። በሕይወቴ! እግዚአብሔር ሊለግስ ከፈቀደው በስተቀር ከዚህ ክብር ጋር ሊወዳደር የሚችል ምንም ክብር የለም። ችግራቸውን በትእግሥት የሚችሉትንና ሥቃያቸውን የሚደብቁትን ድሆች የሚጠብቃቸው ቡራኬ ታላቅ ነው። ሃብታቸውን ለችግረኞች የሚሰጡና እነርሱን ከራሳቸው የሚያስቀድሙትም ሃብታሞች የታደሉ ናቸው።

ድሆች እንዲሠሩና ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለማፍራት እንዲጥሩ አምላክ ፈቃዱ ይሁን። ይህ በዚህ እጅግ በጣም ታላቅ ግልጸት፣ በእያንዳንዱ ላይ የታዘዘ ግዴታ ነው፣ በአምላክም ፊት አንደመልካም ተግባር ይቆጠራል። ይህንን ግዴታ ላከበረ፣ የእርሱ የማይታየው እርዳታ በእርግጥ ያግዘዋል። እርሱ፣ የወደደውን በጸጋ ሊያበለጽገው ይችላል። እርሱ፣ በእውነቱ በሁሉም ላይ ሥልጣን አለውና።

## (112)

የእያንዳንዱ መንግሥተ-ሰማያዊ መጽሐፍ መገለጽ፣ እንዲያውም የእያንዳንዱ በመለኮት የተገለጸ ጥቅስ መሠረታዊ ዓላማ፣

ሰላምና መረጋጋት በእነርሱ መካከል በጥብቅ ይመሠረት ዘንድ፣ ሁሉንም ሰዎች ትክክለኛነትንና መግባባትን ለማላበስ ነው። በሰዎች ልቦች እርግጠኛነትን የሚያሰርጽ ማንኛውም ነገር፣ ደረጃቸውን ከፍ የሚያደርግ ወይም ደስታን የሚጨምርላቸው ሁሉ፣ በአምላክ ፊት ተቀባይነት አለው። ሰው፣ የተመደበለትን ግብ ለማሟላት ቢመርጥ፣ ሊደርስበት የሚችለው ደረጃ እንዴት ከፍተኛ ነው! እንዴት የውርደት ጥልቀት፣ ከፍጡሮች እጅግ በጣም ዝቅተኛው እንኳ ደርሶበት ወደማያውቀው ዓይነት ጥልቀት፣ ወደ ምን ዓይነቱስ አዘቅት ሊሰጥም ይችላል! ወዳጆች ሆይ፣ ይህ ቀን የሚያቀርብላችሁን ዕድል ያዙ፤ በብዛት ያለማቋረጥ ከሚፈሰው ጸጋውም ራሳችሁን አትንፈጉ። በዚህ የተባረከ ቀን፣ ራሱን በንጹሕና በተቀደሱ ተግባራት ጌጥ ለማስዋብ እያንዳንዱን በጸጋው እንዲያስችለው አምላክን እማጸናለሁ። እርሱ፣ በእውነቱ፣ የፈቀደውን ሁሉያደርጋልና።

## (113)

ሕዝብ ሆይ፣ እኔ፣ በእውነት ለምነግራችሁ አድማጭ ጆሮ ይኑራችሁ። ክብሩ ይስፋና፣ አንዱ እውነተኛ አምላክ፣ የሰዎችን ልቦች እንደራሱ፣ እንደ ግል ሀብቱ ቆጥሯቸዋል፣ መቈጠሩንም ይቀጠላል። ሌላውን ሁሉ፣ የምድርም ሆነ የባሕርን፣ ሀብትንም ሆነ ክብርን፣ ለምድር ነገሥታትና መሪዎች አውርሷቸዋል። መጀመሪያ ከሌለው መጀመሪያ ጀምሮ፣"እርሱ የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋል" የሚሉትን ቃላት የሚያውጀው ዓርማ በሙሉ ድምቀቱ በእርሱ ክስተት ፊት ተዘርግቷል። በዚህ ቀን ለሰው ዘር የሚያስፈልገው ለእነዚያ በሥልጣን ላይ ላሉት ታዛዥ መሆንና፣ የጥበብን ገመድ በታማኝነት አጥብቆ መያዝ ነው። ለሰው ዘር የቅርብ መከላከያ፣ ለደህንነቱና ለዋስትናው አስፈላጊ የሆኑት መሣሪያዎች ለኅብረተ-ሰቡ ገዢዎች እጆች በአደራ ተሰጥተዋል፣ በመዳፋቸውም ውስጥ ይገኛሉ። ይህም

የእግዚአብሔር ፍላጎትና ድንጋጌ ነው። ከምድር ነገሥታት አንዱ፣ ለእግዚአብሔር ብሎ፣ ለእነዚህ ለተገፉት፣ ለእነዚህ ለተጨቆኑት ሕዝቦች ድል አድራጊነት እንደሚነሣ ተስፋ እናደርጋለን። እንዲህ ያለው ንጉሥ፣ ለዘለዓለም ይመሠገናል፣ እንዲሁም ይከበራል። ይህ ሕዝብ የሚረዳቸውን ማንኛውንም ሰው የመርዳት፣ እርሱን የሚጠቅሙትንም ነገሮች የመሥራትና፣ ለእርሱም ዘላቂ ታማኝነታቸውን የማሳየት ግዴታን እንዲፈጽሙ አምላክ አዟቸዋል። እኔን የሚከተሉ ሁሉ፣ በማናቸውም ሁኔታዎች፣ለእኔ እምነት ድል አድራጊነት የሚነሡትን ሁሉ ደህንነት ለመጠበቅ ለመጣርና በማንኛውም ጊዜ ለእነርሱ ያላቸውን ፍቅርና ታማኝነት ማረጋገጥ አለባቸው። ምክሬን የሚያዳምጥና የሚያከብር ሰው ደስተኛ ነው። ፍላጎቴን ለማይፈጽም ግን ወዮለት!

## (114)

እናንት የዓለም ሕዝቦች ሆይ! ያልታሰበ መዓት እየተከተላችሁ መሆኑን፣ አስፈሪ ቅጣትም እንደሚጠብቃችሁ በእርግጥ ዕወቁ። የፈጸማችኋቸው ተግባሮች ሁሉ በእኔ ዘንድ የተረሱ አይምሰላችሁ። በውበቴ! ተግባሮቻችሁን በሙሉ ጉልህ በሆኑ ፊደላት በከበረ ድንጋይ ጽላቶች ላይ ቀርጿቸዋል።

## (115)

ሁሉን አዋቂው ሐኪም ጣቱን በሰው ዘር ልብ ትርታ ላይ አሳርፏል። በሽታውን ያውቃል፤ በሥሕተት አልባው ጥበቡም፣ መድኃኒቱን ያዝል። እያንዳንዱ ዘመን የራሱ ችግር፣ እያንዳንዱም ነፍስ የተለየ የራሱ ፍላጎት አለው። ለዓለም በዛሬው ጊዜ መከራዎችዋ የሚያስፈልጋት መድኃኒት ለሚቀጥለው ዘመን ከሚያስፈልገው ጋር አንድ ዓይነት ሊሆን ከቶ አይችልም። ለምትኖርበት ዘመን ፍላጎቶች

የኃላፊነት ስሜት የተመላበት ሃሳብ ይኑራችሁ፤ ምክክራችሁም በአጣዳፊና በአስፈላጊ ጉዳዮቿ ላይ እንዲያተኩር አድርጉ።

መላው የሰው ዘር እንዴት ስፍር ቁጥር በሌላቸው ታላላቅ መከራዎች እንደተከበበ በግልጽ እያየን ነው። ከፉኛ ተፈትኖና ግራ ተጋብቶ በበሽተኛ አልጋ ላይ በመማቀቅ ላይ ሆኖ እናየዋለን። እነዚያ በትዕቢት የሰከሩት በእርሱና (በሰው ዘርና) በማይሳሳተው መለኮታዊ ሐኪም መካከል ራሳቸውን ደንቅረዋል። ሁሉንም ሰዎች፣ ራሳቸውንም ጭምር በተንኮላቸው መረብ ውስጥ እንዴት እንዳቆላለፉ አስተውሉ። የበሽታውን ምክንያት ለማግኘት አይችሉም፤ ስለመድኃኒቱም ምንም ዕውቀት የላቸውም። ቀጥታውን እንደጠማማ አስበዋል፤ ወዳጃቸውንም እንደ ጠላት ቆጥረዋል።

ጆሮዎቻችሁን ወደዚህ እሥረኛ ጣፋጭ ዜማ አቅኑ ምናልባት እነዚያ በጣም ያንቀላፉት ይነቁ እንደሆን፣ ተነሡ፣ ድምጾቻችሁንም ከፍ አድርጉ። እንዲህ በሉ፦ እናንተ እንደሬሳ የሆናችሁ ሆይ! የመለኮታዊ በረከት እጅ የሕይወትን ውሀ ያሳልፍላችኋል። ፈጠን ብላችሁ እስከትረኩ ጠጡ። በዚህ ቀን እንደገና የተወለደ ማንም ሰው ከቶ አይሞትም፣ እንደሞተ የቀረውም፣ ከቶ አይኖርም።

## (116)

እርሱ ጌታችሁ የሆነው፣ ፍጹም መሐሪው፣ በልቡ መላውን የሰው ዘር እንደ አንድ አካል ለማየት ይመኛል። የተፈጠሩትን ሌሎች ቀኖች ሁሉ በሚያስንቀው በዚህ ቀን፣ ከአምላክ መልካም ጸጋና ምሕረት ድርሻችሁን ለማግኘት ፍጠኑ። የአምላክ የሆኑትን ነገሮች ለማግኘት ባለው ፍላጎት፣ ያለውን ነገር ሁሉ እርግፍ አድርጎ የሚተወውን ሰው የሚጠብቀው ሐሴት እንዴት ታላቅ ነው!እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከአምላክ ብሩካን መካከል አንዱ መሆኑን እንመሠክራለን።

## (117)

ሕዝቦች ሆይ፣ ለእናንተ የተወሰነ ጊዜ አለን። በተወሰነውም ሰዓት ወደ አምላክ ሳትመለሱ ከቀራችሁ፣ እርሱ፣ በእውነቱ የቁጣ እጁን ያሳርፍባችኋል፣ ከባድ ሥቃይም ከሁሉ አቅጣጫ እንዲወርድባችሁ ያደርጋል። ጌታችሁ በዚያን ጊዜ እናንተን የሚቀጣበት ቅጣት፣ በእርግጥ፣ እንዴት ከባድ ነው!

## (118)

ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፡- እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! የአምላክን እምነትና ሃይማኖት ከመሠረቱ የሚያንቀሳቅሰው ኃይል፣ የሰውን ዘር ጥቅም ለመጠበቅና አንድነቱንም ለማጠናከር፣ በሰዎችም መካከል የወንድማማችነትንና የፍቅርን መንፈስ ለማዳበር ነው። የልዩነትና የንትርክ፣ የጥላቻና የጠላትነት ምንጭ እንዲሆን አታደርጉት። ይህ ትክክለኛው መንገድ፣ ቋሚና የማይናወጥ መሠረት ነው። በዚህ መሠረት ላይ የተገነባ ማንኛውም ነገር የዓለም መለዋወጥና አጋጣሚዎች ቢያጋጥሙት እንኳ፣ ጉልበቱን አያዳክሙትም። የእልፍ አእላፋት ምዕተ ዓመታት ማለፍም እንኳ መሠረቱን አይበረቡሩትም። ተስፋችን የዓለም የሃይማኖት መሪዎችና ገዢዎቿ፣ ለዚህ ዘመን መሻሻልና ለዕድሎቹ መቃናት ተባብረው እንደሚነሡ ነው። በሚያስፈልጓት ነገሮች ላይ ከአሰላሰሉ በኋላ፣ በአንድ ለይ በመመካከር፣ በልባዊና ጥንቃቄ በተመላበት ምክክር፣ ለታመመችውና ከፉኛ ለተሠቃየችው ዓለም የሚያስፈልጋትን መድኀኒት ይስጡ።. . .እነዚያ በሥልጣን ላይ ያሉት በሁሉ ነገር ሚዛናዊነትን መጠቀም ይገባቸዋል። ከመጠን የሚያልፍ ማንኛውም ነገር ጠቃሚ ውጤት ማስከተሉን ያቋርጣል። ለምሳሌ እንደ ነፃነት፣ ሥልጣኔና የመሳሰሉትን ነገሮች ተመልከቱ። የመረዳት ችሎታ ያላቸው ሰዎች የፈለገውን ያህል እንደመልካም ነገሮች

ቢቆጥሩአቸውም፣ ከመጠን እንዲያለፉ ቢደረጉ በሰዎች ላይ ጎጂ ተጽዕኖ ያስከትላሉ።... አምላክ ፈቃዱ ከሆነ፣ በገዢዎቻቸው፣ እንዲሁም በሰዎች መካከል በሚገኙ ጠቢባንና ምሑራን ከፍተኛ ጥረቶች ምክንያት የዓለም ሕዝቦች ይበልጥ የሚጠቅማቸውን ወደ ማወቅ ይመራሉ። የሰው ዘር አስከ መቼ በአመጸኝነቱ ይቆያል? ፍትሕ አልባነት እስከ መቼ ይቀጥላል?ብጥብጥና ውዥንብር እስከ መቼ በሰዎች መሐከል ይነግሣሉ? አለመግባባት የኅብረተ-ሰቡን ገጽታ እስከመቼ ያውካል? እነሆ የተስፋ መቁረጥ ነፋሶች ከሁሉም አቅጣጫ እየነፈሱ ናቸው፤ የሰውን ዘር የሚከፋፍለውና የሚያሠቃየውም ጠብ ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ ነው። ያለው ሥርዓት በሚያሳዝን ሁኔታ ብልሹ ሆኖ በመገኘቱ ያንዣባቢው ነውጥና የትርምስ ምልክቶች አሁን በመታየት ላይ ናቸው። እርሱ የምድርን ሕዝቦች በጸጋው እንዲያነቃቸው፣ የፀባያቸውም ዓላማ የሚጠቅማቸው ይሆን ዘንድ፣ ያንንም ለደረጃቸው ተገቢ የሆነውን ለመፈጸም እንዲረዳቸው፣ ክብሩ ይስፋና፣ አምላክን እማጸናለሁ።

(119)

ለረዥም ዓመታት፣ ምድርን ያሠቃዩትን ብጥብጦች፣ ሕዝቦቿንም የያዟቸውን ሁከቶች ተመልከት። በጦርነት ስትፈራርስ፣ ወይንም በቅጽበታዊና ባልተጠበቁ መቅሰፍቶች ስትሠቃይ ቆይታለች። ምንም እንኳ ዓለም በሥቃይና በጭንቀት የተከበበች ብትሆንም፣ የዚያ ምክንያት ወይም መንሥኤ ምን እንደሆነ ለማወቅ ቆም ብሎ ያሰላሰለ ማንም ሰው የለም። እውነተኛው መካሪ አንድ የምክር ቃል በተናገረ ቁጥር፣ እነሆ፣ እነርሱ ሁሉም እንደተንኮል ቀስቃሽ አውግዘውታል፣ ቃሉንም ሳይቀበሉ ቀርተዋል። እንዲህ ያለው ጠባይ፣ እንዴት ግራ የሚያጋባ፣ እንዴት የሚያደናግር ነው! ላይ ላዩን ወይም ከልብ ተባብረዋል ሊባሉ የሚችሉ ሁለት ሰዎች

ሊገኙ አይችሉም። ምንም እንኳ ሁሉም ለስምምነትና ለኅብረት የተፈጠሩ ቢሆኑም፣ በሁሉም ሥፍራ የመለያየትና የክፋት ምልክቶች ግልጽ ናቸው። ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፡- እናንተ በጣም የተወደዳችሁ ሆይ! የአንድነት ደንኳን ተተክሏል፤ እርስ በርሳችሁ እንደ ባዕዳን አትተያዩ። እናንተ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች፣ የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ። የፍትሕ ብርሃን በዓለም ላይ እንደሚያበራና ከጭቆና እንደሚያነፃት ጽኑ ተስፋ አለን። ክብሩ ይስፋና፣ የአምላክ ኃይል ምልክቶች የሆኑት፣ የምድር ገዢዎችና ነገሥታት ቢነሡና የመላውን የሰው ዘር ከሁሉ የሚበልጡ ጥቅሞች ለሚያዳብሩ ለማናቸውም ነገሮች ራሳቸውን ለመስጠት ቢስማሙ፣ በሰው ልጆች መካከል ፍትሕ የሚሰፍንበት ዘመን ያለጥርጥር ይመሠረታል፤ የብርሃኑም ደማቅ ጮራ መላዋን ምድር ይሸፍናል። ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፡- የዓለም መረጋጋትና ሥርዓት መዋቅር የቆመው፣ ሕይወት ማግኘቱንም የሚቀጥለው፣ በመንትዮች የሽልማትና የቅጣት ምሰሶዎች ላይ ነው። … በሌላ ጽሑፍ እንዲህ በማለት ጽፏል፡- ተጠንቀቁ፣ የዓለም ገዢዎች ሆይ!በምድር ላይ በድል አድራጊነት ሥልጣኑ የፍትሕንና የጥበብን ኃይል ሊስተካከል የሚችል ኃይል የለም።… የጥበብ ሰንደቅ በፊቱ ተዘርግቶ፣ የፍትሕ ሠራዊቶችም ከኋላው ተሰልፈው የሚጓዝ ንጉሥ የተባረከ ነው። እርሱ በእውነቱ የሰላምን ግንባርና የደህንነትን ገጽታ የሚያጌጥ ነው። የጭቆና ደመናዎች የጋረዱት የፍትሕ የቀን ኮከብ ብርሃኑን በሰዎች ላይ ቢፈነጥቅ፣ የምድር ገጽታ ሙሉ በሙሉ እንደሚለወጥ ምንም ዓይነት ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

## (120)

የክርስቲያን ዓለም ነገሥታት ሆይ! የአምላክ መንፈስ የሱስ፣ *"እሄዳለሁ፤ እንደገናም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፣"*ያለውን

ቃል አልሰማችሁምን? ገጹን እንድታዩ፣ ከእነዚያም ወደ እርሱ መቅረብን ከተቀዳጁት እንድትሆኑ፣ በሰማይ ደመናዎች እንደገና ወደ እናንተ በመጣ ጊዜ ታዲያ ወደ እርሱ ሳትቀርቡ ለምን ቀራችሁ?በሌላ ጽሑፍ እንዲህ ይላል፡- *"እርሱ፣ የእውነት መንፈስ ሲመጣ፣ ወደ ሁሉ እውነት ይመራችኋል።"* ሆኖም እርሱ እውነትን በአመጣ ጊዜ ፊቶቻችሁን ወደ እርሱ መመለሱን እንዴት እምቢ እንዳላችሁ፣ በጊዜ ማሳለፊያዎቻችሁና በከንቱ ፍላጎታችሁም እንዴት እንደቀጠላችሁ ተመልከቱ። ባለመቀበላችሁና ቅርበቱንም ባለመፈለጋችሁ የፍጹም ኃያሉን፣ ፍጹም ክብር የተመላውን፣ የፍጹም ጠቢቡን አምላክ ሰፊ ጥበብ መሳተፍ አልቻላችሁም። ሳትፈልጉ በመቅረታችሁም ምክንያት የአምላክ እስትንፋስ በላያችሁ ላይ እንዳይነፍስ አደረጋችሁ፤ የመዓዛውንም ጣፋጭነት ነፍሳችሁን ነፈጋችሁ። በእርኩስ ፍላጎታችሁ ሸለቆ ውስጥ በእርካታ መመላለሳችሁን ቀጥላችኋል። እናንተና ያላችሁም ሃብት ሁሉ ያልፋል። ያለምንም ጥርጥር፣ በእርግጥ፣ ወደ አምላክ ትመለሳላችሁ፤ በእርሱ፣ መላውን ፍጥረት አንድ ላይ በሚሰበስበው ፊት ለአድራጎቶቻችሁ ትጠየቃላችሁ።...

## (121)

ታላቁ ሕያው፣ ለዓለም ሰላምና መረጋጋት ለሕዝቦቿም ዕድገት በቅድሚያ ተፈላጊ የሆኑትንነገሮች ለመግለጽ በመሻት የሚከተለውን ጽፏል። ሰፊና ሁሉን አቀፍ የሰዎች ጉባኤ የማድረግ ፍጹም አስፈላጊነት ሁለንተናዊ ግንዛቤ የሚያገኝበት ጉዞ መምጣት አለበት። በዚህ ጉባኤ የምድር ገዢዎችና ነገሥታት መገኘት አለባቸው። በውይይቱም በመሳተፍ፣ በሰዎች መካከል ታላቁ የዓለም ሰላም መሠረቶች የሚጣሉበትን መንገዶችና ዘዴዎች መቀየስ ይገባቸዋል። እንዲህ ያለው ሰላም ኃያላን መንግሥታት ለምድር ሕዝቦች ሰላም ሲሉ በመካከላቸው መሉ በሙሉ ለመስማማት

እንዲወስኑ ይጠይቃል። ማንኛውም ንጉሥ በሌላው ላይ የጦር መሣሪያ ቢያነሣ፣ ሁሉም በአንድነት ተነሥተው እርሱን መግታት አለባቸው። ይህ ቢደረግ፣ የዓለም መንግሥታት የግዛቶቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅና በሀገሮቻቸው ውስጣዊ ሥርዓት ለማስከበር ዓላማ በቀር ምንም ጦር መሣሪያ አያስፈልጋቸውም። ይህም ለእያንዳንዱ ሕዝብ፣ መንግሥትና ነገድ ሰላምንና ጸጥታን ያረጋግጣል። የኃያሉና ጺጋ የተመላው አምላክ ስም አንጸባራቂዎች የሆኑት የምድር ነገሥታትና ገዥዎች ለዚህ ደረጃ እንደሚደርሱ፣ የሰውንም ዘር ከግፍ ጭፍጨፋ እንደሚመክቱ ሙሉ ተስፋ አለን፤ ...

(122)

እናንተ የዓለም ገዢዎች ሆይ! የፀሐይን ብርሃን የጋረዳችሁ፣ እንዳታበራም ያደረጋችኋት ለምንድነው? እናንተና ድሆች ሠላምና ፀጥታ ታገኙ ዘንድ በእጅግ በጣም ከፍተኛው ብዕር የተሰጣችሁን ምክር አድምጡ። የምድር ነገሥታት ሠላምን በምድር ላይ ለመመሥረት እንዲችሉ እንዲረዳቸው አምላክን እንማጸነዋለን። እርሱ በእውነቱ የፈቀደውን ያደርጋልና።

የምድር ነገሥታት ሆይ! በየዓመቱ ወጫችሁን እየጨመራችሁ ሸክሙንም በተገዢዎቻችሁ ላይ ስትጭኑ እናያችኋለን። ይህ በእውነቱ አሳፋሪና ፍጹም በደል ነው። የዚህን ግፍ የደረሰበትን ኃዘንና እንባ ፍሩ። በሕዝቦቻችሁም ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሸክም አትጫኑ። ለራሳችሁ ቤተ-መንግሥቶችን ለመሥራት አትዝረፉአቸው፤ ይልቁንም ለራሳችሁ የምትመርጡትን ለእነርሱም ምረጡላቸው፤ የምትገነዘቡስ ከሆነ የሚጠቅማችሁን በዚህ አኳኋን እንገልጽላችኋለን። ሕዝቦቻችሁ ሃብቶቻችሁ ናቸው። አገዛዛችሁ የአምላክን ትእዛዛት እንዳይጥስና አደራችሁን ለቀማኛ እንዳታስረክቡ ተጠንቀቁ። በእነርሱ ትገዛላችሁ፤ በሃብታቸው ትተዳደራላችሁ፣ በእነርሱም እርዳታ ድል ታደርጋላችሁ። ይህ ሁሉ

ሆኖ ሳለ በእንዴት ያለ ንቀት ትመለከቷቸዋላችሁ! እንዴት አስገራሚ ነው፣ እንዴት በጣም አስገራሚ ነው!

እንግዲህ እጅግ በጣም ታላቁን ሰላም አንቀበልም ስላላችሁ፣ ምናልባት የራሳችሁንና የጥገኞቻችሁን ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለማሻሻል እንድትችሉ ታናሹን ሰላም አጥብቃችሁ ያዙ።

እናንተ የምድር ገዢዎች ሆይ! አገሮቻችሁንና ግዛቶቻችሁን ለማስከበር ከሚጠቅማችሁ በላይ የጦር መሣሪያዎች እንዳያስፈልጋችሁ በመካከላችሁ ስምምነትን መሥርቱ። የታማኙንና የሁሉን አዋቂውን ምክር ከመቀበል ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ።

የምድር ነገሥታት ሆይ፣ ተባበሩ፤ የምትረዱት ከሆነ በዚህ መንገድ በመካከላችሁ ያለው የጥላቻ ማዕበል ጸጥ ይላል፤ ሕዝቦቻችሁም እፎይታ ያገኛሉና፣ ከመካከላችሁ አንዱ በሌላው ላይ የጦር መሣሪያ ቢያነሣ፣ ተባብራችሁ ተነሡበት፤ ይህ ግልጽ የሆነ ፍትሕ እንጂ ሌላ አይደለምና።

## (123)

እናንተ በየአገሩ የተመረጣችሁ የሕዝብ እንደራሴዎች ሆይ! ከእነዚያ በጥንቃቄ ከሚያስተውሉት ብትሆኑ፣ በአንድ ላይ ተወያዩ፤ ሃሳባችሁም ለሰው ዘር በሚጠቅምና ሁኔታቸውን በሚያሻሽል ተግባር ላይ ብቻ ይሁን። ዓለምን፣ ሲፈጠር ሙሉና ፍጹም ሆኖ ሳለ፣ በልዩልዩ ምክንያት፣ በአደገኛ ሕመምና በሽታዎች እንደተሠቃየ፣ እንደ ሰው አካል ቁጠሯት። ለአንድ ቀን እንኳ እረፍት አላገኘችም፤ ይልቁንም ለግል ፍላጎታቸው ብቻ ሙሉ ነፃነት በሰጡና፣ በጣም በተሳሳቱ መሐይማን ሐኪሞች እጅ በመውደቋ፣ በሽታዋ እየጠና ሄዷል። ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ችሎታ ባለው ሐኪም ሕክምና አማካኝነት አንዱ የዚያ አካል ክፍል ቢፈወስም የቀሩት ግን በነበሩበት ሁኔታ መሠቃየት ቀጥለዋል። ሁሉን አዋቂው፣ ጠቢቡ እንዲህ በማለት ገልጾላችኋል።

በዛሬው ጊዜ በኩራት ሰክረው፣ እንኳንስ እንዲህ ያለውን አስጨናቂና ተፈታታኝ ግልጸት ቀርቶ ለራሳቸው ይበልጥ ጠቃሚ የሆነውን በግልጽ ለማስተዋል በማይችሉ ገዢዎች እጅ ወድቃ እናያታለን። ከእነርሱ መካከል አንዳንዱ ሁኔታዋን ለማሻሻል ጥረት ቢያደርግም፣ ዓላማው በግልጽም ይሁን በሥውር ለራሱ ጥቅም በመሆኑ የዚያ ዓላማ ከንቱነት የማዳን ኃይሉን ውስን አድርጎታል።

ጌታ ከፍተኛ ፈውስና እጅግ በጣም ታላቅ መሣሪያ አድርጎ ለመላው ዓለም መፈወሻ ያዘዘው የሕዝቦችዋን በአንድ ዓለም አቀፋዊ ዓላማ፣ በአንድ የጋራ እምነት ሥር መሰባሰብ ነው። ይህም በጠቢብ፣ በፍጹምኃያልና፣ በተገለጸለት መለኮታዊሐኪምአማካይት በስተቀር በምንም ዓይነት ሊፈጸም አይችልም። በእርግጥ እውነቱ ይህ ነው፤ የቀረው ሁሉ ግንሥሕተት ነው።

## (124)

ወንድሜ ሆይ! እውነተኛ ተመራማሪ ወደ ቀናት ቀደምቱ ዕውቀት በሚያመራው መንገድ የፍለጋ እርምጃ ለመውሰድ ሲወስን፣ ከሁሉ አስቀድሞ የአምላክ ግልጸት ውስጣዊ ምሥጢራት መኖሪያ የሆነውን ልቡን ከሚጋርድ የተገበየ ዕውቀት አቧራና ከሰይጣናዊ ከንቱ ሃሳብ ማጎደሮች ከሚሰነዝሩት ሥውር አባባሎች ሁሉ ማንፃት አለበት። የተወዳጁ ነዋሪ ፍቅር መኖሪያ የሆነውን ልቡንም ከእያንዳንዱ ርኩሰት ማንፃት፣ ነፍሱንም ከውሃና ከሸክላ አፈር ከሆነው ሁሉ፣ ተጨባጭ ካልሆነና ዕድሜ ከሌለው ነገር ሁሉ ቁራኛነት ንጹሕ ማድረግ አለበት። ምንም የፍቅርም ሆነ የጥላቻ ርዝራዥ በዚያ እንዳይቀር ልቡን በጣም ማንፃት አለበት፤ ያለበለዚያ ያ ፍቅር በጭፍን ወደ ሥሕተት ይመራዋል፤ ወይም ያ ጥላቻ ከእውነት ያርቀዋል። በዚህ ቀን፣ አብዛኞቹ ሰዎች እንዲህ ባለው ፍቅርና ጥላቻ ምክንያት፣ ከማይሞተው ገጽ እንዴት እንደተነፈጉ፣ ከመለኮታዊው ምሥጢሮች ማጎደሮች መንገድም ወጥተው እንዴት

በጣም እንደራቁ፣ ያለ እረኛም በመረሳትና በሥሕተት ምድረ በዳ ውስጥ እንዴት በመንከራተት ላይ እንዳሉ አንተው ራስህ ታያለህ።

ያተመራማሪ፣ ሁል ጊዜ፣ እምነቱን በአምላክ ላይ መጣል አለበት፤ የምድርን ሕዝቦች መተው አለበት፤ ከትቢያ ዓለም ራሱን ማላቀቅና የጌቶች ጌታ የሆነውን አጥበቆ መያዝ አለበት። ከማንም ሰው በላይ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ፍጹም መሻት የለበትም። ማንኛውንም ኩራትንና ከንቱ ውዳሜን የመሻት ቅሪት ከልቡ ጽላት ላይ ማንፃት አለበት፤ ከራሱ ፍላጎት መላቀቅንና ትዕግሥትን አጥብቆ መያዝ፣ ዝምተኛ መሆንና ከከንቱ ንግግር መቆጠብ አለበት። ምክንያቱም ምላስ የሚያበግን እሳት፣ ትርፍ ንግግርም አደገኛ መርዝ ነውና። ቁሳዊ እሳት አካልን ይጨርሳል፣ የምላስ እሳት ግን ልብንም ነፍስንም ያወድማል። መጀመሪያ የተጠቀሰው ኃይሉ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው፣ ቀጥሎ የተጠቀሰው ግን መዘዙ ለምዕተ-ዓመት ይቀጥላል።

ሐሜት የልብን ብርሃን የሚያጨልም፣ የነፍስንም ሕይወት የሚያጠፋ ስለሆነ፣ ያ ተመራማሪ ሐሜትን እንደ ከባድ ሥሕተት መቁጠርና ራሱን ከክልሉ ማራቅ አለበት። በትንሽ መርካትና ከመጠን ካለፈ ፍላጎት ሁሉ ነፃ መሆን አለበት። የእነዚያን ዓለምን የናቁትን ሰዎች ወዳጅነት እንደ ውድ ነገር ማየት ፣ ከጉረኞችና ዓላማውያን ሰዎች መራቅንም እንደትልቅ ጥቅም መቁጠር አለበት። በየዕለቱ ጎህ ሲቀድ ከአምላክ ጋር መነጋገር፣ በሙሉ ነፍሱም የተወዳጁን ፍለጋ ሳይታክት መቀጠል አለበት። እያንዳንዱን የተዛባ ሃሣብ፣ ፍቅር በተመላበት ስሙን ማንሣት ነበልባል ማቃጠልና ከእርሱ በቀር ሌላውን ሁሉ እንደ መብረቅ በፈጠነ ፍጥነት ማለፍ አለበት። የተነጠቀውን መርዳት አለበት፣ ለችግረኛውም ልግሥናውን በፍጹም መከልከል የለበትም። ለእንስሳት ርኅራኄ ማሳየት አለበት፣ የመናገር ኃይል ለተሰጠው ለወገኑ ለሰው ልጅ ደግሞ በጣም የበለጠ። ለተወዳጁ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት ማመንታትም ሆነ፣ የሕዝቡ

ተቃውሞ ከእውነት እንዲያዘረው መንገድ መስጠት የለበትም። ለራሱ የማይመኘውን ለሌሎች መመኘት፣ የማይፈጽመውንም ነገር ቃል መግባት የለበትም። ከክፉ አድራጊዎች ጓደኝነት በሙሉ ልቡ መራቅና ኃጢአታቸውም እንዲሰረይላቸው መጸለይ አለበት። ለኃጢአተኛው ይቅርታ ማድረግ አለበት፤ በዝቅተኛነቱም ሁኔታ ሳቢያ ፍጹም መናቅ የለበትም፤ ምክንያቱም የራሱ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ማንም አያውቅምና። ኃጢአተኛ በመሞቻው ሰዓት የእምነት ህልውና የተቀዳጀውና ሞት አልባውን ጠበል በመጨለጥ ወደ ሰማይ ሠራዊት የበረረው ስንት ጊዜ ነው! ጥልቅ አማኝ ደግሞ በነፍሱ ማረጊያ ሰዓት በጣም ከመለወጡ የተነሣ መጨረሻ አዘቅት እሳት ውስጥ የወደቀው ስንት ጊዜ ነው!

እነዚህን አሳማኝና ክብደት ያላቸውን ንግግሮች የመግለጽ ዓላማችን፣ ከአምላክ በቀር ሌላውን ሁሉ እንደጊዜያዊ ማየት ያለበት መሆኑ፣ የሥግደት ሁሉ ዓላማ ከሆነው፣ ከእርሱ በቀር ሌላውን ሁሉ ፍጹም እንደሌለ ነገር መቁጠር ያለበት መሆኑ በተመራማሪው ውስጥ እንዲሰርጽ ለማድረግ ነው።

## (125)

በታማኝ አገልጋዮቻችን መካከል፣ በሥራዎቻችሁ የፍትሕ ማስረጃዎች እንዲገለጹ ለራሳችሁም ለሌሎችም ትክክለኞች ሁኑ። የጎረቤታችሁን ሀብት እንዳትነኩ ተጠንቀቁ። ለእርሱ አደራና እምነት የበቃችሁ መሆናችሁን አስመሥክሩ፤ የአምላክ ጸጋ ያጎናጸፋችሁን ስጦታዎች ለድህው፤ አትንፈጉ። እርሱ በእውነቱ ለጋሾችን ይክሳል፤ እነርሱ የለገሡትንም በእጥፍ ይመልስላቸዋል። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። መላው ፍጥረት ከነግዛቱ የእርሱ ነው። እርሱ ስጦታዎችን ለፈለገው ይሰጣል፤ ላልፈለገው ደግሞ ይከለክላል፣ እርሱ ታላቁ ሰጪ፣ እጅግ በጣም ቸሩ፣ ደጉ ነውና።

በሉ፦ የባሃ ሕዝብ ሆይ፣ የአምላክን እምነት አስተምሩ፤

ምክንያቱም አምላክ መልዕክቱን የማወጅ ተግባር እንዲያከናውን እያንዳንዱን ሰው አዞአልና፤ ከተግባሮች ሁሉ ይበልጥ እንደሚያስመሠግን ተግባርም ይቆጥረዋልና። እንዲህ ያለው ተግባር ተቀባይነት የሚኖረውም፣ ያ እምነቱን የሚያስተምረው ራሱ አስቀድሞ በላቀው ጠባቂ፣ ጸጋ በተመላው፣ በፍጹም ኃያሉ አምላክ ጥብቅ አማኝ ከሆነ ብቻ ነው። እርሱ ከዚህም በላይ፣ የእርሱን እምነት ማስተማር በሰዎች የንግግር ኃይል እንጂ፣ ኃይልን በመጠቀም እንዳይሆን አዟል። ትእዛዛቱ በዚህ ዓይነት ከእርሱ፣ እጅግ በጣም ከተከበረው፣ ከፍጹም ጠቢቡ መንግሥት ተልኳል። ከማንም ጋር እንዳትከራከሩ ተጠንቀቁ፣ ይልቁንም ደግነት በተመላበት ሁኔታና በሚያሳምን ምክር እውነቱን እንዲረዳ ለማድረግ ጥረት አድርጉ። ሰሚአችሁ ከተቀበለ ለራሱ ጥቅም ነው፤ ካልተቀበለ ተውት፤ ፊታችሁንም የአንጸባራቂ ቅድስና መኖሪያ ወደሆነው፣ ወደ አምላክ የተቀደሰ መንበር አዙሩ።

የዚህን ዓለም ነገሮችና ጉዳዮች በሚመለከት ከማንም ጋር አትከራከሩ፤ ምክንያቱም አምላክ ለእነዚያ ፍቅሮቻቸውን ለአሳረፉባቸው ትቷቸዋልና። እርሱ ከመላው ዓለም የግልጸትና የልሳን ሠራዊት ሊገሯቸው የሚችሉትን የሰዎች ልቦች መርጧል። በእርሱ፣ በላቀው አዛዥ፣ በሁሉንአዋቂው ፈቃድ፣ በአምላክ የማይሻር ትእዛዝ ጽላት ላይ በባሃ ጣቶች የታዘዘው በዚህ ሁኔታ ነው።

## (126)

በብልጽግናህ ጊዜ ለጋሥ፣ በችግርህም ጊዜ አመሥጋኝ ሁን። ለጎረቤትህ ለመታመን የበቃህ ሁን፣ በሚየበራና በወዳጅነት ገጽታ ተመልከተው። ለድሃው የሃብት ምንጭ፣ ለሃብታሙ መካሪ፣ ለችግረኛው ጩኸት መልስ ሰጪና የቃል ኪዳንህ ቅድስና ጠባቂ ሁን። በፍርድህ ትክክል በንግግርህም ጥንቁቅ ሁን። ማንንም አትበድል፤ ለሁሉም ሰው ፍጹም ትሕትና አሳይ። በጨለማ ውስጥ

ለሚሄዱትእንደመብራት፣ ለኃዘንተኛው ደስታ፣ ለተጠማው ባሕር፣ ለተሠቃየው ተገን፣ ጭቆና ለደረሰበት ደጋፊና ተከላካይ ሁን። ታማኝነትና ቀጥተኛነት የምግባሮችህ መታወቂያይሁኑ። ለመንገደኛው ቤት፣ ለሚሠቃየው ፈውስ፣ ለስደተኛው የብርታት ምሽግ ሁን። ለዓይነ ሥውር ዓይኖች፣ ለሚሳሳቱ እግሮች የሚመራ ብርሃን ሁን። ለእውነት ገጽታ ጌጥ፣ ለታማኝነት ግንባር ዘውድ፣ የጽድቅ ቤተ-መቅደስ ምሰሶ፣ ለሰው ዘር አካል የሕይወት እስትንፋስ፣ የፍትሕ ሠራዊት ዓርማ፣ ከመልካምምግባሮች አድማስ ላይ የሚያበራ ኮከብ፣ ለሰው ልብ አፈር እንደ ጤዛ፣ በዕውቀት ውቅያኖስ ላይ እንዳለ መርከብ፣ በቸርነት ሰማይ ላይ እንደ ፀሐይ፣ በጥበብ አክሊል ላይ እንደ ዕንቁ፣ በትውልድ ጠፈር ውስጥ የሚያንጸባርቅ ብርሃን፣ የትሕትና ዛፍ ፍሬ ሁን።

## (127)

እርሱን ዘለዓለማዊን እውነት ከማወቅ ቀጥሎ፣ ለሰዎች የታዘዘው የመጀመሪያውና ከሁሉ ቀዳሚየሆነው ተግባር፣ በእርሱ እምነት የመጽናት ተግባር ነው። አጥብቀህ ያዘው፤ ከእነዚያ አዕምሮዎቻቸው በአምላክ ላይ በጥብቅ ካተኮሩትና መሠረት ከያዙት ሁን። ምንም ተግባር የፈለገው ያህል ተመሥጋኝ ቢሆንም እንኳ ተወዳድሮት አያውቅም፤ ሊወዳደረውም አይችልም። ይህ የተግባራት ሁሉ ንጉሥ ነው፤ ለዚህም ጌታህ፣ ከሁሉ የላቀው፣ እጅግ በጣም ኃይል የተመላው ይመሠክራል።...

## (128)

በአምላክ ትክክለኝነት! በአምላክ ዓይን ዓለምና ከንቱ ነገሮቿ፣ ክብሯንም፣ ልትሰጥ የምትችለው ማናቸውም ደስታዎች ሁሉ እንደ አቧራና እንደ አመድ ዋጋ የሌላቸው፣ እንዲያውም ከእነዚህም

ይበልጥ የሚናቁ ነገሮች ናቸው፤ የሰዎች ልቦች ሊገነዘቡት ቢችሉ ኖሮ! የባሃ ሕዝብ ሆይ፣ ከዓለም ርኩሰት፣ ከእሷ ከሆኑት ነገሮች ሁሉ ራሳችሁን ደህና አድርጋችሁ አንጹ። አምላክ ራሱ ይመሠክርልኛል። የምድር ነገሮች ተገቢአችሁ አይደሉም። እነርሱን ለሚፈልጓቸው ጣሏቸውና ዓይኖቻችሁን በዚህ በእጅግ በጣም ቅድስና አንጸባራቂ ትዕይንት ላይ አሳርፉ።

ብታውቁት ኖሮ፣ ተገቢአችሁ አምላክን ማፍቀር፣ የእርሱ ሕልውና ክስተት የሆነውን ማፍቀርና እርሱ ሊያዛችሁ የሚመርጠውን ሁሉ ማክበሩ ነው።

በሉ፡- እውነተኛነትና አክብሮት ማጌጫችሁ ይሁኑ። የቅድስና ጣፋጭ መዓዛዎች ከልቦቻችሁ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ ይናኙ ዘንድ፣ የትዕግሥትና የፍትሕ ልብስ እንድትገፉ አታድርጉ። በሉ፡- የባሃ ሕዝብ ሆይ፣ በእነዚያ ቃሎቻቸው ከሥራዎቻቸው በሚለዩት ሰዎች መንገዶች ከሚሄዱት እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ። የአምላክን ምልክቶች ለምድር ሕዝቦች ለመግለጽና የእርሱንም ትእዛዛት ለማንጸባረቅ ያስችላችሁ ዘንድ ጥረት አድርጉ። የአብዛኞቹ ሰዎች፣ የከፍተኞቹም ሆኑ የዝቅተኞቹ፣ አድራጎቶቻቸው ከንግግሮቻቸው የተለዩ ስለሆኑ፣ የእናንተ ሥራዎች ለሰው ዘር ሁሉ ምሳሌ ይሁኑ። ራሳችሁን ከሌሎች ለይታችሁ ለማሳወቅ የምትችሉት በሥራዎቻችሁ ነው። በእነዚህ አማካይነት የብርሃናችሁ ድምቀት በመላው ምድር ላይ ሊበራ ይችላል። ምክሬን የሚቀበልና በእርሱ በሁሉን አዋቂው፣ በፍጹም ጠቢቡ የታዘዙትን ሕግጋት የሚያከብር ሰው ደስተኛ ነው።

## (129)

የተዋረዱትን ወይም የተረገጡትን ስታገኙ በንቀት ከእነርሱ ዞር አትበሉ፤ የክብር ንጉሥ ምንጊዜም ይጠብቃቸዋል፤ ከእነዚያ ፍላጎታቸውንና ምኞታቸውን ጸጋ ከተመላው፣ ከፍጹም ጠቢቡ

ጌታቸው ፈቃድ ጋር እንዲዋሐዱ ካደረጉት በቀር ማንም ሊለካው በማይችል ጥልቅ ርኅራኄም ይከባቸዋልና። እናንተ የምድር ሃብታሞች ሆይ! በአቧራ ውስጥ ከሚገኘው ድሃ ፊት አትሽሹ፣ ይልቁንም ተወዳጁትና የአምላክ የማይመረመር ትእዛዝ እንዲሠቃይበት ያደረገውን የዋይታዎች ታሪክ እንዲነግራችሁ አድርጉ። በአምላክ ትክክለኝነት! ከእርሱ ጋር በምትነጋገሩበት ጊዜ የሰማይ ሠራዊት ይመለከቷችኋል፤ ያማልዷችኋል፤ ስሞቻችሁን ያወድሣሉ፣ ተግባሮቻችሁንም ያደንቃሉ። በተቀዳጁት ዕውቀት የማይኩራሩ ምሑራን የተባረኩ ናቸው፤ የራሳቸው ጉድለቶች ከሰዎች ዓይኖች እንደተደበቁ ይቀሩ ዘንድ፣ በኃጢአተኞች የማያፌዙ፣ ይልቁንም ሥሕተቶቻቸውን የሚደብቁ ጻድቃንም የበጃቸው ናቸው።

(130)

እያንዳንዳችሁ ለሰዎች የደግነት ሁሉ ምንጭ፣ ለሰውም ዘር የትክክለኝነት ምሳሌ እንድትሆኑ ምኞታችንና ፍላጎታችን ነው። ራሳችሁን ከጎረቤቶቻችሁ እንዳታስቀድሙ ተጠንቀቁ። ትኩረታችሁን በእርሱ በሰዎች መካከል የአምላክ ቤተ-መቅደስ በሆነው ላይ አድርጉ። እርሱ፣ በእውነቱ ለዓለም መዳን ሕይወቱን ቤዛ ሰጥቷል። እርሱ፣ በእውነቱ፣ ፍጹም ሀብታም፣ ጸጋ የተመላው፣ ከሁሉ የላቀው ነው። በመካከላችሁ ማንኛውም ልዩነት ቢነሣ በፊታችሁ እንደቆምኩ ተመልከቱኝ፤ ለእኔም ስም ብላችሁ፣ ለግልጹና ለአንጸባራቂው እምነቴም ላላችሁ ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ፣ የእርስ በርሳችሁን ሥሕተቶች አትመልከቱ። እኛ በሁሉ ጊዜያት በመልካም ፈቃዴ ገነት ውስጥ፣ በወንድማማችነትና በስምምነት ስትወዳጁ ለማየት፣ ከተግባሮቻችሁም የመዋሐድንና የአንድነትን፣ የፍቅራዊ ደግነትንና የጓደኝነትን ሽታ ለማሸተት እንወዳለን።

ሁሉን አዋቂው፣ ታማኙ እንደዚህ ይመክራችኋል። ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እንሆናለን፤ የወንድማማችነታችሁን ሽቶ ከአሸተትን፣

በእርግጥ ልባችን ሐሴት ያደርጋል፤ ከዚህ በቀር ሌላ ምንም ነገር ሊያረካን አይችልምና። ለዚህም እውነተኛ የማስተዋል ችሎታ ያለው እያንዳንዱ ሰው ይመሠክራል።

(131)

ድል ሲገኝ፣ እያንዳንዱ ሰው አማኝ ነኝ ይላል፤ ወደ አምላክ እምነት መጠለያም ይሮጣል። እነዚያ ዓለምን በከበቡት ፈተናዎች ቀናት በእምነቱ በጽናት የቆሙትና ከእውነቱ አንዛነፍም ያሉት ደስተኞች ናቸው።

(132)

እነዚያን እምነታችንን ለማስተማር ዓላማ አገራቸውን ትተው የሚሄዱትን፣ እነርሱን ታማኙ መንፈስ በኃይሉ ያጠናክራቸዋል። በእርሱ፣ ፍጹም ኃያል፣ ፍፁም ጠቢብ በሆነው እንደታዘዘው፣ ምርጥ መላዕክቶቻችንም አብረዋቸው ይሄዳሉ። ፍጹም ኃያሉን ለማገልገል ክብር የበቃውን ሰው የሚጠብቀው ቡራኬ እንዴት ታላቅ ነው! በሕይወቴ! ፍጹም ኃይል በተመላው፣ በፍጹም ኃያሉ አምላክ ከታዘዙት ተግባሮች በቀር፣ ምንም ተግባር፣ ምንም ያህል ታላቅ ቢሆንም፣ ከዚህ ተግባር ጋር ሊወዳደር አይችልም። እንዲህ ያለው አገልግሎት የመልካም ሥራዎች ሁሉ ልዑል፣ የመልካም ተግባሮች ሁሉ ጌጥ ነው። በእርሱ በሉዓላዊው ገላጭ፣ በቀናት ቀደምቱ እንዲህ ታዟል።

እምነታችንን ለማስተማር የሚነሣ ማንኛውም ሰው ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ ራሱን ማላቀቅና ሁልጊዜ የእምነታችንን ድል ማድረግ እንደላቀ ግቡ መቁጥር አለበት። ይህ በእውነቱ፣ በተጠበቀው ጽላት ውስጥ ታዟል። እንዲሁም ለጌታው እምነት ብሎ ቤቱን ትቶ ለመሄድ ሲወስን፣ ለጉዞው ከሁሉም ነገር እንደሚበልጥ

ስንቅ፣ ሙሉ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ያድርግ፤ ራሱንም በመልካም ምግባራት መጎናጸፊያ ያጎናጽፍ። በእግዚአብሔር፣ በፍጹም ኃያሉ፣ በፍጹም ተወዳሹ እንዲህ ታዟልና።

በፍቅሩ እሳት ከተቀጣጠለ፣ የተፈጠሩትንም ነገሮች ሁሉ ከተወ፣ እርሱ የሚናገራቸው ቃላት ሰሚዎቹን በእሳት ያቀጣጥላሉ። በእውነቱ፣ ጌታህ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን የተገነዘበው ነው። ድምፃችንን የሰማ፣ ጥሪአችንንም የተቀበለ ሰው ደስተኛ ነው። እርሱ፣ በእውነቱ፣ ከእነዚያ ወደ እኛ እንዲቀርቡ ከሚደረጉት መካከል አንዱ ነው።

(133)

የሰዎችን አዕምሮ ትንሽነት አስተውሉ። የሚጎዳቸውን ይጠይቃሉ፤ የሚጠቅማቸውን ነገር ደግሞ ይጥላሉ። እነርሱ በእውነቱ፣ ከእነዚያ ከመንገድ በጣም ከራቁት ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ነፃነት ሲመኙ፣ በዚያም ሲኩራሩ እናገኛቸዋለን። እንዲህ ያሉት ሰዎች በድንቁርና አዘቅት ውስጥ ናቸው።

ነፃነት፣(እንዳሻ መሆን)በመጨረሻው ነበልባሎቹን ማንም ሊያጠፉ ወደማይችል ሁከት ይመራል። እርሱ ገምጋሚና ሁሉን አዋቂ የሆነው እንዲህ ያስጠነቅቃችኋል። የነፃነት ተጨባጭ ምሳሌና ምልክቱ እንስሳ መሆኑን ዕወቁ። ለሰው ተገቢው ከራሱ ድንቁርና ለሚጠብቁትና ከተንኮል ሸራቢ ጉዳት ለሚከላከሉለት አንዳንድ መግቻዎች መታዘዝ ነው። ነፃነት ሰውን ከትክክለኛው ደንብ ወሰን እንዲያልፍ፣ የደረጃውንም ክብር እንዲነካ ያደርገዋል። ወደመጨረሻ ብልሹነትና ክፉት አዘቅትም ይጥለዋል።

ሰዎችን ለጥበቃቸው እረኛ እንደሚያስፈልጋቸው እንደ በግ መንጋ ቁጠሯቸው። ይህ በእውነቱ እውነት፣ የተረጋገጠ እውነት ነው። ነፃነትን በአንዳንድ ሁኔታዎች እንፈቅዳለን፤ በሌሎች ደግሞ እንከለክላለን። እኛ በእውነቱ ሁሉን አዋቂው ነን።

በሉ፦ በመጠኑም ቢሆን እንደምታውቁት፣ እውነተኛ ነፃነት

የሰው ለትእዛዞቼ መገዛት ነው። ሰዎች እኛ ከግልጸት ሰማይ የላከንላቸውን ቢያከብሩ፣ በእርግጥ፣ ፍጹም የሆነ ነፃነት ይቀዳጃሉ። የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ከሚናኘው፣ ከፈቃዱ ሰማይእርሱ ከገለፃቸው ከማናቸውም ነገሮች የአምላክን ዓላማ የተገነዘበ ሰው ደስተኛ ነው። በሉ፡- የሚጠቅማችሁ ነፃነት ዘለዓለማዊ እውነት ለሆነው አምላክ ፍጹም ከሆነ አገልጋይነት በቀር ከሌላ ከየትም አይገኝም። የዚህን ጣፋጭነት የቀመሰ ማንም ሰው ለምድርና ለሰማይ ግዛት ሁሉ አይለውጠውም።

(134)

ማንም አንድ ሙሉ ሺህ ዓመት ከማለፉ በፊት ቀጥታ ከአምላክ የመጣ መልዕክት ባለቤት ነኝ የሚል፣ እንዲህ ያለው ሰው በእርግጥ የሚዋሽ አታላይ ነው። እንዲህ ያለውን ሃሣብ እንዲሽርና ሐሰትነቱን እንዲያጋልጥ በጸጋው ይረዳው ዘንድ፣ አምላክን እንለምናለን። ተፀጽቶ ከስሕተቱ ቢመለስ አምላክ ያለጥርጥር ይቅር ይለዋል። ነገር ግን፣ በሥሕተቱ ከቀጠለ፣ አምላክ በእርግጥ ያለ ምሕረት የሚቀጣውን ይልክበታል። በእውነቱ አምላክ በመቅጣት፣ በጣም አስፈሪ ነው! ለዚህ ጥቅስ ከግልጽ ትርጉሙ ሌላ ፍቺ የሚሰጥ ማንኛውም ሰው፣ ከአምላክ መንፈስና የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ከቦ ከሚገኘው ምሕረቱ የተነፈገ ነው። አምላክን ፍሩ፤ ከእውነት የራቁ ከንቱ አስተሳሰቦቻችሁንም አትከተሉ። የለም፣ ይልቁንም የፍጹም ኃያሉን፣ የፍጹም ጠቢቡን ጌታችሁን ትእዛዝ ተከተሉ።

## ከለውሂ አቅዳስ የተወሰዱ

(135)

እንዲህ በል፡- በኔ ነፋስ የተቀሰቀሰ ሽለብተኛ የተባረከ ነው። ሕይወት በሚዘሩ እስትንፋሶቼ ሕይወት የተዘራበት በድን/ሰው/

የተባረከ ነው። በውበቴ ላይ በማተኮር የተጽናና ዓይን የተባረከ ነው። ወደ ክብሬና ወደ ግርማዬ ድንኳን እርምጃዎቹን ያመራው ተጓዥ የተባረከ ነው። ተጨንቆ በድንኳኔ ጥላ ሥር መሸሻ የፈለገ የተባረከ ነው። ከፉኛ ተጠምቶ በዝግታ ወደሚተምሙት የፍቅራዊ ደግነቴ ውሃዎች የፈጠነ የተባረከ ነው። ያልረካና ለእኔ ፍቅር ብሎ የራስ ወዳድነት ፍላጎቶቹን ጥሎ ለሕሩያኖቼ ከመለኮታዊ ሰማይ በላኩት ገበታ ላይ የሚቀመጥ ነፍስ የተባረከ ነው። ውርደት የደረሰበትና የክብሬን ገመድ አጥብቆ የሚይዝ ሰው በሀብቴም ድንኳን ጥላ ሥር የሚገባው ችግረኛ የተባረከ ነው። የዕውቀቴን ምንጭ የሚሻው ዕውቀተ-ቢስ፣ የትዝታዬን ገመድ አጥብቆ የሚይዘውም አመጸኛ የተባረከ ነው። በቀስቃሽ እስትንፋሴ ከሞት የተቀሰቀሰና ወደ መንግሥተ-ሰማያዊ መንግሥቴ ውስጥ መግባትን ያገኘ ነፍስ የተባረከ ነው። ከእኔ ጋር በመገናኘት ጣፋጭ ቃናዎች የተቀሰቀሰና ወደ ግልጸቴ ንጋት የቀረበ የተባረከ ነው። ጌታን ራሱን፣ በታላቅ ክብሩና ግርማ ሞገሡ፣ ታላቅነትንና ገዢነትን ተጎናጽፎ የሰማው ጆሮ የመሠከረውም አንደበት አይቶት ያወቀውም ዓይን የተባረከ ነው። አነዚያ ለቅርበቱ የበቁ የተባረኩ ናቸው። ከቃሌ የቀን ኮከብ የዕውቀት ግልጸት የፈለገ የተባረከ ነው። እርሱ ራሱን በፍቅሬ ዕንቁዎች ያስጌጠ የተባረከ ነው። እርሱ ስለ ኃዘኔ የሰማና በሕዝቤ መካከል ሊረዳኝ የተነሣ የተባረከ ነው። እርሱ በመንገዴ ሕይወቱን የሰጠና ለእኔ ስም ብሎ የተለየዩና ብዙ መከራዎች የቻለ የተባረከ ነው። ስለቃሌ ከተረጋገጠለት በኋላ፣ ከሙታን መካከል ተነስቶ ምስጋናዬን ያወደሰ የተባረከ ነው። በድንቅ ዜማዎቼ የተመሰጠና በኃያልነቴ ኃይል መጋረጃዎችን የቀዳደደ የተባረከ ነው። ለቃል ኪዳኔ ታማኝ ሆኖ የጸና፣ የዓለምም ነገሮች ወደ ቅድስና መንበሬ ከመድረስ ያልከለከሉት የተባረከ ነው። ከእኔ በቀር ከማናቸውም ነገሮች ራሱን ያገለለ፣ በፍቅሬምሰማይ ውስጥ የበረረ፣ ወደ መንግሥቴም መግባትን ያገኘ፣ በክብር ዓለሞቼም ላይ የተኮረ፣ የበረከቴንም የሕይወት

ውሃዎች የተንነጨ፣ ከፍቅራዊ መለኮታዊ ጠባቂነቴ መንግሥተ-ሰማያዊ ወንዝ እስኪረካ የጠጣ፣ ከእምነቴ ጋር ራሱን ያስተዋወቀ፣ እኔ በቃላቴ ግምጃ ቤት ውስጥ የደበቅሁትን የተረዳ፣ እኔን በማመሥገንና ከፍ ከፍ በማድረግ ሥራ ተጠምዶ ከመለኮታዊ ዕውቀት አድማስም የበራ ሰው የተባረከ ነው። በእውነቱ፣ እርሱ ከእኔ ነው። ምሕረቴ፣ ፍቅራዊ ደግነቴ፣ በረከቴና ክብሬ በእርሱ ላይ ይረፍ።

## (136)
## ቢ ሻ ራ ት

*ይህ ከላቀው አድማስ በአቆር እሥር ቤት የታወጀው ፍጹም ክብር የተመላው ጥሪ ነው።*
*እርሱ የሚያብራራው፣ ሁሉን አዋቂው፣ ሁሉ የተገለጸለት ነው።*

ጥሪውን የማሰማትና እጅግ የላቀ ቃሉን የማወጃችን ብቸኛ ዓላማ የመላው ፍጥረት ጆሮ በመለኮታዊ ንግግር የሕይወት ውሃዎች አማካይነት ከውሸት ትረካዎች ጸድቶ ከሰማያት ሠሪውና የስሞች ፈጣሪ ከሆነው የዕውቀት ማኅደሮች ለወጣው ለቅዱሱ፣ ክብር ለተመላውና ለተከበረው ቃል የተከፈተ እንዲሆን ለማድረግ መሆኑን፣ እውነተኛው አምላክ ይመሠክራል፣ የስሞቹና የባሕሪያቱ ገላጮችም ይመሠክራሉ። እነዚያ በትክክል የሚፈርዱ ደስተኞች ናቸው።

### የዓለም ሕዝብ ሆይ!

### የመጀመሪያው የምሥራች

እናቱ መጽሐፍ በዚህ እጅግ ታላቅ ግልጸት፣ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ያስተላለፈው የመጀመሪያ የምሥራች የቅዱስ ጦርነት

ከመጽሐፉ መሠረዝ ነው። የመለካታዊ በረከት በር በሰማይ ውስጥና በምድር ላይ ለሚገኙት ሁሉ ፊት በእርሱ ወለል ተደርጎ የተከፈተው፣ የተትረፈረፈው ጸጋ ጌታ የሆነው፣ ፍጹም መሐሪው የተከበረ ይሁን።

## ሁለተኛው የምሥራች

የዓለም ሕዝቦችና ዘሮች በሐሴትና በደስተኝነት እርስ በርሳቸው ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲያደርጉ ተፈቅዷል። ሕዝብ ሆይ! ከሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮችጋር በወዳጅነትና በወንድማማችነት መንፈስ ተቀላቀሉ። የፈቃዱና የሥልጣኑ የቀን ኮከብ የዓለማት ጌታ ከሆነው አምላክ ትእዛዝ አድማስ ያበራው በዚህ ሁኔታ ነው።

## ሦስተኛው የምሥራች

የተለያዩ ቋንቋዎች ማጥናትን ይመለከታል። ቀድሞ ይህ ትእዛዝ ከእጅግ በጣም ከፍተኛው ብዕር ጎርፏል። አምላክ ይርዳቸውና የዓለም ገዢዎች ወይም የምድር ሚኒስትሮች በአንድ ላይ እንዲመካከሩና ካሉት ቋንቋዎች አንዱን ወይም አዲስ ቋንቋ እንዲሁም አንድ ፊደል በመውሰድ በመላው ዓለም ትምህርት ቤቶች ልጆች እንዲማሩት ማድረግ አለባቸው። በዚህ ሁኔታ መላዋ ምድር እንደ አንድ አገር ትሆናለች። የእርሱን ጥሪ የሚያዳምጥና የታላቁ ዙፋን ጌታ በሆነው አምላክ የታዘዘውን የሚያደርግ የታደለ ነው።

## አራተኛው የምሥራች

አምላክ ይርዳቸውና ከንጉሦች መካከል ማንኛውም ለዚህ ለተጨቆነው ሕዝብ ለመከላከልና ለመርዳት ቢነሣ፣ እርሱን ለማፍቀርና ለማገልገል ሁሉም እርስ በርሱ መሽቀዳደም አለበት። ይህ ተግባር ከእያንዳንዱ ይጠበቅበታል። በዚህ መሠረት እርምጃ የሚወስዱ የታደሉ ናቸው።

## አምስተኛው የምሥራች

ከዚህ ሕዝብ ማንኛቸውም በሚኖሩበት በእያንዳንዱ አገር፣ ለአገሩ መንግሥት የታማኝነት፣ የትክክለኛነትና የእውነተኛነት ባሕርይ ማሳየት አለባቸው። ይህ በትእዛዝ ሰጪው፣ በጥንት ቀናቱ ፈቃድ የተገለጸ ነው።

በአንዳንዶቹ የምድር ሕዝቦች ልቦች ውስጥ የሚነደው የጥላቻ እሳት፣ ምናልባት በመለኮታዊ ጥበብ የሕይወት ውሀዎች አማካይነት በመንግሥተ-ሰማያዊ ምክሮችና ማበረታቻዎች ኃይል ይጠፋ ዘንድ፣ የአንድነትና የስምምነት ብርሃንም በዓለም ላይ ይበራና ጮራውን ይፈነጥቅ ዘንድ፣ ከዘለዓለም ነዋሪው ፈቃድ አድማስ ለመጣው ለዚህ በጣም ታላቅ እምነት እርዳታ መስጠት የእያንዳንዱና የሁሉም የዓለም ሕዝቦች ግዴታና የሚጠበቅባቸው ተግባር ነው።

ክብሩ ከፍ ከፍ ይበልና፣ በአምላክ ኃይል ምሳሌዎች ብርቱ ጥረት በመላው ዓለም የጦር መሣሪያዎች ወደ ግንባታ መሣሪያዎች እንደሚለወጡና ውዝግብና ግጭት ከሰዎች መካከል እንደሚወገዱ ተስፋ እናደርጋለን።

## ስድስተኛው የምሥራች

ስድስተኛው የምሥራች ዝርዝሮቹ ቀደም ተደርጎ እጅግ በጣም ከተከበረው ብዕራችን ስለተገለጸው፣ ስለአነስተኛው ሰላም መመሥረት ነው። ይህን የሚደግፍና በሁሉን አዋቂው፣ በፍጹም ጠቢቡ አምላክ የታዘዘውን ማንኛውንም ትእዛዝ የሚያከብር ቡራኬው ታላቅ ነው።

## ሰባተኛው የምሥራች

የልብስ ምርጫ፣ የጺም አቆራረጥና አስተካከሉ ለሰዎች ተትቷል። ነገር ግን ሕዝብ ሆይ፣ ራሳችሁን የደንቆሮዎች መጫወቻ ነገሮች እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ።

## ስምንተኛው የምሥራች

የአምላክ ሠላም በእርሱ ላይ ይሁንና ከመንፈስ ተከታዮች መካከል የመነኮሳትና የቀሳውስት የጽድቅ ሥራ በእርሱ ዘንድ መታወስን አግኝቷል። ሆኖም፣ በዚህ ቀን፣ የምነናን አኑዋኗር ይተው፣ እርምጃዎቻቸውንም ወደ ሰፊው ዓለም ያምሩ። በዚያም ራሳቸውንና ሌሎችን ወደሚጠቅመው ሥራ ይሠማሩ። የሚታዩና የማይታዩ ነገሮች ጌታ፣ የተከበረው ዙፋን ጌታ የሆነውን፣ የአምላክን ስም የሚጠራ ያመጡ ዘንድ በጋብቻ እንዲተሣሠሩ ፈቃድ ሠጥተናቸዋል።

## ዘጠነኛው የምሥራች

ኃጢአተኛው ከአምላክ በቀር ከሌላው ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሲላቀቅና ነፃ ሆኖ ራሱን ሲያገኝ፣ ከእርሱ ይቅር ባይነትና ይቅርታን መለመን ይኖርበታል። ኃጢአትንና በደልን በሰዎች ፊት መናዘዝ የመለኮታዊ ይቅርባይነት ምክንያት ሆኖ ከቶ ስለማያውቅ፣ ለወደፊቱም ሊሆን ከቶ ስለማይችል፣ አይፈቀድም። ከዚህም በላይ በሰዎች ፊት እንዲህ ያለው መናዘዝ የሰውን እፍረትና ውርደት ያስከትላል፣ አምላክ ደግሞ - ክብሩ ይስፋና - የአገልጋዮቹን ውርደት አይፈልግም። በእውነቱ እርሱ ሩኅሩኅና መሐሪው ነው። ኃጢአተኛው በራሱና በአምላክ መካከል እንዲህ በማለት ከምሕረት ውቅያኖስ ምሕረትን መማጸን፣ ከቸርነት ሰማይም ይቅር ባይነትን መለመን አለበት፦

አቤቱ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ለእኔም ለአባቴም ለእናቴም ይቅር ባይነትህን ትፈቅድልን ዘንድ፣ በጣፋጭ ቃላትህ በጣም በመመሰጣቸው የክብር ቁንጮ ወደ ሆነው፣ ወደ እጅግ በጣም ታላቅ ሰማዕትነት ሥፍራ በፍጥነት በገሠገሡት በእውነተኞች አፍቃሪዎችህ ደም እማለድሃለሁ፤ በዕውቀትህ ውስጥ ተሸፍነው በሚገኙት ምሥጢራትና በበረከትህ ውቅያኖስ ውስጥ በተቀመጡት ዕንቁዎችም እማፀንሃለሁ። ከእነዚያ ምሕረትን ከሚያሳዩት፣ አንተ

በእውነቱ እጅግ በጣም መሐሪው ነህ። ከአንተ ከዘለዓለም ይቅር ባዩ፣ ፍጹም በረከት ከተመላው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ጌታ ሆይ! ይህ የኃጢአተኝነት ሕልውና ወደ ልግሥናህ ውቅያኖስ ፊቱን ሲመልስ፣ ይህም ደካማው የመለኮታዊ ኃይልህን መንግሥት ሲሻ፣ ይህም ድሃው ፍጡር ራሱን ወደ ሀብትህ የቀን ኮከብ ሲያዘነብል ታያለህ። በምሕረትህና በጸጋህ ከበረከትህ ግልጸቶች አትከልክለው፤ በሰማይህ ውስጥና በምድርህ ላይ ለሚኖሩት ሁሉ በሰፊው ከከፈትከው በርህም አታባርረው።

እግዚአ! እግዚአ! ኃጢአቶቼ ወደ ቅድስናህ መንበር ከመቅረብ ከልክለውኛል፤ በደሎቼም ከግርማ ሞገሥህ ድንኳን በጣም ርቄ እንድጠፋ አድርገውኛል። አንተ እንዳላደርግ የከለከልከኝን አድርጌአለሁ፤ እንድፈጽመው ያዘዝከኝንም አልፈጸምኩም።

ወደ አንተ ለመቅረብ የሚያስችለኝን በበረከትህ ብዕር ትጽፍልኝ ዘንድ በኔና በይቅርባይነትህ፣ በይቅርታህም መካከል ከተጋረጡት በደሎቼም ታነፃኝ ዘንድ በእርሱ የስሞች ሉዓላዊ ጌታ በሆነው እለምንሃለሁ።

በእውነቱ አንተ ቻይ፣ በረከት የተመላህ ነህ። ከአንተከኃያሉ፣ በረከት ከተመላው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

## አስረኛው የምሥራች

የዚህ እጅግ በጣም ታላቅ አዋጅ ገላጭ የሆነው፣ የአምላክ ጸጋ ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከመልእክቶች፣ የመጻሕፍትን መቃጠል የሚያዙትን ሕጎች አስወግደናል።

## አስራ አንደኛ የምሥራች

የሳይንስና የጥበብን ትምህርቶች፣ ግን ጠቃሚ ለሕዝቡም ዕድገትና ወደፊት መራመድ ዓላማ ውጤት የሚያመጡትን ሳይንስና

ጥበብ ማጥናት ይፈቀዳል። በእርሱ በትእዛዝ ሰጪው፣ በፍጹም ጠቢቡ እንዲህ ታዟል።

## አስራ ሁለተኛ የምሥራች

እያንዳንዳችሁ በአንዳንድ የእጅ ሥራ፣ የንግድና የመሳሰሉት ሙያዎች ላይ እንድትሠማሩ ታዛችኋል። እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራታችሁን፣ በጸጋችን ለአምላክ፣ ለእውነተኛው ከመስገድ ጋር አኩል ወደ ሆነው ደረጃ ከፍ አድርገነዋል። የአምላክን ጸጋና ቡራኬዎች በልቦቻችሁ አሰላስሉ፤ ለእርሱ በማታና በንጋት ምሥጋና አቅርቡ። ጊዜአችሁን በሥራ ፈትነትና በስንፍና አታባክኑ። ራሳችሁንና ሌሎችን የሚጠቅም ሥራ ያዙ። የጥበብና የንግግር የቀን ኮከብ ከአድማሱ በድምቀት በሚያበራው በዚህ መልዕክት እንዲህ ታዟል።

በአምላክ ፊት ከሰዎች መካከል እጅግ በጣም የተጠሉት እነዚያ በሥራ ፈትነት ተቀምጠው የሚለምኑት ናቸው። ሙሉ እምነታችሁን፣ የሃብት ማፍሪያውን ሁሉ በሚሰጠው አምላክ ላይ በማድረግ፣ የቁሳዊ ሃብት ማፍሪያን ገመድ አጥብቃችሁ ያዙ። ማንኛውም ሰው የእጅ ሥራ ወይም የንግድ ሥራ በሚይዝበት ጊዜ፣ እንዲህ ያለው ሥራ ራሱ በአምላክ ዘንድ እንደ ሥግደት ተግባር ይቆጠራል፤ ይህም የወሰን አልባውና ሁሉንየሚኖኘው በረከቱ ምልክት ነው።

## አስራ ሦስተኛው የምሥራች

የአምላክ ቤተ-ፍትሕ ሰዎች የሕዝቡ ጉዳዮች ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በእውነቱ፣ እነርሱ በእርሱ አገልጋዮች መካከል የአምላክ ባለ አደራዎች፣ በእርሱም አገሮች ውስጥ የሥልጣን የቀን ምንጮች ናቸው።

የአምላክ ሕዝብ ሆይ! ዓለምን የሚያሠለጥነው ፍትሕ ነው፣ በሁለቱ የሽልማትና የቅጣት ምሰሶዎች የተደገፈ ነውና። እነዚህ

ሁለቱ ምሰሶዎች ለዓለም የሕይወት ምንጮች ናቸው። ለእያንዳንዱ ዘመን አዲስ ችግር እያንዳንዱም ችግር ተስማሚ መፍትሔ ያለው ስለሆነ፣ እንደየጊዜው ፍላጎትና እንደሚያስፈልገው የመፍትሔ እርምጃ ይወስዱ ዘንድ፣ እንዲህ ያሉት ጉዳዮች ወደ ቤተፍትሕ ሚኒስትሮች መቅረብ አለባቸው። እነዚያ፣ ለአምላክ ብለው፣ እምነቱን ለማገለገል የሚነሱ፣ ከማይታየው መንግሥት መልኮታዊ መርሖተቀባዮች ናቸው። ለእነርሱ መታዘዝ የሁሉ ግዴታ ነው። አገርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ለቤተ-ፍትሕ መቅረብ ይኖርባቸዋል፤ የሥግደት ተግባሮች ግን አምላክ በመጽሐፉ ውስጥ በገለጸው መሠረት መፈጸም አለባቸው።

የባሃ ሕዝብ ሆይ! እናንተ የአምላክ ፍቅር የሚነጋባቸው ቦታዎች፣ የፍቅራዊ ደግነቱም የቀን ምንጮች ናችሁ። ማንኛውንም ነፍስ በመርገምና በመስደብ አንደበቶቻችሁን አታርክሱ፤ ዓይኖቻችሁንም ተገቢ ካልሆነው ነገር ጠብቁዋቸው። እናንተ ያላችሁን አቅርቡ። በተስማሚ ሁኔታ ከተወሰደ፣ ዓላማችሁ ከግብ ደረሰ፣ ካልሆነ፣ መከራከሩ ከንቱ ነው። ያንን ነፍስ ለራሱ ተውትና ፊታችሁን ወደጠባቂው፣ በገዛ ራሱ ወደሚኖረው ጌታ መልሱ። የመለያየትና የውዝግብ ቀርቶ የኃዘን ምክንያት እንኳ አትሁኑ። በእርሱ የርኅራኄ ምሕረቶች ዛፍ መጠለያ ውስጥ እውነተኛ ትምህርት እንደምታገኙና አምላክ በሚፈልገው መሠረት እንደምትሠሩ በጣም ተስፋ ተደርጓል። እናንት ሁላችሁ የአንድ ዛፍ ቅጠሎች የአንድ ውቅያኖስም ጠብታዎች ናችሁ።

## አስራ አራተኛው የምሥራች

የእነዚያን የሞቱትን ሰዎች አካላት ማረፊያ ሥፍራዎች ለመጐብኘት የተለዩ ጉዞዎች ማድረግ አስፈላጊ አይደለም። ያላቸውና ባለሃብት የሆኑ ሰዎች ወደ ቤተ-ፍትሕ የሚደረገውን የእንዲህ ዓይነቱን ጉዞ ወጪ ለመሸፈን ፈቃደኛነታቸውን ቢገልጹ በአምላክ

ዘንድ አስደሳችና ተቀባይነት ያለው ይሆናል። እነዚያ ትእዛዛቱን የሚያከብሩ ደስተኞች ናቸው።

## አስራ አምሥተኛው የምሥራች

ሪፑብሊካዊ መንግሥት ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ የሚጠቅም ቢሆንም፣ ንጉሣዊ ግርማ ሞገሥከአምላክ ምልክቶች አንዱ ነው። የዓለም አገሮች ከዚህ ተነፍገው እንዲቀሩ አንሻም። ብልሆቹ ሁለቱን በአንድ ላይ ቢያጣምሩ በአምላክ ዘንድ ዋጋቸው ታላቅ ይሆናል።

ባለፉት ሃይማኖቶች እንደ ቅዱስ ጦርነት፣ መጻሕፍትን እንደማጥፋት፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ግንኙትንና ወዳጅነትን እንደ መከልከል ወይም አንዳንድ መጻሕፍትን ማንበብ እንደመከልከል የመሳሰሉ ትእዛዛት እንደየወቅቱ አስፈላጊነት ተደንግገውና ተረጋግጠው ነበር፤ በዚህ ኃያል ግልጸት ግን፣ በዚህ ታላቅ አዋጅ የአምላክ ብዙና ልዩ ልዩ ሥጦታዎችና ችሮታዎች ሰዎችን ሁሉ ጠልለዋል፤ ከዘለዓለም ነዋሪው ጌታ የፈቃድ አድማስም፣ የእርሱ ከሥሕተት ነፃ የሆነው ትእዛዝ እኛ ከዚህ በላይ የዘረዘርነውን አሟል።

እኛ በዚህ በተባረከው፣ በዚህ ክብር የተመላውና ወደር የሌለው ቀን፣ በጸጋው ለገለጸው ለማንኛውም ነገር፣ እርሱ ይክበር ይቀደስና ለአምላክ ምሥጋና እናቀርባለን። በእውነቱ በምድር ላይ የሚኖሩት እያንዳንዳቸው እልፍ አንደበቶች ቢሰጡዋቸውና መጨረሻ እስከማያውቀው መጨረሻ ድረስ፣ ያለማቋረጥ አምላክን ቢያመሥግኑ፣ ስሙንም ከፍ ከፍ ቢያደርጉ ምሥጋናቸው በዚህ መልእክት ከጠቀስናቸው ጸጋ የተመላባቸው ችሮታዎች መካከል ለአንድ እንኳ በቂ አይሆንም። ለዚሁም ጥበብንና ማስተዋልን፣ መረዳትንና ዕውቀትን የታደለው እያንዳንዱ ሰውይመሠክራል።

የሥልጣን ምልክቶችና የክብር የቀን ምንጮች የሆኑት ገዢዎችና ነገሥታት፣ ሕግጋቱንና ትእዛዛቱን እንዲያስከብሩ ይረዳቸው ዘንድ፣ ክብሩ ይስፋና አምላክን አጥብቀን እንማጸነዋለን። እርሱ

በእውነቱ ሁሉን ቻዩ፣ ፍጹም ኃይል የተመላው፣ የሰዎችን ጥሪ የሚመልሰው ነውና።

## (137)

## ከ ታ ራ ዛ ት

አንተ የንግግሬን የወይን ጠጅ ከዕውቀቴ ዋንጫ የጠጣኸው ሆይ! የስሞች ጌታ፣ ከሁሉ እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነው ገነት ውስጥ በመለኮታዊ ኃይል እጅ ከተከላት የመለኮታዊ ሎጥ ዛፍ ኩሽኩሽታ ዛሬ እነዚህ ቅዱስ ቃላት ተሰምተዋል፡-

### የመጀመሪያው ታራዝ

ከእናቱ መጽሐፍ አድማስ የነጋው የመጀመሪያው ታራዝና የመጀመሪያው ጮራ ሰው፣የገዛ ራሱን ማወቅ ደግሞም ወደ ከፍተኝነት ወይም ወደ ዝቅተኝነት፣ ወደ ክብር ወይም ወደ ውርደት፣ ወደ ብልጽግና ወይም ወደ ድህነት የሚያመራውን መለየት እንዳለበት ነው። ለተሟላ ሰውነት ደረጃ ከበቃና ወደ ብስለቱ ከደረሰ በኋላ ሰው ሃብት የሚያስፈልገው ይሆናል፤ በጥበብ ሰዎች አስተያየት፣ በተለይም ዓለምን ለማስተማርና ሕዝቦችዋንም ለመቀደስ ዓላማ ራሳቸውን በሰጡት አገልጋዮች ዓይን፣ በእጅ ሥራ ሙያና በመሳሰሉት የሚገኘውሃብት የሚመሠገንና የሚወደሥ ነው። እነርሱ፣ በእውነቱ፣ ሕይወት የሚሰጥ የዕውቀት ውሀ ጽዋ ተሸካሚዎችና ወደተፈላጊው መንገድ የሚመሩ መሪዎች ናቸው። እነርሱ የዓለምን ሕዝቦች ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራሉ፤ ለሰውም ልጅ ከፍ ማለትና ደስተኝነት የሚበጀውን ያሳውቋቸዋል። ቀጥተኛው መንገድ ወደ ማስተዋል የቀን ምንጭና እውነተኛ መረዳት ወደሚገኝበት ሥፍራ የሚመራው፣ ብልጽግናን፣ ክብርንና ታላቅነትን ወደሚጨምረው የሚያደርሰው ነው።

ሕዝቦች የተፈጠሩበትን ዓላማ ይገነዘቡ ዘንድ፣ በፍጹም ጠቢቡ፣ በሁሉን አዋቂው ፍቅራዊ ደግነት፣ ሽፋኝ አቧራ እንዲወገድና የማስተዋል ኃይል እንዲጠናከር በጣም ተስፋ እናደርጋለን። በዚህ ቀን ዕውርነትን ለመቀነስና የማየትን ኃይል ለመጨመር የሚጠቅም ማንኛውም ነገር ምርምር የተገባው ነው። ይህ የማየት ኃይል ለእውነተኛ ዕውቀት እንደ መሣሪያና እንደ መሪ ያገለግላል። በእውነቱ በጥበብ ሰዎች አስተያየት የመረዳት ብሩህነት በማየት ኃይል ብሩህነት ምክንያት ነው። የባሃ ሕዝብ በማንኛውም አጋጣሚ ትክክለኛውንና ተገቢውን ማድረግና ሕዝቡንም እንዲሁ እንዲያደርግ መምከር አለበት።

## ሁለተኛው ታራዝ

ከሁሉም ሃይማኖቶች ጋር በወዳጅነትና በጓደኝነት መንፈስ መገናኘት፣ በሲና ላይ ተናጋሪው የሰጠውን ማወጅና በጉዳዮች ሁሉ ትክክለኝነትን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

ከሕዝብ ጋር መወዳጀት አንድነትንና ስምምነትን ያዳበረ ስለሆነ፣ ለወደፊቱም ማዳበሩን ስለሚቀጥል፣ ይህም በተራው በዓለም ላይ ሥርዓት ለማስፈንና ለአገሮች ተሃድሶ አመቺ ስለሆነ፣ እነዚያ በእውነተኛነትና በታማኝነት የታደሉት ከሁሉም የዓለም ሕዝቦችና ዘሮች ጋር በሐሴትና በደስተኝነት ማኅበራዊ ግንኙነት ማድረግ ይገባቸዋል። እነዚያ የደግነትንና የፍቅራዊ ምሕረትን ገመድ አጥብቀው የያዙት ከጠላትነትናከጥላቻ ነፃ የሆኑት የተባረኩ ናቸው።

ይህ የተበደለው የዓለም ሕዝቦች በዓለም ጨለማ ውስጥ ሁለት ብርሃኖች፣ የሰውንም ዘር ቅዱስ ለማድረግ ሁለት አስተማሪዎች የሆኑትን፣ የቻይነትንና የትክክለኝነትን ባሕርይ እንዲያዳብሩ ይመክራቸዋል። እዚህ ላይ የደረሱ ደስተኞች ናቸው፤ ግዴለሾች ደግሞ ወዮላቸው።

## ሦስተኛው ታራዝ

መልካም ጠባይን ይመለከታል። መልካም ጠባይ፣ በእውነቱ፣ ከአምላክ የተሰጠ ከሁሉ የላቀ ልብስ ነው። እርሱ በዚህ የተወዳጆቹን አካል ያስጌጣል። በሕይወቴ! የመልካም ጠባይ ብርሃን ከፀሐይ ብርሃንና ከአንፀባራቂነቷ ይበልጣል። ለዚህም የሚደርስ በሰዎች መካከል እንደ ዕንቁ ይቆጠራል። የዓለም ክብርና መንሠራራት በእሱ ላይ መመሥረቱ ግዴታ ነው። መልካም ጠባይ ሰዎች ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚመሩበትና ወደ ታላቁ መግለጫም የሚደርሱበት መሣሪያ ነው። እርሱ በሰማይ ሠራዊት ቅዱስ ባሕርይ የተጌጠ የታደለ ነው።

በሁሉም ሁኔታዎች ትኩረትህን በፍትሕና በትክክለኝነት ላይ ማድረግ ይገባሃል። በሕቡአተ ቃላት ውስጥ ከእጅግ በጣም ታላቁ ብዕራችን ይህ የላቀ ንግግር ተገልጾ ነበር፦

የመንፈስ ልጅ ሆይ!በፊቴ ከሁሉም ነገር ይበልጥ የተወደደች ፍትሕ ናት፤ እኔን የምትሻ ከሆነ ፊትህን አታዙርባት፤ ምሥጥሬንም አካፍልህ ዘንድ ቸል አትበላት። በእርስዋም እርዳታ በሌሎች ዓይኖች ሣይሆን በራስህ ዓይን ታያለህ፤ በጐረቤትህም ዕውቀት ሣይሆን በራስህ ዕውቀት ታውቀለህና። ምን ማድረግ እንደሚበጅህ፣ ዘወትር በልብህ አሰላስል። በእውነቱ ፍትሕ ለአንተ ሥጦታዬ፣ የፍቅራዊ ደግነቴም ምልክት ናት። እንግዲህ በዓይኖችህ አንፃር አኑራት።

እነዚያ በፍርዳቸው ፍትኸኞችና ትክክለኞች የሆኑት የተቀደሰ ደረጃ ይዘዋል፤ ከፍተኛ ማዕረግም አላቸው፤ የጽድቅና የቀጥተኝነት ብርሃን ከእነዚህ ነፍሶች በድምቀት ያበራል። የዓለም ሕዝቦችና አገሮች ከእነዚህ ከሁለቱ ደማቅ ብርሃኖች እንዳይነፈጉ አጥብቀን ተስፋ እናደርጋለን።

## አራተኛው ታራዝ

ለመታመን ሙብቃትን ይመለከታል። በእውነቱ ይህ በምድር

ለሚኖሩት ሁሉ የደህንነት በር፣ የፍጹም መሐሪውም የክብር ምልክት ነው። እርሱ ከዚያ የሚካፈል በእውነቱ ከሃብትና ከብልጽግና ተካፍሏል። ለመታመን መብቃት ወደ ሕዝቡ እርጋታና ደህንነት የሚመራ እጅግ በጣም ታላቅ በር ነው። በእውነት የእያንዳንዱ ጉዳይ መረጋጋት በዚህ ላይ ተመሥርቷል፣ ይመሠረታልም። የኃይል፣ የታላቅነትና የሃብት ዓለማት በዚህ ብርሃን በርተዋል።

ከቅርብ ጊዜ በፊት እነዚህ ቅዱስ ቃላት ከእጅግ በጣም ከፍተኛው ብዕር ተገልጸው ነበር፡-

*"አሁን በጌታህ፣ የኃያሉ ዞፋን ጌታ በሆነው በአምላክ አስተያየት ለመታመን ስለመብቃትና ስለደረጃዋ እንነግርሃለን።"* ከዕለታት አንድ ቀን ወደ አረንጓዴዋ ደሴታችን ሄድን። በደረስን ጊዜ ወንዞቿ ሲወርዱ፣ ዛፎቿም ለምልመው፣ የፀሐዩም ብርሃን ጨረር በውስጣቸው ሲያንፀባርቅ ተመለከትን። ፊታችንን ወደ ቀኝ በመመለስ፣ በዚያ እጅግ በተቀደሰ፣ በዚያ እጅግ በጣም ከፍተኛ፣ በዚያ የተባረከና እጅግ በጣም የከበረ ሥፍራ ብዕር ለመዘርዘር ኃይል የማይኖራትን፣ የሰው ዘር ጌታ ዓይን ያየውንም ለመተንተን የማትችለውን ዓየን። ከዚያም ወደ ግራ በመዞር፣ ከእጅግ በጣም ከፍተኛው ገነት ውበቶች መካከል አንዱ፣ በብርሃን ምሰሶ ላይ ቆማ፡-

*"እናንተ የምድርና የሰማይ ነዋሪዎች ሆይ! ውበቴን፣ ብርሃኔን፣ ግልፀቴን እና ነፀብራቄን ተመልከቱ፤ በእውነተኛው አምላክ! እኔ ለመታመን መብቃትና ግልፀቷ ውበቷም ነኝ። እኔ ወደእኔ የሚጠጋውን፣ ማዕረጌንና ደረጃዬን የሚያውቀውንና ጠርዜንም አጥብቆ የሚይዘውን ማንኛውንም ሰው እከሰዋለሁ። እኔ የባሃ ሕዝብ እጅግ በጣም ታላቅ ጌጥ፣ በፍጥረት ዓለም ለሚገኙትም ሁሉ የክብር ልብስ ነኝ። እኔ ለዓለም ብልፅግና የላቀ መሣሪያ፣ ለሕዋንም ሁሉ የመድህን አድማስ ነኝ፣ በማለት ከፍ ባለ ድምፅ ስትጣራ አየን። እኛ ሰዎችን ወደፍጥረት ጌታ የሚያቀርባቸውን በዚህ ሁኔታ አውርደንልሃል።"*

የባሃ ሕዝብ ሆይ! በእውነቱ ለመታመን ሙብቃት ለአካላችሁ ከሁሉ የላቀ ልብስ፣ ለእራሶቻችሁም እጅግ በጣም ክቡር ዘውድ ናት። በእርሱ በትእዛዝ ሰጪው፣ ሁሉን በተገነዘበው ፈቃድ አጥብቃችሁ ያዟት።

## አምስተኛው ታራዝ

ለአምላክ አገልጋዮች ደረጃዎች መከላከልንና መጠበቅን ይመለከታል። አንድ ሰው የማንኛውንም ጉዳይ እውነተኛነት ቸል ማድረግ አይገባውም፤ ይልቁንም ትክክልና እውነት የሆነውን መግለጽ ይገባዋል። የባሃ ሕዝብ ለማንም ነፍስ የሚገባውን ዋጋ መከልከል የለባቸውም፤ የእጅ ጥበብ ሙያተኞችን በአክብሮት መያዝ አለባቸው፤ እንደቀድሞውም ሕዝብ አንደበታቸውን በስድብ ማርከስ የለባቸውም።

በዚህ ቀን የእጅ ጥበብ ሙያ ፀሐይ፣ ከምዕራብ አድማስ በላይ እያበራች፣ የኪነ ጥበብም ወንዝ ከዚያ ክፍለ አህጉር ባሕር እየፈሰሰ ነው። በትክክለኝነት መናገርና እንዲህ ያለውን በረከት ማመሥገን ይገባል። በአምላክ ሕይወት! ትክክለኛነት የሚለው ቃል ልክ አንደ ፀሐይ ደምቆና አሸብርቆ ያበራል። በጸጋው ጮራውን (ትክክለኝነትን) በሁሉ ላይ እንዲፈነጥቅ አምላክን እንለምናለን። በእውነቱ እርሱ በነገሮች ሁሉ ላይ ኃይል አለው፤ እርሱ ምን ጊዜም የሁሉን ሰዎች ጸሎቶች የሚመልሰው ነውና።

በእነዚህ ቀናት እውነተኛነትና ቅንነት በውሸት መዳፍ ውስጥ ክፉኛ ተጨንቀዋል፤ ፍትሕም በበደል አለንጋ ተሠቃይታለች። የብልሹነት ጢስ ዓለምን ክፉኛ ስለአበላሸ በማንኛውም አቅጣጫ ከጦር ወታደር ሻለቃዎች በቀር ሊታይ የሚችል ምንም ነገር የለም፤ እንዲሁም ከማንኛውም አገር ከሠይፎች መማታት ድምጽ በቀር ምንም አይሰማም። የእርሱን ኃይል የሚጠቀሙትን ለዓለም ተሐድሶን በሚሰጥና ለአገሮች ሕዝቦች ሰላም በሚያመጣ ተግባር ያጠናክራቸው

ዘንድ እውነተኛውን አምላክ እንማፀናለን።

## ስድስተኛው ታራዝ

ዕውቀት ከአምላክ ደንቅ ሥጦታዎች አንዱ ነው። እያንዳንዱ መገብየት አለበት። አሁን ተገልጸው የሚገኙ የኪነጥበባትና የቁሳዊ መሣሪያዎች፣ ከግምጃ ቤቱ፣ የጥበብና የንግግር እንቁዎች፣ እንዲሁም የዓለም ኪነጥበባትና የእጅ ሥራ ውጤቶች ወደ ብርሃን በመጡበት ብዕር፦ በእርሱ እጅግ በጣም ከፍተኛ ብዕር አማካይነት በመልእክቶቹና በጽላቶቹ ውስጥ ተገልጸው በነበሩት በእርሱ ዕውቀትና ጥበብ ምክንያት ሊገኙ ችለዋል።

በዚህ ቀን የምድር ምሥጢሮች በሰዎች ዓይኖች ፊት ያለሽፋን ተዘርግተዋል። ከመቅጽበት የሚወጡት ጋዜጦች ገጾች በእውነቱ የዓለም መስተዋቶች ናቸው። እነሱ የተለያዩ ሕዝቦችንና ዘሮችን ተግባሮችና ሥራዎች ያንፀባርቃሉ። እነሱ ያንፀባርቋቸዋል እንዲታወቁም ያደርጓቸዋል። እነሱ መስማት፣ ማየትና ንግግር የተሰጣቸው መስተዋቶች ናቸው። ይህ አስደናቂና ኃይለኛ ክስተት ነው። ሆኖም ጸሐፊዎቹ ወደ መጥፎ ስሜትና ፍላጎት ከሚገፋፉት ነገሮች በመላቀቅ በፍትሕና በትክክለኝነት ልብስ የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል። በተቻለ መጠን ሁኔታዎችን መመርመርና ነጥቦችን ማረጋገጥ ከዚያም በጽሑፍ ማስፈር አለባቸው....

(138)

**<u>ካሊማት - ኢ - ፍርዳውስያህ</u>**

በእነዚህ ቀናት ምናልባት የተሳሳቱት ነፍሶች ወደ ዘለዓለማዊው ብልጽግና ወደሚመራው ይደርሱ ዘንድ፣ እያንዳንዱ ሰው አንድነትንና ስምምነትን አጥብቆ መያዝና የአምላክን እምነት ለማስፋፋት በትጋት መሥራት አለበት።

በአጭሩ፣ በተለያዩ የሃይማኖት ቅርንጫፎች መካከል ያለው አለመስማማት ለድክመት መንገድ ከፍቷል። እያንዳንዱ የሃይማኖት ቅርንጫፍ ለራሱ መንገድ መርጧል፤ አንድ የተወሰነ ገመድም አጥብቆ በመያዝ ላይ ነው። ምንም እንኳ ግልጽ በሆነ እውርነትና ድንቁርናውስጥ ያሉ ቢሆኑም፣ በግንዛቤያቸውና በዕውቀታቸውይኩራራሉ። ከእነሱ መካከል አንድ የእስላም እምነት ተከታዮች ነን ባዮች፣ አንዳንዶቻቸው ወደ ሥራ ፈትነትና ወደ መገለል በሚመራ ተግባር የሚዘፈቁ ምሥጢራውያን የሚባሉት ናቸው። በአምላክ እምላለሁ!ይህ የሰውን ደረጃ ዝቅ ያደርጋል፤ በኩራትም እንዲያብጥ ያደርገዋል። ሰው ፍሬ ማፍራት አለበት። ፍሬ የማያፈራ፣ በመንፈሱ[1] አባባል ፍሬ እንደማያፈራ ዛፍ ነው፣ ፍሬ የማያፈራውም ዛፍ የሚጠቅመው ለእሳት ብቻ ነው....

## (139)

### ለውህ - ኢ - ዱኒያ

የአምላክ ሕዝብ ሆይ! አክብሮት ከሁሉም በላይ የሆነ የመልካም ምግባሮች ልዑል ስለሆነ፣ አክብሮትን እንድታሳዩ እመክራችኋለሁ። በአክብሮት ብርሃን የበራ የቀጥተኝነትንም ልብስ የለበሰ የበጀው ነው። በአክብሮት የተላበሰ በእውነቱ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል። ይህን የተበደለውንና ሌሎቻችንን ሁሉ ለመገብየት፣ አጥብቆም ለመያዝ፣ በተግባርም ላይ ለማዋል፣ ትኩረታችንንም በእሱ ላይ ለማድረግ እንደሚያስችለን ተስፋ ተደርጓል። ይህ ከእጅግ በጣም ታላቁ ስም ብዕር የኀረፈ ጽኑ ትእዛዝ ነው....

## (140)

የአምላክ ሕዝብ ሆይ! ለሌሎች መርሖ ለመስጠት ራሳቸውን የሚሰጡ ከዝቅተኛና ከስግብግብ ጠባይ ግፊቶች ነፃ የወጡና በጣም

[1]ኢየሱስ ክርስቶስ

የተጠበቁ ጻድቃን የሆኑ ምሁራን፣ በእርሱ የዓለም እሾት በሆነው ፊት፣ የእውነተኛ ዕውቀት ሰማይ ከዋክብት ናቸው። እነርሱን በአክብሮት መያዝ አስፈላጊ ነው። እነርሱ በእውነቱ በእርጋታ የሚወርዱ የውሃ ምንጮች፣ ደማቅ ብርሃን የሚሰጡ ከዋክብት፣ የተባረከው ዛፍ ፍሬዎች፣ መለኮታዊ ኃይል አስፋፊዎች፣ የመንግሥተ - ሰማይ ጥበብም ውቅያኖሶች ናቸው። እነርሱን የሚከተላቸው ደስተኛ ነው። እንዲህ ያለው ነፍስ በእውነቱ የኃያሉ ዙፋን ጌታ በሆነው አምላክ መጽሐፍ ውስጥ፣ ከእነዚያ መልካም ከሚሆንላቸው ጋር ይቆጠራል....

## (141)

## ኢ ሽ ራ ቃ ት

አምላኬ ሆይ፣ በኃዘን እንደ ዓሣ በአቧራ ላይ ስንደፋደፍ ታየኛለህ። አቤቱ አንተ እርዳታው በሰዎች ሁሉ የሚለመን ሆይ፣ አቤቱ አንተ በወንዶችም በሴቶችም ላይ የሥልጣን ልጓም በመዳፉ ውስጥ የሚገኘው ሆይ፣ አድነኝ፤ በእኔ ላይ ምሕረት ይኑርህ። አሳዛኝ ጉድለቶቼንና ከባድ በደሎቼን በማሰላሰልበት ጊዜ፣ ተስፋ መቁረጥ ከሁሉ አቅጣጫ ይወርድብኛል፣ ቆም ብዬ በበረከት ሰጪነትህ ውቅያኖስ፣ በጸጋህ ሰማይና በፍቅራዊ ርኅራኄህ የቀን ኮከብ ላይ በማተኩርበት ጊዜ ደግሞ፣ የምሕረትህ ሰማይ ደመናዎች ዝናባቸውን የሚያዘንቡብኝና እያንዳንዱም የተፈጠረ ነገር ሐሴት የተመላበትን የምሥራች የሚያካፍለኝ ይመስል ከግራም ከቀኝም ከሰሜንም ከደቡብም የሚሰራጨውን የተስፋ ሽውታ አሸታለሁ። በኃያልነትህ፣ አቤቱ አንተ የቅኖች ዋና ድጋፍና የእነዚያ ወደ አንተ በመቅረብ የሚደሰቱት እሾት የሆንከ ሆይ! በእውነቱ፣ ብዙ ልዩ ልዩ ችሮታዎችህና ቡራኬዎችህ፣ እንዲሁም የጸጋህና የፍቅራዊ ደግነትህ ግልጸቶች ድፍረት ሰጥተውኛል። ያለበለዚያ ፍጹም ምንምነት

የእርሱን፣ በአንድ ቃል፣ ፍጥረትን ወደ መኖር ያመጣውን ስም ከፍ ከፍ ለማድረግ እንዴት ይችላል? ኢምንት ፍጡርም እርሱን ምንም ገለፃ ሊገልፀው፣ እንዲሁም ምን ጊዜም ምንም የምሥጋና ቃል ክብሩን ሊያወድሥ እንደማይችል ያሳየውን ለማወደሥ እንዴት ይችላል? እርሱ ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ ከፍጡሮቹ የመረዳት ችሎታ በላይ ሊለካ በማይቻል ሁኔታ የተከበረ፣ ከአገልጋዮቹ የማሰብ ችሎታም የተቀደሰ ነበር።

ጌታ ሆይ! አንተ ይህን ሕይወት አልባ ሰው በፊትህ አንጻር ታየዋለህ፤ በቸርነትህና በረከት በተመላበት ደግነትህ፣ ከዘለዓለማዊ ሕይወት ጽዋ እንዳይነፈግ አድርገው። ይህን የተሦቃየውን በዙፋንህ ፊት ቆሞ ታየዋለህ፤ ከፊውስህ ውቅየኖስ ወደኋላ አትመልሰው። ምንም እንኳ ከአገልጋይ የሚወጣው ማንኛውም ነገር ከነፍሱ ውስን ወሰኖች ሊያልፍ እንደማይችል፣ ለጌታነትህም እንደማይገባ፣ ለክብርህና ለግርማህም መንበር ብቁ እንደማይሆን ደህና አድርጌ ባውቀውም፣ በሁሉ ጊዜና በሁሉም ሁኔታ አንተን ለማስታወስ፣ ስምህን ከፍ ለማድረግና እምነትህን ለማገልገል እንድታስችለኝ እማፀንናለሁ።

ኃይልህ ይመሥክርልኛል! ምሥጋናህን ለማወደሥ ባይሆን ኖሮ፣ አንደበቴ ምንም አይጠቅመኝም፣ ለአንተ አገልግሎት ለማበርከት ዓላማ ካልዋለ፣ መኖሬም አይረዳኝም። የክብር ዓለምህን ታላቅነት ለማየት ደስታ ባይሆን ኖሮ፣ የማየትን ኃይል ለምን እፈልጋለሁ? እጅግ በጣም ጣፋጭ ድምጽህን ለመስማት ሐሴት ባይሆን ኖሮ፣ መስማት ምን ይጠቅማል?....

(142)

### የመጀመሪያ ኢሽራቅ

የጥበብ የቀን ኮከብ ከአምላክ ቅዱስ ዙር /ዘመን/ አድማስ በላይ በወጣበት ጊዜ ይህን ፍጹም ክቡር ንግግር አሰማ፦ እነዚያ ሃብት ያላቸው ሥልጣንና ኃይልም የተሰጣቸው ለሃይማኖት እጅግ

ጥልቅ አክብሮት ማሳየት አለባቸው። በእውነቱ፣ ፈሪሐ-እግዚአብሔር ሰውን መልካሙን አጥብቆ እንዲይዝ ክፉውንም እንዲሸሽ ስለሚያደርገው፣ ሃይማኖት ለዓለም ሕዝቦች ጥበቃና የተሟላ ኑሮ ብሩህ ብርሃንና የማይደፈር ምሽግ ነው። የሃይማኖት መብራት ቢጨልም ብጥብጥና ውዥንብር ይከተላሉ፣ የትክክለኝነትና የፍትሕ፣ የእርጋታና የሰላም ብርሃኖች ብርሃን መስጠታቸውን ያቆማሉ። ለዚህም እያንዳንዱ እውነተኛ የማስተዋል ኃይል ያለው ሰው ይመሠክራል።

## ሁለተኛው ኢሽራቅ

ለሰው ዘር ጥበቃ ከሚጠቅሙት ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ፍቱን የሆነውን አነስተኛውን ሰላም እንዲመሠርቱ የሰውን ዘር ሁሉ አዘናል። ይህ የሁሉን ሕዝቦችና አገሮች ደህንነትና የተሟላ ኑሮ ሊያረጋግጥ የሚችል ልዑል መሣሪያ ስለሆነ፣ የዓለም ነገሥታት፣ በአንድ ላይ ተስማምተው አጥብቀው መያዝ አለባቸው። እነርሱ፣ በእውነቱ፣ የአምላክ ኃይል ገላጮች፣ የሥልጣኑም የቀን ምንጮች ናቸው። በጸጋው፣ በዚያ ለሕዝቦቻቸው ደህንነት በሚጠቅመው ሥራ ይረዳቸው ዘንድ ፍጹም ኃያሉን እንማፀናለን። ይህን ጉዳይ በሚመለከት ከዚህ በፊት ሙሉ መግለጫ በክብር ብዕር ተሰጥቷል፤ በዚህ መሠረት የሚሠሩ የታደሉ ናቸው።

## ሦስተኛው ኢሽራቅ

ለዓለም የሕይወት ምንጭ በመሆናቸው፣ እያንዳንዱ ሰው የአምላክን ቅዱሳት ትእዛዛት ማክበር አለበት። የመለኮታዊ ጥበብ ሰማይ የሚበራው በሁለቱ የምክክርና የርኅራኄ የብርሃን ምንጮች ነው፤ እንዲሁም የዓለም ሥርዓት ድንኳን የተተከለው በሁለቱ የሽልማትና የቅጣት ምሰሶዎች ላይ ነው።

## አራተኛው ኢሽራቅ

በዚህ ግልጸት ግልጸቱን ድል አድራጊ ሊያደርጉት የሚችሉት ሠራዊቶች የአስመሥጋኝ ተግባሮችና የቀጥተኛ ጠባዮች ሠራዊቶች ናቸው። የእነዚህ ሠራዊቶች መሪና አዛዥ ምን ጊዜም፣ ፈሪሐ-እግዚአብሔር፣ ሁሉን ነገሮች የሚያቅፈውና ሁሉን ነገሮች የሚገዛው ፈሪሐ-እግዚአብሔር ነው።

## አምስተኛው ኢሽራቅ

መንግሥታት ከእነዚያ ከሚያስተዳድሩዋቸው ሕዝቦች ሁኔታዎች ጋር ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ማስተዋወቅ፣ እንደየ ዝንባሌያቸውና እንደየ ብቃት ደረጃቸው ሥራ መስጠት አለባቸው። ከሐዲው የታማኙን ቦታ እንዳይቀማ፣ የመታመን ብቃት ባለውም ፈንታ ዘራፊው እንዳይገዛ ይህን ጉዳይ ከሁሉ በበለጠ ጥንቃቄ እንዲያስብበት እያንዳንዱ ገዢና ንጉሥ ታዟል። ከዚህ በፊት በዚህ በታላቁ እሥር ቤት ያስተዳድሩ ከነበሩት ባለሥልጣኖች መካከል፣ ለአምላክ ምሥጋና ይግባውና፣ አንዳንዶች በፍትሕ ያጌጡ ነበሩ፤ ከሌሎቹ ደግሞ፣ ለመጠጊያ ወደ አምላክ እንሸሻለን። ምናልባት የእምነትንና ለመታመን የመብቃትን ፍሬ እንዳይነፈጉ፣ ወይም ከትክክለኝነትና ከፍትሕ ብርሃን እንዳይከለከሉ፣ እያንዳንዳቸውንና ሁላቸውን ይመራ ዘንድ አንዱን እውነተኛ አምላክ እንማፀናለን።

## ስድስተኛው ኢሽራቅ

በሰው ልጆች መካከል ኅብረትና ስምምነት ነው። ጊዜ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የአንድነት ብርሃን መለኮታዊ ጮራዋን በዓለም ላይ ፈንጥቃለች፤ ለዚያ አንድነትም መዳበር ከሁሉ የበለጠው መሣሪያም የዓለም ሕዝቦች አንዱ የሌላውን ጽሑፎችና ንግግር መረዳት ነው። በአለፉት መልዕክቶች ከእነዚያ አሁን ካሉት ቋንቋዎች አንዱን እንዲመርጡ፣ ወይም አዲስ እንዲጠቀሙ፣ በዚሁ ዓይነት

የጋራ ፊደል እንዲመርጡና በሁለቱም (በተመረጡት) በዓለም ትምህርት ቤቶች ሁሉ ትምህርት መሰጠት እንዳለበት የቤተ ፍትሕ ባለ እደራዎችን አዘን ነበር። በዚህ ሁኔታ ዓለም እንደ አንድ አገርና እንደ አንድ ቤት ትቆጠራለች። እጅግ በጣም ድንቅ የዕውቀት ዛፍ ፍሬ ይህ የተከበረ ቃል ነው፡- ሁላችሁ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች፣ የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ። ማንም ሰው አገሩን በመውደድ አይመካ፣ ይልቁንም መሰሉን በመውደዱ ይመካ። ይህን በሚመለከት ከዚህ በፊት ለዓለም በአዲስ መገንባትና ለብሐሮች አንድነት የሚጠቅመውን ገልጸናል። ለዚህ የሚበቁ የተባረኩ ናቸው። በዚህ መሠረት የሚሠሩ የተባረኩ ናቸው።

## ሰባተኛው ኢሽራቅ

የክብር ብዕር ስለ ልጆች ትምህርትና አስተዳደግ እያንዳንዱን ይመክራል። በወህኒ ቤቱ ከተማ በደረስንበት ጊዜ የአምላክ ፈቃድ የገለጸውንና በእጅግ በጣም ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ[1] የመዘገበውን ተመልከቱ። እያንዳንዱ አባት ወንድና ሴት ልጁን የማንበበንና የጽሕፈትን ጥበብ፣ እንዲሁም በቅዱሱ መልእክት የሠፈሩትን ሁሉ እንዲያስተምር ታዟል። ከእርሱ፣ የታዘዘውን ከማይቀበለው፣ ሃብታም ከሆነ፣ ለትምህርታቸው አስፈላጊ የሆነውን ባለአደራዎቹ፣ ከእርሱ መቀበል አለባቸው፤ ካልሆነ ሃላፊነቱ የቤተ-ፍትሕ ይሆናል። በእውነቱ፣ ለድሆችና ለችግሮኞች መጠለያ አድርገነዋል። እርሱ ልጁን ወይም የሌላውን ልጅ የሚያሳድግ፣ ልክ የራሴን ልጅ እንዳሳደገ ይቆጠራል፤ ዓለምን የሸፈነው ክብሬ፣ ፍቅራዊ ደግነቴና ምሕረቴ በእርሱ ላይ ይረፍ።

## ስምንተኛው ኢሽራቅ

በክብር ብዕር አሁን የተጻፈው ይህ ጽሑፍ ከእጅግ በጣም

[1]ኪታቢ አቅዳስ - እጅግ በጣም ቅዱስ መጽሐፍ

ቅዱስ መጽሐፍ ጋር ይቆጠራል፦ የአምላክ ቤተ-ፍትሕ ሰዎች የሕዝቡ ጉዳዩች ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። እነርሱ፣ በእውነቱ፣ በእርሱ አገልጋዮች መካከል የአምላክ ባለ አደራዎች፣ በእርሱም አገሮች ውስጥ የሥልጣን የቀን ምንጮች ናቸው።

የአምላክ ሕዝብ ሆይ! ዓለምን የሚያሠለጥነው ፍትሕ ነው፤ በሁለቱ የሽልማትና የቅጣት ምሰሶዎች ተደግፎ የቆመ ነውና። እነዚህ ሁለቱ ምሰሶዎች ለዓለም የሕይወት ምንጮችናቸው። ለእያንዳንዱ ቀን አዲስ ችግር፣ ለእያንዳንዱም ችግር ተስማሚ መፍትሔ ስላለው፣ አባላቱ እንደየጊዜው ችግሮችና ፍላጎቶች እርምጃ ይወስዱ ዘንድ እንዲህ ያሉት ጉዳዮች ወደ ቤተ-ፍትሕ መቅረብ አለባቸው። አነዚያ፣ ለአምላክ ብለው፣ እምነቱን ለማገልገል የሚነሡ፣ ከማይታየው መንግሥት መለኮታዊ ግልጸት ተቀባዮች ናቸው። ሁሉም ለእነርሱ መታዘዝ አለበት። የአገር ጉዳዮች ሁሉ ለቤተ-ፍትሕ መቅረብ አለባቸው፤ የማምለክ ተግባሮች ግን አምላክ በመጽሐፉ ውስጥ በገለጸው መሠረት መፈጸም አለባቸው።

የባሃ ሕዝብ ሆይ! እናንተ የአምላክ ፍቅር የንጋት ቦታዎች፣ የፍቅራዊ ደግነቱም የቀን ምንጮች ናችሁ። አንደበቶቻችሁን ማንንም ነፍስ በመስደብና በማንቋሸሽ አታርክሱ፤ ዓይኖቻችሁንም ተገቢ ካልሆነው ነገር ጠብቋቸው። ያላችሁን ነገር አቅርቡ። በተስማሚ ሁኔታ ከተወሰደ፣ ዓላማችሁ ተፈጸመ፣ ካልሆነ መከራከሩ ከንቱ ነው። ያንን ነፍስ ለራሱ ተውትና ወደ ጌታው፤ ወደ ጠባቂው፣ በገዛ ራሱም ወደሚኖረው ዞሩ። የመለያየትና የጥላቻ ምክንያት መሆን ቀርቶ፣ የኃዘን ምክንያት እንኳ አትሁኑ። በእርሱ የርኅራኄ ምሕረቶች ዛፍ መጠለያ ውስጥ እውነተኛ ትምህርት እንደምታገኙና አምላክ በሚሻው መሠረት እንደምትሠሩ በጣም ተስፋ ተደርጓል። እናንተ ሁላችሁም የአንድ ዛፍ ቅጠሎች የአንድ ውቅያኖስም ጠብታዎች ናችሁ።

## ዘጠነኛው ኢሽራቅ

ከአምላክ ቅዱስ ፈቃድ ሰማይ እንደተገለጸው የሃይማኖት ዓላማ በዓለም ሕዝቦች መካከል አንድነትንና ስምምነትን ለመመሥረት ነው፤ የመከፋፈልና የጥል ምክንያት አታድርጉት። የአምላክ ሃይማኖትና መለኮታዊ ሕጉ በሰዎች መካከል ለአንድነት ብርሃን መንጋት ከሚያገለግሉት ጠቃሚ ነገሮች መካከል እጅግ በጣም ኃይለኞችና ከሁሉም ይበልጥ አስተማማኝ መሣሪያዎች ናቸው። የዓለም ዕድገት፣ የአገሮች መልማት፣ የሕዝቦች እርጋታና የእነዚያ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ ሰላም በአምላክ መሠረታዊ መመሪያዎችና ትእዛዞች መካከል የሚገኙ ናቸው። ሃይማኖት ሰውን ከሥጦታዎች ሁሉ እጅግ በጣም ክቡር የሆነውን ሥጦታ ያጎናጽፋል፤ የብልጽግናን ጽዋ ይጋብዛል፤ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያካፍላል፤ የማይጠፉ ጥቅሞችንም በሰው ዘር ላይ ያዘንባል። የዓለም መሪዎችና ገዢዎች፣ በተለይም የአምላክ ቤተ- ፍትሕ ባለ አደራዎች፣ የማዕረጉን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ጥቅሞቹን ለማስፋፋትና ደረጃውን በዓለም ፊት ከፍ ከፍ ለማድረግ ኃይላቸው የሚፈቅደውን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው። እንዲሁም ስለሕዝቦቻቸው ሁኔታዎች መጠየቅ፣ በግዛታቸውም ውስጥ ስለሚገኙ የተለያዩ ኅብረተ-ሰቦች ጉዳዮችና እንቅስቃሴዎች በደንብ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ምናልባት ከዚህ ዓለም መለያየትን አስወግደው በስምምነት ብርሃን ያበሩዋት ዘንድ ራሳቸውን እንዲያነሣሱ የአምላክ ኃይል ገላጮች ለሆኑት ለምድር ነገሥታትና ገዢዎች ጥሪ እናደርጋለን...

(143)

## ለውሂ - ኢ - ህክማት

የዓለም ሕዝቦች ሆይ! ክፉውን ሁሉ ተው፣ መልካም የሆነውን አጥበቃችሁ ያዙ። ለሰው ዘር ሁሉ ብሩህ ምሳሌዎች፣

በሰዎችም መካከል እውነተኞች የአምላክ ባሕርያት ማስታወሻዎች ለመሆን ተጣጣሩ። እምነቴን ለማገልገል የሚነሣው ጥበቤን ያንጸባርቃል፤ ድንቁርናንም ከምድር ለማጥፋት ሁሉን ጥረት ያደርጋል። በምክክር ተሳሰሩ፣ በሃሣብ አንድ ሁኑ። እያንዳንዱ ንጋት ከምሽቷ የተሻለች እያንዳንዱም ነገ ከትናንትናዋ የለጸገች ትሁን። ለሰው ተገቢ የሆነው ዋጋ፣ በአገልግሎትና በመልካም ምግባር እነጂ በብልጽግናና በሃበት ትዕይንት አይደለም። ቃሎቻችሁ ከእውነት ከራቁ ከንቱ እምነቶችና ከዓለማዊ ፍላጎቶች የጠሩ፣ ተግባሮቻችሁም ከአታላይነትና ከጥርጣሬ የጸዱ ዕንዲሆኑ ተመከሩ። የውድ ሕይወታችሁን ሃብት ከፉና ርኩስ ፍቅርን በማባረር አታባክኑ፣ ጥረቶቻችሁም የግል ጥቅማችሁን በማዳበር እንዲያልፉ አታድርጉ። በሃብታምነት ቀናችሁ ለጋሦች ሁኑ፣ በእጦት ጊዜም ትዕግሥተኞች ሁኑ። ችግር በድሎት ይተካል፣ ከኃዘንም ሐሴት ይከተላል። ከሥራ ፈትነትና ከስንፍና ተጠንቀቁ፤ ለሰው ዘር ለወጣቱም ሆነ ለሽማግሌ፣ ለትልቅም ሆነ ለትንሽ የሚጠቅመውን አጥብቃችሁ ያዙ። በሰዎች መካከል አለመግባባትን እንዳትዘሩ ወይም በንጹሐንና በደስተኞች ልቦች የጥርጣሬ እሾሆች እንዳትተክሉ ተጠንቀቁ።

እናንተ የጌታ ተወዳጆች ሆይ! የጠራውን የፍቅር ጅረት የሚበክል ወይም ጣፋጩን የወዳጅነት ሽታ የሚያጠፋ ነገር አትፈጽሙ። በጌታ ትክክለኝነት! እናንተ የተፈጠራችሁት እያንዳንዳችሁ ለሌላው ፍቅርን እንጂ ክፋትንና ንትርክን እንድታሳዩ አልነበረም። ራሳችሁን በማፍቀር አትኩራሩ፣ ፍጡራን ወንድሞቻችሁን በማፍቀር እንጂ፤ አገራችሁን በማፍቀር አትመኩ፤ ሁሉን የሰው ዘር በማፍቀር እንጂ። ዓይኖቻችሁ ንጹኃን፣ እጆቻችሁ ታማኞች አንደበቶቻችሁ እውነተኞች፣ ልቦቻችሁም የተገለጸላቸው ይሁኑ። በባሃ ምሁራን የሆኑትን ሰዎች ደረጃ ዝቅ አታድርጉ፣ እንዲሁም የእነዚያን በመካከላችሁ ፍትሕ የሚሰጡትን ገዢዎች ማዕረግ አታዋርዱ። እምነታችሁን በፍትሕ ሠራዊት ላይ አድርጉ፤

የጥበብን የብረት ልብስ ልበሱ፤ ጌጣችሁ ይቅር ባይነትና ምሕረት፣ እንዲሁም የእነዚያን የአምላክ በጣም ተወዳጆች የሆኑትን ልቦች የሚያስደስቱ ነገሮች ይሁኑ...

(144)

## አስል - ኢ - ኩሉል - ከሃይር

በተከበረው፣ በእጅግ በጣም ከፍተኛው በእግዚአብሔር ስም!

የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ በአምላክ መተማመን፣ ለትእዛዙ መገዛት፣ በቅዱስ ፈቃዱና ፍላጎቱም መርካት ነው።

የጥበብ ሕልውናናፈሪሐ-እግዚአብሔር፣ የቁጣውና የቅጣቱ ከፍተኛ ፍርሐት፣ ስለመጪው ፍርዱና ትእዛዙ ጭንቀት ነው።

የሃይማኖት ሕልውና ያንን ጌታ የገለጸውን መመሥከር፣ እርሱ በታላቅ መጽሐፉ የደነገገውም መከተል ነው።

የክብር ሁሉ ምንጭ ጌታ የሰጠውን ማንኛውንም ነገር መቀበል፣ በዚያ አምላክ በአዘዘውም መርካት ነው።

የፍቅር ሕልውና ሰው ልቡን ወደ ተወዳጁ ማዞር፣ ከእርሱም በቀር ከሌላው ነገር ሁሉ ራሱን ማለያየት፣ ከዚያ የጌታው ፍላጎት ከሆነው በቀር ሌላ ምንም አለመፈለግ ነው።

እውነተኛ ማስታውስ የጌታን፣ የፍጹም ተወዳሹን ስም ማንሣትና ከእርሱም በቀር ሌላውን ማንኛንም ነገር መርሳት ነው።

እውነተኛ መተማመን አገልጋዩ ሙያውንና የዚህን ዓለም ሥራውን መከታተል፣ የአገልጋዮቹ ሁሉ ዕድል በእጆቹ ውስጥ ስለሆኑ፣ ጌታን አጥብቆ መያዝ፣ ከእርሱም ጸጋ በቀር ሌላ ምንም አለመፈለግ ነው።

የመላቀቅ ህልውና ሰው ፊቱን ወደ ጌታው መንበሮች ማዞር፣ እርሱ ዘንድ መግባት፣ ገጽታውን መመልከትና እንደ ምሥክር በፊቱ

መቆም ነው።

የመረዳት ሕልውና የራስን ድህነት መመሥከር፣ ለጌታው፣ ለሉዓላዊው፣ ጸጋ ለተመላው፣ ፍጹም ኃይል ለተመላው ፈቃድ መገዛት ነው።

የድፍረትና የኃይል ምንጭ የአምላክን ቃል ማስፋፋት፣ በፍቅሩም ጽኑነት ነው።

የመቸር ሕልውና አገልጋዩ የጌታውን በረከቶች ማውሳት፣ በሁሉም ጊዜና በሁሉም ሁኔታ ለእርሱ ምሥጋና ማቅረብ ነው።

የእምነት ሕልውና የንግግር ማነስና የተግባሮች ብዛት ነው፤ እርሱ ከተግባሮቹ ንግግሩ የሚበዛ፣ ከመኖሩ ሞቱ እንደሚሻል በእርግጥ እወቁ።

የእውነተኛ ደህንነት ሕልውና ዝምታ፣ የነገሮችን የመጨረሻ ዓላማ መመልከትና ዓለምን መተው ነው።

የትልቅነት መጀመሪያ ሰው ሃብቱን ለራሱ፣ ለቤተሰቡና በእምነቱ ውስጥ ለሚገኙት ድሆች ጥቅም ሲያውል ነው።

የሃብት ሕልውና እኔን ማፍቀር ነው፤ የሚወደኝ የሁሉ ነገሮች ባለቤት ነው፤ እርሱ የማይወደኝ ደግሞ በእርግጥ ከድሆችና ከችግረኞች ጋር ይቆጠራል። ይህ ያ የክብርና የግርማ ጣት የገለጸው ነው።

የክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ ሰው ከጌታው መዞርና ልቡን የአምላክ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ማድረግ ነው።

እጅግ በጣም አቃጣይ እሳት የአምላክን ምልክቶች መጠራጠር፣ እርሱ የገለጸውን በከንቱ መከራከር፣ እርሱን መካድና ራስህን በኩራት እፊቱ ማቅረብ ነው።

የዕውቀት ሁሉ ምንጭ፣ ክብሩ ይስፋና፣ የአምላክ ዕውቀት ነው፤ ይህም በመለኮታዊ ክስተቱ ዕውቀት አማካይነት በቀር ሊደረስበት አይቻልም።

የውርደት ሕልውና ከመሐሪው ጥላ ሥር መውጣትና

የከፋውን መጠለያ መሻት ነው።

የሥሕተት ምንጭ በአንድ እውነተኛ አምላክ አለማመን፣ በእርሱ በቀር በሌላ በማንኛውም ነገር ላይ መተማመንና ከትእዛዙ መሸሽ ነው።

እውነተኛ ውድቀት የዚያ ስለራሱ ምንነት በፍጹም ድንቁርና ቀኖቹ ያለፉበት ነው።

የገለጽንልህ ሁሉ ሕልውና ፍትሕ ነው፤ ሰው ከእውነት ከራቀ ከንቱ እምነትና በጭፍን ከመከተል ራሱን ነፃ እንዲያወጣ፣ የእርሱን ድንቅ የእጅ ሥራ በአንድነት ዓይን እንዲያይና፣ ነገሮችን ሁሉ በምርምር ዓይን እንዲመለከት ነው።

ጌታን፣ አምላክህን አመሥጋኝ ትሆን ዘንድ፣ በዚህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል ትደሰት ዘንድ፣ በዚህ ሁኔታ አስተምረንሃል፣ የጥበብንም ቃላት ገልጸንልሃል።

(145)

ማንም የጥበብ ሰው በቃላት አማካይነት በቀር ዕውቀቱን ለማሳየት አይችልም። ይህም በጥንት ጊዜያቱም ሆነ በቅርብ ጊዜያቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እንደተረጋገጠው፣ የቃላትን ጠቃሚነት ያሳያል። ምክንያቱም የዓለም ሕዝብ በእንዲህ ያለ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው በእርሱ ኃይልና ቀስቃሽ መንፈስ ነውና። ከዚህም በላይ ቃላትና ንግግሮች የሚመስጡ፣ ጠልቀውም የሚገቡ መሆን ይኖርባቸዋል። ሆኖም ሙሉ በሙሉ ለአምላክ ተብሎ ካልተነገረ፣ ለወቅቱና ለሕዝቡ ፍላጎቶች ተገቢ ግንዛቤዎች ካልሰጠ ምንም ቃል በሁለቱ ባሕርያት አይሞላም።

ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፦ የሰው ንግግር የራስን የመቀስቀስ ኃይል ለማስተላለፍ የሚፈልግና መመጠን የሚያስፈልገው ሕልውና ነው። ስለኃይሉ ደግሞ፣ ይህ መጠኑ በልዝብነቱ መጠን ይለካል፤ ይህም በተራው በተላቀቁና በንጹኃን ልቦች ይወሰናል።

ስለመጠኑም ቢሆን፣ ይህ በቅዱሳት መጻሕፍትና በመልእክቶች እንደታዘዘው፣ ከብልህነትና ከጥበብ ጋር መጣመር ይኖርበታል።

እያንዳንዱ ቃል መንፈስ ተሰጥቶታል፤ እያንዳንዱ ቃል የሚፈጥረው ስሜት በግልጽ የታወቀ ስለሆነና ሰው ሊገነዘበው ስለሚችል፣ ስለዚህ ተናጋሪው ወይም የሚያስረዳው ሰው በተስማሚው ጊዜና ቦታ ቃሎቹን በጥንቃቄ ማስተላለፍ ይኖርበታል። ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፡- አንዱ ቃል በእሳት ሌላው ደግሞ በብርሃን ይመሰላል፤ ሁለቱም የሚያደርጉት ተጽዕኖ በዓለም ላይ ግልጽ ነው። ስለዚህ የሰው ልጆች በዚያ ያድጉና ይቀደሱ ዘንድ፣ እውነተኛ የመረዳትና የቅድሰና ደረጃ ለሆነው፣ ለሰው መኖር የመጨረሻ ግብ ይበቁ ዘንድ፣ የተገለጸለት የጥበብ ሰው ከሁሉ አስቀድሞ እንደወተት በለሰለሱ ቃላት መናገር ይገባዋል። እንዲሁም እንዲህ ይላል፡- አንዱ ቃል በዕውቀት የጽጌረዳ የአትክልት ቦታ የሚገኙትን ለጋና ታዳጊ ዛፎች እንዲለመልሙና እንዲፋፉ በሚያደርግ የፀደይ ወራት ሲመሰል፣ ሌላው ቃል ደግሞ ልክ እንደ አደገኛ መርዝ ነው። የቃላቱ ጣፋጭነት ሁሉን ሰው ወደዚያ ለሰው ደረጃ ወደሚገባው እንዲደርስ ያደርገው ዘንድ፣ ጥንቁቁ የጥበብ ሰው በላቀ ለዘብታና ትዕግሥት መናገር ይገባዋል....

## (146)

### የቫፋ ምዕራፍ /ሱሪ - ኢ - ቫፋ/

እርሱ ሊረዳኝ የሚችልና የእነዚህን የእምነተ-ቢስ ነፍሶችን ሠይፎች የሚመክትልኝ ሰው ወዴት ነው? የአምላክን ቃላት በራሱ ዓይኖች ዓይቶ ከምድር ሕዝቦች አስተሳሰቦችና ግምቶች ራሱን የሚያላቅቅ ባለ ጥልቅ የማስተዋል ችሎታ ወዴት ነው?

አገልጋይ ሆይ! የማይረዱትን እንዳያስተባብሉ የአምላክን አገልጋዮች አስጠንቅቃቸው። እንዲህ በል፡- ለማንም ያልተገለጸው ይገለጽላችሁ ዘንድ የእውነተኛ መረዳትን በሮች ለልቦቻችሁ

እንዲከፍትላችሁ አምላክን ተማፀኑ። በእውኑቱ፣ እርሱ ሰጪው፣ ይቅር ባዩ፣ ሩኅሩኅ ነውና....

(147)

**ለውሂ-ኢ- ሰይድ-ኢ-ምህዲይ-ኢ-ዳሃጂ**

የተቀደሱ ነፍሶች ስለማስተማር ዘዴዎች በልቦቻቸው ማውጣት ማውረድና ማሰላሰል አለባቸው። በንግግራቸው ወቅት ሁኔታው ሲያስፈልግ መለኮታዊ ጥቅሶች ለመጥቀስ ይችሉ ዘንድ፣ ከመንግሥተ-ሰማያዊ ቅዱሳት መጻሕፍት ለተለያዩ አጋጣሚዎች የሚስማሙ ድንቅ ጥቅሶች በቃላቸው መያዝ አለባቸው፤ እነዚህ ቅዱሳት ኃረጎች እጅግ በጣም/ኃይለኛ/ ፍቱን መድኃኒቶች፣ እጅግ በጣም ታላቅና እጅግ በጣም ኃያል ጠልሰም ያላቸው ናቸውና። የማግባባት ኃይላቸው እጅግ ፍቱን በመሆኑ ሰሚው ለማወላወል ምክንያት አይኖረውም። በሕይወቴ እምላለሁ! ይህ ግልጸት ታላቅ ኃይል የተጎናጸፈ በመሆኑ፣ ለሁሉም የምድር ወገኖችና ዘሮች እንደሚዛን ያገለግላል። ሰው ቆም ብሎ በጥንቃቄ ቢያሰላስል፣ ለማንም ሰው መሸሻ እንደሌለው፣ ሊኖርም እንደማይችል ይረዳል....

**ከሌሎች መልዕክቶች**

(148)

እንዲህ በል፡- የገዢዎች፣ የምሁራንና የጠቢባን ሠራዊት ሆይ! የተስፋ ቃል የተሰጠለት ቀን መጥቷል፤ የሠራዊት ጌታም ተከስቷል። ስለዚህ ስለላቀው የደስ ደስ በታላቅ ሐሴት ተደሰቱ። እንግዲህ በጥበብና በንግግር ኃይል እርዱት። እርሱ ሁልጊዜ “በእውነቱ፣ ከእኔ ከሁሉን አዋቂው፣ ከጠቢቡ በቀር ሌላ አምላክ የለም” በማለት ያወጀው እንዲህ ያዛችኋል።

ክብሩ በአንተ ላይ፣ በእነዚያ ከአንተ ጋር በሚገኙትም ላይ፣

በሚወዱህም ላይ፣ ይህን ኃያል፣ ይህን የላቀ ግልጸት ከፍ ከፍ በማድረግ ለምትናገራቸው ቃላት ጆሯቸውን በሚሰጡትም ላይ ይረፍ።

(149)

ሰው እንደ ዛፍ ነው። በፍሬ ያጌጠ ከሆነ ለምሥጋናና ለሞገሥብቁ ሆኗል፤ ለዘለዓለምም እንዲሁ ይሆናል። ያለበለዚያ ፍሬ የማይሰጥ ዛፍ የሚስማማው ለእሳት ብቻ ነው። የሰው ዘር ዛፍ ፍሬዎች፣ ምርጥ፣ እጅግ የሚፈለጉና በጣም የሚወደዱ ናቸው። ከእነሱም መካከል ትክክለኛ ጠባይ፣ የጽድቅ ምግባራትና መልካም ንግግር ናቸው። የምድራዊ ዛፎች የፀደይ ወራት በየዓመቱ የሚሆን ሲሆን፣ የሰው ዘር ዛፎች ፀደይ ደግሞ፣ ክብሩ ይስፋና በአምላክ ቀናት ይመጣል። በዚህ በመለኮታዊ ፀደይ ወራት ወቅት የሰው ዘር ሕይወት ዛፎች በተጠቀሱት ፍሬዎች ቢያጌጡ፣ የፍትሕ ብርሃን ነጸብራቅ፣ በእርግጥ፣ የምድርን ነዋሪዎች ሁሉ በአበራና እያንዳንዱም ሰው በእርሱ የሰው ዘር ሁሉ ዓላማ በሆነው ጠለላ ሰጭ ጥላ ሥር በእርጋታና በእርካታ በኖረ ነበር። ለእነዚህ ዛፎች የሚሆነው ውሀ በዓለም ተወዳጅ የተነገሩት የተቀደሱ ቃላት የሕይወት ውሃ ነው። እንዲህ ያሉት ዛፎች በአንድ ጊዜ ይተከሉና በሚቀጥለው ደግሞ፣ በመለኮታዊ ምሕረት ዝናብ መዝነብ አማካይነት ቅርንጫፎቻቸው ሰማያት ይደርሳሉ። ነገር ግን የደረቀ ዛፍ ለምንም መጠቀስ በቅቶ ከቶ አያውቅም፣ ለወደፊቱም አይበቃም።

እርሱ የከፍተኛ ጥረት ልብስ የተላበሰና ይህን እምነት ለማገለገል የተነሣው ታማኝ ሰው ደስተኛ ነው። እንዲህ ያለው ነፍስ በእውነቱ ተፈላጊውን ግብ ተቀዳጅቷል፣ የተፈጠረበትንም ዓላማ ተገንዝቧል። ነገር ግን ልክ እንደ ደረቁ ቅጠሎች በአቧራ ላይ ለወደቁት አመጸኞች እልፍ ጊዜ ወዮላቸው። ሳይቆይም የሞት አውሎ ነፋስ ወዲያ ወደ ታዘዘላቸው ሥፍራ ይወስዳቸዋል። ያለ ምንም

ዕወቀት መጡ፣ ያለ ምንም ዕውቀት ሲያውደለድሉ ቆይተው ያለ ምንም ዕውቀት ወደ መኖሪያቸው ተመለሱ።

ዓለም እነዚህን፡- ተጠንቀቁ፣ እኔ አላፊ ነኝ፣ ውጪአዊ መልኮቼና ቀለሞቼም እንዲሁ ናቸው። በውስጤ ስለታቀዱትም ለውጦችና አጋጣሚዎች በማስተዋል ከአንቅልፋችሁ እንድትነቁ ሁኑ፣ የሚሉትን ቃላት ያለማቋረጥእያወጀች ነው። ሆኖም ለማየት የሚያይ ዓይን፣ ለመስማትም ሰሚ ጆሮ የለም።

## ከአብዱል-ባሃ ጽሑፎች

(150)

የዓለም ሕዝቦች ሆይ! የእውነት ፀሐይ መላውን ምድር ለማብራት፣ የሰውንም ኅብረተ-ሰብ መንፈሳዊ ለማድረግ ወጥታለች። ውጤቶችዋና ፍሬዎችዋ ተመሥጋኞች ናቸው፤ ከዚህ ጸጋ የሚገኙ ቅዱስ ምልክቶች ብዙ ናቸው። ይህ ያልተቀየጠ ምሕረትና ፍጹም ንጹህ ቸርነት ነው፤ ለዓለምና ለሕዝቦችዋ ሁሉ ብርሃን ነው፤ ይህ ስምምነትና ወዳጅነት፣ ፍቅርና ኅብረት ነው፤ በእውነቱ ይህ ርኅራኄና አንድነት፣ የባዕድነትም ማከተሚያ ነው፤ ይህ ሙሉ በሙሉ በክብርና በነፃነት፣ በምድር ላይ ከሚኖሩት ሁሉ ጋር አንድ መሆን ነው።

የተባረከው ውበት፡- እናንተ ሁላችሁ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች፣ የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ ይላል። በዚህ ዓይነት ይህንን የሕያውን ዓለም በአንድ ዛፍ፣ ሕዝቦቹንም በአበቦቹ በፍሬዎቹም መሰላቸው። ቅርጫፉ ማበብ፣ ቅጠሉና ፍሬውም መለምለም ያስፈልጋቸዋል፣ የቅጠልና የአበባ መለምለም፣ የፍሬውም መጣፈጥ በዓለም ዛፍ ክፍሎች ሁሉ እርስ በርስ ግንኙነት ይወሰናል።

በዚህ ምክንያት የሰው ዘሮች ሁሉ እርስ በርሳቸው በኃይል መደጋገፍና ዘለዓለማዊ ሕይወትን መሻት አለባቸው፤ በዚህም ምክንያት የአምላክ አፍቃሪዎች በዚህ በምድራዊ ዓለም፣ በዚያ በሚታዩና በማይታዩት ዓለማት መሐሪው ንጉሥ የተላኩ ምሕረቶችና ቡራኬዎች መሆን አለባቸው። የማየት ኃይላቸውን ያነጹና የሰውን ዘር ሁሉ እንደ ሕያው ዛፍ ቅጠሎችና አበባዎች እንደ ፍሬዎቹም ይመልከቱ። በሁሉ ጊዜ፣ ለአንድ ሰው ፍቅር፣ ርኅራኄና አስተዋይነት የመላበት እርዳታ ለመስጠት፣ ለአንድ ወንድማቸው ደግ ነገር ለመሥራት ያስቡ። ማንንም እንደ ጠላታቸው፣ ወይም ክፉ እንደ

ሚመኙላቸው አይመልከቱ፤ ይልቁንም ባዕዱን እንደ ቅርብ ወዳጅ፣ እንግዳውን እንደጓደኛ በመቁጠር፣ ከአጉል ጥላቻ በመራቅ፣ ምንም ወሰን ሳያበጁ የሰውን ዘር ሁሉ እንደ ወዳጆቻቸው ያስቡ።

በዚህ ቀን በጌታ ደጀሰላም የሚመረጠው ያ የታማኝነትን ጽዋ የሚያሳልፈው፣ በጠላቶቹም ላይ እንኳ ሳይቀር፣ የችሮታን ዕንቁ የሚያጎናጽፈው፣ ለወደቀው ጨቋኙም እንኳ፣ የእርዳታ እጅ የሚዘረጋው ነው፤ ከጠላቶቹ መካከል ለእጅግ ከፉው እንኳ፣ ፍቅራዊ ወዳጅ የሚሆነው እርሱ ነው። እነዚህ የተባረከው ውበት ትምህርቶች፣ እነዚህ የእጅግ በጣም ታላቁ ሰላም ምክሮች ናቸው።

እናንተ ውድ ወዳጆች ሆይ! ዓለም በጦርነት ላይ ናት፣ የሰውም ዘር በጭንቅና በአጥፊ ውጊያ ውስጥ ነው። የጥላቻ ጨለማ ሌሊት ነግሷል፣ የመልካም እምነትም ብርሃን ተደምስሷል። የምድር ሕዝቦችና ዘሮች ጥፍሮቻቸውን ስለዋል፤ አንዳቸው ራሳቸውን በሌላው ላይ እየወረወሩ ናቸው። እየጠፋ ያለው የሰው ዘር መሠረት ራሱ ነው። ከሃብት ንብረታቸው የተፈናቀሉና መውደቂያ ቦታ ያጡ በሺህ የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ናቸው፤ እያንዳንዱም ዓመት በአቧራማ ጦር ሜዳዎቻቸው ላይ በሕይወታቸው ደም ውስጥ የሚወራጩ እልፍ አእላፍ የሰው ዘሮች ይታያሉ። የሕይወትና የሐሴት ድንኳኖች ወድቀዋል። ጀኔራሎች ስለአፈሰሱት ደም እየፎከሩ ወደ ጠብ በመገፋፋት እርስ በርሳቸው በመወዳደር ጄኔራልነታቸውን በተግባር እያሳዩ ናቸው። ከመካከላቸው አንዱ:- "በዚህ ሠይፍ የሕዝብን አንገት ቀላሁ!" ይላል። ሌላውም:- *"አገርን ከአፈር ጋር ደባለቅሁ!"* አሁንም ሌላው:- *"መንግሥትን ገለበጥሁ!"* ይላሉ። ሰዎች በእንዲህ ዓይነቶቹ ነገሮች ይኩራራሉ፤ በዚህ ዓይነቱም ይፎክራሉ! በሁሉም ሥፍራ ፍቅር፣ ጽድቅናእነዚህን የመሳሰሉት የሚወገዙ ሲሆኑ፣ ስምምነትንና እውነትን ማፍቀር ጠልተዋል።

የተባረከው ውበት እምነት የሰውን ዘር ወደ ደህንነትና ወደ

ፍቅር፣ ወደ ወዳጅነትና ወደ ሰላም እየጠራ ነው፤ ድንኳኑን በምድር ከፍታዎች ላይ ተክሏል፤ ጥሪውንም ለሁሉም ወገኖች እያሰማ ነው። ስለዚህ፣ እናንት የአምላክ አፍቃሪዎች የሆናችሁ ሆይ፣ የዚህን የውድ እምነት ጠቃሚነት እወቁ፤ ትምህርቶቹን ታዘዙ፣ በዚህ በቀጥተኝነት በተዘረጋው መንገድ ተጓዙ፤ ለሕዝቡም ይህንን መንገድ አሳዩ። ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ የመንግሥተ-ሰማያቱን መዝሙር ዘምሩ። ይህ ዓለም ወደሌላ ዓለም ይለወጥ ዘንድ፣ ይህችም ጨለማ ምድር በብርሃን ትጥለቀለቅ ዘንድ፣ የሞተውም የሰው ዘር አካል ተነሥቶ በሕይወት ይኖር ዘንድ፣ እያንዳንዱም ነፍስ በአምላክ ቅዱስ እስትንፋስ አማካይነት ዘለዓለማዊ ሕይወት ይጠይቅ ዘንድ፣ የአፍቃሪውን ጌታ ሕግጋትና ምክሮች በሁሉ ሥፍራ አሰራጩ።

ከመ-ቅጽበት አላፊ ቀኖቻችሁ በቶሎ ያልፋሉ፤ ዝናችሁና ሃብታችሁ፣ ምቾታችሁና ከዚህ የቆሻሻ ክምር ከሆነው፣ ከዓለም የተገኙት ሐሴቶች፣ ምንም ምልክት ሳይተው ያልፋሉ። እንግዲህ ሕዝቡን ወደ አምላክ ጥሩዋቸው፣ የሰውንም ዘር የሰማይ ሠራዊት ምሳሌ እንዲከተሉ ጋብዙ። እናት አባት ለሌለው ሕፃን አፍቃሪ አባቶች፣ ረዳት ለሌለው ተገን፣ ለደሃው የሃብት መዝገብ፣ ለሕመምተኛውም ፈውስ ሁኑ። ለእያንዳንዱ የጭቁና ተበዳይ ረዳቶች፣ ለዕድለ-ቢሱ አባቶች ሁኑ። ለእያንዳንዱ የሰው ዘር አባል አንዳንድ አገልግሎት ለመስጠት አስቡ። በሚደርስባችሁ ጥላቻና ተቀባይነት ማጣት፣ ንቀት፣ ጠብ-አጫሪነትና የፍትሕ ጉድለት አትረበሹ። በተቃራኒው መንገድ ሥሩ። ከአንገት በላይ ብቻ ሳይሆን፣ ከልብ ደግ ሁኑ። እያንዳንዱ የአምላክ ተወዳጅ ለሰው የጌታ ምሕረት የመሆን፣ የጌታ ጸጋ የመሆን ዓላማ ላይ ሃሣቡን ያትኩር። በመንገድ ለሚያቋርጠው ለእያንዳንዱ ሰው አንዳንድ መልካም ነገር ያድርግለት፤ ለአንዳንድ ጥቅምም ይሁነው። የእያንዳንዱንና የሁሉን ፀባይ ያሻሽል፤ የሰዎችንም አእምሮዎች ያስተካክል። በዚህ መንገዱ፣ የመለኮታዊ መርሖ ብርሃን ይበራል፤ የአምላክም ቡራኬዎች የሰውን

ዘር ሁሉ ያቅፋሉ፡- በማንኛውም መኖሪያ ቢኖር ፍቅር ብርሃን ነውና፤ ጥላቻ ደግሞ በማንኛው ሥፍራ ጎጆውን ቢሠራ፣ ጨለማ ነውና። የአምላክ ወዳጆች ሆይ! ድብቁ ምሥጢር ተገልጾ ይታይ ዘንድ፣ የሁሉም ነገሮች ምሥጢር ሕልውና ይፋ ይወጣ ዘንድ፣ ያንን ጨለማ ለዘለዓለም ለማስወገድ ጥረት አድርጉ።

(151)

እናንተ የመንግሥተ-ሰማያት ሕዝቦች ሆይ! የሕይወቱን ጊዜ በሙሉ በሥግደት ያሳለፈ፣ የሥጋን ሥቃይ የቻለ፣ ወደ መንግሥቱ ለመግባት የናፈቀ፣ ነገር ግን ሳይችል የቀረ ስንት ነፍስ ነበር፤ እናንተ ግን ያለልፋት ወይም ሥቃይ ወይም ያለ ራስን መንፈግ፣ ሽልማቱን አግኝታችሁ ገብታችኋል።

ልክ ጥብቅ ሥግደትም ሆነ ራስን የማሠቃየት ልምድ ያልነበራቸው እንደነጴጥሮስ፣ ዮሐንስና እንድሪያስ እንደአሸነፉበት፣ ፈሪሳውያንና የእምነት ሰዎች ግን ያለምንም ድርሻ እንደቀሩበት እንደ መሲሁ ጊዜ ነው። ስለዚህ የዘለዓለም ክብርን ዘውድ በራሳችሁ ላይ ስለደፋላችሁ፣ ሊለካ የማይቻለውን ጸጋ ስለፈቀደላችሁ አምላክን አመሥግኑ።

ለዚህም ሥጦታ ምሥጋና ማቅረቢያ፣ እያንዳንዳችሁ፣ በዚህ የአምላክ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ፣ ልክ እንደ ሌሊት ዘማሪ ወፍ የሠራዊቱን ጌታ የምታወድሥበት፣ በምድር ላይ ለሚኖሩት ሁሉ አስተማሪዎች ትሆኑ ዘንድ ቀን በቀን በተተካ ቁጥር በእምነትና በጽናት ልታድጉበት፣ ያለማቋረጥም ወደ ጌታችሁ፣ ወደ አምላክ ልትቀርቡበት የሚገባችሁ፣ በጣም በመነቃቃታችሁና በጣም በመቀጣጠላችሁ ምክንያት፣ የተወዳጁ ምሥጋናናቅዱስ ዜማችሁ ወደ ላይ ወደ ሰማይ ሠራዊት መድረስ ያለበት ጊዜ መጥቷል።

(152)

ወዳጆችን ማገልገል የአምላክን መንግሥት ማገልገል ነው፤ ለድሃው ርኅራኄ ማሳየትም ከአምላክ እጅግ በጣም ታላላቅ ትምህርቶች አንዱ ነው።

(153)

እናንተ የበራችሁ ወዳጆችና እናንተ የመሐሪው ሴት አገልጋዮች ሆይ! የድንቁርና፣ መለኮታዊ ዓለምን ቸል የማድረግና ከአምላክ የመጋረድ ከባድ ሌሊት ዓለምን ሸፍኖ በነበረበት ጊዜ፣ ብሩህ ንጋት ነጋና በመውጣት ላይ የነበረው ብርሃን የምሥራቅን ሰማይ አበራ። ከዚያም የእውነት ፀሐይ ወጣና የመንግሥቱም ጮራዎች በምሥራቅና በምዕራብ ላይ ብርሃናቸውን ፈነጠቁ። እነዚያ ለማየት ዓይኖች የነበሯቸው በደስታው ዜናዎች ሐሴት በማድረግ *'ወይ ድንቅ፣ ተባርከናል፣ ተባርከናል!'* በማለት ጮሁ፤ የነገሮችንም ውስጣዊ እውነታ አዩ፤ የመንግሥተ- ሰማያቱንም ምሥጢሮች ገለጡ። ከዚያም ከእውነት ከራቁ ከንቱ እምነቶቻቸውና ከጥርጣሬዎቻቸው ነፃ ወጥተው፣ የእውነቱን ብርሃን ተመለከቱ። የአምላክንም ፍቅር ጽዋ በመጎንጨታቸው በጣም የተደሰቱ በመሆናቸው ምክንያት፣ ዓለምንና የገዛ ራሳቸውን ፍጹም ረሱ። በሐሴት እየጨፈሩ ወደ ሰማዕትነታቸው ሥፍራ ፈጥነው ሄዱ፤ እዚያም ሰዎች ለፍቅር በሚሞቱበት ቦታ፣ ጭንቅላቶቻቸውንና ልቦቻቸውን ወረወሩ።

ነገር ግን እነዚያ የሚያዩ ዓይኖች ያልነበሯቸው በዚህ ዋካታ ተደነቁ፤ *'ብርሃኑ የት አለ?'* በማለት ጮሁ፤ እንደገናም፣ *'እኛ ምንም ብርሃን አልታየንም! ለእኛ ምንም እየወጣ ያለ ፀሐይ ዓይታየንም! እዚህ እውነት የለም። ይህ ሕልም እንጂ ከዚህ የተለየ ምንም አይደለም'* አሉ። እንደ ሌሊት ወፍ ወደ ምድር ውስጥ ጨለማ ሸሹ፤

እዚያም፣ እንደ አስተሳሰባቸው፣ ውስን እርካታና ሰላም አገኙ።

ሆኖም፣ ይህ ገና የንጋቱ መጀመሪያ ብቻ ነው፤ እየወጣ ያለውም ፀሐይ ሙቀቱ ገና ሙሉ ኃይሉ ላይ አልደረሰም። ፀሐዩ አንዴ ወደ አኩለ ቀን ከፍታው ከወጣ በኋላ፣ እሳቱ በጣም ግሎ ስለሚነድ ከምድር በታች ሆነው በሆዳቸው የሚሳቡትን ነገሮች እንኳ ያንቀሳቅሳል፤ ብርሃኑን ለማየት ባይችሉም እንኳ፣ ሁላቸውም በሙቀቱ ኃይል ወደ ተደናገረ እንቅስቃሴ ይንቀሳቀሳሉ።

ስለዚህ፣ እናንተ የአምላክ ተወዳጆች ሆይ፣ በንጋቱ ቀን፣ ፊታችሁን ወደ ዓለም ብርሃን ስለመለሳችሁና አንፀባራቂነቱን ስለተመለከታችሁ ምሥጋና አቅርቡ። ከእውነት ብርሃን ድርሻ ተቀብላችኋል፤ ከእነዚያ ለዘለዓለም ከሚኖሩት ቡራኬዎችም ድርሻ ተካፍላችኋል፤ ስለዚህም፣ ለዚህ ፀጋ አጻፋ ምሥጋና ለማቅረብ ለአንድ አፍታም አትረፉ፣ በዝምታም አትቀመጡ፤ የመንግሥተ-ሰማያትን የደስታ ዜና ወደ ሰዎች ጆሮዎች አድርሱ፣ የአምላክን ቃል በሰፊው አሰራጩ።

በጌታ ምክሮች መሠረት ሥሩ፡- ይህም፣ ለዚህ ዓለም አካል ሕያው ነፍስ ለመስጠት፣ ይህንንም ጨቅላ ልጅ፣ የሰውን ዘር ወደ አዋቂነት ደረጃ ለማምጣት በሚያስችል ከፍ ያለ ሁኔታና ከፍተኛ ጥረት ተነሡ። እስከቻላችሁ ድረስ፣ በእያንዳንዱ ስብሰባ የፍቅር ሻማ አቀጣጥሉ፤ በርኅራኄም እያንዳንዱ ልብ ሐሴት እንዲያደርግና እንዲደሰት አድርጉ። የማታውቀትን ሰው ልክ የራሳችሁን ሰው እንደ ምትንከባከቡት ተንከባከቡት፤ ለባዕዳን ነፍሶች ልክ ለታማኝ ወዳጆቻችሁ የምትሰጡትን ዓይነት ፍቅራዊ ደግነት አሳዩዋቸው። ማንም በአናንተ ላይ ጠብ ቢያሣ፣ ከእርሱ ጋር ለመወዳጀት ሞክሩ፤ ማንም ሰውልባችሁን ቢወጋ፣ ለቁስሎቹ ፈዋሽ ቅባት ሁኑለት፤ ማንም ሰው ቢተናኮላችሁና ቢያፌዝባችሁ፣ በፍቅር ቅረቡት። ማንም ወቀሳውን ቢከምርባችሁ፣ እናንተ አሞግሡት፤ አደገኛ መርዝ ቢሰጣችሁ፣ በለውጡ እጅግ በጣም ምርጥ ማር ስጡት፤

ለሕይወታችሁ ቢያስፈራራችሁ፣ ለዘለዓለም የሚፈውሰውን መድኃኒት ስጡት። ውጋት ራሱን ቢሆን፣ መድኃኒቱ ሁኑ፤ እርሱ እሾህ ቢሆን፣ እናንተ ጽጌረዳዎቹና ጣፋጭ ቅመሞች ሁኑለት። እንዲህ ዓይነቱ የእናንተ መንገድና ቃላት ምናልባት በመጨረሻው ይህን ጨለማ ዓለም ወደ ደማቅ ብርሃን እንዲለወጥ ያደርገው ይሆናል፤ ይህን አቧራማ ምድር ወደ መንግሥተ-ሰማይ ይለውጣል፤ ይህንን ዲያብሎሳዊ የእሥር ቦታ የጌታ ንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት እንዲሆን፣ ጦርነትና ጥል አልፈው እንዳልነበሩ ይሆኑና ፍቅርና መተማመን በዓለም ቁንጮዎች ላይ ድንኳናቸውን ይተክላሉ። የአምላክ ምክሮች ሕልውና እንዲህ ያለ ነው፤ በጥቅሉ ለባሃ ዘመን የተሰጡት ትምህርቶች እንዲህ ያሉ ናቸው።

## (154[1])

በወንጌል እንደተፃፈው፣ ክርስቶስ ከሃያ መቶ ዓመታት በፊት በተገለጸ ጊዜ፣ ምንም እንኳ አይሁዶች የእርሱን መምጣት በጉጉት ሲጠባበቁና እያለቀሱ *‘አምላክ ሆይ፣ የመሲህን መገለጽ አፋጥንልን*እያሉ በየዕለቱ እንባቸውን እያፈሰሱ ይጸልዩ የነበሩ ቢሆንም፣ የእውነቱ ፀሐይ በመጣ ጊዜ ግን፣ ካዱትና እጅግ በጣም በከፋ ጠላትንት ተነሡበት፤ በመጨረሻም ከፉ ብኤልዘቡል ብለው ሰይመው፣ ያንን መለኮታዊ መንፈስ፣ ያንን የአምላክ ቃል ሰቀሉት። አይሁዶች ክርስቶስን የሰቀሉበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው፡- በኦሪት መጻሕፍት ግልጽ ጽሑፍ መሠረት፣ የክርስቶስ መገለጽ በአንዳንድ ምልክቶች የሚረጋገጥ ሲሆን፣ እነዚህ ምልክቶች ሳይፈጸሙ እኔ መሢሕ ነኝ የሚል ሁሉ ግን አታላይ ነው። ከእነዚህ ምልክቶች አንዱመሢሕ ካልታወቀ ቦታ ይመጣል የሚል ነው፤ ሆኖም ይህ ሰው ከናዝሬት መምጣቱን ሁላችንም እናውቃለን፤ ከናዝሬት መልካም ነገር ሊመጣ ይችላልን? ሁለተኛው ምልክት ደገሞ በብረት

---

1 በተለይ ለዶ/ር ኤስሌሞንት ‘ባሃኦላህና አዲሱ ዘምን’፣ ሕያው ለሆነው ሥራቸው የተጻፈ።

በትር፣ ማለትም ሠይፍን በእጁ ጨብጦይገዛል የሚል ነው፤ ይህ መሢህ ግን የእንጨት በትር እንኳ የለውም። ከመለያዎቹና ከምልክቶቹ መካከል አንዱ ደግሞ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ የዳዊትን መንግሥት ያቋቁማል የሚል ነው። ይህ ሰው ግን እንኳንስ በዳዊት ዙፋን ሊቀመጥ ቀርቶ የሚያርፍበት ሰሌንየለውም። ከመለያዎቹ መካከል ሌላው፣ መሢሐ ሲመጣ የኦሪትን ሕግጋት ሁሉ ያጸናል የሚል ነበር። ሆኖም፣ ምንም እንኳ ነቢይ ነኝ የሚልና ተአምራትን የሚሠራ የቅዳሜን ቀን ከሻረ መገደል አለበት የሚል ግልጽየኦሪት ጽሑፍ ያለ ቢሆንም፣ ይህ ሰው ግን እነዚህን ሕግጋት፣ የቅዳሜንም ቀን ጭምር ሻረ። ሌላው ምልክት ደግሞ በዚህ ሰው ዘመነ-መንግሥት ፍትሕ በጣም ስለሚበዛ፣ ጽድቅና በጎ አድራጎት ከሰዎች ተርፎ ወደ እንስሳትም ዓለም አለፎ እባብና አይጥ አንድ ጉድጓድ፣ ንሥርና ድርጭት አንድ ጎጆ ይጋራሉ። አንበሣና ፌቆ በአንድ ሜዳ ይሠማራሉ። ተኩላና የፍየል ግልገል ከአንድ ምንጭ ይጠጣሉ የሚለው ሲሆን በእርሱ ዘመን ግን ፍርድ በመጉደሉና ጭካኔ ከመብዛቱ የነሣ እርሱን ራሱንም ሰቀሉት። መሟላት ያለበት ሌላው ምልክትደግሞ በመሢሕ ዘመንአይሁዶች ይበለጽጋሉ፤ የዓለምንም ሕዝቦች ሁሉ ድል ይነሣሉ የሚለው ሲሆን በእርሱ ዘመን ግን እጅግ በጣም በተዋረደ ሁኔታና በሮም ንጉሠ-ነገሥት ግዛት በባርነት ሥር ይኖሩ ነበር። እንግዲህ በኦሪት ውስጥ የተሰጠው መሢሕ ይህ ሊሆን እንዴት ይችላል?

ምንም እንኳ ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርግጥ ያው በኦሪት ውስጥ የተተነበየለት ቢሆንም፣ ያንን የእውነት ፀሐይ በዚህ ሁኔታ ተቃወሙት። ነገር ግን የእነዚህን ምልክቶች ትርጉም ስላልተረዱ የአምላክን ቃል ሰቀሉት። የኦሪት ምልክቶች የተገለጹት በምሳሌ ስለሆኑ አይሁዶች በገሙቱት መንገድ ባይሆንም፣ በክርስቶስ መገለጽ ምልክቶቹ ሁሉ እንደተፈጸሙ ባሃኢዎች ያምናሉ። ለምሳሌ ከምልክቶቹ አንዱ ስለ ንጉሥነት ነው። ባሃኢዎች የክርስቶስ

ንጉሥነት ለጥቂት ጊዜ ደምቆ እንደ ትቢያ በኖ እንደሚጠፋው እንደነናፖሊዮን ያለ ንጉሥነት ሣይሆን የሰማይ፣ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ንጉሥነት ነው ይላሉ። የክርስቶስ መንግሥት ከተጀመረ ጊዜው ወደ ሁለት ሺህ ዓመታት ተቃርቧል፤ አሁንም እንዳለ ነው፤ እስከ ዘለዓለምም ይህ መለኮታዊ ሕያው በዘለዓለማዊ ዙፋን ላይ ይከበራል።

በዚሁ ዓይነት ሌሎቹም ምልክቶች ሁሉ ተፈጽመዋል፤ ነገር ግን አይሁዶች አልገባቸውም። ምንም እንኳ ክርስቶስ መለኮታዊ ግርማን ተጎናጽፎ ወደዚህ ዓለም ከመጣ ሁለት ሺህ ዓመታት ያህል ያለፉ ቢሆንም፣አይሁዶች ግን እስከ አሁንም የመሢሕን መምጣት በመጠባበቅ ራሳቸውን እንደ እውነተኞች፣ ክርስቶስን ደግሞ እንደ ሐሰተኛ አድርገው ይገምታሉ።

(155)

በሕይወት ዛፍ ላይ ያለሽ ቅጠል ሆይ! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው፣ የሕይወት ዛፍ ባሃኣላህ ነው፤ የመንግሥተ-ሰማይ ሴት ልጆችም በዚያ የተባረከ ዛፍ ላይ ያሉ ቅጠሎች ናቸው። እንግዲህ ከዚያ ዛፍ ጋር ስለተዛመድሽ፣ ለምለም፣ ሊጋና ቡቃያ ስለሆንሽ አምላክን አመሥግኚ።

የአምላክ መንግሥት በሮች በሰፊው ተከፍተዋል፣ እያንዳንዱም የተመረጠ ነፍስ ከዚያ ከመንግሥተ-ሰማያዊ ድግሥ ድርሻውን እየተቀበለ በጌታው የግብር ገበታ ተቀምጧል። አምላክ ይመሥገን፣ አንቺም ደግሞ፣ በዚህ ገበታ ላይ ሆነሽ፣ ከመንግሥተ-ሰማያት የሆነውን የተትረፈረፈ ምግብድርሻሽን በመውሰድ ላይ ትገኚያለሽ፦ የአምላክን መንግሥት እያገለገልሽ ነው፣ የአብሃን ገነት ጣፋጭ መዓዛዎችንም ደህና አድርገሽ አውቀሻቸዋል።

እንግዲህሕዝቡን ለመምራት በሙሉ ኃይልሽ ጥረት አድርጊ፤

ከሰማይ ከወረደውም ምግብ እንድትበይ ይሁን። *'እኔ ከሰማይየወረድኩት የሕይወት እንጀራ ነኝ፤ ከዚህም እንጀራ የበላ ለዘለዓለም ይኖራል፤'*[1] የሚሉት የክርስቶስ ቃላት ትርጉም ይህ ነውና።

(156)

እንደ ታዳጊና ለምለም ቅርንጫፍ በአምላክ ፍቅር ነፋሶችውስጥ የምትርገበገቢ የአምላክ ሴት አገልጋይ ሆይ! ስለተትረፈረፈው ፍቅርሽ፣ ስለ ጥልቅ መስዋዕትነትሽ፣ ጌታሽንም በመዘከር ስለመጠመድሽ የሚናገረውን ደብዳቤሽን አንብቤአለሁ።

በአምላክ ላይ ተማመኚ። ለእርሱ ሴት አልጋዮችም ቅድስት፣ መንፈሳዊት፣ ከአምላክ መንግሥትም የመሆን ምሳሌ ትሆኚ ዘንድ፣ የራስሽን ትተሽ የእርሱን ፈቃድ፣ የራስሽን ምኞት ወደጐን አድርጊና የእርሱን ያዢ።

ሴት አገልጋዬ ሆይ፤ በባሃ ዓይን፣ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል እንደሆኑ፣ አምላክም የሰውን ዘር በሙሉ በራሱ አምሳል፣ በራሱ ምስያ እንደፈጠረ እወቂ። ይህም ማለት፣ ወንዶችም ሴቶችም በአንድ ዓይነት የስሞቹና የባሕርይዎቹ ገላጮች ናቸው፤ ከመንፈሳዊ ሁኔታ አንፃር ሲታዩ በመካከላቸው ምንም ልዩነት የለም ማለት ነው። ወንድም ሆነ ሴት፣ ይበልጥ ወደ አምላክ የቀረበው ይበለጥ የተወደደ ነው። ለእምነቱ የጋለ ስሜት የነበራቸውና ራሳቸውን የሰጡ፣ ጥላ በሚሰጠው የባሃ ጠላይ ጥላ ሥር ከወንዶች የላቁ መሆናቸውን ያስመሠከሩ ከምድር ዝነኞችም በልጠው የተገኙ ሴት አገለጋዮች ነበሩ።

ይሁን እንጂ፣ በማያከራክር የአምላክ ሕግ ጽሑፍ መሠረት የዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትሕ (አባልነት)፣ ለወንዶች ብቻ የተወሰነ ነው፤ ይህም ሳይቆይ ከመጨረሻ ከፍታ እንደምታበራ የቀትር ፀሐይ በግልጽ

[1] ዮሐንስ 6.51፡58

ለሚገለጸው የጌታ የአምላክ ጥበብ ነው።

የሰማይ የሆኑትን ሽታዎች ያፈቀራችሁ ሌሎች ሴት አገልጋዮች ሆይ፤እናንተ ደግሞ መፈንፈሳዊ ጉባኤዎችን አቋቁሙ፤ ቅዱስ ስብሰባዎችን አዘጋጁ፣ እነዚህ የአምላክ ጣፋጭ መዓዛዎች ማሰራጭያ፣ ቃሉን ከፍ ከፍ ማድረጊያ፣ የጸጋውን ፋኖስ ከፍ ማድረጊያ፣ የእርሱን ሃይማኖት ማወጃና ትምህርቶቹን ማስፋፊያ መሠረቶች ናቸውና፤ ከዚህም የበለጠ ምን አለ? እነዚህ መንፈሳዊ ጉባኤዎች በአምላክ መንፈስ ይታገዛሉ፣ ተከላካያቸው አብዱል-ባሃ ነው። እርሱ በእነርሱ ላይ ክንፎቹን ይዘረጋል። ከዚህ የበለጠ በረከት ምን አለ? እነዚህ መንፈሳዊ ጉባኤዎች የሚያበሩ ፋኖሶችና የቅድስና ሽታዎች በሁሉ አካባቢዎች ላይ የሚሰራጩበት፣ የዕውቀት ብርሃኖችም በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ የሚያበሩባቸው መንግሥተ-ሰማያዊ የአትክልት ቦታዎች ናቸው። ከእነርሱ የሕይወት መንፈስ ወደ ሁሉም አቅጣጫ ይጎርፋል። እነሱ፣ በእውነቱ በሁሉ ጊዜያትና በሁሉ ሁኔታዎች የሰው ዕድገት ፍቱን ምንጮች ናቸው። ከዚህ የበለጠ ምን በረከት አለ?

(157)

ለእነዚያ በአንድ ላይ ለሚመካከሩት ከሁሉ ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑ ባሕርይዎች፣ የዓላማ ንጽህና፣ የመንፈስ ብሩህነት፣ ከአምላክ በቀር ከሌላው ሁሉ መላቀቅ፣ ወደ መለኮታዊ መዓዛዎቹ መሣብ፣ በተወዳጆቹ መካከል ትሕትናና ዝቅተኛነት፣ በችግር ጊዜ ታጋሽነትና ቻይነት፣ በተከበረው ደጇ- ሰላሙም አገልጋይነት ናቸው። እነዚህን ባሕሪያት ለመገብየት በእርሱ ጸጋ ቢታገዙ፣ ከማይታየው የባሃ መንግሥት ድል ይሰጣቸዋል።

## (158)

አባላቱ[1] ለቅሬታና ለመለያየት ምክንያት የሚሆን ምንም ሁኔታ በማይፈጠርበት አኳኋን በአንድ ለይ መመካከር አለባቸው። ይህ ሊገኝ የሚቻለው እያንዳንዱ አባል በፍጹም ነፃነት ሃሣቡን ሲገልጽና ማሳመኛ ነጥቦቹንም ሲዘረዝር ነው። በጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ ውይይት ካልተደረገባቸው ትክክለኛው መንገድ ሊገለጽ አይቻልምና፤ ማንም ቢቃወም በምንም ዓይነት ቅር መሰኘት የለበትም። የእውነት አንፀባራቂ ብልጭታ የሚከሰተው ከተለያዩ አስተሳሰቦች ግጭት በኋላ ብቻ ነው። በጉዳዩ ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ ውሳኔው በሙሉ ድምፅ ቢተላለፍ በጣም መልክም ነው፣ ነገር ግን፣ ጌታ አይበለውና፣ የሃሣብ ልዩነት ቢያጋጥም፣ የድምጽ ብልጫው ወገን መጽናት አለበት።

## (159)

ስለእያንዳንዱ የባሃኢ ወር (19ኛ ቀን) በዓል ጠይቀሃል። ይህ በዓል የሚደረገው ወዳጅነትንና ፍቅርን ለማዳበር፣ አምላክን ለማስታወስና በፀፀትና ንስሐ በመጠየቅ በተሞሉ ልቦች፣ እርሱን ለመማፀን የበጎ ሥራዎችንም ለማበረታታት ነው። ይህም ማለት፣ ወዳጆች በዚያ ሃሣባቸውን በአምላክ ላይ ማሣረፍ፣ ጸሎቶችንና ቅዱሳት ጥቅሶችን ማንበብ፣ በከፍተኛ ስሜትና ፍቅር እርስ በርሳቸው መወዳጀት አለባቸው ማለት ነው።

## (160)

አሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ደግሞ፣ ለአእምሮና ለልብ ሐሴትን ይሰጣል። ይህ በዓል በትክክለኛው መንገድ ቢደረግ፣ ወዳጆቹ በአሥራ ዘጠኝ ቀን አንዴ፣ በመንፈስ ታድሰው፣ ከዚህ ዓለም ባልሆነ ኃይልም ተሞልተው ራሳቸውን ያገኛሉ።

---

[1] የመንፈሳዊ ጉባኤ አባላት

## (161)

ስለ አብሃ ውበት በጣፋጭ ሁኔታ የምትዘምሪ ወፍ ሆይ! በዚህ አዲስና ድንቅ ዘመን፣ የአጉል አምልኮ መጋረጃ ተቀዷል፤ የምሥራቅ ሕዝቦች አጉል ጥላቻዎችም ተወግዘዋል። በአንዳንድ የምሥራቅ ሕዝቦች መካከል ሙዚቃ እንደሚከለከል ነገር ይቆጠር ነበር፤ ነገር ግን በዚህ በአዲሱ ዘመን ግልጹ ብርሃን፣ በቅዱስ መልዕክቶቹ፣ ሙዚቃ ሲዘምሩት ወይም /በሙዛሪያ/ ሲጫወቱት ለነፍስና ለልቦና ምግብ እንደሆነ ገልጿል።

የሙዚቀኛው ጥበብ ከእነዚያ ከፍተኛ ምሥጋና ከሚገባቸው ጥበባት አንዱ ነው፤ የእነዚያን የሚያዝኑትን ሰዎች ሁሉ ልብ ይቀሰቅሳል። ስለዚህ፣ አንተ ሻህናዝ[1] ሆይ! ሰሚው ከሃሣብና ከኃዘን ሰንሰለት ነፃ ይውጣ፣ ነፍሱም በሐሴት ትዝለል ወደ ክብር ዓለም በፀሎት ራስዋን ዝቅ ታድርግ ዘንድ፣ በወዳጆች ስብሰባዎች የአምላክን ቅዱሳት ቃላት በድንቅ ዜማ ተጫወት እንዲሁም ዘምር።

## (162)

በነጭና በጥቁር መካከል ሕብረትንና ስምምነትን ለማምጣት፣ በዚህም መንገድ የቀለም ልዩነት ሥፍራ የማያገኝበትን፣ ይልቁንም ልቦች ብቻ የሚታዩበትን የባሃኢን ዓለም አንድነት ለማስመሥከር በልብም በነፍስም ጥረት አድርጉ። ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይግባውና፣ ወዳጆች፣ ከምሥራቅ ሆኑ ከምዕራብ፣ ከሰሜን ወይም ከደቡብ፣ ጀርመናዊም ሆኑ ፈረንሳዊ፣ ጃፖናዊም ሆኑ አሜሪካዊ፣ ከነጭም ሆኑ ከጥቁር፣ ከቢጫውም ሆኑ ከጠይሙ ዘር፣ ልቦቻቸው ተባብረው በአንድነት ተሣሥረዋል። በባሃኢ እምነት የቀለም፣ የአገርና የዘር ልዩነቶች ቁም ነገር የላቸውም። ይልቁንም፣ የባሃኢ አንድነት እነዚህን ልዩነቶች ሁሉ ያሸንፋል፤ እነዚህንም ከእውነት የራቁ ከንቱ እምነቶችና አስተሳሰቦች ያስወግዳል።

---

[1]ሻህናዝ፣ ይህ ጽላት ለተጻፈለት ሰው የተሰጠ ስም ነው። የሙዚቃ ዓይነት ስምም ነው።

## (163)

አንተ የበራ ልብ ያለህ ሆይ! የእግዚአብሔር ፍቅር በሕያውነትህ የመጨረሻ ጥልቀት ላይ ጨረሮቹን ስለፈነጠቀና ፊትህን ወደ ጌታህ መንግሥት ስለመለሰከ፣ አንተ ልክ የብርሃኑ የራሱ ምንጭ እንደሆነችው፣ እንደ ዓይን ብሌን ነህ።

በአሜሪካ፣ በነጩና በጥቁሩ መካከል፣ ጥላቻው የጠነከረ ነው፤ ነገር ግን ተስፋዬ፣ የአምላክ መንግሥት ኃይል፣ እነዚህን ሁለቱን በወዳጅነት እንደሚያስተሣሥር፣ እንደመፈወሻ ቅባትም እንደሚያገለግላቸው ነው።

እነርሱ ሰውን ልቡን እንጂ ቀለሙን አይመልከቱ። ልቡ በብርሃን የተሞላ ከሆነ፣ ያ ሰው ወደጌታው ደጀ ሠላም የቀረበ ነው፤ ካልሆነ ግን፣ ነጭም ይሁን ጥቁር፣ ያ ሰው ስለጌታው ግዴለሽ ነው።

## (164)

አንቺ ውድ የእግዚአብሔር ሴት አገልጋይ ሆይ! ደብዳቤሽ ደርሷል፤ የይዘቱም ነጥቦች ተስተውለዋል።

ጋብቻ፣ በሰፊው ሕዝብ መካከል፣ የአካል መቆራኘት ነው፤ ይህም በመጨረሻው በአካል መለያየት እንደሚያከትም አስቀድሞ የታዘዘ ስለሆነ፣ ይህ መተሣሠር ሊሆን የሚችለው የጊዜያዊ ብቻ ነው።

ነገር ግን፣ በባሃ ሕዝብ መካከል፣ ባልም፣ ሚስትም ሁለቱም በአንድ ዓይነት ወይን ጠጅ የተጋጋሉ፣ ሁለቱም በአንድ ዓይነት መንፈስ የሚኖሩና የሚንቀሳቀሱ፣ ሁለቱም በአንዱ ብርሃን የበሩ ስለሆኑ፣ ጋብቻ የአካልም የመንፈስም መተሳሰር መሆን አለበት። በመካከላቸው ይህ ግንኙነት መንፈሣዊ ነው፤ ስለዚህም ለዘለዓለም የሚኖር መቆራኘት ነው። እንዲሁም፣ ጋብቻው በመንፈስና በአካል ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ ያ መተሣሠር እውነተኛ መተሣሠር ነውና፣ ስለዚህም ዘላቂ ስለሚሆን፣ በምድራዊ ዓለምም ደግሞ በጠንካራና

በዘላቂ መተሣሠር ሐሴት ያደርጋሉ። ሆኖም፣ መቆራኘቱ ከአካል በቀር ሌላ ምንም ነገር ከሌለው፣ የጊዜያዊ ብቻ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፤ ስለዚህም በማይለወጥ ሁኔታ በመለያየት መደምደም አለበት።

ስለዚህ፣ የባሃ ሕዝብ ለመጋባት በሚነሣበት ጊዜ፣ በእያንዳንዱ የሕይወት ደረጃ በእግዚአብሔርም ዓለማት ሁሉ፣ መተሣሠራቸው ቋሚ ይሆን ዘንድ፣ መቆራኘቱ እውነተኛ ግንኙነት፣ መንፈሳዊ እንዲሁም ሥጋዊ ግንኙነት መሆን አለበት። ይህ እውነተኛ አንድነት የአምላክ ፍቅር መንፀባረቅ ነውና።

በዚህ መንገድ፣ ነፍሶች ሁሉ አድገው እውነተኞች አማኞች በሚሆኑበት ጊዜ፣ ወደእርስ በርስ መንፈሳዊ ግንኙነት ደረጃ ይደርሳሉ፤ ከዚህ ዓለም ያልሆነ ርኅራኄም ያሳያሉ። እነርሱ ሁሉም፣ ከመለኮታዊ ፍቅር መጠጥ ይደሠታሉ፤ ያ የእነርሱ መተሣሣርም፣ ያ ግንኙነትም ደግሞ ለዘለዓለም ይኖራል። ነፍሶች ማለትም ራሳቸውን አሳልፈው ለመረሳት የሚሰጡ፣ የሰውን ዘር ጉድለቶች ከራሳቸው የሚያወርዱ፣ ከሰው ዘር ባርነት ሠንሠለትም ራሳቸውን የሚያላቅቁ፣ ያለምንም ጥርጥር በመንግሥተ-ሰማያዊ የአንድነት ብርሃን ይበራሉ፤ በማይሞተው ዓለምም ሁላቸውም እውነተኛ መተሣሠርን ያገኛሉ።

## (165)

በእግዚአብሔር ሕግ ሥር ጋብቻን ስለሚመለከት ጥያቄህ ደግሞ:- መጀመሪያ ደስ የምትልህን መምረጥ አለብህ፤ከዚያም ጉዳዩ በአባትና በእናት ፍቃድ ይወሰናል። ምርጫህን ከማድረግህ በፊት ጣልቃ ለመግባት ሙብት የላቸውም።

## (166)

የባሃኢ ጋብቻ የሁለቱ /ተጋቢዎች/ ቃል መግባባት፣ እንዲሁም የአዕምሮና የልብ መተሣሠር ነው። ሆኖም፣ በመካከላቸው

የሚያቆራኛቸው ቃል ኪዳን ለዘለዓለም የሚኖር መተሣሠር ይሆን ዘንድ፣ እያንዳንዳቸው ከሌላው ጠባይ ጋር በደንብ ለመተዋወቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ዓላማቸው ይህ መሆን አለበት፡- የሚፋቀሩ ባልንጀሮች፣ ጓደኞችና አንዳቸው ከሌላው ጋር ለአንዴና ለዘለዓለም በአንድ ላይ ለመሆን...

እውነተኛው የባሃኢዎች ጋብቻ ይህ መሆን አለበት፤ አንዳቸው የሌላውን መንፈሳዊ ሕይወት ለማሻሻል፣ በአምላክ ዓለማትም ሁሉ በዘለዓለማዊ አንድነት ለመኖር፣ ባልና ሚስት በሥጋዊውም በመንፈሳዊውም ረገድ አንድ መሆን አለባቸው። ይህ የባሃኢ ጋብቻ ነው።

(167)

የጌታ ሴት አገልጋዮች ሆይ! በዚያ በበራው ከተማ ያቋቋማችሁት መንፈሳዊ ጉባኤ ለሥራ መቃናት እጅግ በጣም አስፈላጊ /ጥሩ ምልክት/ ነው። ታላላቅ እርምጃዎች አድርጋችኋል፤ ሌሎችን በልጣችኋል፤ ቅዱስ ደጀ ሠላሙን ለማገልገል ተነስታችኋል፤ መንግሥተ-ሰማያዊ ስጦታዎችንም አግኝታችኋል። አሁን በሙሉ የጋለ መንፈሳዊ ፍላጎት በዚያ በተገለጸለት ጉባኤ መሰብሰብ፣ ቅዱሳት ጽሑፎችን ማንበብና ጌታን በማስታወስ ሥራ ላይ መሠማራት አለባችሁ። የእርሱን መገለጫዎችና ማስረጃዎች አሰራጩ። ትናንሽ ልጆቻቸውን ከዕድሜአቸው መጀመሪያ ቀናት ጀምረው ያለማቋረጥ በተሟላ ሁኔታ በማሠልጠን እንዲያስተምሯቸው፣ መልካም ጠባይና መልካም ግብረ ገብነት እንዲኖራቸው አድርገው እንዲያሳድጓቸው፣ ወደሰው ዘር መልካም ምግባሮች ሁሉ እንዲመሯቸው፣ ለወቀሳ የሚያደርስ ምንም ፀባይ ከማዳበር እንዲከለክሏቸውና፣ በባሃኢ ትምህርት አንቀልባ እንዲያሳድጓቸው በዚያ አገር ለሚገኙ ሴቶች መርሖ የሚሆን ሥራ ሥሩ፤ወጣት ልጃገረዶችንና ልጆችንም አስተምሩ። በዚህ መንገድ እነዚህ ጨቅላ ሕፃናት ከአምላክ

ዕውቀትና ከፍቅሩ ጡት ይመገባሉ። በዚህም ሁኔታ ያድጉና ያብባሉ፤ ስለፅድቅና ስለሰው ዘር ክብር፣ ጽናትን፣ ጥረት ማድረግንና ችግር መቻልን እንዲማሩ ይደረጋሉ። በዚህ ሁኔታ በሁሉም ነገሮች ተስፋ አለመቁረጥን፣ ዕድገት የማድረግ ፍላጎትን፣ ከፍተኛ አስተሳሰብንና ከፍተኛ አወሳሰንን፣ የጋብቻ ንጽሕናንና የሕይወት ንጽህናን ይማራሉ። በዚህም ሁኔታ የሚጀምሩትን ማናቸውንም ነገር ወደተቃና ፍጻሜ ለማድረስ እንዲችሉ ይደረጋሉ።

እናቶች የልጆችን ትምህርት የሚመለከት ማንኛውንም ነገር የመጀመሪያ ቅድሚያ እንዳለው ይቁጠሩ። ቅርንጫፉ ሲጋና ለምለም እያለ እንዳቀኑት ስለሚያድግ፣ በዚህ አንፃር ሁሉም ጥረት ያድርጉ። ስለዚህ እናቶች ልክ አትክልቶቹን በሚንከባከቡበት ዓይነት ልጆቻቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል። በልጆቻቸው እምነትና እርግጠኝነትን፣ ፈሪሐ-እግዚአብሔርን፣ የእርሱን የዓለማት ተወዳጁን ፍቅር፣ ሁሉንም መልካም ባሕርያትና ጠባዮች በልጆቻቸው ለማስረጽ ሌት ተቀን ጥረት ያድርጉ። እናት፣ ልጁ መልካም ነገር ሰርቶ በአገኘችው ቁጥር ታመስግነውና ታጨብጭብለት፣ ልቡንም ታስደስተው፤ እጅግ በጣም ትንሽም ቢሆን፣ የማይፈለግ ጠባይ ራሱን ቢገልፅ፣ ልጁን ትምከር፣ ትቅጣው፤ በምክንያት ላይ የተመሠረተ ዘዴ ትጠቀም፤ ትንሽ የቃል ቅጣትም እንኳ ቢሆን፣ ካስፈለገ። ሆኖም፣ ቢደበደብና የቃል ስድብ ቢወርድበት፣ የልጁ ጠባይ ሙሉ በሙሉ ስለሚበላሽ፣ ልጁን መምታት ወይም ማዋረድ አይፈቀድም።

(168)

በዚህ አሁን ባለው ቁስ አካላዊ ሥልጣኔና ከቤተ-ፍትሕ ከሚገኙት ጥቅሞች አንዱ በሆነው በመለኮታዊ ሥልጣኔ መካከል ስላለው ልዩነት ደግሞ፣ ልዩነቱ ይህ ነው፡- ቁስ አካላዊ ሥልጣኔ፣ በቅጣትና በበቀል ላይ በተመሠረቱ ሕግጋት ኃይል፣ ሕዝቡን ወንጀል ከመፈጸም ይገታል። ይህ እንዲህ ቢሆንም፣ እንደምታየው፣ በሰው

ላይ ለመበቀልና እርሱን ለመቅጣት ሕግጋት ያለማቋረጥ እየጨመሩ ሲሄዱ፣ እርሱን ለመሸለም ግን ምንም ሕግ የለም። በአውሮፖና በአሜሪካ ከተሞች ሁሉ ለወንጀለኞቹ እንደእሥር ቤት የሚያገለግሉ ሰፋፊ ሕንፃዎች ተገንብተዋል።

ነገር ግን፣ መለኮታዊ ሥልጣኔ፣ ብዛታቸው እስከዚህም ከማያሣስብ ጥቂት በቀር ማንም ወንጀል በማይሠራበት ሁኔታ እያንዳንዱን የኅብረተ-ሰብ አባል ያሠለጥናል። ስለዚህ ወንጀልን ኃይል በመጠቀምና በበቀል ላይ በተመሠረቱ እርምጃዎች በመግታትና ሕዝቡ ያለምንም የቅጣት ወይም የበቀል ፍራቻ ከወንጀል ተግባሮች ሁሉ በሚርቅበት ሁኔታ በማሠልጠን፣ በማስተማርና መንፈሣዊነታቸውን በማዳበር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። እነርሱ፣ በእውነቱ ወንጀል መፈፀሙን ራሱን እንደትልቅ ውርደትና በራሱ ከቅጣቶች ሁሉ እጅግ በጣም ከባድ ቅጣት እንደሆነ ይመለከቱታል። የሰውን ዘር ፍፁምነቶች አፍቃሪዎች ይሆናሉ፤ እንዲሁም ለዓለም ብርሃንን የሚያመጣውንና እነዚያን በአምላክ ቅዱስ ደጀ - ሠላም ተቀባይነት ያላቸውን ባሕርያት ለሚያራምድ ለማንኛውም ነገር ሕይወታቸውን ቤዛ ይሠጣሉ።

እንግዲህ በቁስአካላዊ ሥልጣኔንና፣ በመለኮታዊው መካከል ያለው ልዩነት እንዴት ሠፊ እንደሆነ ተመልከቱ። ቁስ አካላዊ ሥልጣኔ፣ በኃይልና በቅጣቶች ሕዝቡን ከክፋት፣ በሕብረተ -ሰቡ ላይ ጉዳት ከማድረስና ወንጀሎችን ከመፈፀም ለመግታት ይፈልጋል። በመለኮታዊ ሥልጣኔ ግን፣ እያንዳንዱ ሰው በጣም በትክክል በመሠልጠኑ ያለቅጣት ፍራቻ ወንጀሎችን ከመፈፀም ተግባር ይሸሻል፤ ወንጀልን እራሱን እንደ እጅግ በጣም ከባድ ሥቃይ ያየዋል፤ በትጋትና በሐሴት የሰውን ዘር መልካም ምግባሮች ወደ መገብየት፣ የሰውን ዘር ዕድገት ወደማራመድ፣ በመላው ዓለም ብርሃንን ወደ ማሠራጨት ተግባሮች እራሱን ያሠማራል።

## (169)

የባሃኢ ልጆች በአምላክ ፀጋ አንቀልባ እንክብካቤ ያደጉ ስለሆኑ፣ የሳይንስና የጥበብን ዕውቀት በመገብየት ረገድ ከሌሎች ልጆች ልቀው መገኘት አለባቸው።

ሌሎች ልጆች በአንድ ዓመት የሚማሩትን ማንኛውንም ትምህርት፣ የባሃኢ ልጆች በአንድ ወር ይማሩት። የአብዱል-ባሃ ልብ፣ የባሃኢ ወጣት ሰዎች እያንዳንዳቸውና ሁላቸው፣ በመላው ዓለም በዕውቀታቸው ደረጃ ልቀው የታወቁ ሆነው ለማግኘት ባለው ፍቅሩ ይናፍቃል። የሳይንስና የጥበብ ዕውቀቶችን ለመገብየት በሙሉ ጥረታቸው፣ በጉልበታቸውና በኩራት ስሜታቸው ሙሉ ኃይል ጥረት እንደሚያደርጉ ምንም አያጠራጥርም።

## (170)

የቅዱሱና የሁሉን ቻዩ አምላክ ወዳጆች ሆይ! በሁሉም ነገሮች ንጹሕና ቅዱስ መሆን የተቀደሰ ነፍስ ባሕርይና ባርነት ያልደረሰበት አእምሮ መሠረታዊ መታወቂያ ምልክት ነው። ከፍጹምነት ባሕርይዎች ሁሉ የላቀው ጉድፍ አልባ ንጽህናና ራስን ከእያንዳንዱ ጉድለት ነፃ ማውጣት ነው። አንድ ሰው አንዴ ከሁሉ አንፃር ከነፃና ንጹህ ከሆነ በኋላ ከዚያ ወዲያ ግልጹን ብርሃን የሚያንፀባርቅ የብርሃን ማዕከል ይሆናል።

በአንድ ሰው የአኗኗር ሁኔታ የመጀመሪያው ንጽህና መሆን አለበት፤ ከዚያም ብሩህነት፣ የአካልና የአለባበስ ንጽህናና የመንፈስ ነፃነት ናቸው። በመጀመሪያ የወንዙ ወለል መጽዳት አለበት፤ ከዚያ በኋላ ጣፋጩ የወንዝ ውሃ ሊገባበት ይችላል። ንጹህ ዓይኖች የጌታን ውብማ ትዕይንት በማየት ሐሤት ያደርጋሉ፤ ይህም መገናኘት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ፤ ንጹሕ የማሽተት ኃይል፣ ከእርሱ ፀጋ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ የሚነፍሰውን መልካም ሽታ ያሸታል፣ የተወለወለ ልብ የእውነትን ውብ ፊት ያሳያል።

*ቍርአን፡- 'ንጹህ ውሀም ከመንግሥተ-ሰማያት ወደታች አንልካለን፤'*[1] እንደሚል፣ ወንጌልም፡- *አንድ ሰው ከውሀና ከመንፈስ ካልተጠመቀ፣ ወደ አምላክ መንግሥት ለመግባት አይችልም፣*[2] እንደሚል ሁሉ፣ በቅዱሳት ጽሑፎች፣ የመንግሥተ-ሰማያት ምክሮች በውሀ የተመሰሉት ለዚህ ነው። ስለዚህ ከአምላክ የሚመጡት ትምህርቶች መንግሥተ-ሰማያዊ የጸጋ ጐርፎች እንደሆኑ ግልጽ ነው፤ እነዚህ የመለኮታዊ ምሕረት ዝናብ ዶፍ መውረድ ናቸው፤ የሰውን ልብ ያጥባሉ።

የንግግሬ ትርጉም ይህ ነው፤ በእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ፣ ንጽህናና ቅድስና፣ የአካልና የአለባበስ ንጽህናና ረቂቅነት /የአኗኗርና የአስተሳሰብ/፣ የሰውን ሁኔታ ደረጃ ከፍ ያደርጋል፤ የሰውንም ውስጣዊ እውንነት መዳበር ይጨምራል። በሥጋዊ ዓለምም እንኳ ቢሆን፣ ቅዱሳት ጽሑፎች በግልጽ እንደሚናገሩት፣ የአካልና የአለባበስ ንጽህና ለመንፈሳዊነትአመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። ምንም እንኳ አካላዊ ንጽህና የሥጋዊ ነገር ብቻ ቢሆንም፣ ይሁን እንጂ፣ በመንፈስ ሕይወት ላይ ኃይለኛ የመለወጥ ኃይል አለው። ልክ በግሩም ሁኔታ ጣፋጭ እንደሆነ ድምጽ፣ ወይም እንደተጫወቱት ዜማ ነው፡- ምንም እንኳድምጾች በጆሮ የመስማት ሥሮች ላይ ለውጥ የሚያስከትሉ የአየር ውስጥ እርግብግቦሽ ብቻ ቢሆኑም፣ እርግብግቦሾች በአየር ውስጥ ወደፊት እንዲጓዙ የተደረጉ የአጋጣሚ ሁኔታዎች ብቻቢሆኑም፣ እንዴት ልብን እንደ ሚያንቀሳቅሱ ተመልከቱ። አንድ ድንቅ ዜማ ለመንፈስ ክንፍ ነው፤ ነፍስንም በሐሴት እንድትንቀጠቀጥ ያደርጋል። ምሳሌው አካላዊ ንጽህናም ደግሞ በሰው ነፍስ ላይ የራሱን የመለወጥ ግፊት እንደሚያደርግ ነው።

በእግዚአብሔር ፊት የሰውነት ንጽህና እንዴት አስደሳች እንደሆነ፣ በነብያት ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት በተለይ ተጠናክሮ እንደተነገረ አስተውሉ፤ ቅዱሳት ጽሑፎቹ የማንኛውንም ንጹህ

---

[1]ቁርአን 25፡50 [2] ዮሐ. 3፡5

ያልሆነ ነገር መብላት ወይም መጠቀም ይከለክላሉና። ከእነዚህ ክልከላዎች መካከል አንዳንዶቹ ፍጹም ክልከላዎች የሆኑ፣ በሁሉም ላይ ተፈጻሚነት የነበሯቸው ነበሩ፤ የተወሰነውን ሕግ የተላለፈውም ማንም ሰው በአምላክ የተጠላ በአማኞቹም የተወገዘና ከአነርሱ የተባረረ ነበረ። ለምሳሌ፣ ፍጹም የተከለከሉ፣ እነሱን መፈጸሙ እንደ እጅግ በጣም ከባድ ኃጢዓት ይቆጠር የነበሩ ነገሮች፣ ከመካከላቸውም እጅግ አስጸያፊ ተግባሮች ከመሆናቸው የተነሣ ስማቸውን እንኳ መጥቀስ አሳፋሪ የነበሩት እንዲህ ያሉ ነበሩ።

ነገር ግንወዲያው ጉዳት የማያስከትሉ፣ ጎጂ ውጤቶቻቸው ቀስ በቀስ ብቻ የሚደርሱ ሌሎች የተከለከሉ ነገሮች አሉ፦ እነዚህም ተግባሮች ለአምላክ የሚያስጸይፉ በእርሱም ፊት አስወቃሾችና የሚያስጠሉ ናቸው። የእነዚህ ፍጹም ክልክልነት ግን፣ በጽሑፉ ውስጥ በግልጽ አልተገለጹም ነበር፤ ነገር ግን ለንጽህና ለሞራልና ለሰውነት፣ ለጤና መጠበቅና ከሱስ ነፃ ለመሆን ሲባል ከእነርሱ መራቁ አስፈላጊ ነው።

ከእነዚህ ከኋለኞቹ መካከል፣ ቆሻሻ፣ የሚከረፋና ግም የሆነ አደገኛ ሱስ፣ ጎጂነቱም ቀስ በቀስ ለሁሉም ግልጽ የሚሆነው፣ ትንባሆን ማጨስ ነው። እያንዳንዱ በሞያው የተካነ ሐኪም፣ ከትንባሆ ንጥረ-ነገሮች አንዱ አደገኛ መርዝ መሆኑን፣ የሚያጨሰውም ሰው ለብዙና ለልዩ ልዩ በሽታዎች የተጋለጠ መሆኑን ገልጿል፤ ይህም በሙከራ ተረጋግጧል። ከሐይጅንም አንፃር ሲታይ፣ ማጬስ አስጸያፊ እንደሆነ በግልጽ የሚነገረው ለዚህ ነው።

ባብ፣ በተልዕኮው መጀመሪያ ላይ፣ ትንባሆን በማያጠራጥር ሁኔታ ከልክሏል፤ ወዳጆችም እያንዳንዳቸውና ሁላችው መጠቀሙን ትተው ነበር። ነገር ግን በእነዚያ ጊዜያት ማንነትን በይፋ አለማስታወቅ የተፈቀደበት ጊዜ ስለነበር፣ ከማጬስ የተገለለ እያንዳንዱ አማኝም ለሥቃይ፣ ለስድብና ለሞትም ሳይቀር የተጋለጠ ስለነበር፣ ወዳጆች እምነታቸውን በይፋ ላለማስታወቅ፣ ያጬሱ ነበር።

ቆይቶ የአቅዳስ /እጅግ በጣም ቅዱስ/ መጽሐፍ ተገለጸ፤ በዚያ ትንባሆን ማጨስ ተለይቶ ስላልተከለከለ፣ አማኞች አልተውትም። ሆኖም፣ የተባረከው ውበት፣ እንደ ሚጠላው ሁል ጊዜ ይገልጽ ነበር። ደግሞ ምንም እንኳ፣ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት፣ ትንሽ ትንባሆ የሚያጨስበት ምክንያቶች የነበሩ ቢሆንም፣ ከጊዜ በኋላ ፈጽሞ አቆመ። እነዚያ በሁሉ ነገሮች እርሱን የተከተሉትም የተቀደሱ ነፍሶች መጠቀሙን አቆሙ።

ይህንንም ማለቴ፣ ትንባሆን ማጨስ፣ በአምላክ ፊት የተወገዘ፣ የተጠላ፣ የመጨረሻ ቆሻሻ፣ እንዲሁም፣ ቀስ በቀስ ይሁን እንጂ፣ ለጤንነት እጅግ በጣም ጐጂ ነው ማለቴ ነው። ደግሞም ገንዘብንና ጊዜን የሚያባክን ነው፤ የሚወስደውንም ሰው ለመርዛም ሱስ ተጠቂ ያደርገዋል። ስለዚህ ምርምርን ከተከተለ ምክንያትም፣ ከተሞክሮም አንፃር ሲታይ፣ ይህ ልማድ፣ ለእነዚያ በቃል ኪዳኑ ጽኑ ሆነው ለቆሙት የተከለከለ ነው፤ እሱን መተውም ለሰዎች ሁሉ እፎይታንና ሰላምን ያመጣል። ከዚህም አልፎ፣ የማይገማ አፍና ያልቆሸሹ ጣቶች፣ ከግማትና ከአስጸያፊ ሽታ ነፃ የሆነ ፀጉር እንዲኖረን ያስችላል። ይህን መልዕክት ሲቀበሉ ወዳጆች ያለጥርጥር በማንኛውም መንገድ /ቀስ በቀስ/ ረዘም ባለ ጊዜም እንኳ ቢሆን፣ ይህን አደገኛ ልማድ ይተዋሉ። ተስፋዬ ይህ ነው።

ኦፒዬም ደግሞ፣ መጥፎና የተረገመ ነው። እግዚአብሔር በተጠቃሚው ላይ ከሚያወርደው ቅጣት እርሱ ራሱ ይጠብቀን። በእጅግ በጣም ቅዱስ መጽሐፍ ግልጽ ጽሑፍ መሠረት፣ የተከለከለ ነው፤ መጠቀሙም ፍጹም ተወግዟል። ምክንያትን የተከተለ ምርምር፣ ኦፒዬምን ማጨሱ እንደ አንድ ዓይነት የአእምሮ መቃወስ እንደሆነ ያሳያል፤ ሙከራም ወሳጁ ከሰው ዓለም ሙሉ በሙሉ የተዘጋ መሆኑን ያረጋግጣል። የሰው ዘር መሆን የሆነውን መሠረት ራሱን ወደ ትቢያ የሚለውጠውን፣ ወሳጁንም ሰብአዊነቱን ለዘለዓለም እንዲቀማ የሚያደርገውን፣ እንዲህ ያለውን አሰቃቂና አሳፋሪ ተግባር ከመፈጸም

አምላክ ሁሉንም ይጠብቅ። አፒዬም የወሳጁ ሕሊና እንዲሞት፣ አዕምሮውም እንዲደመሰስ፣ የመገንዘብ ችሎታውም እንዲሸረሽር በነፍስ ላይ ይጣበቃልና። በሕይወት የነበረውን ወደ ሙት ይለውጣል። የተፈጥሮን ሙቀት ያጠፋል። አፒዬም ከሚያደርሰው የባሰ ጉዳት ሊታሰብ አይችልም። እነዚያ ስሙን እንኳ ከቶ የማያነሡ የታደሉ ናቸው፤ እንግዲህ ተጠቃሚው እንዴት ያለ ዕድለ ቢስ እንደ ሆነ አስቡ።

እናንተ የአምላክ አፍቃሪዎች ሆይ! በዚህ በፍጹም ኃያሉ አምላክ ዕውደት፣ ኃይል መጠቀምና ኃይል፣ ማስገደድና ጭቆና፣ ሁሉም ተወግዘዋል። ሆኖም፣ ምናልባት የሰው ዘር ከዚህ ከቸነፈሮች ሁሉ እጅግ በጣም ከባድ ከሆነው ነፃ ይወጣ ዘንድ፣ አፒዬምን መጠቀም በፈለገው በማንኛውም መንገድ እንዲቆም ማድረግ ግዴታ ነው። ያለበለዚያ፣ ለጌታው ያለበትን ኃላፊነት በሚያጓድል በማንም ሰው ላይ 'ዋ' ያለበት ሥቃይና ጸጸት![1]

መለኮታዊ ጠባቂ ሆይ! የባሃን ሕዝብ በማንኛውም ረገድ ቅድስናንና ንጽህናን አጎናጽፋቸው። ከርኩሰት ሁሉ ነፃ እንዲሆኑ፣ ከሱሶችም ሁሉ እንዲላቀቁ ፈቃድህ ይሁን። ንጹህና ነፃ፣ ጤነኞችና በሰውነት ከመቆሸሽ ነፃ የሆኑ፣ በቅዱስ ደጅ-ሰላምህ ለማገልገልና ከጌታቸው ጋር ለመዛመድ ብቁ ሆነው ለመኖር እንዲችሉ፣ ምንም አስጸያፊ ድርጊት ከመፈጸም አድናቸው፤ ከእያንዳንዱ ክፉ ልማድ ሰንሰለትም አላቅቃቸው። ከሚያሠክሩ መጠጦችና ከትንባሆ ነፃ አውጣቸው፤ አድናቸው። ከዚህ ዕብደት ከሚያመጣው አፒዬም አደጋ አውጣቸው። ልክ፦ *'በመጠጥ ግምጃ ቤትህ ያለህ ሁሉ የፍቅሬን ጥማት አያስታግሥምና፣ የጽዋ አሳላፊ ሆይ፣ ከመንፈስ ወይን ጠጅ እንደ ባሕር የሆነውን ሙሉ ዋንጫ አምጣልኝ!'* እንዳልከው ነውና፣ ከመለኮታዊ ፍቅር ምሥጢራዊ ጽዋ ረክተው እንዲጠጡ፣ ፍጹም ክብር ወደተመላውም ዓለም ሠርክ ይበልጥ

[1] ቆርን 39፡57

እየተጠጉ የመሄድን ሐሴት እንዲያውቁ፣ በቅድስና ጣፋጭ ጣዕም እንዲደሰቱ አድርጋቸው።

እናንት የአምላክ ተወዳጆች ሆይ! ከማጨስ፣ ከሚያሰክር መጠጥና ከኦፒዮም መራቅ እንዴት ወደ ጤናና የንቃት ኃይል፣ ወደ አዕምሮ ስፋትና ብልህነት፣ እንዲሁም ወደ አካል ጥንካሬ እንደሚመራ ተሞክሮ አሳይቷል። በአሁኑ ጊዜ፣ ትንባሆ፣ የሚያሠክር መጠጥና ኦፒዮም አጥብቆ የሚሸሽ አንድ ሕዝብ[1] አለ። ይህ ሕዝብ በአካል ጥንካሬና በጉልበት ብርታት፣ በጤና፣ በውበትና በደም ግባት ከሌላው ሕዝብ ጋር ሲነፃፀር በጣም የላቀና ወደር የሌለው የበላይነት አለው። ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከሌላው ጎሳ እስከ አሥር ሰው መቋቋም ይችላል። ይህ ሁኔታ በመላው ሕዝብ ውስጥ ያለ እውነት መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም ማለት አባል ለአባል ሲወዳደር እያንዳንዱ የዚህ ኅብረተ-ሰብ ሰው ከሌላው በማንኛውም ረገድ የበላይነት አለው ማለት ነው።

ስለዚህ፣ አብዱል-ባሃ ከሁሉም በላይ የወደደው ንጽህናና ቅድስና የባሃን ሕዝብ ከሌሎች ለይቶ እንዲያሳውቅ፣ በእያንዳንዱም የልቀት ዓይነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሌላው የሰው ዘር ሁሉ እንዲበልጥ፤ በውሳጣዊውም በውጪአዊውም ረገድ ከተቀሩት የበላይሆኖ እንዲገኝ፤ በንጽህና፣ በእንከን አልባነት፣ በአዕምሮ ረቂቅነትና በጤና አጠባበቅ የግንባር ቀደም አዋቂዎች ውስጥ መሪ እንዲሆን፣ ከመጥፎ ልማድ ነፃ በመሆን፣ በዕውቀቱ፣ ራሱን በመቆጣጠር ረገድ ከንጹሃን፣ ከነፃዎችና ከጠቢባን መካከል የመጀመሪያ እንዲሆን፣ ሁላችሁም ከፍተኛ ጥረት አድርጉ።

## (171)

ከበሽታ ለመዳን ሁለት መንገዶች አሉ፣ ዓለማዊና መንፈሳዊ መንገዶች። የመጀመሪያው በሐኪሞች ሕክምና ነው፤ ሁለተኛው፣

[1] በህንድ አገር የሚገኝ የሲክ ሕዝብ

መንፈሳውያን ወደ እግዚአብሔር ጸሎት በማድረስ፣ ፊታቸውንም ወደ እርሱ በመመለስ በሚያደርጉት ልመና የሚገኝ ነው። ሁለቱም ዘዴዎች በጥቅም ላይ መዋልና መለመድ አለባቸው።

በቁሳዊ ምክንያት የሚደርሱ ሕመሞች በሐኪሞች በሕክምና መድኃኒቶች መታከም አለባቸው፤ እነዚያ በመንፈሳዊ ምክንያት የሚመጡት በመንፈሳዊ ዘዴዎች ይጠፋሉ። ይኸውም በሥቃይ፣ በፍርሐት፣ በአዕምሮ ስሜት የመጣ በሽታ ከዓለማዊ ሕክምና ይልቅ በመንፈሳዊ ዘዴ በተሻለ ውጤት ይፈወሳል። ስለዚህ፣ ሁለቱንም የማከሚያ ዘዴዎች መከተል ይገባል፤ አንዱ ሌላውን አይቃረንምና። እነዚህም አገልጋዮቹከዚህ ዓይነት ሕክምና ጥቅም ያገኙ ዘንድ፣ የሕክምናን ሳይንስ ከገለጸው፣ ከአምላክ ምሕረትና ልግሥና የመጡ ስለሆኑ፣ ዓለማዊ መድኃኒቶችንም መቀበል አለብህ። ለመንፈሳዊ ሕክምናም እኩል ትኩረት መስጠት አለብህ፤ ድንቅ ውጤቶች ያስገኛሉና።

አሁን የሰውን ልጅ ከማንኛውም በሽታ ፈውሶ እውነተኛውን ፈውስ ለማግኘት የሚያስችለውና የመለኮታዊውን መንግሥት ጤንነት የሚሰጠው ምን እንደሆነ ለማወቅ ብትፈልግ የአምላክ ሕግጋትና ትምህርቱ መሆኑን እወቅ። ሃሳብህንም በእነሱ ላይ አትኩር።

## (172)

የሰው ዘር ወዳጅ ሆይ! ደብዳቤህ ደርሷል፤ አምላክ ይመሥስገንና ስለጤንነትህና ስለደህንነትህ ይናገራል። በፊተኛው ደብዳቤህ ከጻፍከው መልስህ፣ በራስህና በወዳጆች መካከል የፍቅር ስሜቶች መመሥረት ላይ እንደሆኑ ይመስላል።

ሰው በእያንዳንዱ የሰው ዘር ለመመሥገን ብቁ የሚሆነውን ብቻ ማየት አለበት። ይህ ከተደረገ፣ ማንኛውም ሰው የመላው የሰው ዘር ወዳጅ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሰዎችን ከሥሕተታቸው አንፃር ብንመለከት፣ በዚያን ጊዜ ለእነርሱ ወዳጅ መሆን አስቸጋሪ ተግባር

ይሆናል።

የዓለም ሕይወት ለእርሱ መስዋዕት፣ ይሁንና፣ በክርስቶስ ጊዜ አንድ ቀን፣ በጥንብ፣ በሚከረፋ፣ በአስቀያሚ፣...አካላቱ በሰብሰው በመለያየት ላይ በሚገኙ፣ በአንድ የውሻ ሬሣ አጠገብ አለፈ። ከእርሱ ጋር ከነበሩት አንድ፡- *'ግማቱ እንዴት መጥፎ ነው!'* አለ። ሌላውም፡- *'እንዴት ትውከት የሚያመጣ! እንዴት አስጸያፊ ነው!'* አለ። ነገሩን ለማሳጠር፣ እያንዳንዳቸው ለዝርዝሩ የሚጨምሩት አንዳንድ ነገር ነበራቸው።

ከዚያ በኋላ ግን ክርስቶስ ራሱ ተናገረ፤ እንዲህም አለ፡- *'የዚያን ውሻ ጥርሶች ተመልከቱ! እንዴት የሚያንፀባርቅ ነጭ ነው!'*

የመሢሑ ኃጢአት ሸፋኝ ዓይን ለትንሽም ጊዜ በዚያ ጥንብ አስጠሊነት ላይ አላረፈም። በዚያ ውሻ ሬሣ ያልተበላሸ ክፍል የጥርሶቹ ክፍል ብቻ ነበር፤ የሱስም በንጣታቸው ተመለከተ።

ስለዚህ፣ ዓይናችንን ወደሌሎች ሰዎች በምናዞርበት ጊዜ ጉድለታቸውን ሣይሆን ብልጫ የሚያሳዩበትን ማየት ይኖርብናል።

ለአምላክ ምሥጋና ይግባውና፣ የአንተ ዓላማ የሰውን ዘር ደህንነት ለማዳበርና ነፍሶች ጉድለቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ለመርዳት ነው። ይህ መልካም ዓላማ አሥመሥጋኝ ውጤቶች ያመጣል።

## (173)

እያንዳንዱ ነፍስ ያለምንም ልዩነት ዘለዓለማዊ ሕይወት ያገኛልን? ላልከው ጥያቄህ፡- ዘለዓለማዊ ሕይወት የእነዚያ ከአምላክ የሕይወት መንፈስ የተተነፈሰባቸው ነፍሶች ብቻ መሆኑን እወቅ። ከእነዚህ በስተቀር ሌሎች ሁሉ፣ ልክ ክርስቶስ በወንጌል እንደገለጸው... ሕይወት አልባ፣ ሙታን ናቸው። ጌታ ዓይኖቹን የከፈተለት ሰው የሰዎች ነፍሶች ከሥጋቸው ከተለዩ በኋላ በሚይዙዋቸው ደረጃዎቻቸው ያያቸዋል። ሕያዋን በጌታቸው ከልሎች ውስጥ

ሲያድጉና ሲያብቡ፣ ሙታን ደግሞ ዘለዓለማዊ ኩነኔ ባለበት በታችኛው አዘቅት ውስጥ ሲሰጥሙ ያገኛቸዋል።

በሚወለድበት ጊዜ እያንዳንዱ ነፍስ ንጹህና ቅዱስ ሆኖ በእግዚአብሔር ባሕርይ የሚፈጠር መሆኑን እወቅ። ሆኖም፣ በኋላ፣ ግለ-ሰቦቹ እያንዳንዳቸው ከዚህ ዓለም በሚገበዩዋቸው መልካም ወይም መጥፎ ምግባሮች መጠን ይለያያሉ። ምንም እንኳ ሕያዋን ፍጡሮች በተፈጥሯቸው በየማዕረግ ወይም በየደረጃ የተፈጠሩ በመሆናቸው በችሎታቸው ይዘት የተለያዩ ቢሆኑ፣ እያንዳንዱ ግለ-ሰብ ቅዱስና ንጹህ ሆኖ ይወለዳል፤ ከዚያ በኋላ ብቻ የተበላሸ ይሆን ይሆናል።

በተጨማሪም፣ ምንም እንኳ ፍጡሮች በደረጃዎች የተለያዩ ቢሆኑ፣ ሁሉም መልካም ናቸው። የሰውን አካል፣ ቅልጥሞቹን፣ ብልቶቹን፣ ዓይኖቹን፣ ጆሮዎቹን የማሽተቻና የመቅመሻ ሕዋሳቶቹን፣ እጆቹን ጥፍሮቹን ተመልከት። ምንም እንኳ በእነዚህ የአካል ክፍሎች ሁሉ መካከል ልዩነት ቢኖር፣ እያንዳንዱ ክፍል በራሱ ተፈጥሮ ውስን ክልሎች ውስጥ ሆኖ፣ በኅብረት በሚሠራው ሙሉ አካል ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ሥራውን መሥራት ቢያቅተው መፈወስ አለበት። መድኃኒት ካልተገኘለት ያ የታመመው ክፍል መወገድ አለበት።

## (174)

እነዚያ፣ በዚህ ቀን፣ ወደ መለኮታዊ መንግሥት የሚገቡና ዘላለማዊ ሕይወት የሚቀዳጁ ነፍሶች፣ ምንም እንኳ በሥጋ በመሬት ላይ ቢኖሩም፣ በእውነቱ ግን በመንግሥተ-ሰማያት ዓለም ውስጥ ይመጥቃሉ። አካሎቻቸው በምድር ላይ ይመላለሳሉ፤ ነገር ግን መንፈሶቻቸው በሰፊው ጠፈር ውስጥ ይጓዛሉ። አስተሳሰብ በሰፋና በበራ ቁጥር፣ የሙብረር ኃይል አግኝቶ ሰውን ወደ አምላክ መንግሥት ያሸጋግረዋልና።

(175)

አንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆይ! በደረሰብህ ሥቃይና መከራ አትዘን። ሥቃዮችና መከራዎች ሁሉ ለሰው የተፈጠሩት በጣም የተቆራኘበትን ይህን አላፊ ዓለም ከራሱ አሽቀንጥሮ ለመጣል እንዲችል ነው። ከባድ ፈተናዎችንና ችግሮችን በሚቀምስበት ጊዜ ተፈጥሮው ያፈገፍጋል፤ ከሥቃዮችና ከመከራዎች የተቀደሰውንም ዘለዓለማዊውን ዓለም ይመኛል። ብልህ የሆነው ሰው የሚያደርገው እንዲህ ነው። እርሱ በመጨረሻ መራራ ከሆነው ጽዋ ደግመኛ ከቶ አይጠጣም፤ እንዲያውም ከዚያ ጋር ተፃራሪ በሆነው፣ ንጹህና የጠራ ውሃ ጽዋ ይፈልጋል። ከዚያ በመርዝ ከተለወሰ ማር አይቀመስም።

አንተ ለመፈተንህና እንዲህ ያለውን ፈተና በማየትህ አምላክን አመሥግን። ታጋሽና አመሥጋኝ ሁን። ፊትህን ወደ መለኮታዊ መንግሥት አዙርና ይቅር ባይ ባሕርያትን ለመገብየትና የበራህ ለመሆን፣ የመግሥተ-ሰማያትንና የጌታን ባሕርያት ለመገብየት ተጣጣር። ለዚህ ዓለም ደስተና ለምቾትዋ ስሜት የሌለህ ለመሆን፣ ለቃል ኪዳኑ ጥብቅና ጽኑ ሆነህ ለመቆየትና የአምላክን እምነት ለማሰራጨት ጥረት አድርግ።

ይህ ለሰው ደስታን የሚያስገኝ፣ የክብሩና የመዳኑ ምክንያት ነው።

(176)

የጌታን መንገድ ተከተል፤ ጆሮዎች ለመስማት የማይችሉትንም አትናገር፤ እንዲህ ያለው ንግግር ለትናንሽ ሕፃናት እንደሚሰጥ እንደሚያስጎመጅ ምግብ ነውና። ምግቡ የፈለገውን ያህል የሚጥም፣ ብርቅና የበለፀገ ቢሆንም፣ ጡት ባልጣለ ሕፃን የማንሸራሸሪያ አካላት ሊፈጭ አይችልም። ስለዚህ መብት ላለው ለእያንዳንዱ ሰው ለእርሱ የተለካ መጠን ይሰጠው። ‘አንድ ሰው

*የሚያውቀው ነገር ሁሉ ከጊዜው ጋር እንደሚስማማ ሊቆጠር አይችልም፤ ከጊዜው ጋር ተስማሚ የሆነውም ንግግር ሁሉ ለእነዚያ ለሚሰሙት የመረዳት አቅም ተስማሚ እንደሆነ ሊታሰብ አይችልም።’*

በሥራህ ወቅት መከተል ያለብህ ትልቁ ጥበብ እንዲህ ያለ ነው። ስለዚህ በሁሉም ሁኔታዎች የተግባር ሰው ለመሆን ብትሻ፣ አትርሳ። በመጀመሪያ በሽታውን መርምረህ እወቅ፣ ሕመሙንም ለይ፣ ከዚያም መድኃኒቱን እዘዝ። የአዋቂ ሐኪም ሥሕተት የሌለበት ዘዴ ይህ ነውና።

## (177)

አስተማሪው፣ በሚያስተምርበት ጊዜ፣ ልክ እንደ እሳት ነበልባል፣ የመሳብ ኃይል እንዲፈጥርበትና የራስ ወዳድነትንና የምድራዊ ፍላጎትን ስሜት ሽፋን እንዲያቃጥል፣ እርሱ ራሱ ሙሉ በሙሉ መቀጣጠል አለበት። እንዲሁም ሌሎች በመንፈሳዊ ረገድ እንዲጠቀሙ፣ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉና ኢምንት እንዲሆኑ፣ እርሱ በሰማይ ሠራዊት ዜማ እንዲያስተምር ፍጹም ትሑት መሆንና ራሱን ዝቅ ማድረግ አለበት። ያለበለዚያ የእርሱ ማስተማር ውጤት አይኖረውም።

## (178)

አቤቱ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! የእውነተኛ አፍቃሪዎችን ግንባር አብራ። በመልአካዊ የተረጋገጠ ድል ሠራዊትም ደግፋቸው። የእምነትህን ደህንነት በመጠበቅ፣ እምነታቸውን በአንተ ትዝታ ላይ በማድረግ፣ ልቦቻቸውን ለአንተ ፍቅር በመስጠት፣ ውበትህን በማወደሥና አንተን የሚያስደስቱበትን መንገድ በመፈለግ፣ ለሃብታቸው ሳይሳሱ የለገሥካቸውን ሁሉ በኀዳናህ በማዋላቸው፣ እግሮቻቸውን በቀጥተኛ መንገድህ ላይ አበርታላቸው፤ ከጥንታዊው

ቸርነትህም የቡራኬዎችህን በሮች በፊቶቻቸው ከፈትላቸው።

ጌታዬ ሆይ! የተትረፈረፈ ድርሻ፣ የተመደበ ካሣና የተረጋገጠ ሽልማት አዘዝላቸው።

በእውነቱ አንተ ደጋፊው፣ ረዳቱ፣ ቸሩ፣ በረከት የተመላው፣ ዘለዓለም ሰጪው ነህና።

## (179)

ይህን ጸሎት ራስን ዝቅ በማድረግና በጋለ ስሜት የሚያደርግ ማንም ሰው፣ ለዚህ አገልጋይ ደስተኝነትንና ሐሴትን ያመጣል፤ ልክ እርሱን በግንባር እንደማግኘት ይሆናል።

እርሱ ፍጹም ክብር የተመላው ነው!

አቤቱ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! በዝቅተኝነትና በእንባ በተሞላሁ ሁኔታ፣ ከምሁራን ዕውቀትና ከአወዳሾችህ ውዳሴ ሁሉ በላቀው ደጅ-ሰላምህ አቧራ ላይ ግንባሬን በመድፋት፣ ተማፃኝ እጆቼን ወደ አንተ አነሳለሁ። በጸጋህ፣ በደጃፍህ ትሑትና ዝቅተኛ የሆነውን አገለጋይህን በምሕረትህ ዓይን ተመልከተው፤ በዘለዓለማዊውም የጸጋህ፣ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥመው።

አቤቱ ጌታ ሆይ! እርሱ ምስኪንና ዝቅተኛ አልጋይህ ነው፤ በአንተ ተመስጦ እየተለማመጠህ፣ በእጅህ ውስጥ ያለ ምርኮኛ በመሆን ወደ አንተ በጋለ ስሜት እየጸለየ፣ እምነቱን በአንተ ላይ በመጣል በፊትህ እንባውን እያዘነበ፣ ወደ አንተ እየተጣራ እንዲህ በማለት ይማፀንሃል፡-

አቤቱ ጌታ አምላኬ ሆይ! ተወዳጆችህን አገለግል ዘንድ ጸጋህን ስጠኝ። ለአንተ አገልጋይ እንድሆን አበርታኝ። በቅድስናህ መንበር አንተን በማምለክና ለታላቅነት መንግሥትህ በመጸለይ ብርሃን ግንባሬን አብራው። በመንግሥተ-ሰማያት መግቢያ በርህ ላይ ራሴን ከመውደድ የነፃሁ፣ በቅዱስ ክልልህም ውስጥ ከሁሉ ነገሮች የተላቀቅሁ እንድሆን እርዳኝ። ጌታ ሆይ! ከራስ ወዳድነት ከመራቅ

ጽዋ እጠጣ ዘንድ ስጠኝ፤ በካባውም አልብሰኝ፤ በውቅያኖሱም ውስጥ አስጥመኝ። የፍጹም ከፍተኛው ክብር ጌታ ሆይ፣ በተወዳጆችህ መንገድ ላይ እንዳለው አቧራ አድርገኝ፤ በመንገድህ በምርጦችህ እርምጃዎች ለተቀደሰው አፈር ነፍሴን እንድሰዋ ፈቃድህ ይሁን።

አገልጋይህ በማለዳና በውድቅት በዚህ ጸሎት ይጠራሃል። ጌታ ሆይ! የልቡን ምኞች አሟላለት፤ እምነትህንና አገልጋዮችህን ያገለግል ዘንድ፣ ልቦናውን አብራለት፤ ልቡን አስደስትለት፤ ብርሃኑንም አቀጣጥልለት።

አንተ ሰጪው፣ አዛኙ፣ እጅግ በጣም ለጋሡ፣ ጸጋ የተመላው፣ መሐሪው፣ ሩኅሩኁ ነህና።

<u>ለቀረቡት አንዳንድ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች</u>

<u>ከሚባለው መጽሐፍ</u>

(180)

ስለባብ[1] ደግሞ፤ … ነፍሴ የእርሱ መስዋዕት ትሁንና! በወጣትነት ዕድሜው፣ ማለትም፣ ለተባረከው ሕይወቱ ሃያ አምሥተኛ ዓመት በደረሰ ጊዜ፣ እምነቱን ለማወጅ ተነሣ። በምንም ትምህርት ቤት እንዳልተማረ፣ ከምንም አስተማሪ ዕውቀት እንዳልገበየ ሺአውያን በሙሉ አምነዋል፤ የሺራዝ ሕዝብም በሙሉ ስለዚህ ይመሠክራሉ። ይሁን እንጂ፣ እርሱ እጅግ በጣም በተሟላ ዕውቀት ተላብሶ፣ ድንገት በሕዝቡ ፊት ተገኘ። እርሱ ነጋዴ ቢሆንም፣ የፋርስን ኡላማዎች[2] ሁሉ የሚይዙትን አሳጣቸው። ብቻውን፣ ሊታሰብ ከሚቻል ውጪ በሆነ ሁኔታ፣ለሃይማኖት አክራሪነቱ በታወቀው በፋርስ ሕዝብ መካከል እምነቱን አስፋፋ። ይህ ታላቅ ነፍስ በጣም ከፍተኛ በሆነ ኃይል ከመነሣቱ የተነሣ የፋርስን አገር የሃይማኖት፣ የግብረ-ገብነት፣ የሁኔታዎች የልማዶችና የባሕሎች መሠረቶች አናጋ፤ አዳዲስ ደንቦች፣

---

[1]ሃድራት-ኢ-አላህ (ልዑሉ፣ ከፍተኛነቱ፣ ክቡርነቱ) በሚለው ስያሜው ፈንታ እዚህ ይበልጥ በታወቀበት ስያሜው፣ ማለትም ባብ በሚለው ተጠርቷል።

[2]የእስላም ሃይማኖተ ዶክትሮች

አዳዲስ ሕግጋትና አዲስ ሃይማኖት መሠረተ። ምንም እንኳ የመንግሥቱ ታላላቅ ሰዎች፣ ከጥቂቶች በቀር ሁሉም ካህናትና የሕዝቡ ታዋቂ ሰዎች፣ ሊያጠፉትና ሊደመስሱት ቢነሡበትም፣ እርሱ ብቻውን ተቋቋማቸው፤ መላውንም ፋርስ አንቀሳቀሰ።

ብዙ ካህናትና የታወቁ ሰዎች እንዲሁም ሌሎች ሰዎች፣ በእርሱ እምነት ውስጥ ሐሴት በተመላበት ሁኔታ ሕይወታቸውን ሰውተዋል፤ ወደ ሰማዕትነትም መስከ ገሥግሠዋል።

መንግሥቱ፣ አገሩ፣ ሃይማኖታዊ ዶክተሮችና ታላላቅ ሰዎች፣ የእርሱን ብርሃን ለማጥፋት ተመኙ፤ ግን አልቻሉም። የእርሱ ጨረቃ ወጣች፤ የእርሱ ኮከብ በራች፤ የእርሱ መሠረቶች ጥብቅ በሆነ ሁኔታ ተመሠረቱ፤ የእርሱም የንጋት ሥፍራ አንፀባራቂ ሆነ። እርሱ ብርሃን ላላገኙት ብዙሃን መለኮታዊ ትምህርት ሰጠ፤ በፋርስ ሕዝብ አስተሳሰብ፣ ግብረ-ገብነት፣ ባሕሎችና ሁኔታዎች ላይ ግሩም ውጤቶች አመጣ። ለተከታዮቹ ስለባሃ ፀሐይ ግልጸት አስደሳች ዜና አወጀ፣ እንዲያምኑም አዘጋጃቸው።

በአንድ ወጣት ነጋዴ የእንዲህ ዓይነቶቹ ድንቅ ምልክቶችና ታላላቅ ውጤቶች መገኘት፣ በሕዝቡ አእምሮና በነበሩት አስተሳሰቦች ላይ የተፈጠሩት ውጤቶች፣ የዕድገት መሠረቶች፣ የሥራ መቃናትና የብልጽግና መሠረተ-ሃሳቦች መደራጀት፣ እርሱ ፍጹም መምህር እንደነበረ የሚያሳዩ፣ ለሁሉም ታላላቅ ማስረጃዎች ናቸው። ትክክለኛ ሰው ይህንን ለማመን ፍጹም አያመነታም።

## (181)

ባሃኡላህ[1] የፋርስ ግዛት በጥልቀት ሥር በሰደደ ኋላቀርነትና ድንቁርና ውስጥ በሰጠመበትና በእጅግ በጣም ጭፍን አክራሪነት ውስጥ በወደቀበት ጊዜ ተከሰተ።

በአለፉት ምዕተ ዓመታት ስለፋርስ ግብረ-ገብነት፣ ባሕልና

[1]የተባረከው ውበት፣ ለባሃኡላህ የተሰጠ ስያሜ ነው። ከሁሉ በፊት የነበረው ውበት ወይም የጥንቱ ውበት ሌላው ስያሜው ነው። እዚህ ግን በምዕራብ በታወቀበት ባሃኡላህ በሚለው

አስተሳሰቦች ውድቀት በአውሮጳውያን ታሪክ ውስጥ ሰፊ ዝርዝር እንዳነበባችሁ ጥርጥር የለውም። እነሱን መድገሙ አይጠቅምም። በአጭሩ፣ ፋርስ በጣም ከመውደቋ የተነሣ፣ ይህቺ ጥንት በጣም የተከበረችና የሠለጠነች አገር፣ አሁን የተበላሸች፣ የተንኮታኮተችና የተበጣበጠች መሆኗ፣ ነዋሪዎችዋም ክብራቸውን ማጣታቸው፣ ለውጭ አገር ጐብኚዎች የሚያሳዝን ጉዳይነበር እንላለን።

ባሃኦላህ የተከሰተው በዚህ ጊዜ ነበር። አባቱ ከኡላማዎች አንዱ ሳይሆን፣ ከሚኒስትሮች አንዱ ነበር። የፋርስ ሕዝብ ሁሉ እንደሚያውቀው፣ ባሃኦላህ በምንም ትምህርት ቤት ገብቶ ከቶ አልተማረም፤ ከኡላማዎች ወይም ከተማሩ ሰዎችም ጋር ግንኙነት አልመሠረተም። የሕይወቱ የመጀመሪያ ክፍል በእጅግ በጣም ደስተኛነት አለፉ። የእርሱ ወዳጆችና ጓደኞች የተማሩ ሰዎች ሳይሆኑ፣ የላቀ ማዕረግ የነበራቸው የፋርሰ ሰዎች ነበሩ።

ወዲያው ባብ እንደተገለጸ፣ ባሃኦላህ፣ *'ይህ ታላቅ ሰው የጽድቅ ጌታ ነው፤ ሁሉም በእርሱ ማመን አለበት፤'* ብሎ ተናገረ። መስተዳድሩ ባብን እንዲቃወምና እንዲቋቋመው የአገሩሃይማኖት ኡላማዎች፣ የፋርስን መንግሥት ቢያስገድዱትም፣ ከዚህም አልፈው የእርሱ (የባብ) ተከታዮች እንዲፈጁ፣ እንዲዘረፉ፣ እንዲሠቃዩና እንዲባረሩ አዋጅ አውጥተው የነበሩ ቢሆንም፣ እርሱ ባብን ለመርዳት ተነሣ፤ ስለእርሱ እውነትነትም ብዙ ማረጋገጫዎችንና ተጨባጭ ማስረጃዎችን አቀረበ። በየክፍላተ-አገሩም ሁሉ የባብን ተከተዮች መግደል፣ ንብረታቸውን ማቃጠል፣ መዝረፍ፣ በሴቶችና በልጆችም ላይ እንኳ ሳይቀር አደጋ መጣል ጀመሩ። ይህም ሳይገታው፣ ባሃኡላህ የባብን ቃል በእጅግ በጣም ታላቅ ጥንካሬና ኃይል ለማወጅ ተነሣ፤ እርሱ ለአንዳፍታም አልተሸሸገም፤ እርሱ ከጠላቶቹ ጋር በግልጽ ይቀላቀል ነበር። ማስረጃዎችንና ማረጋገጫዎችን በማቅረብ ሥራ ተሠማራ፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል አዋጅ ነጋሪም ታወቀ ነበር።

በብዙ አጋጣሚዎች እጅግ በጣም ከባድ የሆኑ ችግሮችን ተቋቋመ፤ በእያንዳንዱም ወቅት ሰማዕት የመሆንን አደጋ ተጋፈጠ። እርሱ በሰንሰለት ታሠረ፤ ከምድር ወለል በታች በተሠራ እሥር ቤት ውስጥ እንዲወሰን ተደረገ። ሰፊ ንብረቱና በውርስ ያገኘው ሃብት ተዘረፈ፣ ተወረሰ። አራት ጊዜ ከአገር ወደ ሌላ አገር እንዲሰደድ ተደርጓል፤ እረፍትም ያገኘው *'በእጅግ በጣም ታላቁ እሥር ቤት'* [1] ብቻ ነበር።

ይህም ሁሉ ሆኖ የእግዚአብሔርን እምነት ታላቅነት ማወጁን ለአንዳፍታም አቋርጦ ከቶ አያውቅም። እርሱ በጣም ትልቅ መልካም ምግባር፣ ዕውቀትና ፍጹምነት ከማሳየቱ የተነሣበመላው ፋርስሕዝብ ተደናቂ ሆነ። እንዲህም ከመሆኑ የተነሣበቴህራን፣ በባግዳድ፣ በቁስጥንጥኒያ፣ በሩሜሊያ፣ በአቆርም እንኳ ሳይቀር፣ እርሱ ዘንድ የቀረቡ ምሑራንና የሣይንስ ሰዎች፣ ወዳጆችም ሆኑ ጠላት፣ ላቀረቡት ለማንኛውም ጥያቄ፣ አጅግ በጣም አርኪና አሳማኝ መልስ ሳይቀበሉ ቀርተው ከቶ አያውቁም። ሁሉም እርሱ በሁሉም ፍጹምነቶች ብቸኛና የተለየ እንደነበረ ብዙ ጊዜ ተናገረዋል።

በባግዳድ ብዙ ጊዜ አንዳንድ የእስላም ኡላማዎች፣ የአይሁድ ራቢዎችና ክርስቲያኖች ከአውሮጳ ከመጡ ሊቃውንት ጋር በተባረከው ግንኙነት በአንድ ላይ ይገናኙ ነበር፡- እያንዳንዳቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ ነበራቸው። ምንም እንኳ የተለያየ የባሕል ደረጃ የነበሯቸው ቢሆኑም እያንዳንዳቸው በቂና የሚያሳምን መልስ በመስማት ረክተው ይሄዱ ነበር። በካርቢላና በናጃፍ የነበሩ የፋርስ ኡላማዎችም እንኳ ከመልዕክት ጋር ወደ እርሱ የላኩት አንድ ጠቢብ ሰው ነበር፤ ስሙም ሙላ ሃሰን አሙ ነበር። እርሱ ቅዱሱ በነበረበት ዘንድ መጣ፤ በኡላማዎቹም ስም በርካታ ጥያቄዎች አቅርቦ፣ ባሃኡላህ መልስ ሰጠባቸው። ከዚያም ሃሰን አሙ እንዲህ አለ፡- 'ኡላማዎቹ ያለምንም ማመንታት የባሃኡላህን ዕውቀትና መልካም ምግባር ይቀበላሉ፤ ቃላቸውንም ይሰጣሉ፤ እንዲሁም በሁሉም ዕውቀት ወደር

---

[1] በመጀመሪያ ወደ ባግዳድ፣ ቀጥሎ ወደ ቁስጥንጥኒያ፣ ከዚያም ወደ አድሪያኖፕል፣ በመጨረሻም ወደ አቆር እሥር ቤት ተሰደደ።

ወይም አቻ እንደሌለው በአንድ ድምጽ ያምናሉ፤ ደግሞም ይህንን ዕውቀት አጥንቶት እንዳልሆነ ወይም እንዳልገበ የግልጽ ነው፤ ይሁን እንጂ ኡላማዎቹ፣ *“በዚህ አልረካንም፤ በእርሱ ጠቢብነትና ፃድቅነት ምክንያት ብቻ የእርሱን መልዕክት እውነተኛነት አንቀበልም። ስለዚህ ልቦቻችንን ለማርካትና ለማረጋጋት ተዓምር እንዲያሳየን እንጠይቃለን”* ይላሉ።’

ባሃኡላህ መለሰ፡- *“እግዚአብሔር ፍጡሮቹን መፈተን አለበት እንጂ እነሱ አምላክን መፈተን ስለማይገባቸው፣ ይህን ለመጠየቅ መብት ባይኖራችሁም፣ ይህን ጥያቄ ፈቅጄ እቀበላለሁ። የአምላክ እምነት፣ በየእለቱ አዳዲስ የጊዜ ማሳለፊያ የሚጠየቅበት፣ በየሰዓቱ ለትርኢት የሚቀርብ ትያትር አይደለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ የእግዚአብሔር እምነት ልክ እንደ ሕፃን ጨዋታ በሆነ ነበር።”*

‘ስለዚህ ኡላማዎቹ ተሰብስበው በአንድ ድምጽ የተስማሙበት ተዓምር መምረጥና፣ ከዚህ ተዓምር መከናወን በኋላ ስለእኔ ጥርጣሬ ማሳየት እንደሚያቆሙ፣ ሁላቸውም ስለ እምነቴ እውነትነት የሚቀበሉና የሚመሠክሩ መሆናቸውን መጻፍ አለባቸው። ይህን ወረቀት ያሽጉና ወደኔ ያምጡ። የሚቀበሉት ሁኔታ እንዲህ መሆን አለበት፡- ተዓምሩ ከተከናወነ፣ ለእነርሱ ምንም ጥርጣሬ አይቀርም፤ ካልተከናወነ በአታላይነት ወንጀል በእኛ ላይ ፍርድ ይፈረዳል።’ ምሑሩ ሰውዬ፣ ሃሳን አሙ፣ ተነሥቶ መልስ ሰጠ፡- ‘ከዚህ በላይ የሚነገር ነገር የለም፤’ ከዚያም አማኝ ባይሆንም እንኳ፣ የእርሱን የተባረከውን ጉልበት ስሞ ሄደ። ኡላዎቹን ሰበሰበና የተቀደሰውን መልዕክት ሰጣቸው። እነርሱም በአንድ ላይ ተመካከሩና እንዲህ አሉ፡- ‘ይህ ሰው አስማተኛ ነው፣ ምናልባት አስማት ይሠራ ይሆናል፤ ከዚያም እኛ ምንም ነገር ለማለት አንችልም።’ በዚህ እምነት ላይ ተመሥርተው፣ እነርሱ ጉዳዩን

ሊገፉበት አልደፈሩም።[1]

ይህ ሰው፣ ሃሳን አሙ፣ ይህን እውነት በብዙ ስብሰባዎች ጠቀሰ። ካርቢላን ለቅቆ ከሄደ በኋላ ወደ ከርማንሻህና ወደ ቴህራን ሄደ፤ የዚህንም ታሪክ ዝርዝር፣ የኡላማዎቹን ፍርሐትና ወደኋላ መመለስ እያጋነነ ወደ ሁሉ ቦታ አሰራጨ።

በአጭሩ፣ በምሥራቅ የሚገኙ ጠላቶቹ ሁሉ ታላቅነቱን፣ ታዋቂነቱን፣ እውቀቱንና መልካም ምግባሩን አምነዋል፤ ምንም እንኳ ጠላቶቹ ቢሆኑም፣ ሁልጊዜ ስለእርሱ ‘ታዋቂው ባሃኦላህ’ እያሉ ይናገሩ ነበር።

ይህ ታላቅ ብርሃን በድንገት ከፋርስ አድማስ በላይ በወጣ ጊዜ፣ ሕዝቡ፣ ሚኒስትሮቹ፣ ኡላማዎቹ፣ የሌሎች መደቦች ሰዎች ሁሉ፣ በመጨረሻ /የከፋ/ ጠላትነት እርሱን በመከታተልና፣ ይህ ሰው ሃይማኖቱን፣ ሕጉን፣ ሕዝቡንና፣ ግዛቱን ለመጨቆንና ለማጥፋት ይፈልጋል ብለው በማወጅ በእርሱ ላይ ተነሡ። በክርስቶስም ላይ ይኸው ተብሎ ነበር። ነገር ግን ባሃኦላህ ብቻውንና ያለምንም ድጋፍ፣ ምንም ዓይነት ድክመት ሳያሳይ፣ ሁላቸውንም ተቋቋመ። እነርሱ በመጨረሻው፡- ‘ይህ ሰው በፋርስ እስካለ ድረስ ሰላምና እርጋታ አይኖርም፤ ፋርስ ወደመረጋጋት ትመለስ ዘንድ፣ ከአገር ማስወጣት አለብን’ አሉ።

ከፋርስ ለመውጣት ፈቃድ እንዲጠይቅ ለማስገደድ ኃይል የተጠቀሙት የእርሱ እውነት ብርሃን በዚህ መንገድ ይጠፋል ብለው በማሰብ ነበር፤ ነገር ግን ውጤቱ ከዚህ በጣም ተቃራኒ ነበር። እምነቱ ጎልቶ እንዲታወቅ ሆነ፤ ነበልባሉም ይበልጥ አየለ። በመጀመሪያ በፋርስ ውስጥ ብቻ ተስፋፋ፤ ነገር ግን የባሃኦላህ መሰደድ የእምነቱን ወደሌሎች አገሮች መሠራጨት ውጤት አስከተለ። በኋላ ጠላቶቹ፣ *‘ኢራቅ አረቢ[1] ከፋርስ እሩቅ አይደለም፤*

---

[1] በዚህ ጊዜ የባሃኦላህ ጥልቅ የማወቅ ችሎታ፣ ምን ተአምር እንደሚጠይቁ እንኳ ለመስማማት ከቶ በማይችሉት የጠላቶቹ ከፋት ላይ ድል አድራጊነት አገኘ።

*ከዚህ ይበልጥ ወደ ራቀ ግዛት መላክ አለብን'* አሉ። የፋርስ *መንግሥት* ባሃኡላህን ከኢራቅ ወደ ቁስጥንጥኒያ ለመላክ የቆረጠው ለዚህ ነበር። አሁንም ድርጊቱ እምነቱን በምንም ዓይነት እንዳላዳከመ ተረጋገጠ። እነርሱ እንደገና፣ 'ቁስጥንጥኒያ ለተለያዩ ዘሮችና ሕዝቦች መተላለፊያና ማረፊያ ነው፤ በእነርሱ መካከል ብዙዎቹ የፋርስ ሰዎች ይገኛሉ። የፋርስ ሰዎች በዚህ ምክንያት ከዚያም ርቆ ወደ ሩሜሊያ እንዲሰደድ አደረጉት፤ ነገር ግን፣ እዚያ በነበረበት ጊዜ፣ ነበልባሉ ይበልጥ ኃይለኛ፣ እምነቱም ይበልጥ የተከበረ ሆነ። በመጨሻም የፋርስ ሰዎች፣ *'ከእነዚህ ሥፍራዎች አንዱም ከእርሱ ኃይል አያመልጥም፤ እርሱ ወደ ኃይል አልባነት ወደ ሚለወጥበት፣ ቤተ-ሰቡና ተከታዮቹም ፍጹም አሰቃቂ ስቃዮች ወደ ሚቀበሉበት ቦታ መላክ አለብን'* አሉ። ስለዚህ በተለይ ለነፍስ ገዳዮች፣ ለሌቦችና ለቀማኞች የተመደበውን የአቁርን ወህኒ ቤት መረጡ፤ በእርግጥም ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ጋር ቆጠሩት። ነገር ግን የአምላክ ኃይል የተገለፀ ሆነ፡- ፋርስ ከአንዱ ሁኔታ ወደሌላ ሁኔታ እንድትራመድ ያደረገው፣ ጠላቶቹን ሁሉ ያሸነፈው፣ እምነቱንም ሊቀቋሙት እንደማይችሉ ያረጋገጠላቸው፣ ከዚህ ወህኒ ቤትና በእንዲህ ያለ የሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ሆኖ ስለነበር፣ በዚያን ጊዜ ቃሉ ታወጀ፤ የባሃኡላህም ታላቅነት ግልጽ ሆነ። የእርሱ ቅዱስ ትምህርቶች አካባቢዎችን ሁሉ ዘልቀው ገቡ፤ እምነቱም ተመሠረተ።

በእውነቱ፣ በፋርስ ውስጥ በሁሉ ቦታዎች ጠላቶቹ የእርሱን አማኞች በማሠር፣ በመግደልና በመደብደብ፣ በሺህ የሚቆጠሩ መኖሪያ ቤቶችን በማቃጠልና፣ ከመሬት ጋር በመደባለቅ፣ በሁሉ መሣሪያና ዘዴ እምነቱን ለማድቀቅና ለመደምሰስ፣ በመጨረሻ የከፋ ጠላትነት በእርሱ ላይ ተነሡበት። ይህም ሁሉ ሆኖ፣ እምነቱ ከነፍሰ ገዳዮች፣ በመንገድ ከሚዘርፉ ቀማኞችና ከሌቦች ወህኒ ቤት የታወቀ ሆነ። ትምህርቶቹ ተሠራጩ፣ ምክሮቹ እነዚያን እጅግ በጣም በጥላቻ

---

[1] ባግዳድ የምትገኝበት አውራጃ።

ተሞልተው ከነበሩት ብዙዎቹን ለወጧቸው፤ ጥብቅ አማኞችም አደረጓቸው። የፋርስ መንግሥት ራሱ እንኳ ሥሕተቱን እንዲገነዘብ ተደረገ፤ በኡላማዎቹ ሥሕተት ምክንያት በተፈጸመውም ነገር ተጸጸተ።

ባሃኦላህ በቅድስት አገር ወደሚገኘው ወደዚህ ወህኒ ቤት በመጣበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ነቢያት የሠራዊት ጌታ በቅድስት አገር መገለጽ እንዳለበት ገልጾና መልካሟን ዜና ሰጥቶ ስለነበር፣ ጠቢባን ሰዎች እርሱ ከሁለት ወይም ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት በነብያት አንደበት የሰጣቸው የደስታ ዜናዎች እንደገና መገለፃቸውን፣ አምላክም ለሰጣቸው የተስፋ ቃል ታማኝ መሆኑን ተገነዘቡ። እነዚህ የተስፋ ቃላት ሁሉ ተፈጽመው ነበር። በጠላቶቹ ጭቆና፣ በእርሱ ከአገር መባረርና መሰደድ ባይሆን ኖሮ፣ ባሃኦላህ እንዴት ከፋርስ አገር እንዲወጣ ሊገደድና በዚህች ቅድስት አገር ድንኳኑን ሊተክል ይችል እንደነበር ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። ጠላቶቹ በእርሱ መታሠር የተባረከውን እምነት ሙሉ በሙሉ ይጠፋና ይደመሰሳል ብለው አስበው ነበር፤ ነገር ግን በእውነቱ ይህ እሥር ቤት እጅግ በጣም አጋዥ ነበር፤ የዕድገቱም መሣሪያ ሆነ። የባሃኦላህ መለኮታዊ ታዋቂነት ወደ ምሥራቅም ምዕራብም ደረሰ፤ የእምነቱም ፀሐይ ጨረሮች ዓለምን ሁሉ አበሩ። ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይድረሰው! እርሱ እሥረኛ የነበረ ቢሆንም፣ የእርሱ ድንኳን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተተከለ፤ በላቀ ግርማም ተንቀሳቀሰ። ወደ እርሱ ዘንድ የገባ እያንዳንዱ ሰው፣ 'ይህ እሥረኛ አይደለም፣ ልዑል እንጂ' በማለት ይናገር ነበር።

ወዲያው እዚህ እሥር ቤት እንደደረሰ፣ በፈረንሣይ አምባሳደር በኩል የላከውን መልዕክት ለናፖሊዮን[1] ጻፈ። የመለእክቱ ዋና ሃሳብ፡- 'ወንጀላችን ምን እንደሆነ፣ ለምን በዚህ እሥር ቤትና ጨለማ ወህኒ ቤት እንደታሠርን ጠይቅ' የሚል ነበር። ናፖሊዮን

[1] ናፖሊዮን 3ኛ።

መልስ አልሰጠም። ከዚያም፣ በሱሪ ኢ ሃይካል[1] ውስጥ የሚገኝ ሁለተኛ መልእክት ተልኮ ነበር። ይህም በአጭሩ፡- 'ናፖሊዮን ሆይ፣ አዋጄን ስላላዳመጥህ፣ መልስም ስላልመለስክ፣ ሳይቆይ ግዛትህ ይወሰደብሃል፤ አንተም ፍጹም ትጠፋለህ' የሚል ነው። ይህም መልእክት ለናፖሊዮን የተላከው፣ የስደት አጃቢዎቹ በሆኑት ሁሉ እንደሚታወቀው፣ በሴሳር ኬታፉኩ[2] በኩል በፖስታ ነበር። ኪታቢ ሃይካል በፋርስ ውስጥ የተሠራጨው በዚህ ጊዜ ስለነበር፣ ይህም መልዕክት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት አንዱ ስለነበረ፣ የዚህ ማስጠንቀቂያ ይዘት ለመላው ፋርስ አገር ተዳርሶ ነበር። ይህ በ1869 ዓ.ም ሆነ፤ ይህም ሱሪ ፡ ኢ - ሃይካል በፋርስና በህንድ አገር ተሰራጭቶ ስለነበረ፣ በአማኞቹም ሁሉ እጅ ስለነበረ፣ ምን እንደሚደርስ ሲጠባበቁ ነበር። ብዙ ሳይቆይ፣ በ1870 ዓ.ም በጀመርመንና በፈረንሣይ መካከል ጦርነት ተነሣ፤ ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ የጀርመንን ድል አድራጊነት የጠበቀ ሰው ያልነበረ ቢሆንም፣ ናፖሊዮን ተሸነፈና ክብሩ ተገፈፈ፤ እጁን ለጠላቶቹ ሰጠ፤ ክብሩም ወደ ጥልቅ ውርደት ተለወጠ።

መልእክቶች[3] (Tablets) ለሌሎችም ንጉሦች ተልከው ነበር፤ ከእነርሱም መካከል አንዱ ግርማዊነታቸው ናሲረድ-ዲን-ሻህ ነበሩ። ባሃኡላህ በዚያ መልዕክት፡- 'እኔን አስጠራኝ፤ ኡላማዎችን ሰብስባቸው፤ እውነትና ውሸትይለይ ዘንድ፣ ማስረጃዎችንና ክርክሮችን ጠይቅ' አላቸው ግርማዊ ናሲረደ-ዲን የተባረከውን መልዕክት ወደ ኡላማዎች ላኩና ይህንን ተልዕኮ እንዲቀበሉ ሃሳብ አቀረቡላቸው፤ ነገር ግን እነርሱ ይህን ለማድረግ አልደፈሩም። ከዚያም እርሳቸው ከእነርሱ መካከል በጣም የታወቁትን ሰባቱን ለመልዕክቱ መልስ እንዲጽፉ ጠየቁአቸው። እነርሱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ 'ይህ ሰው የሃይማኖት ተቃዋሚና የሻህ ጠላት ነው' በማለት

---

[1] ባሃኡላህ ከተገለጸ በኋላ ከተጻፉት መጽሐፎቹ አንዱ፡

[2] ከባሃኡላህ ጋር ወዳጅነት የነበረው በሶሪያ የቆንሲል ልጅ። [3]ለባሃኡላህ መልዕክት የተሰጠ ስም

የተባረከውን ደብዳቤ መልሰው ላኩ። ግርማዊ የፋርስ ንጉሥ በጣም ተናደው፣ 'ይህ የማስረጃዎችና የክርክሮች፣ የእውነት ወይም የውሸት መለየት ጥያቄ ነው፤ ከመንግሥት ጠላትነት ጋር ምን አገናኘው? አዬ ጉድ! ለዚህ መልዕክት መልስ ለመስጠት እንኳ የማይችሉትን እነዚህን ኡላማዎች ምን ያህል ስናከብራቸው ነበር' በማለት ተናገሩ።

በአጭሩ፡- ለነገሥታት በተጻፉ መልእክቶች ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉ እየተፈጸሙ ናቸው፤ ከ1870 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጸሙትን ድርጊቶች ብናስተያይ፣ የተፈጸመው እያንዳንዱ ነገር እንደ-ተተነበየው ተፈጽሞ እናገኘዋለን፤ ወደፊትም የሚገለጹ ጥቂት ነገሮች ብቻ ይቀራሉ።

እንዲሁም ደግሞ አማኞች ያልሆኑ የውጭ አገር ሕዝቦችና የሃይማኖት ቅርንጫፎች ስለ ባሃኦላህ ብዙ ድንቅ ነገሮች ተናግረዋል። አንዳንዶቹ እርሱ ጻድቅ[1] እንደነበረ ያምኑ ነበር፤ አንዳንዶች ስለእርሱ ታሪክ /ሃተታ/ እንኳ ጽፈዋል። ከእነዚህ መካከል ስይድ ዳው ዲ፣ የባግዳድ ሱኒ ሊቅ፣ የባሃኦላህን ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ድርጊቶች የገለጸበትን አጭር ታሪክ ጽፏል። እስከ አሁንም፣ በምሥራቅ በብዙ ቦታዎች፣ ምንም እንኳ በባሃኦላህ ግልጸት ባያምኑ፣ ነገር ግን ጻድቅ ነው ብለው የሚያምኑትና በእርሱ ላይ እምነት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ።

ለማጠቃለል፣ ተቃዋሚዎቹም ወዳጆቹም እንዲሁም እነዚያ በተቀደሰውነጥብ ዘንድ መቅረብ የተፈቀደላቸው ሁሉ የባሃኦላህን ታላቅነት ተቀብለዋል፤ ወደ ተቀደሰው ሥፍራ ገብተው፣ በባሃኦላህ ፊት እንደቀረቡ፣ ወዲያው የባሃኦላህ ቅርበት በአበዛኞቻቸው ላይ በጣም ታላቅ የመለወጥ ኃይል ስለሚፈጥርባቸው፣ አንድ ቃል እንኳ ለመናገር አይችሉም ነበር። እጅግ በጣም ከሚጠሉት ጠላቶቹ አንዱ፣ 'እርሱ ዘንድ ስቀርብ እንዲህና እንዲህ እለዋለሁ፣ እንዲህ ብዬም እከራከረዋለሁ' ብሎ ወስኖ፣ ነገር ግን ወደ ቅዱሱ ቅርበት

[1] ዋሊ

በገባበት ጊዜ ተደንቆና ፈርቶ ምንም የማይናገርበት ብዙ ጊዜ ነበር።

ባሃኦላህ የአረብኛ ቋንቋ ተምሮ አያውቅም፤ የግል አሰልጣኝም ሆነ አስተማሪ አልነበሩትም፤ ትምህርት ቤትም ገብቶ አያውቅም፤ ይሁን እንጂ በአረብኛ ቋንቋ የሰጣቸው የተቀደሱ የእርሱ ገለፃዎች ልሳነቅንነትና ውበት፣ እንዲሁም የአረብኛ ቋንቋ ጽሑፎቹ፣ እጅግ በጣም የተዋጣላቸው የአረብኛ ቋንቋ ሊቃውንት እንዲደነቁባቸውና ቃል በማይገኝለት ሁኔታ እንዲገረሙባቸው አድርገዋቸዋል፤ ሁሉም እርሱ ተወዳዳሪም ሆነ አቻ እንደሌለው ተገንዝበው ለዚሁም መሥከረዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎችን በጥንቃቄ ብንመረምር፣ መለኮተዊው ክስተት ለማያምኑት 'የፈለጋችሁትን ማንኛውንም ተዓምር እሠራለሁ፤ የምታቀርቡትንም ፈተና ሁሉ እቀበላለሁ' ብሎ ከቶ እንደማያውቅ እናያለን። ነገር ግን ለሻህ በጻፈው መልዕክቱ፣ ባሃኦላህ 'ማስረጃዎችና ማረጋገጫዎች እንዲመሠረቱ ኡላማዎችን ሰብሰበህ ጥራኝ'[1] ብሎ በግልጽ ተናግሯል።

ለሃምሣ ዓመታት ባሃኦላህ ጠላቶቹን እንደተራራ ተጋትሯቸዋል፡- ሁሉም ሊደመስሱት ተመኙ፣ የእርሱንም መጥፋት ፈለጉ። ሺህ ጊዜ ሊሰቅሉትና ሊያጠፉት አቅደው ነበር፤ በእነዚህም በሃምሣ ዓመታት ጊዜ ሁሉ እርሱ በማያቋርጥ አደጋ ሥር ነበር።

በዚያን ጊዜ ፋርስ በመውደቅና በመፈራረስ ላይ ስለነበረች፣ እውነተኛውን ሁኔታ የሚረዱ አዋቂ ሰዎች ሁሉ፣ ፋርሳውያንም ሆኑ የውጭ አገር ሰዎች የእሷ ዕድገት፣ ሥልጣኔዋና እንደገና መገንባቷ የሚወሰነው፣ በዚህ ታላቅ ሰው ትምህርቶችመታወጅና በመሠረተ ሃሳቦቹም መስፋፋት መሆኑን ይገነዘባሉ።

ክርስቶስ በእርሱ የተቀደሰ ጊዜ በእውነቱ አሥራ አንድ ሰዎችን ብቻ አስተማረ፡- ከሁላቸውም ታላቁ፣ በተፈተነ ጊዜ ክርስቶስን ሦስት ጊዜ የካደው ጴጥሮስ ነበር። እንደዚህም ሆኖ፣

---

[1] ለዚህ ምሳሌ እንዲህ ያለ ትልቅ ዋጋ በመስጠት፣ አብዱል-ባሃ ተአምራት ለክስተቱ ማሳመኛነት ጥቅም እንደሌላቸው ለማስረዳት በማሰብ ነው።

የክርስቶስ እምነት ከዚያን ወዲህ በዓለም ሁሉ ተሠራጨ። በአሁኑ ዘመን ባሃኦላህ፣ በሠይፍ ስለት አደጋ ሥር እያሉ 'ያ ባሃኦላህ አብሃ፤'[1] የሚለውን ጥሪ ወደ እጅግ በጣም ከፍተኛው ሰማይ ያደረሱ፣ በፈተና እሳት ውስጥም ፊቶቻቸው እንደ ወርቅ የበሩ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ነፍሶችን አስተምሯል። እንግዲህ ወደፊት ምን ድንቅ ነገር እንደሚፈጸም አሰላስሉ።

በመጨረሻም፣ ትክክለኞች ሆነን ይህ ታላቅ ሕያው እንዴት ያለ አስተማሪ እንደነበረ፣ በእርሱ እንዴት ያሉ አስደናቂ ምልክቶች እንደተገለጹ፣ እንዴት ያለ ሥልጣንና ኃያልነት በእርሱ አማካይነት እንደተገኙ እንዳገኘ መረዳት ይገባል።

## (182)

የእያንዳንዱ ሕያው ፍጡር ክብርና ከፍተኛነት የሚመዘነው ከመንሥኤዎችና ከሁኔታዎች ጋር በማነጻጸር ነው።

የምድር ልቀቷ፣ ጌጧና ፍጹምነቷ በፀደይ ደመና ጸጋ አማካይነት አረንጓዴ መሆንና መለምለም ነው። ዕፅዋት ይበቅላሉ፤ አበቦችና መልካም ሽታ የሚሰጡ ቅጠላ ቅጠሎች ይፈልቃሉ፤ ፍራፍሬ የሚሰጡ ዛፎች በአበቦች የተሞሉ ይሆናሉ፤ አዳዲስና የበሰሉ ፍራፍሬዎች ያፈራሉ። የአትክልት ሥፍራዎች የተዋቡ ይሆናሉ፤ መስኮችም ያጌጣሉ፤ ተራሮችና ሜዳዎች አረንጓዴ ልብስ ይለብሳሉ፤ የአትክልት ሥፍራዎች፣ መስኮች፣ መንደሮችና ከተሞች ያሸበርቃሉ። ይህ የማዕድናት ዓለም ብልጽግና ነው።

የዕጸዋት ዓለም ክብርና ፍጹምነት ከፍተኛ ደረጃ፣ ዛፍ በንጹህ ወንዝ ዳር ሲበቅል፣ ልዝብ ነፋስ ሲነፍስበት፣ የፀሐይ ሙቀትና ብርሃን ሲያገኝ፣ ሲያበራበት፣ የአትክልተኛ እንክብካቤ ሲደረግለት፣ ከዕለት ተዕለትም ሲያድግና ፍሬ ሲያፈራ ነው። ነገር ግን እውነተኛ ብልጽግናው ወደ እንስሳትና ወደ ሰው ዓለም ሲሸጋገርና፣ ከእንስሳትና

[1] ባሃኢዎች በባሃኦላህ እምነታቸውን የሚገልጹበት ቃል፤ ቃል በቃል "አቤቱ የክብሮች ክብር ሆይ!" ማለት ነው ።

ከሰዎች አካላት የጎደለውን ሲተካ ነው።

የእንስሳት ዓለም ክብሩ፡- ሙሉ አካላት፣ የውስጥ ብልቶችና የሕዋሳት ኃይሎች ሲኖሩትና ፍላጎቶቹ በሙሉ ሲሟሉለት ነው። ይህ ዋና ጸጋው፣ ክብሩና ከፍተኛነቱ ነው። ስለዚህ የእንስሳ ከፍተኛ ደስታ የለመለመና አረንጓዴ መስክ፣ በጣም ንፁህ ወራጅ ውሀ፣ ተወዳጅና የለመለመ ደን ማግኘት ነው። እነዚህ ነገሮች ከቀረቡለት፣ ከዚህ በላይ የሆነ ብልጽግና ለእሱ ለማሰብ አይቻልም። ለምሳሌ አንዲት ወፍ በአረንጓዴና በፍሬ በተመላ ደን ውስጥ፣ በተዋበና በከፍተኛ ሥፍራ፣ በጠንካራ ዛፍ ከፍተኛ ቅርንጫፍ ጫፍ ላይ ጎጆዋን ብትሠራ፣ የሚያስፈልጓትን ፍራፍሬዎችና ውሃ ሁሉ ብታገኝ፣ ይህ ፍጹም ብልጽግናዋ ነው። ግን ለእንስሳት እውነተኛው ብልጽግና ከእንስሳት ዓለም ወደ ሰው ዓለም መሸጋገር ነው። በውሃና በአየር አማካይነት ወደ ሰው አካል ገብተው ከአካላቱ ውስጥ የተቃጠሉትን በመተካት እንደሚዋሐዱ ረቂቃን ነፍሳት ማለት ነው። ይህ ለእንስሳት ዓለም ከፍተኛ ክብርና ብልጽግና ነው፤ ከዚህ የበለጠ ክብር ለእሱ ሊታሰብለት አይችልም።

ስለዚህ ይህ ብልጽግና፣ ምቾትና ዓለማዊ መትረፍረፍ የማዕድናት፣ የዕጸዋትና የእንስሳት ፍጹም ብልጽግና እንደሆነ የታወቀና ግልጽ ነው። ምንም ሃብት፣ ብልጽግናና ምቾት ወይም የምድራዊ ዓለም እርካታ ከወፏ ብልጽግና ጋር ሊስተካከል አይችልም። የእነዚህ ሜዳዎችና ተራሮች ክልሎች በሙሉ መኖሪያዋ ናቸው፤ ፍራፍሬዎችና ምርቶች ሁሉ ምግቦቿዋና ሃብቶቿ ናቸው። አገሮች፣ መንደሮች፣ መስኮች፣ የግጦሽ ሥፍራዎች፣ ደኖች፣ ምድረ-በዳዎች ሁሉ ንብረቶቹ ናቸው። አሁን ይበልጥ ሃብታሙ ይህች ወፍ ናት ወይስ እጅግ በጣም ሃብታሙ ሰው ነው? ምክንያቱም የፈለገችውን ያህል ፍራፍሬ ብትወስድ ወይም ብትሰጥ ሃብቷ አይቀንስምና።

እንግዲህ እስካሁን ግልጽ የሆነው የሰው ልጅ ክብርና

ደስተኝነት ከምድራዊ ሃብት የበለጠ መሆን እንደሚኖርበት ነው። ምድራዊ ምቾት አንዱ ቅርንጫፍ ብቻ ነውና። የሰው ደስተኝነት መሠረት የእውነታው ማስጌጫ የሆነ መልካም መታወቂያ ጠባይና ምግባሩነው። እነዚህም መለኮታዊ መከሰቶች፣ መንግሥተ-ሰማያዊ በረከቶች ፣ፍጹም የተከበረ ስሜት፣ የእግዚአብሔር ፍቅርና ዕውቀት፣ ሁለንተናዊ ጥበብ፣ ምሁራዊ ግንዛቤ፣ ሳይንሳዊ ግኝቶች፣ ፍትሕ፣ ርትዕ ፣ እውነተኝነት፣ በጎ አድራጎት፣ የተፈጥሮ ድፍረት፣ ተፈጥሯዊ ጥንካሬ፣ መብቶችን መጠበቅ፣ ስምምነቶችንና ቃል ኪዳኖችን ማክበር፣ በማናቸውም ሁኔታ ቀጥተኝነት፣ በማናቸውም ሁኔታዎች እውነትን ማገልገል፣ ለሁሉም ሕዝብ ሲባል የራስን ሕይወት መሰዋት፤ ለሁሉም ወገኖች ደግነትና ከበሬታ፣ ለእግዚአብሔር ትምህርቶች መታዘዝ፣ በመለኮታዊ መንግሥት ውስጥ ማገልገል፤ ሕዝብን መምራትና ወገኖችንና ዘሮችን ማስተማር ናቸው። የሰው ልጅ ዓለም ብልጽግና ይህ ነው፣ የሰው ልጅ ከፍተኝነት ይህ ነው! ዘለዓለማዊ ሕይወትና መንግሥተ-ሰማያዊ ክብር ይህ ነው!

እነዚህ መልካም ምግባሮች በእግዚአብሔር ኃይልና በመለኮታዊ ትምህርቶች አማካይነት ካልሆነ በቀር ከሰው እውነታ ውስጥ ሊገለጹአይችሉም፣ ምክንያቱም ለእነሱ መገለጽ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል ያስፈልጋቸዋልና። በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ የእነዚህ ባሕርያት ፈለግ ሊታይ ይችል ይሆናል። ነገር ግን እነዚህ ቋሚናዘላቂ አይደሉም፣ በግድግዳ ላይ እንዳረፉ የፀሐይ ጨረሮች ናቸው።

ሩኅሩኅ አምላክ፣ እንዲህያለ የጽድቅ ዘውድ በሰው እራስ ላይ ስለደፋ፣ የዚህ ዘውድ አንጸባራቂ ዕንቁዎች ለመታየት እንዲችሉ ሰው ጥረት ማድረግ አለበት።

## (183)

የሰው መንፈስ መኖሩን[1] ስላሳየን፣ ቀጥለን ደግሞ የማይሞት ስለመሆኑ ማስረጃ መስጠት አለብን።

---

[1] በሰውና በእንስሳ መካከል ስላለው ልዩነት በገጽ (185) ተመልከት

ስለመንፈስ አለመሞት በቅዱሳት መጻሕፍት ተጠቅሷል። ይህም የመለኮታዊ ሃይማኖት ዋናው መሠረት ነው። አሁን ቅጣትና ዋጋ /ሽልማት/ ሁለት ዓይነት ናቸው ተብሏል። የመጀመሪያው የዚህ ዓለም ቅጣትና ዋጋ፣ ሁለተኛው የወዲያኛው ዓለም። ነገር ግን የመኖር ገነትና ሲኦል በሁሉም የአምላክ ዓለማት፣ ማለትም በዚህም ዓለም፣ በአምላክም መንፈሳዊ ዓለማት ይገኛሉ። ይህን ዋጋ ማግኘት ዘለዓለማዊ ሕይወት ማግኘት ነው። ክርስቶስ፦ 'ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ትገቡ ዘንድ፣ ከውሃና ከመንፈስ ትወለዱ ዘንድ፣ ተግባራችሁ ዘለዓለማዊ ሕይወትን በሚያስገኝላችሁ ሁኔታ ይሁን፣' ያለው ለዚህ ነው።

የዚህ ዓለም ዋጋዎች የሰውን ሰውነት የሚያስጌጡ መልካም ምግባሮችና ፍጹም የሆኑ ባሕርያት ናቸው። ለምሳሌ ጨለማዊ ነበር፣ ብሩህ ሆነ፤ ያላወቀ ነበር፣ ጥበበኛ ሆነ፤ ቸልተኛ ነበር፣ ንቁ ሆነ፤ አንቀላፍቶ ነበር፣ ከእንቅልፍ የነቃ ሆነ፤ ሙት ነበር፣ ሕይወት ያለው ሆነ፤ እውር ነበር፣ የሚያይ ሆነ፤ ደንቆሮ ነበር፣ ሰሚ ሆነ፤ ምድራዊ ነበር፣ የመንግሥተ-ሰማያት ሆነ፤ ቁስ አካል ነበር፣ መንፈሳዊ ሆነ። በእነዚህ ዋጋዎች አማካይነት በመንፈስ መወለድን ይቀዳጃል፤ አዲስ ፍጡርም ይሆናል። በወንጌል ስለ ደቀ-መዛሙርቱ 'በደም ወይም በሥጋ ፈቃድ፣ ወይም በሰው ፈቃድ አልተወለደም፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ'[2] ተብሎ የተጻፈው ጥቅስ መገለጫ ይሆናል፤ ይህም ማለት፣ የሰው ጠባይና ባሕርይ ከሆነው ከእንስሳዊ ጠባይና ባሕርይ ነፃ ወጥተው፣ የእግዚአብሔር ሥጦታ የሆኑት መለኮታዊ ጠባዮች አገኙ ማለት ነው። የዳግም ልደትም ትርጉም ይህ ነው። እንዲህ ላሉት ሰዎች ከአምላክ ከመጋረድ የበለጠ ሥቃይ የለም፤ ከሥጋዊ ክፉ ምግባር፣ ከጨለሙ ባሕርያት፣ ከዝቅተኛ ጠበይ፣ በሥጋዊ ፍላጎት ስሜት ከመዋጥ ይበልጥ የከፋ ቅጣት የለም። በእውነት ብርሃን አማካይነት ከእነዚህ መጥፎ ምግባራት ጨለማ ነፃ ወጥተው በእውነት

[1] ዮሐንስ 1፥13

ፀሐይ ብርሃን ሲያንፀባርቁ፣ በመልካም ምግባሮች ሁሉ ሲቀደሱ፣ ይህን እንደ እጅግ በጣም ታላቅ ዋጋ ይቆጥሩታል፤ እውነተኛ ገነትም እንደሆነ ያውቃሉ። በዚህ ሁኔታ የመንፈስ ቅጣት፣ ይህም ማለት የሕይወት ሥቃይና ቅጣት፣ በፍጥረት ዓለም መገዛት፣ ከእግዚአብሔር መጋረድ፣ ጨካኝና ደንቆሮ መሆን፣ ወደ ክፉ የሥጋዊ ስሜት መውደቅ፣ በእንስሳዊ ድክመት መዋጥ፣ እንደ ውሸት፣ አጥቂነትና ጭካኔ፣ ከዓለማዊ ነገር ጋር እንደ መጣበቅ፣ በሰይጣናዊ ሃሳቦች ውስጥ እንደመነከር የመሳሰሉ የጨለሙ ባሕርያት መያዝ እንደሆነ ይቆጥሩታል፤ ለእነርሱ እነዚህ እጅግ በጣም ከባድ ቅጣትና ሥቃይ ናቸው።

እንደዚሁም የሌላው ዓለም ዋጋዎች በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱት ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ መለኮታዊ ፍጹም ባሕርያት፣ ዘለዓለማዊ በረከቶችና ለዘለዓለም የማያልፍ ደስታ ናቸው። የሌላው ዓለም ሽልማቶች፣ ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ የሚገኙ ፍጹምነቶችና ሰላም ሲሆኑ፤ የዚህ ዓለም ሽልማቶች ደግሞ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚሆኑ፣ በዚህ ዓለም የተደረሰባቸው እውነተኛ አንጸባራቂና ፍጹም ባሕርያት ናቸው፤ ምክንያቱም የሕያው እውነተኛ ዕድገት ማለት እነዚህ ናቸውና። ይህም ለአንድ ሰው ከእንጭጭነት ወደ ብስለት እንደመድረስና'ከፈጣሪዎች ሁሉ እጅግ በጣም የላቀው ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን 'የሚሉት ቃላት መገለጫ እንደመሆን ነው። የሚቀጥለው ዓለም ዋጋዎች ሰላም፣ መንፈሳዊ ጸጋዎች፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች፣ የልብንና የነፍስን ፍላጎት ማግኘትና በዘለዓለማዊው ዓለም ከእግዚብሔር ጋር መገናኘት ናቸው። በዚሁ መንገድ የሚቀጥለው ዓለም ቅጣት፣ ይኸውም ማለት የሚቀጥለው ዓለም ሥቃይ፣ ልዩ መለኮታዊ ቡራኬዎችንና ፍጹም የሆኑ በረከቶችን ማጣት፣ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መውደቅን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህን መለኮታዊ ሥጦታዎች ያጣ፣ ከሞት በኋላ የሚቀጥል

ቢሆንም፣ በእውነት ሰዎች ዘንድ ግን እንደሞተ ይቆጠራል።

የመንፈስ አለመሞት ተቀባይነት ሊኖረው በሚችል ምክንያት ላይ የተመረኮዘ ማረጋገጫ ይህ ነው፡- ከሌለ ነገር ምልክት ሊመጣ አይችልም፤ ይኸውም ከፍጹም አለመኖር ምልክት ሊመጣ አይችልም ለማለት ነው፤ ምክንያቱም ምልክት የመኖር ውጤት ነውና፤ ውጤትም የሚወሰነው በዋናው ነገር፣ ማለትም በመኖር ነውና። እንግዲህ ከሌለ ፀሐይ ብርሃን ሊበራ አይችልም፤ ከሌለ ባሕር ማዕበል አይመጣም፤ ከሌለ ደመና ዝናብ አይዘንብም፤ የሌለ ዛፍ ፍሬ አያፈራም፤ የሌለ ሰውምንም አይገለጽም ወይም አያፈራም። ስለዚህ የመኖር ምልክቶች እስካሉ ድረስ፣ እነሱ የምልክቶቹ ባለቤት መኖር ማረጋገጫዎች ናቸው።

ዛሬ የክርስቶስ መንግሥት እንዳለ አስተውሉ፡- ከሌለ ንጉሥእንዲህ ያለ ታላቅ መንግሥት እንዴት ሊገለጽ ይችላል? ከሌለ የአትክልት ሥፍራ እንዴት እንዲህ ያለ መዓዛ የተሞላበት ንፋስ ሊነፍስ ይችላል? ማዕድን፣ ዕጸዋትም ሆኑ እንስሳት፣ የዚያ ፍጡር ልዩ ልዩ ክፍሎቹ ከተበታተኑና ንጥረ ነገሮቹ ከበሰበሱ በኋላ፣ ምንም የኃይሉ ውጤት፣ ምንም ምልክት፣ ምንም ግፊትም እንደማይኖረው አስተውሉ። ከክፍሎቹ መፈራረስ፣ ከብናኞቹ መበታተንና ከውህደቱ መጥፋት በኋላ የሚኖረው፣ መሥራቱንም የሚቀጥለውና ኃይል የሚኖረው የሰው እውነታና የሰው መንፈስ ብቻ ነው።

ይህ ጥያቄ እጅግ በጣም መሠረታዊ ነው፡- ልብ ብላችሁ አሰላስሉት። ይህ ብልህ ሰው በምክንያትና በፍትሕ ሚዛን ይመዝነው ዘንድ፣ እኛ የምንሰጠው ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ነገር ግን የሰው መንፈስ ቢደሰትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሳብ፣ ውስጣዊ የማየት ኃይሉ ቢከፈት፣ መንፈሳዊ ስሜቶቹም ቢያይሉ፣ ልክ ፀሐይን እንደሚያያት ሁሉ የመንፈስንም አለመሞት ያያል፤ የደስታ ዜናና የእግዚአብሔር ምልክቶች ይከቡታል።

(184)

የፍጡር ሁኔዎች በአገልጋይነት፣ በነቢይነትና በመለኮታዊነት ሁኔታዎች የተወሰኑ፣ ነገር ግን የመለኮታውና የምድራዊ ፍጹምነቶች ወሰን እንደሌላቸው እወቁ። ጠለቅ አድርጋችሁ ስታሰላስሉ፣ በውጪአዊውም ሁኔታ፣ የፍጡር ፍጹምነቶችም ደግሞ ወሰን የሌላቸው ሆነው ታገኟቸዋላችሁ። ምክንያቱም አንዱን ፍጡር ከእሱ የበለጠ ሌላ ፍጡር የለም ብሎ ለማሰብ የሚቻልበት ደረጃ ድረስ ፍጹም ሆኖ ለማግኘት አይቻልምና። ለምሳሌ፣ አንድ ሩቢ ከማዕድን ዓለም፣ አንዲት ጽጌረዳ ከዕጸዋት ዓለም፣ አንዲት ዘማሪ ወፍ ከእንስሳት ዓለም ዓይታችሁ ከነዚያ የተሻሉ ናሙናዎች የሉም ብላችሁ ለማሰብ አትችሉም። መለኮታዊ ሥጦታዎች መጨረሻ እንደሌላቸው ሁሉ፣ እንዲሁም ለሰው ልጅ ፍጹምነት መጨረሻ የለውም። የፍጹምነት መጨረሻ ላይ ለመድረስ ቢቻል ኖሮ፣ ከክስተታዊ ፍጡር እውነታ መካከል አንዱ ከእግዚአብሐር ቁጥጥር ውጪ የሆነ ሁኔታ ላይ ይደርስና፣ ክስተታዊው የመጨረሻ ፍጹምነት ሁኔታን ይቀዳጅ ነበር። ነገር ግን ለሁሉም ፍጡር ሊያልፈው የማይችለው ነጠብ አለው፤ ይህም ማለት፣ በአገልጋይነት ሁኔታ ውስጥ የሆነው፣ ምንም ያህል ወሰን አልባ የፍጹምነት ዕድገት ቢያገኝ፣ የመለኮታዊ ሁኔታ ላይ ከቶ አይደርስም። ሌሎቹም ፍጡራን እንደዚሁ ናቸው፡- አንድ ማዕድን የፈለገውን ያህል በማዕድን ዓለም ዕድገት ቢያደርግ፣ የዕጸዋትን ኃይል ሊቀዳጅ አይችልም፤ ደግሞም አበባ በእጽዋት ዓለም የፈለገችውን ያህል ዕድገት ብታደርግ፣ የሕዋሳት ኃይሎችን አታገኝም። እንዲሁም ይህ የብር ማዕድን የመስማት ወይም የማየት ኃይል ሊቀዳጅ አይችልም፤ በራሱ ሁኔታ ብቻ ለመሻሻል፣ ፍጹም ማዕድንም ለመሆን ይችላል፤ ነገር ግን የማደግ ኃይል ለማግኘት ወይም የስሜት ኃይል ወይም ሕይወት ለመቀዳጀት አይችልም፤ የሚችለው በራሱ ሁኔታ ብቻ ዕድገት ለመቀጠል ነው።

ለምሳሌ፣ ጴጥሮስ ክርስቶስን ሊሆን አይችልም። ሊሆን

የሚችለው በአገልጋይነት ሁኔታ፣ ወሰን የሌለው ዕድገት መቀዳጀት ነው፤ ምክንያቱም ነባሪ እውነታ ሁሉ መጨረሻ የሌለው ዕድገት ለማድረግ ችሎታ አለውና። የሰው መንፈስ ይህን ቁሳዊ ቅርጽ ካወለቀ ከበኋላ ዘለዓለማዊ ሕይወት ስላለው፣ በእውነትም ማንኛውም ፍጡር የመሻሻል ዕድገት ለማድረግ ችሎታ ስላለው፣ ስለዚህ ለአንድ ሰው ከሞተ በኋላ የመሻሻል እርምጃ እንዲያገኝ፣ ይቅርታ፣ ምሕረት፣ ደግነት፣ ቡራኬዎች መጠየቅ የተፈቀደ ነው፤ ምክንያቱም ፍጡር የመሻሻል ችሎታ አለውና። በባሃኦላህ ጸሎቶች ውስጥ ለሞቱ ሰዎች ይቅርታና የኃጢዓት ሥርየት የሚጠየቅላቸው ስለዚህ ነው። ከዚህም በላይ፣ ሰዎች በዚህ ዓለም እግዚአብሔር እንደ ሚያስፈልጋቸው ሁሉ፣ በሚቀጥለውም ዓለም ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ዓለምም ሆነ በሚቀጠለው ዓለም ፍጡራን ምን ጊዜም ጥገኞች ናቸው፤ እግዚአብሔር ግን ከጥገኝነት ፍጹም ነፃ ነው።

የሚቀጠለው ዓለም ብልጽግና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው። በዚህ ምክንያት እነዚያ ወደ መለኮታዊ መንበር የቀረቡት እንደ ሚያማልዱ ይህም ማማለድ በእግዚአብሔር የተፈቀደ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። ነገር ግን የሚቀጥለው ዓለም ማማለድ እንደዚህኛው ዓለም ማማለድ አይደለም። ሌላ ነገር ነው፤ በቃል ሊገጽ የማይቻል፣ ሌላ እውነታ ነው።

አንድ ሃብታም ሰው በመሞቻው ጊዜ ለድሆና ለችግረኞች ሥጦታ ቢሰጥ፣ ከሃብቱም ከፊሉን ለእነርሱ ወጪ እንዲደረግላቸው ቢሰጥ፣ ምናልባት ይህ አድራጎት ለትንሹም ለትልቁም ጥፋቱ ይቅርታ፣ በመለኮታዊ መንግሥትም የዕድገቱ ምክንያት ይሆን ይሆናል።

ደግሞ አባትና እናት ለልጆቻቸው እጅግ በጣም ከባድ ችግርና መከራን ያሳልፋሉ፤ ብዙ ጊዜምልጆቹ የብስለት ደረጃ እንደደረሱ ወላጆቹ ወደሚቀጥለው ዓለም ያልፋሉ። አባትና እናት ለልጆቻቸው ላደረጉት እንክብካቤና ችግር በዚህ ዓለም ዋጋቸውን ለማየት የሚደርሱ አልፎ አልፎ ነው። ስለዚህ ልጆች፣ ለዚህ

እንክብካቤና ችግር ውለታ መመለሻ፣ ለወላጆቻቸው ቸርነትና ደግነት ማሳየት፣ ለትንሹም ለትልቁም በደላቸው ይቅርታን መማፀን አለባቸው። እንግዲህ፣ አባታችሁ ላሳያችሁ ፍቀርና ደግነት ብድር መመለሻ፣ ስለእርሱ ብላችሁ ለድሆች መመጽወት፣ በታላቅ ታዛዥነትና ትሕትና ለኃጢዓቱ ይቅርታና ሥርየት መማፀን፣ ከፍተኛ ምሕረትንም መጠየቅ አለባችሁ።

የእነዚያ በኃጢአትና ባለማመን የሞቱት ሰዎች ሁኔታ እንኳ ሊለወጥ ይችላል፤ ይህም ማለት በእግዚአብሔር ፍርድ ሣይሆን በጸጋው ምሕረት ሊያገኙ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ጸጋ ያለ ዋጋ መስጠት ሲሆን፣ ፍርድ ግን እንደሥራው መስጠት ነውና። ለእነዚህ ነፍሶች እዚህ ሆነን ለመጸለይ እንደምንችል ሁሉ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነው የሚቀጥለው ዓለምም ልንጸለይላቸው ይኸው ኃይል አለን። በዚያ ዓለም የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጡራን አይደሉምን? ስለዚህ በዚያም ዓለም ደግሞ ዕድገት ለማድረግ ይችላሉ። እዚህ በመማፀን ተግባራቸው ብርሃን እንደሚያገኙ ሁሉ፣ እዚያም ደግሞ ለይቅርታ ሊማፀኑ ይችላሉ፤ በመለመን፣ ልባዊ ጸሎት በማድረግና በመማፀን ብርሃን ሊቀበሉይችላሉ። እንዲሁም በዚህ ዓለም ያሉ ነፍሶች፣ በቅዱሳን ልመናና ጸሎት አማካይነት እንደሚሻሻሉ ሁሉ፣ ከሞት በኋላም እንዲሁ ነው። ደግሞም በራሳቸው ጸሎትና መማፀን አማካይነት፣ ከሁሉም በላይ የቅዱሳን ክስተቶች ማማለድ ተቀባዮች ከሆኑ፣ ሊያድጉ ይችላሉ።

## <u>የመለኮታዊ ሥልጣኔ ምሥጢር ከሚባለው መጽሐፍ</u>

(185)

በስሜትና በከንቱ ምኞት ከንፎች የምንዋልለው እስከ መቼ ነው፤ በድንቁርናና በርኩሰት ጥልቀት ውስጥ እንደተዋጡ አረመኔዎች ጊዜያችንን የምናጠፋው እስከ መቼ ነው?በዙሪያችን ያለውን ዓለም ተመልከተን፣ ሥልጣኔንና የኑሮን ጥበብ የሚያራምደውን ማንኛውንም

ነገር እንይዝ ዘንድ እግዚብአሔር ዓይኖችን ሰጥቶናል። ስለሊቃውንትና ስለፈላስፋዎች ጥበብ ሰምተናል፣ ተጠቅመን እንነሣ፣ እናሰራጨውና ሥራ ላይ እናውለው ዘንድ አርሱ ጆሮዎችን ሰጥቶናል። ለጠቅላላው ደህንነት አገልግሎት ላይ እንድናውለው፣ እኛ፣ ከሁሉ ዓይነት ፍጡራን በማስተዋልና በማመዛዘን የታወቅነው፣ በሁሉም ጊዜና በሁሉም መስመር፣ አጋጣሚው ትንሽም ይሁን ትልቅ፣ ተራም ይሁን የተለየ፣ የሰው ዘር ሁሉ በሰላም ወደ ጠንካራ የዕውቀት ምሽግ እስኪሰበሰብ ድረስ እንሥራበት ዘንድ፣ የሕዋሳትንና የልዩ ተውህቦን ኃይል አጎናጽፎናል። ያለማቋረጥ ለሰው ደስታ አዲስ መሠረት መመሥረት፣ ወደዚህም ግብ የሚያደርስ አዲስ መሣሪያ መፍጠርና ማዳበር አለብን። ሰው ኃላፊነቱን ለማሟላት ቢነሣ እንዴት እጅግ በጣም ታላቅና ከብር የተመላው ነው፤ ለኅብረተ-ሰቡ ደህንነት ዓይኑን ቢጨፍንና ከቡር ጊዜውን የራሱን ፍላጎትና የግል ጥቅሙን በማሳደድ ቢያባክንደግሞ እንዴት ዕድለ-ቢስና የሚነቀፍ ነው?

በከፍተኛ ጥረት ሠንጋ ፈረስ ወደ ሥልጣኔና ወደ ፍትሕ ሜዳ ሲጋልብ፣ የእግዚአብሔርን ምልክቶች ከዓለምና ከሰው ነፍስ ያያል፤ ከፍተኛ ደስታም የእርሱ ይሆናል። 'እኛ በእውነቱ ምልክቶቻችንን በዓለምና በውስጣቸው እናሳያቸዋለን።'[1]

የማይሠራ፣ የማይገደው፣ ደነዝ፣ ከራስ ዝቅተኛ ፍላጎት ጋር ብቻ የተዛመደ ሆኖ መኖር፣ የሰው ፍጹም የመጨረሻው ዕድለ-ቢስነት ይህ ነው። እንደዚህ በሆነ ጊዜ፣ ሰውነቱን እጅግ በጣም ጥልቅ በሆነ ድንቁርናና አውሬነት ውስጥ ጥሏል፤ ከጨካኝ አራዊትም ዝቅ ወዳለ ውርደት ውስጥ ሰጥሟል። 'እነርሱ እንደ ጨካኝ አውሬዎች ናቸው፡- አዎን፣ ወደ ባሰ ሥሕተት ይሄዳሉ ... በእግዚአብሔር ዓይን፣ አስከፊዎቹ አውሬዎች፣ ድንቆሮዎቹ፣ ዲዳዎቹ፣ የማይረዱት ናቸውና።[2]

---

[1] ቁርአን 41፡53

[2] ቁርአን 7፡178፣ 8፡22

አሁን ተነሥተን እነዚያን ለመላው የሰው ዘር ሰላምን፣ ደህንነትንና ደስታን፣ ዕውቀትን፣ ባሕልንና ሥራን፣ ዋጋንና ደረጃን ለማዳበር የሚጠቅሙትን ነገሮች ሁሉ አጥብቀን ለመያዝ በከፍተኛ ቆራጥነት እንወስን። በዚህ ሁኔታ የሰው ችሎታዎች መሬት ሕይወትን በሚያድሱ በንጹህ ሃሳብና የራስ ወዳድነት በሌለበት የጥረት ውሃ አማካይነት በራሱ ድብቅ ኃይል ይጠራና ወደ ተመሥጋኝ ባሕርይዎች ያብባል፤ ፍሬ ያፈራና ይበለጽጋል፤ ከዚያም የቀድሞ አባቶቻችን ከነበረው የዕውቀት ጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ጋር እስከ መወዳደር ይደርሳል። ከዚያ በኋላ ይህ የፋርስ ቅዱስ መሬት በሁሉም መንገድ የሰው ፍጹምነት መታያ ማዕከል ይሆናል፤ ልክ በመስተዋት ውስጥ እንደሚያንፀባርቅ ዓይነት የሆነ የዓለምን ሥልጣኔ ሁሉ ማጎደር ያንፀባርቃል።

በፍጹም ጥበቡ ጨረር መሠራጨት በሁሉን አቀፍ ዕውቀቱ እነዚያ የያትሪብና /መዲናና/ የባዛ ጨካኝ ነዋሪዎች በተአምርና በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ከድንቁርናቸው አዘቅት እንዲወጡ፣ ወደ ዕውቀት ጫፎችም ከፍታ እንዲመጥቁ፣ የጥበብ፣ የሳይንስና የሰው ዘር ፍጹምነቶች ማዕከል፣ የደስታና የእውነተኛ ሥልጣኔም ከዋክብት እንዲሆኑና ከዓለም አድማሶች እንዲያበሩ ስለተደረጉ፣ ለመለኮታዊ ጥበብ የቀን ምንጭ፣ ለግልጸት ንጋት ነጥብ /ለሙሐመድ/ ለቅዱሳን ተከታይ ዘሮቹም ሁሉ ምሥጋናና ክብር ይሁን።

## (186)

የእግዚአብሔር መንፈስ /ኢየሱስ/ ቅዱስ እስትንፋስ በፍልስጥኤምና በገሊላ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻዎችና በእየሩሳሌም አካባቢ ባሉት ክፍለ-ሀገሮች ላይ ጣፋጭነታቸውን በሚያሰራጩበት፣ የወንጌል ድንቅ ዜማዎችም በመንፈሳዊ ሁኔታ በበሩት ሰዎች ጆሮዎች ይሰሙ በነበሩበት ወቅት፣ የኢሲያ፣ የአውሮጳ፣ የአፍሪቃና የአሜሪካ፣

የፖስፊክንና የህንድ ውቅያኖስን ደሴቶችና የተጫፈሩ ደሴቶች የሚጠቃልለው የውቅያኒያ ሕዝቦች ሁሉ እሳት አምላኪዎችና አረመኔዎች፣ "በቃል ኪዳኑ"[1] ስለተናገረው መለኮታዊ ድምጽ የማያውቁ እንደ ነበሩ አስታውስ። አይሁዶች ብቻቸውን የእግዚአብሔርን መለኮታዊነትና አንድነት አመኑ።

ከየሱስ ማወጅ በኋላ፣ ንጹሕና ሕይወት ሰጪ የአንደበቱ እስትንፋስ ለሦስት ዓመታት ጊዜ በእነዚያ ክፍለ ሀገሮች በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ዘለዓለማዊ ሕይወት አጎናጸፈ፤ በዚያን ጊዜ ለታመመው የዓለም አካል እጅግ በጣም አስፈላጊ መድኃኒት የነበረውም የክርስቶስ ሕግ በመለኮታዊ ግልጸት አማካይነት ተመሠረተ። ክርስቶስ በሕይወቱ በነበረበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ፊታቸውን የመለሱ ጥቂት ምዕመናን ብቻ ነበሩ፤ እንዲያውም በእውነቱ አሥራ ሁለቱ ደቀ-መዛሙርቱና ጥቂት ሴቶች ብቻ አማኞች ሆኑ፣ ከደቀ-መዛሙርቱም ውስጥ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ፣ አሥራ አንዱን በመተው፣ በክሕደት ከእምነቱ ወጣ። ከየሱስ ወደ ክብር ዓለም ዕርገት በኋላ፣ እነዚህ ጥቂት ነፍሶች በመንፈሳዊ ባሕርይዎቻቸው፣ ንጹህና ቅዱስ በሆኑ ተግባራት ተነሥተው ቆሙ፤ በእግዚአብሔር ኃይልና ሕይወት በሚሰጠው በመሢሕ እስትንፋስ አማካይነት፣ የምድርን ሕዝቦች ሁሉ ለማዳን ተነሡ። ከዚያም ጣዖት አምላኪ ወገኖች፣ እንዲሁም ይሁዳውያን በእየሩሳሌም መብራት የተቀጣጠለውን መለኮታዊ እሳት ለማጥፋት በሙሉ ኃይላቸው ተነሡ። "የአምላክን ብርሃን በአፎቻቸው ለማጥፋት ይፈልጋሉ፤ ከሐዲዎች ቢጠሉትም እንኳ፣ አምላክ ግን የእርሱን ብርሃን ፍጹም ለማድረግ ፈቅዷል።"[2] እነዚህን ቅዱሳን ነፍሶች እጅግ በጣም የከፋ ሥቃይ አሳይተው እያንዳንዳቸውን ለሞት አሳለፏቸው፤ የግማሾቹን ንጹህ የሆኑና ያልተበከሉ አስከሬኖች፣ በልኳንዳ አራጅ መቁረጫዎች ቆራርጠው በብረት ማቅለጫ ጋኖች ውስጥ አቃጠሏቸው፤

---

[1] መጪዎቹን የአዳም ዘሮች በመጥራት፣ እግዚአብሔር፡- "አምላካችሁ አይደለሁምን?" ያለበት ቀን፣ እነርሱም 'አዎን፣ እኛ እንመሠክራለን' በማለት መልስ ሰጡ።

[2] ቁርአን 7፡171

ገሚሶቹንም አሥረው በመወጠሪያ መግሪያ በመወጠር ጎትተው አሰቃይተው፣ በመጨረሻም በሕይወት እያሉ ቀበሯቸው። ምንም እንኳ ይህ አሰቃቂ ድርጊት ቢደርስባቸውም፣ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን እምነት ማስተማራቸውን ቀጠሉ፤ ሠይፎቻቸውን ከአፎቶቻቸው መዝዘው ወይም ጉንጩን እንኳ ጭረው ከቶ አያውቁም ነበር። ከዚያም በመጨረሻ በአውሮፖና በአሜሪካ የሌሎች ሃይማኖቶች ምልክቶች ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ የክርስቶስ እምነት ምድርን ሁሉ ሸፈነ፤ ዛሬ በኢሲያና በአፍሪቃ፣ እንዲሁም በውቅያኒያ ብዙ ሰፊ ሕዝቦች በአራቱ ወንጌሎች መቅደስ ክልል ውስጥ በመኖር ላይ ናቸው።

የእግዚአብሔር እምነት በሰው ዘር ፍጹምነቶች፣ እጅግ በጣም ጥሩና አስደሳች በሆኑ ባሕርይዎችና በመንፈሳዊ ጠባዮች አማካይነት መሰራጨት እንዳለበት አሁን ከዚህ በላይ በቀረቡት ሊረቱ በማይችሉ ማስረጀዎች አማካይነት በተሟላ ሁኔታ ተረጋግጧል። አንድ ነፍስ በራሱ ፍላጎት ወደ እግዚአብሔር ቢቀርብ በአንድነት ደጀ-ሠላም ተቀባይነትን ያገኛል፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሰው ለግል ከማሰብ፣ ከስስትና ከራስ ወዳድነት ፍላጎት ነፃ ነው፤ በጌታውም ጥላ ሰጪ ጥበቃ ሥር ጥገኝነትን ወስዷልና። በሰዎችም መካከል፣ እምነት የሚጣልበትና እውነተኛ፣ ታጋሽና ጥንቁቅ፣ ከፍተኛ አስተሳሰብ ያለውና ታማኝ፣ የማይበላሽና ፈሪሐ-እግዚአብሔር ያደረበት በመባል ይታወቃል። በኋለኛው ሕይወት ደስታን፣ በዚህኛው ሥልጣኔንና የጠባይ መራቀቅን የማስገኘቱ የመለኮታዊ ሕግ የመጀመሪያ ዓላማ በዚህ መንገድ ከግቡ ይደርሳል። ሠይፍ ደግሞ፣ ላይ ላዩን አማኝ፣ ውስጥ ውስጡን ግን ከሐዲና ሃይማኖቱን የሚከዳውን ሰው ብቻ ያፈራል።

(187)

እኛ እዚህ ለሁሉም በአርአያነት ሊያገለግል የሚችል ታሪክ እንተርካለን። የአረቦች ዜና መዋዕል፣ ሙሐመድ ከመምጣቱ በፊት

በነበረው ጊዜ፣ የመንግሥቱ መቀመጫ በሂሪ ከተማ የነበረ፣ በድንቁርና ዘመን የአረብ ንጉሥ የነበረ፣ የለከማይቱ ሙንድሀር ልጅ ኑማን፣ አንድ ቀን ብዙ ጊዜ ወደ ወይን ጠጅ ዋንጫው በመመላለሱ ምክንያት አዕምሮው ደነዘዘና የማመዛዘን ኃይሉ ከዳው። በዚህ በተንጀባረረና ማስተዋል በተሣነው ሁኔታ፣ ሁለት ደስተኞች ባልንጀሮቹ፣ የቅርብና በጣም የተወደዱ ወዳጆቹ፣ የሙዳሊል ልጅ ከሃልድና የሙሳድ ካልዲህ ልጅ አምር እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጠ። ከሥካሩ ሲነቃ ስለሁለቱ ወዳጆቹ ጠየቀና አሳዛኙ ዜና ተነገረው። ከልቡ አዘነና ለእነርሱ በነበረው ጥልቅ ፍቅርና ናፍቆት ምክንያት፣ በመቃብራቸው ላይ ሁለት ድንቅ ሐውልቶች አሠራ፤ እነዚህንም በደም የተበከሉ ብሎ ሰየማቸው።

ከዚያም በኋላ፣ ለሁለቱ ጓደኞቹ ማስታወሻ እንዲሆኑ፣ ከዓመት ውስጥ ሁለት ቀኖች መደበ፤ አንዱን የከፋት ቀን፣ አንዱን ደግሞ የጸጋ ቀን ብሎ ሰየማቸው። በየዓመቱ በእነዚያ በተወሰኑ ቀናት በግሩም ሠልፍ ይወጣና በሐውልቶቹ መካከል ይሰየማል። በከፋት ቀን፣ ዓይኑ በማንኛውም ነፍስ ላይ ቢያርፍ፣ ያ ሰውይገደላል፤ በጸጋ ቀን ግን፣ በፊቱ ያለፈው ሁሉ በሥጦታዎችና በጥቅሞች ይንበሸበሻል። በኃያል መሐላ የታተመና ሁል ጊዜበጥብቅ ይከበር የነበረው ውሳኔው እንዲህ ነበር።

አንድ ቀን ንጉሡ ማህሙድ ተብሎ የሚጠራውን ፈረሱን ተቀምጦ ለአደን ወደ መስኩ ጋለበ። ከሩቅ የዱር አህያ በድንገት ታየው። ኑማንም ይደርስበት ዘንድ ፈረሱን ቀስቅሶ በጣም ከመጋለቡ የተነሣ፣ ከተከታዮቹጋር ተጠፋፉ። ሌሊት እየተቃረበ በመጣበት ጊዜ፣ ንጉሡ ተስፋ በሚያስቆርጥበት ሁኔታ ጠፋ። ከዚያም፣ እሩቅ በረሃ ውስጥ አንዲት ድንኳን ታየችው፤ እርሱም ፈረሱን ወደ ድንኳኗ አዞረና ወደርሷ አመራ። ወደ ድንኳኗም መግቢያ በደረሰ ጊዜ፣ “እንግዳ ትቀበላላችሁ ወይ?” ብሎ ጠየቀ። ባለድንኳኑም /የታይ ተወላጁ የአቡ ገሃፍሬይ ልጅ፣ ሃንዛላ/ አዎን ብሎ መለሰ። ወደ

እርሱም ቀረብ ብሎ ኑማንን ከፈረስ እንዲወርድ ረዳው። ከዚያም በኋላ ወደ ባለቤቱ ሄዶ እንዲህ ሲል ነገራት። “በዚህ ሰው ሁኔታ ግልጽ የሆኑ የታላቅነት ምልክቶች ይታያሉ። *መሥተንግዶ* ታሳይው ዘንድ የተቻለሽን አድርጊ፤ ግብዣም አሰናጂ፣” አላት። ባለቤቱም፡- “አንዲት በግ አለችን። እረዳት። ለእንደዚህ ያለ ቀን የሚሆን ዱቄትም አስቀምጫለሁ፤” አለችው። ሃንዛላ በመጀመሪያ በጓን አለበና ወተቷን በወጪት ለኑማን ወሰደ፤ ከዚያም አረዳትና ምግብ ተዘጋጀ፤ ከእርሱ አጫዋችነትና ፍቅር ከተመላበት ደግነት ጋር ኑማን ያንን ሌሊት በሰላምና በምቾት አሳለፈ። ሲነጋ፣ ኑማን ሊሄድ ተዘጋጀ፤ ለሃንዛላም እንዲህ አለው፡- “ተቀብለኸኝ አስተናግደኸኛል፤ ከፍተኛ ቸርነትም አድርገህልኛል። እኔ ኑማን የሙንድህር ልጅ ነኝ፤ የአንተን መምጣት በቤተ-መንግሥቴ በጉጉት እጠባበቃለሁ፡”

ጊዜው አለፈ፤ በታይም ሀገር ረሃብ ሆነ፤ ሃንዛላም ተቸገረና ንጉሡን ፍለጋ ሄደ። በሚያስገርም አጋጣሚ “በክፉት ቀን” ላይ ደረሰ። የኑማንም መንፈስ በእጅጉ ታወከ። ወዳጁንም እንዲህ እያለ መውቀስ ጀመረ፤ *“ካላጣኸው ቀን ለምን በዚህ ቀን መጣህ? ይህ ቀን የክፉት ቀን፣ ማለትም የቁጣና የጭንቀት ቀን ነውና። በዚህ ቀን ዓይኔ በአንዱ ልጄ በቃቡስ ላይ እንኳ ቢያርፍ በሕይወቱ አያመልጥም። አሁን የፈለግኸውን ማንኛውንም ውለታ ጠይቀኝ።”*

ሃንዛላም፡- “እኔ ስለአንተ የክፉት ቀን ምንም አላወቅሁም። ስለዚህ ዓለም *ሥጦታዎች* ከሆነ ደግሞ፣ በሕይወት ለሚኖሩት ናቸው፤ እኔ ግን በዚህ ሰዓት የሞት ጽዋ መጠጣት ስላለብኝ፣ አሁን የዚህ ዓለም ግምጃ ቤቶች ሁሉ ምን ሊረዱኝ ይችላሉ?” አለው።

ኑማንም፡- “ለዚህ ምንም የሚደረግ ነገር የለም” ሲል መለሰ።

ሃንዛላ፡- *“ወደ ባለቤቴ ሄጄ ኑዛዜዬን አዘጋጅ ዘንድ ጊዜ*

ስጠኝ። በሚቀጥለው ዓመት በክፋት ቀን እመለሳለሁ” በማለት ጠየቀው።

ከዚያም ኑማን፣ ሃንዛላ ቃሉን ካጠፈ በእርሱ ፈንታ ዋሱ እንዲገደል፣ ዋስ እንዲጠራ ጠየቀው። ሃንዘላ ያለረዳት ቀርቶና ተጨንቆ፣ ዙሪያውን ተመለከተ። ከዚያም በኋላ ከኑማን አጃቢዎች መካከል በአንዱ፣ የሼይባኑ ተወላጅ፣ የቂይስ ልጅ በሆነው በአምር ልጅ፣ በሼሪክ ላይ ዓይኑ አረፈ፤ ለእርሱም የሚከተሉትን ጥቅሶች ጠቀሰ፦ “ሽርካዬ የአምር ልጅ ሆይ! ከሞት አንዳች ማምለጫ አለ ወይ? አንተ የተሠቃየው ሰው ሁሉ ወንድም ሆይ! አንተ ወንድም ለሌለው ወንድም የምትሆን ሆይ! የኑማን ወንድም ሆይ! ዛሬ ለሽይክ መድህን በአንተ ነው። ፍጹም መሐሪው ውለታ ያድለውና፣ የተቀደሰው ሽይባን ወዴት ነው!” ሼሪክ ግን፣ ወንድሜ ሆይ! ሰው በሕይወቱ ቁማር አይጫወትም የሚል መልስ ብቻ መለሰለት። ከዚያም በኋላ ሚስኪኑ ወዴት እንደሚዞር ለማወቅ አልቻለም። ከዚያም የካልባይት ተወላጅ የሆነው የአድጃ ልጅ ቃራድ ተብሎ የሚጠራው ሰው ብድግ ብሎ፣ በሚቀጥለው የቁጣ ቀን ፍርጃው የወረደበትን ለማቅረብ ካልቻልኩ፣ ንጉሡ በእርሱ፣ ማለትም በቃራድ ላይ፣ የፈለገውን እንዲያደርግ በመስማማት ራሱን እንደመድህን አቀረበ። ከዚያም ኑማን ለሃንዛላ አምሥት መቶ ግመሎች ሰጥቶ ወደ ቤቱ ሰደደው።

በሚቀጥለው ዓመት በክፋት ቀን፣ ወዲያው እውነተኛው ንጋት እንደነጋ፣ ኑማን እንደልማዱ በግሩም አጀብና ሰልፍ ወጥቶ “በደም የተበከሉ” ተብለው ወደተሰየሙት፣ ወደ ሁለቱ መቃብሮች አመራ። ቃራድንም ንጉሣዊ ቁጣውን ሊያወርድበት ይዞት ሄደ። ምናልባት ሃንዛላ ይመጣ ይሆናል ብለው ተስፋ አድርገው ስለነበር፣ የአገሩ ምሰሶዎች አንደበቶቻቸውን አለስልሰው፣ ቃራድን እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ጊዜ ሰጥቶ እንዲያቆየው ንጉሡን እየተማፀኑ ምሕረት

ለመኑ። የንጉሡ ሃሣብ ግን በሃንዛላ ፈንታ ቃራድን በመግደል፣ ሃንዛላን አትርፎ የመሥተንግዶውን ብድር ለመክፈል ነበር። ፀሐይዋ መጥለቅ ስትጀምር፣ የቃራድን ልብስ አውልቀው፣ ራሱን ለመቁረጥ አዘጋጁት። በዚያች ደቂቃ በከፍተኛ ፍጥነት እየጋለበ በመምጣት ላይ ያለ ፈረስ ጋላቢ ከሩቅ ታየ። ኑማን ለሠይፈኛ "ምን ትጠብቃለህ" አለው። ሚኒስትሮቹም፣ "እየመጣ ያለው ምናልባት ሃንዛላ ይሆናል" አሉ። ጋላቢውም እየቀረበ በመጣ ጊዜ ሃንዛላ ራሱ መሆኑን አዩ።

ኑማን በጣም ተናዶ ነበር። እንዲህም አለ፡- "አንተ ሞኝ! አጥብቆ ከመጣብህ የሞት እጅ አንዴ አምልጠህ ነበር፤ አሁን እንደገና እሱን መቀስቀስ ይገባሃልን?" በማለት ጠየቀ።

ሃንዛላም መለሰ፡- "የገባሁትን ቃል ኪዳ እያሟላሁ ስሞት፣ ሞት በአፌ ጣፋጭ፣ በምላሴም ላይ አስደሳች ነው።"

ኑማን፣ "የዚህ ዓይነቱ ታማኝነት፣ የዚህ ዓይነቱ የግዴታ ማክበርና ለመሐላህም መጨነቅ ምክንያቱ ምን ይሆን?" በማለት ጠየቀ። ሃንዛላም መለሰ፡- "ለአንዱ አምላክና ከሰማይ ለወረደው መጽሐፍ ያለኝ እምነት ነው።" ኑማንም፣ "በምን እምነት ታምናለህ?" ሲል ጠየቀ። ሃንዛለም፣ "ወደ ሕይወት ያመጣኝ የየሱስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው። የእግዚአብሔር መንፈሱን፣ የክርስቶስን ቀጥተኛ መንገድ እከተላለሁ፣" አለ። ኑማንም፣ "እስቲ እነዚህንየመንፈስ ጣፋጭ መዓዛዎች ላሸት" አለ።

ሃንዛላ ከእግዚአብሔር የፍቅር ጉያ የእርሱን የመሪነት ነጭ እጅ የዘረጋው፣[1] የተመልካቾቹንም ውጫዊና ውስጣዊ የማየት ችሎታን በወንጌል ብርሃን ያበራው በዚህ ሁኔታ ነበር። መረዋ

[1] ቁርአን 27፡12፣ ለሙሴ ሲናገር፡- "እጅህን ወደ ጉያህ ከተት ነጭ ሆኖ ይወጣል…"፣ ለፈርዖንና ለሕዝቡ ከታዩት ሰባት ምልቶቸ አንዱ… እንዲሁም ቁርአን 7፡105፣ 20፡23 እና 28፡3፡ እንዲሁም ኦሪት ዘፀዐት 4፡6። ደግሞም የኤድዋርድ ፍስጌራልድ "የአማር ካያም ሩባይያት" ተመልከት።

በመሰሉ ድምጾቹ ከወንጌል ውስጥ ጥቂት መለኮታዊ ጥቅሶች ከጠቀሰላቸው በኋላ፣ ጣዖቶቻቸውናሥግደት ያንገፈገፋቸው፣ ኑማንና ሚኒስትሮቹ በሙሉ በእግዚአብሔር እምነት በማመናቸው የፀኑ እንዲሆኑ ተደረጉ። እንዲህ አሉ፤ ‘‘ወዮ ለእኛ! ሺህ ጊዜወዮ! እስከ ዛሬ ድረስ ለዚህ ወሰን ለሌለው ምሕረት ግድ ያልነበረን፣ ከዚህም የተጋረድን፣ ከዚህም ከእግዚአብሔር ጸጋ ደመና ከሚዘንበው ዝናብ የተነፈግን።’’ ከዚያም ንጉሡ በቀጥታ ‘‘በደም የተበከሉ’’ የተባሉትን ሁለቱን ሐውልቶች አፈራርሶ፤ ስለጭካኔውም ንስሐ ገብቶ፣ በአገሩ ላይ ፍትሕን መሠረተ።